# ከአሜን ባሻገር



## በዕውቀቱ ሥዩም



© በዕውቀቱ ሥዩም፤ 2008 ዓ.ም።
የጸሐፊው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
በመጀመሪያ ሕዳር 2008 ዓ.ም. ታተመ።

Copyrights © Bewketu Seyoum, 2015.
All rights reserved, including the right to reproduce
This book or portions thereof in any form whatsoever.

የሽፋን ሥዕል፤ ዐወቀ ስመወርቅ



## ምሥጋና

በዚህ ምድር ያለውን ውጣ ውረድ ላቀለላችሁልኝ ወዳጆቼ ሁሉ፣ ምሥጋናየ ባላችሁበት ይድረሳችሁ።

እንዲሁም ምርምርና የድርሰት ሥራዎቼን ስሠራ ቤታችሁንና ቤተ መጻህፍታችሁን ከፍታችሁ ላስተናገዳችሁኝ ለዶክተር አበበ ካሳሁን፣ ዶክተር በድሉ ዋቅጅራ፣ አቶ ሰለሞን ተከላይ፣ አርቲስት ዓለምጸሃይ ወዳጆ፣ ብሩክ አብዱ፣ ጎሩይ አብዱ፣ አቶ መኮንን ጌታሁን (ሚሩ) እና አቶ ጌታቸው ወልደማርያምን አጥብቄ አመሰግናለሁ። በመጨረሻም፤ የዚችን መጽሐፍ ፍጻሜ ላሳመሩልኝ ወዳጆቼ ሕይወት ማሩና ዳኘነት መኮንን ውለታ ከፋይ ያድርገኝ እላለሁ።

"ከውስጥ ሲያስተጋባ የወንጀሉ ትእዛዝ ሥርዓትና ወጉ
እሜን ብቻ ሆኗል የመሃይም (ን) ወጉ"

(ጸገዩ ወይን ገብረመድህን (ናስተማስለኪ.))






| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 7 |
| የገነት በር | 13 |
| ደስታና ቀቢጸ ተስፋ | 19 |
| የላስታ ገጸበረከት | 25 |
| ከቸርችል ጎዳና ወደ ቸርችል ደመና | 40 |
| የጎበና ቅኝት | 60 |
| የመጨረሻው ምሳ | 78 |
| ሦስቱ ኤልሻዳዮች | 89 |
| ስምና ማንነት | 97 |
| ስለገብረእግዚአብሔር | 113 |
| ገመና ገላጭ | 128 |
| ሴቶች በዋሉበት | 138 |
| የማይድን ናፍቆት | 149 |
| ጁገልን ጥሰው የገቡ ሐሳቦች | 161 |
| ምኒልክና አርሲ | 178 |
| ምኒልክ የጭካኔ ቁንጮ የሆነው ከማን ጋር ተወዳድሮ ነው? | 192 |
| ሲደጋገሙ እውነት የሚመስሉ ውሸቶች | 202 |
| የንቀት ውሃ ሙላት ሲወስድ እያሳሳቀ ነው | 214 |
| አሜሪካን አየን | 230 |
| ነጻ መሬት | 238 |






© በዕውቀቱ ሥዩም፤ 2008 ዓ.ም።
የጸሐፊው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

በመጀመሪያ ሕዳር 2008 ዓ.ም. ታተመ።

Copyrights © Bewketu Seyoum, 2015.
All rights reserved, including the right to reproduce
This book or portions thereof in any form whatsoever.

የሽፋን ሥዕል፤ ዐወቀ ስመወርቅ



## ምሥጋና

በዚህ ምድር ያለውን ውጣ ውረድ ላቀለላችሁልኝ ወዳጆቼ ሁሉ፣ ምሥጋናዬ ባላችሁበት ይድረሳችሁ።

እንዲሁም ምርምርና የድርሰት ሥራዎቼን ስሠራ ቤታችሁንና ቤተ መጻህፍታችሁን ከፍታችሁ ላስተናገዳችሁኝ ለዶክተር አበበ ካሳሁን፣ ዶክተር በድሉ ዋቅጅራ፣ አቶ ሰለሞን ተከላይ፣ አርቲስት ዓለምጸሃይ ወዳጆ፣ ብሩክ አብዱ፣ ጎሩይ አብዱ፣ አቶ መኮንን ጌታሁን (ሚሩ) እና አቶ ጌታቸው ወልደማርያምን አጥብቄ አመሰግናለሁ። በመጨረሻም፤ የዚችን መጽሐፍ ፍጻሜ ላሳመሩልኝ ወዳጆቼ ሕይወት ማሩና ዳኘነት መኮንን ውለታ ከፋይ ያድርገኝ እላለሁ።

## ፖለቲካ ቀመስ

ባንድ ወቅት ከብርቱካን ሚደቅሳ ጋር ዋሽንግተን አንድ ቡን ቤት ተገናኘተን ቡና ጠጣን። ካንዲት ተጽእኖ ፈጣሪ አብዮተኛ ጋር ስለተቀመጥኩ ይሁን በሌላ ምክንያት እንጃ ፤ያለወትሮየ ጡረጴዛ እየደበደብሁ ፖለቲካ ማውራት ጀመርሁ። ብርቱካን ፈገግ እያለች አልፎ አልፎም ከት ብላ እየሳቀች ከማዳመጥ በቀር ሐሳቤን ለመሞገት ወይም ከሐሳቤ ጋር ለመስማማት ምልክት አላሳየችም። በኋላ እቤቴ ገብቼ ፈገግታዋን ለመተርጎም ሞከርሁ። በሙሉቀን መለሰ ዜማ፤ "እይሀ እይህና ሳቅ ይከጅለኛል፤ እኔ ያሳለፍሁት ባንተ ይታየኛል" የምትለኝ መሰለኝ። ታጋዮች በትግላቸው ተስፋ ቆርጠው ወይም ተሰላችተው ወደ ግል ኑሮአቸው በመነኑበት ሰዓት እኔ ስለሀገር አስተዳደር በመከራከር ለምን የማይነጋ ህልም አልማለሁ፤ ለምን ዐርፌ የራሴን ኑሮ አልኖርም? ያልኩበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። እየቆየሁ ሳስበው ዐርፎ መኖር የሚባለው ነገር ትርጉም የለሽ መሆኑ ገባኝ። በርግጥ ተናግሮ ማሳመን፤ ታግሎ መጣል ሁልጊዜ አይሳካም። ያም ሆኖ እስከረታ ድረስ ካልታገልሁ፤ እስከታፈን ድረስ ካልተናገርሁ፤ የረባ ኑሮ ኖርሁ ማለት ይከብደኛል።

ጠንከር ያለ የርዕዮተ ዓለም ትንታኔ ማንበብ የሚወድ ሰው በፖለቲካ ቀመስ መጣጥፎቼ ውስጥ የሚፈልገውን ማግኘቱን እጠራጠራለሁ። መጣጥፎቼ የእንጉርጉሮና የልግጫ ድብልቅ ናቸው። የሐሳብ እርእያዎቼ እንጎራጓሪ ሴቶች የእንጉርጉሮ ... እንጂ ፕሮፌሽናል ፖለቲከኞች አይደሉም። የጥንት እንጎራጓሪ ሴቶች ከባድ በደል ሲደርስባቸው ስሜታቸው ይገነፍላል። ያን ጊዜ ንጉሥና ካህን ከፊቀደላቸው ወሰን አልፈው ይናገራሉ ፤ ይገጥማሉ። መነሻቸው ግለ ታሪካቸው ነው። ለምሳሌ፤

"ልብሴንም ገፈፈው፤ ለበሰው እርዘኛ
በሬየንም ነድቶ፤ አረደው ነፍጠኛ
ንጉሥ የቀረዎት፤ ጥቂት ዐማርኛ
ምነው ሆድ አይዘርፉ፤ ዐርፌ እንድተኛ"





ብላ ያንጎራጎረችው ሴትዮ ፤ የግል ገጠመኟንና አቤቱታዋንና ቁጭቷን ባንድ ላይ ጠቅልላ ገልጻለች። እኔም ከዚህ የተለየ እንዳላደረግሁ ወደ ዝርዝሩ ስትዘልቅ ትገነዘባለህ።

## ታሪክ ቀመስ

ታሪክ ቀመስ መጣጥፎቼ፤ አላግባብ የተወቀሱትን ከማወደስ፤ አላግባብ የተረሱትን ከማስታወስ ያለፈ ዓላማ አላቸው። ባንድ ወቅት ፕሮፌሰር አንድርያስ እሸቴ ቲቪ ላይ ቀርቦ ሲናገር "ታሪካችን ይጫነናል" የምትል ብትቀጥንም ጠጅ የሆነች ነገር ጣል አድርጓል። አሁን ሳስበው ላለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ታሪክ መጻፍ ማለት የበደለኝነትን ስሜት ማሸከም ማለት ሆኗል። በዘመናችን በብሔረሰብ ፖለቲካ የነበዝ አለቆች መካከል የሚደረገው የሥልጣን ትግል፤ "የታሪክን ጸጋዎች ለራስ ጠቅልሎ መውሰድ የታሪክን ዕዳዎች ለሌላው ጠቅልሎ መስጠት" በሚል ያልተጻፈ መርህ ላይ የተመሠረተ ነው። የፖለቲካ ክበርቴዎቻችን የታሪክን ቀንበር በጋራ ለመሸከም ከመስናዳት ይልቅ በወደረኞቻው ጫንቃ ላይ ለመጫን ሲታገሉ ቆይተዋል።

ርግጥ ነው፤ አንዳንዶች እንደሚያስቡት ታሪክ አሮጌ መጻሕፍት ውስጥ ተጠርዞ የቀረ ነገር አይደለም። ያለፈውን ትተን ወደፊት እንገስግስ የሚለው "ሾላ በድፍን" የሆነ አባባልም ትርጉም የለሽ ነው። ያለፈውን ዘመን ችል ብንለው ችል አይለንም። የዛሬው ዘመን ምን ቢታገል ካለፈው ዘመን ተለይቶ ጎጆ መውጣት አይችልም። ያለፈው ዘመንና የዛሬው ዘመን እንዳይፋቱ ሆነው ተቆራኝተዋል። አንዳዴ ሳስበው፤ "ዘንድሮ" በሚለው ቃል ውስጥ "ድሮ" የሚለው ቃል መገኘቱ ባጋጣሚ አይመስለኝም።

ያለፈውን ዘመን ተቀብለን ካለፈው ተምረን የተሻለ የጋራ ቤት መሥራት እንችላለን።

ታሪክን ቁርጭምጭሚታችን ላይ እንደ ታሠረ አለሎ የሚያኩብዱብን የዘመናችን ደረቅ ብሔርተኞች ናቸው። እንዴት? ላብራራ።





አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእለት ጉርስ ያመት ልብስ ለማግኘት ሲኳተን ሲወድቅ የሚኖር ነው። ባንጻሩ በብሔረሰባቸው ላይ ራሳቸውን የነበዝ አለቃ አድርገው የሾሙ ሰዎች በመከረኛው ሕዝብ ስም ቂም ሲያጠራቅሙ፤ ሲያሳድሙ እንዲሁም በማኅበራዊ ገጾች ላይ ተሰላልፈው ሲፋለሙ ይውላሉ። "ሕዝቤ፤ ብሔረሰቤ፤ ማንነቴ፤ መስዋእትነቴ" የሚሉ ቃላትን ሲያመነዥኩ ስታያቸው ለህዝባቸው ለብሔረሰባቸው የሚቆረቆሩ ይመስልሃል። ግን ጭንብላቸውን ገልበህ ስታይ መሰሪ ራስ ወዳድነታቸውን ትደርስበታለህ።

በራስ ወዳድነትና በመሰሪ ራስ ወዳድነት መካከል ልዩነት አለ። እኔ ራሴን እወዳለሁ። ራሴን ስለምወድ የግል ሐሳቤን ለርዕዮተ ዓለም፤ ለሥጋ ዝምድና፤ ለፓርቲ ፍቅር ስል አልሰዋም። እንዲሁም ለራሴ ያለኝን ፍቅር የሕዝብ ፍቅር፤ የድርጅት ፍቅር የሚል መሰሪ ካባ አላለብሰውም። ለምሳሌ በዚች መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ሐሳቦች የማንም ቡድንና ሕዝብ ተወካይ ሆኘ አልጻፍኳቸውም። በሐሳቤ ምክንያት የሚመጣውን መዐት ለብቻየ ራሴን ችየ ልጋፈጠው ዝግጁ ነኝ። የብሔረሰብ የነበዝ አለቆች ራሳቸውን ችለው ቆመው እንደማይመከቱ እውቃለሁ። ራሳቸውን የሕዝብ እደራ ተረክበው እንደሚታገሉ አድርገው የሚያስተዋውቁትን ያከል ጠላታቸውን የሌላ ሕዝብ ድርጅት ወኪል አድርገው ሊያቀርቡት ይሞክራሉ። በዘመናችን ምሁራዊ ውይይት ነጥፎ እድማና ሴራ ያንሠራራበት ምክንያት ይህ ነው።

እነ እጅሬ ትግላቸው ህዝባቸውን ሳይሆን ኪሳቸውን ነጻ ለማውጣት ነው። እንባቢ ሆይ የብሔረሰብ ፖለቲካ ወፍራም እንጀራ መሆኑን ካላወቅህ ተሸውደሃል። ባሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የብሔር ፖለቲከኞች ሉቅ ናቸው። የብሔረሰብ ሚድያ ለመክፈት፤ የሽንፈት ወይም የድል ሐውልት ለማቆም፤ እንዲሁም ቤተመዘከር ለመገንባት ተብሎ ከድኻው መዋጮ ይሰበሰባል። የተሰበሰበው ገንዘብ ባብዛኛው በጌቶችና በሸፍቶች ኪስ ውስጥ ይገባል። ራሱን ችሎ መቆም የማይችል፤ ዝናብ እንደመታው ፍየል ጥግ ላይ አንገት ላንገት ተቆላልፎ ካልቆመ በስተቀር የኖረ የማይመስለው የኅብረተሰብ ክፍል በየትኛውም ሀገር በየትኛውም ዘመን አለ። ገንዘቡን ብቻ ሳይሆን፤





ምቾቱንና እድሜውን በቡድን ስም ለሚያጭበረብሩት አስማተኞች ለመገበር ዝግጁ የሆነ ዜጋ ሞልቷል።

በዘመናችን ብሔርተኝነት ማለት ሳይደክሙ የሌሎችን የድካም ውጤት መቀማት መሆኑን አውቃለሁ። አንድ ሰው በግሉ ስኬት መቀዳጀት ሲያቅተው በጥረታቸው ብልጫ ያስመዘገቡ ግለሰቦችን ስኬት ወደ ብሔር ስኬት ለውጦ ባዶነቱን ለመሙላት ይሞክራል። ሌላው፤ እልም ያለ ፈሪ ሆኖ ሳለ "የበላይ ዘር" እያለ ይፎክራል። ብብቱ ውስጥ ገብተው ካልደገፉት በቀር እልጋ ላይ መውጣት የማይችለው ሰውዬ፤ አበበ ቢቂላ ቡተንሣ ቁጥር "አበበ ኬኛ" እያለ ይኩራራል። በላይና አበበ ያስመዘገቡት ድል በላብና በደም የተገኘ የግለሰብ ጥረት ውጤት ነው። ድል በዘር አይተላለፍም። የአባቶች ታላቅነት በዘር ወደ ልጆች የሚተላለፍ ቢሆን ኖሮ ግሪኮች በዛሬይቱ የአውሮፓ እግር ሥር እንደጉድፍ ወድቀው ባልተገኙ ነበር። ብሔርተኝነት የግለሰብ ጥረትን ሰርቆ የራስን ድክመት ለመሙላት የሚደረግ መሰሪ እንቅስቃሴ ነው።

ከውስጥ ዐዋቂ የሰማሁት አንድ ገጠመኝ ምስክር ይሁነኝ። የአንድ የብሔር ጎበዝ አለቃ የሆነ ሽማግሌ በኢትዮጵያ ባንዱ ክፍል ይኖራል። ሁለት አርብቶ አደር ብሔሮች በግጦሽ ሳር ወይም በውሃ ምክንያት ይጣላሉ። ይኸኔ ይህ ሽማግሌ በዘመናዊ ላንድ ክሩዘር ወደ አዲስ አበባ ተጠርቶ ይመጣና ግጭቱን እንድያስቆም ትዛዝ ይተላለፍለታል። ለግጭት መቆጣጠርያም ተብሎ ዳጎስ ያለ ብር በሰፊው ኪሱ ውስጥ ሻጥ ይደረግለታል። ሽማግሌው ወደ ግጭቱ ቦታ ተመልሶ ከተቃራኒው ወገን የተሰለፉትን እቻ የጎሳ መሪዎች ይጠራና ከተመደበለት ጉርሻ ያካፍላቸዋል ። እነሱም በራሳቸው መንገድ የተቀሰቀሰውን ግጭት ያበርዱታል።

የጎሳ መሪ ሽማግሌዎች ገንዘባቸው ሲያልቅ እንደገና በእጅ አዙር ግጭቱን ይቀሰቅሱታል። ጎበዛዝት ይዘነጣጠላሉ። ጎጆዎች ይቃጠላሉ። ያዲስ አበባው መንግሥት ባለስልጣናት ሽማግሌውን እንደገና ጠርተው ይለማመጡታል። የደም ገንዘብ የለመዱ ሰላምን እርቀው ይቀብሯታል።

የዘመናችን የብሔረሰብ የኀብዝ አለቆች በተወለዱበት ከተማ ውስጥ ሆስፒታል ለመሥራት አምስት ሳንቲም አያወጡም። ይሁን እንጂ የጀርመን ተራድኦ ድርጅት ሆስፒታል ቢያቆም በየትኛው ቋንቋ የተጻፈው ስሙ ይቅደም የትኛው ይከተል በሚለው ዙርያ ዱላ ቀረሽ ክርክር ሊያደርጉ ይችላሉ።

ባብዛኛው በንፍገት ችግር የሚሰቃዩ ናቸው። ንፍገትን ፖለቲካዊ ካባ ስላለበሰከው ንፍገትነቱን አይለውጥም። አሜሪካ ወይም አውሮፓ ቤት ሠርቶ ዜጎች የሚያገኙትን መብት አግኝቶ እየኖረ፤ "ከክልላችን ውጡልን" የሚል መፈክር የሚያስተጋባ ሰው ከስስታምነት በቀር ምን ይገልጸዋል? ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚኖሩ ብሔረሰቦች ውስጥ እንደ ሰርዶ ከመሬት በቅሎ የተገኘ አንድ እንኳ የለም። ሁሉም በቅምያ የተገኘ መሬት ወርሶ የሚኖር ነው። አባቶቻችን በቅምያ ያገኙትን ሀገር በጋራ በእኩልነት ከመጠቀም ውጭ ማንም ተነሥቶ በተጎራባች ህዝቦች ማኸል የቻይና ግንብ የማቆም መብት የለውም።

በሰላም ሀገር እየኖሩ፤ ወንድማማች ህዝቦችን ወደ ፍጅት የሚገፉ ሰዎችን አመለካከት በዚች መጽሐፍ ውስጥ ለማጋለጥ ሞክርያለሁ።

በመጽሐፏ ውስጥ ታሪካቸውን በልዩ አድናቆት ያወሳሁላቸው ሰዎች አሉ። እኒህን ሰዎች በግለሰብ ብቃታቸው የማደንቃቸው ናቸው። ኢትዮጵያን የሚያክል ሀገር መመሥረት ቀላል ነገር አይደለም። ልበ ሙሉነት፣ ትጉነትና የማደራጀት ተሰጥኦ ይጠይቃል። ከየትም ይምጡ ከየት በታሪካችን ውስጥ ልዩ ብልጫ ያስመዘገቡ ግለሰቦችን ከማድነቅ አልቦዝንም። ዝርዝሩን ወደ ውስጥ ስትዘልቅ ታገኘዋለህ።





# የገነት በር

አሜሪካን ለማየት የነበረኝ ጉጉት ድሮ ሀገር ቤት ሳለሁ አዲስ አበባን ለመጎብኘት ከነበረኝ ጉጉት ጋር ይመሳሰላል። ድሮ ልጅ ሆኜ ከብላቴኖች አፍ የማይጠፋ አንድ ስመጥር ዘፈን ነበር። ዘፈኑ፤

"አዲስ አበባ ላይ፤ ወድቄ ብነሣ
የሠራ አከላቴ፤ወርቅ ይዞ ተነሣ" ... እያለ ይወርዳል።

የልጅነት ምኞቴ፣ ፓይለት መሆን፣ ዶክተር መሆን ሳይሆን፣ አዲስ አበባ ውስጥ እንደምንም ገብቶ ጧ ብሎ መውደቅ ነበር። አዲስ አበባ ላይ የወደቀ ሰው ፍግ እንጂ ወርቅ ይዞ እንደማይነሣ ለማወቅ ጥቂት ዓመታት መጠበቅ ነበረብኝ።

"ኪነት የገሀዱ ዓለም ነጸብራቅ ናት"፣ ያለው ሰውዩ የወጣለት ቀጣፊ መሆን አለበት። ኪነት የገሀዱ ዓለም አብሾ፤ የገሀዱ ዓለም ጌሾ ናት። ጉቶውን ሰማይ ጠቀስ ፎቅ አድርጎ ማሳየት ዋና ጠባይዋ ነው። በዘፈን ጠብድሎ የታየን፤ አጠገቡ ሰንገኝ ደብዝዞ፤ እዚህ ግባ የማይባል ሆኖ እናገኘዋለን። "የጠላን አቀበት ዝንጀሮ አይወጣውም" በሚለው የዓለማየሁ እሸቴ ዘፈን ስጭበረበር





እንደኖርሁ የገባኝ ከጠላ ተራራ ፊትለፊት የቆምሁ ቀን ነው። ይሄንን አቀበት እንኳን ዝንጀሮ፣ እኔ ራሴ ከስክስ ጫማ አድርጌ፣ መቶ አለቃ ግርማን አዝየ መውጣት ያቅተኛል? ዓለማየሁ እሸቴ ከጠላ ወሰል ሥር የተመለከተው ዝንጀሮ አካለ ስንኩል መሆን አለበት።

አሜሪካ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዝግጅቴን እንዳቀርብ በ"ምነው ሸዋ ኢንተርቴይመንት" አማካኝነት ግብዣ ሲቀርብልኝ አላቅማማሁም። አሜሪካ ገብቼ ከተቻለ፣ አንድ ከረጢት ዶላር ካልተቻለ ደግሞ አንድ ከረጢት ወሬ ይዤ እመለሳለሁ ብየ አሰብሁ።

ለጉዞ የሚገፉ ሌላ ሰበብም ነበረኝ። በቅርብ ጊዜ ወዲህ የቤት ለቤት ደራሲነት ስልችቶኛል። በኔና በቢጤዎቼ መዝገበ ቃላት፤ በማየት፣ በመመርመርና በመጎብኘት ሳይሆን ከበርጩማው ላይ ሳይነሣ የሚጽፍ ሰው "የቤትለቤት ጋዜጠኛ" ወይም "የቤትለቤት ደራሲ" ይባላል። ዓለምን እቤታችን በርጩማ ላይ ሆነን ስናያትና ኮርቻ ላይ ሆነን ስናያት ለየቅል ናት። እኔና የዘመን ጓዶቼ ኮርቻው ላይ ብዙም የለንበትም። ካባቶቻችን እና ከውጭ ሀገር ጋዜጠኞች ጋር ስንመዛዘን ወደ ኋላ የቀረን ይመስለኛል።

አባቶቻችን ስል፣ በአገራችን ታሪክ እንደ መጀመርያዎቹ ጋዜጠኞች ሆነው ሊቆጠሩ የሚገባቸውን የዜና-መዋእል ጸሐፊዎችን እያሰብኩ ነው። እኒህ ጸሐፊዎች ከልቦናቸው አፍልቀው ሲጽፉና በቦታው ተገኝተው ሲዘግቡ ልዩነቱ ለየቅል ነው። በርጩማቸው ላይ ተወስነው ሲጽፉ ወይም በእነሱ አባባል፣ ከልቦናቸው አፍልቀው ሲጽፉ፣ ብዙ ፍሬከርስኪ ነገር ብራናቸውን ያጣብበዋል። ትልቅ ገድል የተፈጸመበትን ጦርነት በጥቂት መስመሮች አቀጭጨው፣ እኮስምነው ይዘግቡታል። ምድራዊውን ክስተት ሰማያዊ ያደርጉታል።

የዘመን ጓድ፤ አንድን ዘመን የሚጋራ ሰው ማለት ነው፡፡ይህን ቃል ፈጥሮ ወደ ፀማርኞችን የጨመረው ይድነቃቸው ተሰማ ነው፡፡ በእንግሊዝኛ contemporary የሚል አቻ አለው፡፡





ከላይ የጠቀስኳቸው ሰበቦች ባይኖሩ ኖሮ እንኳ የአሜሪካን ግብዣ እግኝቶ "ይለፈኝ" የምልበት ምክንያት አልነበረኝም። እንደ ብዙዎቹ የዘመን ጓዶቼ የአሜሪካን መስህብ መቋቋም የሚችል ወኔ ያለኝ አይመስለኝም። አንዳንዴ ሳስበው፤ በዘመናችን አሜሪካ ለመግባት የሚደረገው ውጣ ውረድ አባቶቻችን በእምላክ ፊት ሞገስ ለማግኘት ከነበራቸው መጠመድ ጋር የሚመሳሰል ነው። ለነገሩ ይህ መሆኑ ምን ይገርማል? አሜሪካ ሁሉን-ቻይና ሁሉን-ዐወቅ ብቻ አይደለችም። ከዚያም በላይ ናት። አንድ የፖለቲካ ሊቅ ያለውን መጥቀስ የምለውን ያደምቅልኛል፤

"የዛሬይቱ ዓለም ሥርዓት ጉዳይ፣ በከፊል የአሜሪካ ፖሊሲ ጉዳይ ነው። ዓለም አቀፍ ስትራቴጂ ያላት ሀገር አሜሪካ ናት። ቀሪው የዓለም ክፍል ለአሜሪካ አጸፋ የሚመልስ፣ አሜሪካን የሚፈራ፣ በአሜሪካ ጥበቃ ውስጥ የሚኖር፣ በአሜሪካ የሚቀና፣ አሜሪካን የሚጠላ፤በአሜሪካ ላይ የሚያሴርና በአሜሪካ ላይ ተማምኖ የሚኖር ነው። ሌላው ሀገር ሁሉ የሀገር አስተዳደር መርሁን ከአሜሪካ እንጻር ይቀርጻል።" [2]

እንግዲህ መንግሥታትን በዚህ መንገድ የማረከው የአሜሪካ ኃያልነት ግለሰቦችን ቢያማልል አይገርምም።

ኤምባሲ የምገባበት ቀን ሲቃረብ አንዱ ባለንጀራየ፤

"ቃለ መጠይቁን በእንግሊዝኛ ነው የምታደርገው ወይስ በዐማርኛ?" ሲል ጠየቀኝ።

"ይችን ይወዳል ሰውየው! ቅኔ እዘርፍበታሁ ብየ የምተማመንበትን የእንግሊዝኛ ችሎታየን ትጠራጠረዋለህ?"

"ግዴለህም በእንግሊዝኛ ቃለመጠይቅ ማድረግ ይቅርብህ"

[2]Robert Cooper, The breaking of Nations (Page 45)

"እኮ ለምን?"

"ምን ያደርግልሀል። የኢምባሲ ቃለመጠየቅ የቁሪስት ጋይድ ፈተና አይደለም። የቋንቋ ቻልክ አልቻልክ ግድ የላቸውም።"

"በዐማርኛ እንዳደርግ ነው የምትፈልገው?"

"አዎ"

"የሚያሳምን ነገር ንገረኝ"

"ዐየህ፣ አስተርጓሚዎች ለተጠየቅከው ነገር የምትሰጠው ምላሽ አጥጋቢ መስሎ ካልታያቸው ወይም ካልጣማቸው፣ ያግዙሀል። ማለት የፈለግከውን ሳይሆን ማለት የሚገባህን አርመው ያስተላልፉሀል። ይሄ ቪዛ የማግኘት እድልህን ከፍ ያደርገዋል። ግልጽ ነኝ?"

ጓደኛየ ግልጽ ብቻ ሳይሆን ትክክል ነበር።

ኤምባሲ የቃለመጠይቅ ተራየ ደርሶ የዶርዜ ነጃ ከሚያከል አሜሪካዊ ፊት ቆምኩ። መቸም ያሜሪካዊ ሸንቃጣና የቻይናዊ በርጫም ማግኘት ከባድ ነው። የፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽን ግልብነት ያለመታከት በሙተቸት የሚታወቀውን ማይክል ሙር የተባለውን ጋዜጠኛ አስታወሰኝ። በህዝቡ ማኸል ኖረህ ስታየው ተርታው አሜሪካዊ የማይክል ሙርን ሰውነትና የጆርጅ ቡሽን አእምሮ አስተባብሮ የያዘ ሆኖ ታገኘዋለህ።

ባስተርጓሚ ብዙ ጥያቄ ተጠየቅሁ። ተገቢውን መልስ ሰጠሁ።

መጨረሻ ላይ፣

"ከባህል ቡድኑ ጋር መሥራት ከጀመርክ ስንት ጊዜ ሆነህ? " የሚል ጥያቄ ተወረወረልኝ።

"የመጀመርያየ ነው" አልሁ።





አስተርጓሚው አፉን ወደ መስኮቱ አቅርቦ፣ "አልገባህም ጥያቄው" አለኝ።

"ጉብኝቶኛል የመጀመርያዬ ነው" ብየ መለስኩ።

"አሁንም አልገባህም" ሲለኝ ምላሼን እንዳርም ፍንጭ እየሰጠኝ መሆኑ ገባኝ።

"አንድ ዓመቴ ነው" ብየ ሸመጠጥሁ። አስተርጓሚው ውሸቴን ለፈረንጁ ተረጎመለት።

ቪዛው ሲመታልኝ፣ በልቤ እንደ ባሕርዳሩ መዳኒት ዐዋቂ፣ እንደ አያ አስረስ "እውነት መቀመቅ ከታኝ ነበር፣ ውሸት ነጻ አወጣችኝ" ብየ ፈገግ አልኩ

ነገሩ ከጥቂት ዓመታት በፊት የተከሰተ ነው። በባሕርዳር ከተማ በባህል ህክምና የሚተዳደሩት አያ አስረስ ለአንዲት በሽተኛቸው አጉል ቅጠል ሰጥተው ገደሏት። በፖሊሶች ቁጥጥር ሥር ሲውሉ ታድያ፣ "እኔ ልጤ የተራሰ፣ ጉድጓዴ የተማሰ ሽማግሌ ነኝ። በዚህ እድሜየ መዋሸት አይገባኝም። እውነት ነው፤ መዳኒቱን ስሰጣት ስተት ብላ ግጥም ብላብኛለች፤ በእጄ ላይ ሙታብኛለች" ብለው ተናዘዙ።

ጠበቃው ይሄንን ሲሰማ፣ የዋህነታቸውን ወቅሶ፣ እንዲያስተባብሉ አሰለጠናቸው። እናም በሚቀጥለው ቀጠሮ ሲቀርቡ፣ "ክቡር ፍርድ ቤት፣ ፖሊሶች ባልወለደ አንጀታቸው እየነረቱ፣በግድ እንዳምን አድርገውኝ ነው እንጂ፣ ከልጅቱ ደም እጄ ንጹህ ነው" ብለው አስተባበሉ። ፍርድ ቤቱም የዋስ መብታቸውን ፈቅዶ አሰናበታቸው። ታድያ የጎረቤት ጠያቂ "እግዜር አንኳን አስፈታዎ እያለ ሲጠይቃቸው፣ "ወገኖቼ፤ እውነት መቀመቅ ከትታኝ ነበር፤ ውሸት ነጻ አወጣችኝ" ብለው መለሱ ይባላል።

እኔም እውነት መቀመቅ ልትከተኝ እንደነበር እያሰብኩ ከኤምባሲው ወጣሁ።

ገና ከግቢ እንደወጣሁ አንዱ እንኳን ደስ አለህ ብሎ እንደ ሐረግ ተጠመጠመብኝ። እንደምንም ከዕቅፉ ራሴን መንጭቄ አውጥቸ ቀና ብየ ስመለከተው ያለዛሬም አይቼው አላውቅ። "እስቲ የደስደስ የሆነ ነገር





ልቀቅብኝ" ሲለኝ፣ ከፊቴ የቆመው "ፈላጭ[3]" መሆኑ ገባኝ። እጄን ከኪሴ ሳትቸ ሳወጣው አምሳ ብር ይዞብኝ ተመለሰ። "ዝርዝር አለህ?" ልለው ስሰናዳ አምሳ ብር በቂ ነው እለና ከመንጠቅ በማይተናነስ መንገድ፣ እጄ ላይ ያንከረፈፍኩትን ተቀበለኝ። ወድያው ፈገግታውን አቀጣጥሎ ወደ ሌላዋ ባለ እድል ሲሄድ ተመለከትኩት።

የዚህን "ፈላጭ" ዘዴኝነት ባሰብኩት ቁጥር ዛሬ ድረስ ይደንቀኛል። የሽሮሜዳው አራዳ፣ የሰው ስነልቡና ዘይቤ ተገልጦለታል። ሰዎች በተደሰቱበት ቅጽበት መንፈግና መቆጠብ ትዝ አይላቸውም። ለኛ ኢትዮጵያውያን የአሜሪካ ቪዛ የደስታ ጣራችን ነው። ቪዛን ያክል ነገር በእጅህ ገብቶ እንዴት ስለ ንፍገት ታስባለህ? የዶላር ተራራ ከፊት ለፊትህ እየታየህ ስለአምሳ ብር እንዴት ልትጨነቅ ትችላለህ? እንዲህ አይነቱ የደስታ ቅጽበት አባ ሆናን አባ መስጠት እንዲሆን ያስገድድዋል።

ደስታ የሚባለው ነገር ሰዎችን እንዴት መልካምና ገራም እንደሚያደርጋቸው ያየሁበት ጊዜ አይቸዋለሁ። ያን ቀን፣ ሰዎች ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ዋንጫ ማጣርያ ያለፈች ጊዜ አይቸዋለሁ። ያን ቀን፣ ሰዎች ሁሉ ከንፋቸውን ያራገፉ መላእክት ሆኑ። ለወትሮው ጎዳናውን እንደርስት እየተሻሙ ስድብ የሚቀባበሉ ያዲሳባ ባለመኪኖች አንተ እለፍ፣ አንተ ቅደም እየተባባሉ ሲገባበዙ አየሁ። ባለመኪኖች መንገደኛውን ሁሉ የመሳፈሪያ ዋጋ ሳይጠይቁ ጫኑ። ደስታ የሰዎችን ፊት ሁሉ አንድ አደረገው። ምናልባት ደግ ለመሆን የሚያስፈልገን የግብረገብነት ትምርት አይደለም። የሚያስፈልገን ትንሽ ድልና ትንሽ የምሥራች ይሆናል።

³ባራዶች መዝገበቃል እግባብቶና ተለማምጦ ገንዘብ የሚቀበል ፈላጭ ተብሎ ይጠራል። ደረጃው ከተመጽዋችነት ከፍ ያለ ነው።





# ደስታና ቀቢጸ ተስፋ

ውሃ ልማት በተባለው የኛ ሠፈር ውስጥ፣ ሁለት ዝነኛ ተማሪ ቤቶች ይገኛሉ። የመጀመርያው እንደ ቅርስ የሚቆጠረው አንጋፋው፣ ብርሃንህ ዛሬ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፣ ሁለተኛው የሐዲስ ዓለማየሁ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምርትቤት ነው። በሁለቱ ትምርትቤቶች መካከል በግምት ሦስት መቶ ሜትር ርዝመት ያለው የእግር መንገድ ተዘርግቷል። ከእግር መንገዱ ግራናቀኝ፣ መጻሕፍት ቤቶች፣ አለያም የጽሕፈት መሣሪያ መሸጫ ሱቆች አይታዩም። አካባቢውን የወረሩት መሥረሪያ ቤቶች (ፔንሲዮኖች) ብቻ ናቸው። ከበዛኔ ቀኖቼ ባንዱ፣ ሥራየ ብየ ግራ ቀኙን ማስተዋል ጀመርኩ። አቦካዶ ፔንሲዮን፣ ዜድ ቢ ፔንሲዮን፣ ጌት ፔንሲዮን፣ኀይሌ ፔንሲዮን፣ ኒውዴይ ማሳጅ፣ አህመድና ወዳጆ ጫት ቤት፣ መሲ ራያ ባር፣ አሪዮን ፔንሲዮንና ክላሲክ ፔንሲዮን በግራቀኜ ተሰልፈዋል።

የፔንሲዮኖች ሠልፍ በሚጠናቀቅበት ቦታ ላይ፤ "ሴማህ የማህጸን ክሊኒክ"፤ ባልጋ ላይ ጦርነት የተጎዱ ቁስለኞችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ስትራቴጂካዊ ቦታ መርጦ ጉብ ብሏል። ባጠቃላይ፤ እዚህ አካባቢ የሙገዘ ልጣጭ ያዳለጠው መንገደኛ የሚወድቀው አልጋ ላይ ነው።

ይህ የእኛ ሠፈር መልክ ከሞላ ጎደል የዛሬይቱ ኢትዮጵያ መልክ ነው። ያጋነንኩ ከመሰላችሁ ሠፈራችሁን ግራና ቀኝ ተመልከቱ። በመቋቋም ላይ የሚገኙት የንግድ ቤቶች፤ ከመብል ቤት፤ ከመጠጥ ቤት፤ ከልብስ ቤት፤ ከመኝታ ቤትና ከጭፈራ ቤት አያልፉም። ባሁኑ ጊዜ "እንገቴን ወለም" አለኝ ስትል፤ ሙታንታህ ሥር ገብተው የሚያሹህ ማሳጅ ቤቶች፤ በሽተኛ የጫነ አምቡላንስ ደጃፍ ላይ አቁሞ የሚቅም ሾፌር ሳይቀር የሚያስተናግዱ ጫት ቤቶች፤ ድፍን መንደር እንደ ጋን ገልብጠው በጭስ የሚያጥኑ ሺሻ ቤቶች ተበራክተዋል።

በግሌ እንደ ከበደ ሚካኤል "ደስታ ጭቅቅት ነው፤ ነፍስን ያሳድፋል" የምል መናኝ አይደለሁም። ምድራዊ ተድላ ባለበት ቦታ ሁሉ ታጥቄ ብሰማራም አልጠላም። የሚከተለውን የምጽፈው የመደሰቻ ቤቶችን መፍላት ለማውገዝ አይደለም። ዓላማየ አዲሱ የደስታ ዝንባሌ ከየት እንደመነጨ ያቅሜን ያኸል ለማሳየት ነው።

"የመሥሪያ ቤቶች፤ የጫት ቤቶች የመጠጥ ቤቶች ወዘተ… በየቦታው እንደ ከረምት እግቢ መፍላት፤ ደስታ መግዛት የሚችሉ ሰዎች መበራከታቸውን ያሳያል። በተዘዋዋሪም የሀገሪቱን ማደግ ያመለክታል። ታድያ ምናባህ ቆርጦህ ታማርራለህ?" የሚል አይጠፋም። እኔን የሚያሳስበኝ ያእምሮ ተቋማትና የተድላ ቤቶች ጎን ለጎን አለማደጋቸው ነው። የመዲናይቱ መመኪያዎች የነበሩት የቡክ ወርልድ መጻሕፍት ሱቆች በፍጥነት መዘጋታቸው፤ በባንኮችና በአበባ ሱቆች መተካታቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። አራት ኪሎ የሚገኘው አንጋፋው የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት ሳይቀር ዓይናችን እያየ ወደ ካፍቴሪያ ተቀይሯል። ከጥቂት ዓመታት በፊት መጽሐፍ መሸጫ የነበረው ቦሌ መድኀኔዓለም ላይ የነበረው ሱቅ አሁን የዶሮ ሥጋ መሸጫ ሆኗል። የምርምር ማዕከሎች፤ ቤተመዘከሮችና ማተሚያ ቤቶች በግንባታ መስመር ላይ





አይታዩም። ከፈጠራ፤ ከምርምር እና እንቅቅልሾችን ከመፍታት የሚገኝ ደስታ ደብዛው የለም። ያለው ሥጋዊ ደስታ ብቻ ነው።

ከጥቂት ጊዜያት አስቀድሞ፤ ከመንፈቀ ሌሊት በፊት መንገድ ዳር የምትቆም ሴት ታክሲ ጠባቂ የቤት እመቤት ስትሆን፤ ከመንፈቀ ሌሊት በኋላ መንገድ ዳር በክፉል ተራቁታ የምትቆም ሴት ደግሞ ደንበኛ የምትጠባበቅ ሴተኛ አዳሪ ናት፤ ብየ እሰብ ነበር፤ አሁን ሴተኛ አዳሪዎች ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ሲቆሙ አያለሁ። አሁን ያለው ማኅበራዊ ሞገድ ብርቱ ከመሆኑ የተነሣ የቤት እመቤቶችን ጊዜና የሴተኛ አዳሪዎችን ጊዜ የሚለየውን ድንበር አፍርሶታል። የወሲብ ገበያ፤ በጠፍ ጨረቃ፤ በሽሽግ የሚካሄድ መሆኑ ቀርቷል።

አዲሱ ለውጥ በግብረገብ ስብከት የሚቀለበስ አይመስለኝም። ምክንያቱም የዜጎች ጠባይ ካገዛዙ ሥርአት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው።

የፖለቲካ ጭቆና በበረታበት ሀገር ውስጥ፤ ወሲባዊ ልቅነት የመጨረሻው የነጻነት አማራጭ ተደርጎ ይወሰዳል። አመንዝራነት፤ ዜጎች ሌላው ቢቀር ብልታቸው በመንግሥት ቁጥጥር ሥር አለመሆኑን የሚያሳዩበት መንገድ ነው።

አባቶቻችን ከእኛ የተሻለ የደስታ ምንጮች ነበሯቸው። ቢያንስ ከጀብዱ የሚገኝ ደስታ ነበራቸው። አንድ ሰው ከጦርነት የሚገኝ ግዳይ ባይቀናው እንኳ ቆላ ወርዶ፤ የፈረደባትን ቀጭኔ ገድሎ በመመለስ ቤቱ ውስጥ ከበሮ ማስደለቅ ይችል ነበር። "ደስታ ማለት ኃይለኛ የመሆን ስሜት ነው"፤ የሚለው የኒቼ ሐሳብ በጊዜው የተፈተነ ሐቅ መሆኑን እንርሣ።

ከዓለም ተነጥላ በብህትውና የምትኖር ሀገር ውስጥ መኖር በራሱ የሚያጎናጽፈው ያላዋቂነት ደስታ ነበር። ቀደምቶቻችን ራሳቸውን ከሌሎች አገሮች ብልጽግና ጋራ አነጻጽረው እርር ድብን የሚሉበት አጋጣሚ አልነበረም።

ስለራሳቸውና ስለአካባቢያቸው የነበራቸው እምነት በእርካታ የተሞላ ነበር። እዚህ ላይ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ስለአዲስ አበባ ምስረታ የጻፉትን ማንሳት አሰብኩ። እንዲህ ይላሉ፡-





"ወይዘሮ ጣይቱ… ከዚያች ከፍል ውሃው አጠገብ ከተሠራችው ቤት ወርደው ተቀመጡ፤ ሰራዊቱም ቤቱን ይሠራ ጀመር። አገሩም እጅግ ያማረ ሆነ። ወይዘሮ ጣይቱም ይሄን ከተማ ስሙን አዲስ አበባ በሉ ሰራዊቱም ወደደው። ወይዘሮ ጣይቱም ይሄን ከተማ ስሙን አዲስ አበባ በሉ ብለው አዘዙ።"

አዲስ አበባ የተቆረቆረች ሰሞን የነበራትን መልክ በፎቶ የተመለከተ የዛሬ ዘበን ሰው፤ "አገሩም እጅግ ያማረ ሆነ"፤ የሚለው የጸሐፊ ትእዛዙ አስተያየት ሰማይ የሚያክል ቀልድ ይሆንበታል። ከተማይቱ ባብዛኛው የደሳሳ ጎጆዎች ጥርቅም ነበረች። ደግነቱ፤ እቴጌ ጣይቱ የከተማይቱን ትልልቅ የወፍ ጎጆዎች ከፓሪስና ከለንደን ማለፍያ ሕንጻዎች ጋራ አወዳድረው የሚሸማቀቁበት እድል አልነበረም። የከተማይቱ እጅግ የተጋነነ ስያሜ ይሄን ያሳያል። እቴጌ፤ ከተማይቱን አደይ አበባ፤ ጽጌረዳ አበባ፤ የሱፍ አበባ ብለው መጥራት ይችሉ ነበር። ግን በጊዜው የነበረው የአበባ ዝርያ ሁላ " እጅግ ያማረ ሆኖ" የተባለውን የከተማይቱን ውበት ለመግለጽ በቂ ሆኖ ስላላገኙት፤ "አዲስ አበባ" ለማለት ተገደዱ። አለማወዳደር ደጉ!

እኛ እኒህ የደስታ ምንጮች ደርቀውብናል። ሌላው ቢቀር ባለህመሩን ባለጸጋና ባለዊልቼሩን ለማኝ እኩል የሚያስፈነድቁት የእግር ኳስና የሩጫ ድሎች እየተመናመኑብን በመሄድ ላይ ናቸው። ይህ አልበቃ ብሎ፤ ያገራችንን ስቃይ፤ ከሌሎች ሲሳይ ጋራ የምናወዳድርበት መስኮት በየቦታው ይጠብቀናል።

ባንድ ምሽት ኤድናሞል በተባለው ስመጥር የቦሌ ሕንጻ ሥር አልፋለሁ። አንድ ትንሽ ለማኝ ልጅ ካፍያ እየመታው አዳፋ ነጠላውን ተከናንቦ፤ ኩርትም ብሎ ተቀምጦ ቀና ብሎ ሕንጻው ላይ ያለውን ባለግዙፍ ስክሪን ቲቪ ይመለከታል። ከቴሌቪው የሚፈልቅ ሰማያዊ ብርሃን በመከረኛ ፊቱ ላይ ዐርፎ አቫተርን አስመስሎታል።

አልፌው ስሄድ በስክሪኑ ውስጥ የሚመለከተውን ለመገመት አልተቸገርኩም። ተዋናይት ሙሉ ዓለም ታደሰ፤ ምኞት ያሳመራቸውን ብላቴኖች ያኩሪ እተር ፍርፍር ስትመግብ ያያል። የጠገቡ ፈረንጆች ሲዘሉ ያያል። መከረኛ ሕይወቱን ስክሪኑ ውስጥ ከሚያየው በድሎት የተሞላ ዓለም ጋራ





ሲያወዳድረው ምን ይሆን የሚሰማው? በዲጂታል ሚድያ በተጥለቀለቀ ዘመን ውስጥ የብዙ ኢትዮጵያውያን እድል ከዚህ የተለየ አይደለም።

ከድል የሚመነጭ ደስታ ካጣን፤ በማወዳደር ምክንያት ማግኘት የሚገባንን ደስታና ርካታ ካጣን የመጨረሻው አማራጭ ምንድን ነው? በጦር ሜዳ ወይም ባደን ያጣነውን ጀብዱ ባንዲት ድሃ ሴት ላይ ጉልበታችንን በመፈተን ልናካክሰው እንሞክራለን። በምርቃና፤ በስካር እና በቀለጠ አሸሸ ገዳሜ ውስጥ ገብተን እስፈሪውን ኑሯችንን ለማምለጥ እንሞክራለን።

ቅጥ ያጣ የደስታ ፍላጎት ከቀቢጸ ተስፋም ይመነጫል። ቱሲዲደስ የተባለ የጥንት ግሪክ ጸሐፊ ባንድ ወቅት አቴንስን አጥቅቷት ስለነበረው ወረርሽኝ ጽፏል። ጸሐፊው ዜጎች በበሽታው እንደዝንብ ተራ ሞት እየሞቱ ማለቃቸውን ከዘገበ በኋላ የሚከተውን ይጨምራል፤

"ወረርሽኙ ድንገት ባቴናውያን ላይ የልቅነት ጸባይ አሰፈነ። ባለጸጎች ድንገት ሲሞቱ ድሆች የሞቱ ባለጠጎችን ንብረት ወረሱ። ይህንን የተመለከቱ ሰዎች ጥንት በጓዳቸው ውስጥ ሸሽገውት ያኖሩትን አመላቸውን ወደ አደባባይ አወጡት። ገንዘባቸውን በፍጥነት እየመዘዙ ደስታ ሊሸምቱበት ተጣደፉ። ገንዘብና ሕይወት እኩል ዐላፊ ጠፊ መሆናቸውን አይተዋልና። በጊዜው ሕግ የማክበር ፍላጎት የነበረው አንድም ሰው አልነበረም። በሕይወት ተርፌ ለፍርድ እቀርባለሁ ብሎ የሚያስብ ሰው አልነበረም። በጊዜው ዋጋ ያለው ነገር ጊዜያዊ ፌሽታ ብቻ ነበር። ፈሪሐ እግዚአብሔርም ሆነ ሰው ሠራሽ ሕግ ፋይዳ አልነበራቸውም። ሁሉም ሰው የሞት ፍርድ የተፈረደበት ሰው እድርጎ ራሱን ይቆጥር ስለነበር የስቅላቱ ጊዜ ከመድረሱ በፊት የተገኘችውን ደስታ ለማጣጣም ተሽቀዳደመ።"

የዘመኔ ጀግና እንዲህ የሚል ይመስለኛል፤

"በኔ ዘመንና በጥንት አቴናውያን የቸነፈር ዘመን መካከል መሠረታዊ መመሳሰል አለ። በሁለቱም ዘመኖች ውስጥ ለነገ ተስፋ ማድረግ የሚባል ነገር የለም። ለፍቼ የሠራሁት ቤቱን ባቡር ይሁን ስርጓጅ መርከብ በውል ያልታወቀ ነገር ጥሶት የሚያልፍ ከሆነ ቤት ለመሥራት እንዴት ላቅድ እችላለሁ ? ሰባት ሙቶ

ሺህ ብር የገዛሁትን ቤቴን በክረምት አፍርሶ ደርዘን ጃንጥላ የማይገዛ ፍራንክ ሸጎጥ አድርጎ፣ ቤተመቅደስ እንደገባች ውሻ አካልቦ የሚያባርረኝ ባለሥልጣን ባለበት ሀገር ውስጥ ጎጆ ለምን እቀልሳለሁ። ጌቶች፣ ለችግር ቀኔ ያጠራቀምኩትን ብር በጥጋብ ዘመናቸው የሚወርሱብኝ ከሆነ የባንክ ደብተር የማወጣው ለምንድነው? ልጄ በሕይወት እያለሁ እንደ ማውታ ሊሆን እንደሚችል እያወቅሁ፣ "የዛሬ ዓመት የማሙሽ ልደት" እያልሁ የምዘፍንበት ምክንያት ምንድነው? "ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር" ከሚለው መፈክር በስተቀር ኢትዮጵያን ለዘላለም የሚያኖራት መሠረት መፍረሱን እያወቅሁ ለሚቀጥለው ዓመት እንዴት ሳቅድ እችላለሁ? ተው ባክህ! እኔም እንደጥንቱ አቴናውያን የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት ሰው እኖራለሁ። የመሰቀያው ገመድ አንገቴ ውስጥ እስቲገባ ድረስ የጥንቱ ባላገር ግጥም በቃሌ እወጣለሁ።

"የራብህም ብላ፤ የጠማህም ጠጣ፤  
ከዚህ የተሻለ፤ ምንም ቀን አይመጣ፡፡  
ላገኝ ነው በማለት፤ ሞትኩኝ በሰቀቀን፤  
ሂዶ ሂዶ አለቀ፤ የምጠብቀው ቀን።"





# የላስታ ገጸ-በረከት

የላሊበላ አዳራሾችን በቃላት ወይም በፊልም ለማስረዳት መሞከር አሪፍ ቅኔን በዱዳ ቋንቋ ለመተርጎም እንደ መሞከር ነው። የላሊበላን አዳራሾች ምን ብለን እንጥራቸው?? ካንድ ፀለት የተፈለፈሉ መቅደሶች የሚለው አገላለጽ ያንስባቸዋል። አንድ ሥዕል ከሺህ ቃላት የበለጠ ይናገራል ቢባልም፣ የቱሪዝም ቢሮ ፖስት ካርድ ቤተ-ጊዮርጊስን በወርድ በቁመቱ የማሳየት አቅም የለውም። ቀርበህ ስታየው ሰው ድንጋይን እንደ ላስቲክ እያጣጠፈ፣ እንዲህ ሳይጠጡ የሚያሰክር ነገር መሥራት የሚችል ፍጡር መሆኑን አስበህ ትደነቃለህ። የላሊበላ ሕንጻዎችን ግብጻዊም ይሥራቸው አገው፣ ግሪክም ይሥራቸው አበሻ፣ ሰው ከንቱ ሳይሆን የብርቱዎች ብርቱ ፍጡር ለመሆኑ ማረጋገጫ ናቸው።

የገድለ ላሊበላ ጸሐፊ ላሊበላን መናኝ መነኩሴ ሊያደርገው ይቃጣዋል። ግን ዓለምን የሚንቅ ሰው ስሙን በድንጋይ ላይ አትሞ በዓለም ላይ ዝነኛ ለመሆን ለምን ይጥራል? ላሊበላ ደካማ ሰዎች የተጋነነ ሕልም ነው ብለው ሊያበርኑት የሚችሉትን ሐሳብ ወደ እውነታ የቀየረ ብርቱ ሰው መሆን አለበት።

እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ባላገሮች ከየማእዘኑ በእግርና በበቅሎ ወደ ላሊበላ የሚገሰግሱት ጽድቅን ፍለጋ ነበር። ሀገር ቤት ሳለሁ፣ የጥምቀት ለታ፣ አንድ ባልቴት፤





"እኔስ ሄጃለሁ፤ ላሊበላ  
እንግዲህ ዲያብሎስ፤ ምን ትበላ" ብላ ትዘፍናለች።

ጎረምሳው ምእመን ደግሞ ዲያብሎስን ወክሎ፤

"እኔስ አላጣም ልክስክስ  
እኔስ አላጣም ልክስክስ  
ሮብ ለት ማለዳ ማንካ የምትልስ።" ብሎ ይመልሳል።

የባላገር ምእመን ላሊበላን በመሳሚ ብቻ መንግሥተ ሰማያት እገባለሁ ብላ ማሰቧ ያስቀኝ ነበር። አሁን ግን እንደተሸወድሁ ገብቶኛል። እምነቱን ወደ ጎን እንተውውና ላሊበላን ማየት የሚያጎናጽፈው ፍስሀ ራሱ መንግሥተሰማያት ካልሆነ ምን ሊሆን ነው? የላሊበላን አዳራሾች ማየትና መዳሰስ በቀላሉ የማይበርድ ምርቃና ያጎናጽፋል።

እኔ በላሊበላ ቦታ ብሆን ኖሮ፣ በዚያ የቋጥኝ ማጎደር በሆነ ሀገር ውስጥ ስሡፍር መጀመርያ ወደ አእምሮየ የሚመጣው ከአካባቢው ርቆ መሰደድ ወይም ወደ ለምለሙ የጎረቤት ሀገር መዝመት ይሆናል። ላሊበላ ግን እንደ እኔ አይደለም። ከዚያ ደነዝ ቋጥኝ ላይ ብሩህ መንደር አፈለቀ። ይህንን አድርጎ በለምለም ሀገር የሚኖሩ ሰዎች ወደ ርሱ ሰፈር እንዲሰደዱ ማድረግ ቻለ። ከስምንት መቶ ዓመታት በኋላ የላሊበላን አርአያ የተከተለች ሀገር ብትኖር እሥራኤል ናት። አስቀያሚውን ውብ ማድረግ፣ ቅርጽ አልባውን ቅርጽ ማስያዝ፣ ከምድረበዳ ውሃ ማፍለቅ እንደሚቻል ማሳየት የላስታውያን አብነት ነው።

የላሊበላ ሕንጻዎች ማሩን የተገፈፈ ቀፎ ናቸው ማለት ይቻላል። ባዶ ናቸው። ካዳራሾቹ መካከል ጥቂቶቹ ቤተመንግሥት እንደነበሩ ማወቅ ተችሏል። ታድያ ንጉሡና ንግሥቲቱ የተጠቀሙባቸው እቃዎች እንደ ሕንጻዎቹ የተራቀቁ ይሆኑ?

ላሊበላ በምን ዓይነት አልጋ ላይ ሲተኛ ኖረ? ቁርሱን በምን ዓይነት ሰሀን ይበላ ይሆን? ሚስቱ መስቀል ክብራ ማለዳ ከምኝታዋ ተነሥታ ፊቷን በምን ታይ





ነበር? ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሰጠኛል ብየ ያሰብኩት የላሊበላ ሙዚየምን መጎብኘት ነበር። ግምቴ የተሳሳተ መሆኑን ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም። ሙዚየሙ ውስጥ ከተደረደሩት የመስታወት ሳንዱቆች ባንዱ ውስጥ የተቀመጠ አንድ የመጥረቢያ ዛቢያ ተመለከትሁ። የመጥረቢያውን ምንነት እንዲያስረዳኝ ነጠላውን እመሳቅሎ ለብሶ የቆመውን ትሁት አስጎብኚ ጠየቅሁት።

"ይህ እንግዲህ ንጉሥ ላሊበላ ቤተመቅደሶችን ለመጥረብ የተጠቀመበት መጥረቢያ ነው" ብሎኝ አረፈ።

"በዚህ መናኛ መጥረቢያ እንኳን ያንን የሚያክል ቋጥኝ፣ የበሰበሰ ጉቶ መፍለጥ ይቻላል?" በማለት ጥርጣሬየን ላስጎብኚው አካፈልኩት።

"እንግዲህ እኛ ተችሎታል ብለን እናምናለን" ብሎኝ ትክሻውን ሰበቀ።



ዐለፍ ስል በሌላ መስታወት ውስጥ ተደፍቶ የተቀመጠ የነሐስ ደወል ተመለከትሁ። በደወሉ ወገብ ላይ፤ "ንጉሥ ዳዊት" የሚል ያማረ የፊደል አጣጣል ያለው ጽሑፍ ተፈልፍሎበታል። አንጥረኛውን የሚደንቅ ባለሙያ መሆኑን መመስከር አይከብድም።

አስጎብኚው ያየሁትን እያየ ቀጠለ፤ "ይሄ ደወል ከንጉሥ ዳዊት ለላሊበላ በስጦታ የተላከለት ደወል ነው" አለ።

ዕብራዊው ንጉሥ ዳዊት ስሙን በግእዝ ፊደል ደወል ላይ የሚያስቀርጽበት ታሪካዊ አግባብ እንደሌለ ስለማውቅ ያስጎብኘውን አስተያየት ቸል አልኩት። ደወሉ የኢትዮጵያዊው ንጉሥ የዳዊት ሊሆን ይችላል።

ዞር ዞር ስል፤ የሚዚየሙን መደርደርያ ያጨናነቁት፣ በኋለኛው ዘመን በስጦታ መልክ ለላሊበላ ቤተመቅደስ የተበረከቱ ንዋያተ-ቅዱሳንና ንዋያተ-ነገሥታት መሆናቸውን አረጋገጥሁ።

ኢትዮጵያ የምትባል መከረኛ ሀገር ስንት ሞገድ ተሻግራ እዚህ እንደ ደረሰች የሚያውቅ ሰው፣ በላሊበላ አዳራሾች ውስጥ የነበሩት ቁሳቁስ ወደዚህ ዘመን አለመድረሳቸው አይገርመውም። የዛጉዬ ነገሥታት በሸዋ መፈንቅለ-መንግሥት አድራጊዎች ስልጣናቸውን ሲቀሙና መንግሥት ሲዘዋወር፣ ሊጠፉና ሊወድሙ የሚችሉትን ብርቅ ንብረቶች እናስብ። እንድያውም አዳራሾቹን በነበሩበት ቆመው ያገኘናቸው በበቅሎ ለመጫን ስለማይመቹ ወይም በእሳት ማቃጠል ስለማይመቹ መሆን አለበት።

ቤተመቅደሶች እንዴት እንደተሠሩ የሚናገር መጽሐፍ ሳይደርሰን መቅረቱ እንደ እግር እሳት አያንገበግብም? ፖርቱጋሉ መንገደኛ አልቫሬዝ፣ እነዚህ ከድንጋይ ተጠርበው የተሠሩ ቤተክርስትያኖች ሁሉ በሀያ አራት ዓመት ውስጥ ተሠርተው መጠናቀቃቸውን የሚገልጽ ጽሑፍ መኖሩን ያገኑ ሰዎች እንደነገሩት መዝግቧል። የተባለው መጽሐፍ ዛሬ ድራሹ የለም።

በኋለኛው ዘመን የተጻፉ ገድሎች ሕንጻዎቹን የመላእክት ሥራ ያደርጓቸዋል። ደበበ ሰይፉ በዚህ ተገርሞ፤





"የሮሀ መቅደሶች
ዝነኛ ሕንጻዎች፤ ከዐለት ማህጸን ፤ተፈልፍለው የወጡ፤
ነው አሉ በመላእክት፤ ከአርአያም ወርደው፤ በሌሊት የመጡ።" ብሎ
ገጥሟል።

መላእክት ይህንን መለኮታዊ ፕሮጀክት በሀያ አራት ሰአት ማጠናቀቅ እየቻሉ ሀያ አራት ዓመት የሚለፉበት ምክንያት ሊኖር አይችልም። አልቫሬዝ በጠቀሰው መጽሐፍ ውስጥ የተገለጠው ዘመን የላሊበላ አዳራሾች የሰው የረጅም ጊዜ ልፋትና ጥረት ውጤት መሆናቸውን ያሳያል።

## የግራኝ ጉብኝት

ግራኝ አህመድ ባንድ ወቅት ላሊበላን በቁጣው ጎብኝቶት ነበር። ዐረብ ፋቂህ የተባለው ጸሐፊ ያይን ምስክርነቱን ሲሰጥ እንዲህ ይላል።

"አህመድ ጧኦት አምላኪዎች ላሊበላ በተባለው ቤተክርስትያን ዙርያ መከማቸታቸውን ሰማ። ተራሮችን አቆራርጦ ደረሰባቸው። ቤተክርስትያኒቱ ዘንድ ሲደርሱ መነኮሳቱ ለመሰዋእትነት ተዘጋጅተው አገኛቸው። አህመድ ቤተክርስትያኒቱን ተዟዙሮ ሲጎበኝ አቻ አላገኘላትም። አምዶቹና ሕንጻው ከዐለት ተፈልፍሎ የወጣ ነበር። በሕንጻው ውስጥ አንዲት የእንጨት ጉማጅ አትገኝም።

"ኢማሙ መነኮሳቱን ጠርቶ፤ እንጨት ለቅመው እንዲመጡ አዘዛቸው። ከዝያ እንጨቱን ደምረው አነደዱ። እሳቱ ሲንቀለቀል፤ አህመድ፤ 'ከእናንተ አንድ ከእኛ አንድ ሰው ወደ እሳቱ ይግባ' በማለት ሊፈትናቸው ተናገረ። የመነኩሴዎች አለቃ፤ 'በደስታ እገባለሁ' አለ። ይሁን እንጂ አንዲት ሴትዮ ብድግ ብላ፤ 'እርሱ የወንጌል መምህሬ ነው። ከኔ በፊት ሊሞት አይገባውም'





ብላ ራሷን ወደ እሳቱ ወረወረች። ኢማሙም፤ 'ጎትታችሁ አውጧት' በማለት አዘዘ። ጎትተው ሲያወጧት ከፊል ፊቷ ተቃጥሎ ነበር።"

በዚህ ታሪክ ውስጥ ብዙ አስገራሚ ነገሮችን እናገኛለን። አስቡት፤ አንድ መነኩሴ፤ በድል አድራጊ ጠላቱ ፊት፤ መሬት ተከፍታ ብትውጠኝ በሚያሰኝ ሁኔታ ውስጥ የእሳት ግብዣ በደስታ ለመቀበል ሲዘጋጅ እናያለን። እንዴት ያለ ወንድ ነው ! ብለን አድንቀን ሳንጨርስ ሴትዮዋ ከመምህሬ ያስቅድመኝ ብላ ዘላ ወድ እሳት ገብታለች። የሐሳብ ኃይል፤ የእምነት ኃይል እንግዲህ ይህን ያህል ነው። እምነት፣ የሚንቀለቀለውን ደመራ፤ በንጹህ ውሃ እንደ ተሞላ የመዋኛ ገንዳ ዘለህ እንድትገባበት የሚያስችልህ ልበሙሉነት ይሰጥሀል።

የግራኝ አህመድ ነገር ይባስ። የቀለደው ኢደገኛ ቀልድ ወደ እውነት ሲለወጥ ቢያይ መቋቋም አቃተው። "ጎትታችሁ አውጧት" በማለት ጮኸ። እውን ይህ ቃል የወጣው ከግራኝ ነው ወይስ የታሪክ ጸሐፊው ጃሮ ተጭበርብሮ ነው? የግራኝ ነው ብለን እንመን። አንድ ሰው ምንም ግፈኛ ቢሆን፣ በምስጢር ኪሱ ይዟት የሚዞር ስሙኒ የምታክል ርህራሄ አያጣም።

የላሊበላ ምድር የአህመድ ግራኝ ብቻ ሳይሆን የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የእግር ዱካም ዐርፎበታል። ግርማዊነታቸው፤ በሁለተኛው የጣልያን ጦርነት ላይ፣ ወደ ላሊበላ መጥተው፣ ሁለት ቀን ሙሉ እንጀራ ባፋቸው ሳይዞር፣ ውሃ በጉሮሯቸው ሳይወርድ፣ ሱባኤ ገብተው ነበር። እናም፣ የወደቀ ሞራላቸውን በጸሎት ድጅኖ አስነሥተው፣ የወኔ ነዳጃቸውን ሞልተው ባልሞት ባይ ተጋዳይ ከተፍጨረጨሩ በኋላ ወደ ውጭ ሀገር መርሸዋል። የላሊበላ ውቃቢ፤ ድል ባይሰጣቸውም፣ የስልታዊ ማፈግፈግ ጥበብ አልነፈጋቸውም። ላሊበላ ራሱ ከስድስት መቶ ዓመታት በፊት ከወንድሙ ጋር ሲጣላ፣ ወደ ኢየሩሳሌም አፈግፍጎ፣ ሰራዊት አደራጅቶ በመመለስ ድል ነስቷል ይባላል።





## "እርጅና መጣና ድቅን አለ ፊቴ"

"የቅዱስ ላሊበላ ሕንጻ እንደ ሙሴ ድንኳን እርጅና አይነካትም። ወይም አሕዛብ እንዳፈረሱት እንደ ሰለሞን ምኩራብ አይደለችም። ሰማያዊት ኢየሩሳሌም በምድር ላይ እስከትታይ ድረስ የቅዱስ ላሊበላ ሕንጻ አትጠፋም አታረጅም።"

ይህን የሚለው የገድለ ላሊበላ ደራሲ ነው። ደራሲው የላሊበላ አዳራሾች የመለኮት እጅ ሥራ ናቸው ብሎ ስለሚያምን፣ ራሱ እግዜሩ በመጨረሻው ቀን እስኪያጠፋቸው ድረስ ጸንተው እንደሚቆሙ ርግጠኛ ሆኗል። ርግጥ ነው፤ እኒያ ግሩም ጥበቦች፣ ለሰባት መቶ ዓመታት ያክል በተፈጥሮና በሰው ትግል ተፈትነው አይበገሬነታቸውን አስመስክረዋል። ያም ሆኖ የጊዜ ገልቱ ክንድ፤ በኃይለኛ ክንዱ እንዳዳከማቸው ማየት ይቻላል። ቤተጊዮርጊስን በወርድ በቁመቱ የወረረው አረንጓዴ ሽበት ሕንጻው ምን ያህል እዱብ ድንቅ ቢሆን ከእርጅና እንዳላመለጠ ምስክር ነው። ለነገሩ፤ ፍጡነ ረድኤቱ ዩኔስኮ በአዳራሾች ጣርያ ላይ የዘረጋው ግዙፍ የዝናብና የጸሓይ መከላከያ ጃንጥላ ለአዳራሾች እድሜ ማራዘሚያ ሆኖ ለልጅ ልጆቻችን እንደሚያቆይልን ተስፋ አለኝ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ሌላው ድንቅ ክስተት የሆነው ያከሱም ሐውልት፤ በሁለት ግዙፍ የብረት ምርኩዞች ባይደገፍ ኖሮ ቆሞ አይገኝም ነበር። እውነታውን እንጋፈጠው። ከዋክብት እንደ ኮቸሮ በሚሻግቱበት ህዋ ውስጥ የድንጋይ ሐውልቶች ለዘላለም ጸንተው እንዲኖሩ መመኘት ተላላነት ነው። የድንጋይ ሐውልቶች ለዘላለም ጸንተው እንዲኖሩ መመኘት ተላላነት ነው። መልክቴ ግልጽ ነው። በጉብዝናህ ወራት በእርጅና ላይ ያሉትን ሐውልቶች ጎብኝ።

## የቅድስና ቀለም ነጭ ነውን?

በላሊበላ መቅደሶች ውስጥ በቅርብ ጊዜ የገቡ ባውሮፓውያን ሠዓሊዎች የተሣሉ የቅዱሳን ሥዕሎች ማየቴ የፈጠረብኝን ቅሬታ በዛው ላገኘኋቸው አንድ ቄስ አልሸሸግሁም። ቤተመድኅኒዓለም ውስጥ ጣቱን በሽጉጥ ቅርጽ የቀሰረ፤ ሜል ጊብሰንን የመሰለ ባለሰማያዊ ዓይን ፈረንጅ ኢየሱስ ሆኖ ቀርቧል። ይህ ቅዱሳንን ነጭ አድርጎ የማሰብ አባዜ በአክሱም ሙዚየም ውስጥ በሚገኘው የያሬድ ሥዕል ላይም ተንጸባርቋል።

ኢትዮጵያ ከነጭ ሊቀጳጳስ ይልቅ በጥቁር ሊቀጳጳስ መመራት እንደሚሻላት ለመጀመርያ ጊዜ ሐሳብ ያቀረበው ሐርቤ የተባለው የላሊበላ ወንድም ነው። ሐርቤ ቅድስናን ከነጭነት ጋር የሚያይዘውን ግብጻዊ የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ የታገለ ታላቅ ሰው ነው። ከላስታ ቤተመቅደሶች ውስጥ ባለሰማያዊ ዓይንና ባለ ወርቃማ ጸጉር ቅዱሳንን ማስቀመጥ የዚህን ሰውየ ትግል ማቃለል ይመስለኛል። ይህን አመለካከት የኢአማኒ ነቀፋ አድርጎ የሚያስብ ምእመን ካለ የሚከተለውን ያባ ጎርጎርዮስ ጥልቅ አስተያየት እስታውሰዋለሁ።

"በራሳችን ሠዐሊዎች የተሣሉና የራሳችንን የኪነጥበብ የሚመስከሩ ሥዕሎች በቤተክርስትያን በብዛት አይታዩም። በተለይ በከተማ ሕዝቡ እየገዛ ለቤተክርስትያን የሚሰጠውና በግሉም በቤቱም የሚይዘው የላቲንና የግሪክን ኪነጥበብ የሚያሳዩ የሚመስከሩ ሥዕሎችን ነው። ይህ በኢትዮጵያ ትውፊታዊ ኪነጥበብ እንዲለወጥ ካህናት ለራሳቸው ተረድተው ምእመናንንም ማስረዳት አለባቸው። ሥዕሎችም በተቻለ መጠን ደበስ ባለ ቀለም መሣል አለባቸው። ጥቁርን በክፉ፤ ነጭን በደህና ነገር መሥሎ ማቅረብ ከነጮች የተወረሰ ነውና"
(የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ታሪክ፤ ገጽ 10)

የሸዋው ጳጳስ ይህንን በሳል ምክር ከሰጡ አርባ ዓመታት አልፈዋል። ምክራቸው የተደመጠ አይመስለኝም።





## ትናንትና ዛሬ

በላሊበላ ከተማ፤ በድሮና በዘንድሮ መካከል ያሉ ብቸኛ ድልድዮች ንቦች ናቸው። የዛሬ ስምንት መቶ ዓመት ገደማ አንድ ጉደኛ ሕጻን ሮሀ ውስጥ ተወለደ። ንቦችም ወረሩት። ይህን የተመለከቱ ወላጆቹ በአገውኛ ላሊበላ ብለው ጠሩት። ላሊበላ ማለት የንብ ማረፍያ ማለት ነው። ወደ ከተማይቱ በገባሁበት ሰሞን ብዙ የኢትዮጵያ ከተሞች የሰማእታት መታሰቢያ ለመገንባት በመሽቀዳም ላይ ነበሩ። ላሊበላ ግን የማር ሙዚየም ስትገነባ አገኘኋት። ንጉሥ ላሊበላን የወረሩት ንቦች፤ ዛሬ በከተማው ዝነኛ የሆነውን ቶርፒዶ ጠጅ ቤት ዙርያ ያንዣብባሉ።

ላሊበላ ቅዱስ ሀገር ነው። የጠጅም ሀገር ነው። ቅምቀማና ቅድስና የሚጋጩ ሚመስላችሁ ካላችሁ ተሳስታችኋል። የግዜር ምርጦች እነኖህ፤ እነሎጥ፤ እነሰሎሞን ይቀመቅሙ ነበር። ኢየሱስ በቃና ዘገሊላ ተገኝቶ የውሃ በርሚሉን ወደ ወይን በርሚልነት ቀይሮት ነበር። የሸዋው ንጉሥ ሣሕለ ሥላሴ፤

"ከትልቁ ዛፍ ከማዎቱ አጠገብ ተቀምጠው ጠጅ በቀንድ ቀርበ (ላቸው) ሠንጠረዥ እየተጫዎቱ አንች ሀገር ዳዋ ሰፍሮብሻል ኋላም የልጅ ልጄ ቤት ይሠራብሻል ብለው ተናግረው ነበር"[4]

ሣሕለ ሥላሴን ትንቢት ያናገራቸው ጠጁ፤ ይሁን መንፈስ ቅዱስ፤ አልታወቀም። ብቻ ትንቢታቸው ሰምሮ፤ "አንች ሀገር"፤ የተባለችው አዲስ አበባ ሆነች። አዲስ አበባን ለጊዜው ትተን ወደ ላሊበላ እንመለስ።

"አሸንተን ማርያም" ተራራ ላይ ወጣሁና ከተማይቱን ዝቅ ብየ ፈለግኋት። ከተራራው ላይ ተንከባሎ የወደቀ ግዙፍ ብርሌ ስብርባሪ መሰላ ታየችኝ። ቆርቆሮ ቤቶችና የሰኔል ጃንጥላ የመሳሰሉ ጎጆ ቤቶች ተሰባልቀው ተደርድረዋል። የትናንቱን መዓዛ ፈለግሁት። በርግጥ በላስታ ነገሥታት ስም

[4]ገብረሥላሴ፤ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ፤(ገጽ 138)





የተሰየሙ የንግድ ምልክቶች በየቦታው አሉ። የቤተ ጊዮርጊስን ሥዕል በየሄድክበት ታየዋለህ። ግን አስተካክሎ የሚሥለው የለም። ሰካራም የረገጠው የኩብሪት ቀፎ የሚመስል የተወለጋገደ የቤተጊዮርጊስ ሥዕል ማየት የተለመደ ነው።

ባንጻሩ ባክሱም ከተማ በየቡና ቤቱ ግድግዳ ላይ ቅርስና ባህልን ያሳያሉ ተብለው የተዘጋጁ ሥዕሎችን ታያለህ። ለምሳሌ በአክሱም ሐውልት ፊትለፊት ቁምጥ ብላ ጥጥ የምትፈትል ባለሹርባ ቆንጆ ሴት ፖስትካርድ የትም ይታያል። እንዝርት አያያዝዋ እንደ አይስክሬም ነው። እና ፎቶ ማንሳቱ ሲጠናቀቅ፤ እንዝርቷን አሽቀንጥራ፤ ላፕቶፕዋን ወደ ጭኗ የምትመልስ ያዲስ አበባ ሞዴል መሆኗን መገመት አያቅትም።

ባክሱም ከተማ ከሚገኙ ሆቴሎች ባንዱ ያየሁት የንግሥተ ሳባ ሥዕል አሁንም ይመጣብኛል። ንግሥቲቱ ሹርባ ከመሠራቷና ያበሻ ቀሚስ ከመልበሷ ውጭ አንጀሊና ጆሊን ትመስላለች። እንደ ላላ አምፖል ካፎቱ ለመውደቅ በቋፍ ላይ ያለ ትልልቅ ዐይን ያላቸው አጃቢዎች ይከተሏታል። ንጉሥ ሰለሞን ፈገግ ብሎ እየጨበጠ ይቀበላታል። ለነገሩ ማን የሚያደርገውን ሲያስብ ፈገግ ማለት ሲያንሰው ነው!! ከንግሥተ ሳባ አጃቢዎች አንዱ የተጫኜ ግመል ልጓም ይዞ አዳራሹ ማኸል ላይ ቆሟል። ንግሥተ ሳባ ሰለሞንን ለማየት እጅግ ከመጓጓቷ የተነሣ ከነጫማዋ ብቻ ሳይሆን፤ ከነግመሏ ነው ወደ ቤተመንግሥቱ የገባች። ሠዓሊው የማኸል ሀገር ሰው መሆኑን የጠረጠርኩት የግመሉን መልክ ላይ ነው። አላየንም እንዲህ ያለ ግመል!! ላባውን ያራገፈ ሰጎን ይመስላል። ግመል መሆኑን የተረዳሁት ከጀርባው ላይ ያለው አቆማዳ ፍንጭ ስለሰጠኝ ነው።

በሌላ ቦታ ንግሥተ ሳባና ሶሎሞን ራት ሲበሉ ይታያል። ሳባ ሶሎሞንን እያጎረሰችው ነው። እስከ አንባር ማሰርያዋ ድረስ ያለው መዳፏን አፉ ውስጥ ሰላጠለቀችው እንጥሉን እየቆረጠች እንጅ እያጎረሰችው አትመስልም። ወይም ስታጎርሰው፤የጠፋባትን የጣት ቀለበት አፉ ውስጥ እየፈለገች መሆን አለበት። ደሞ ከሥዕሉ ሥር "ጠቢቡ ሰለሞን ንግሥተ ሳባና ከሠራዊቱ ጋር ግብር ሲያገባ" ይላል። ከንግሥተ ሳባ ውጭ ያሉት አራት ሰዎች ስለሆኑ ከቦዲጋርዶቹ





ጋር ተብሎ እንዲስተካከል ሐሳብ አቀረብሁ። በሥዕሎች ላይ እቃቂር ማብዛቴ ይገባኛል። ለነገሩ እንደኔ ካለ ከከሸፈ ሠዐሊ ከዚህ ሌላ ምን ይጠበቃል??

በነገራችን ላይ ያክሱምም ሆነ የላስታ ነገሥታት የራሳቸውን ምስል የማምለክ ልማድ የነበራቸው አይመስለኝም። ርግጥ ነው አክሱሞችን ፊታቸውን ኪሳችን ውስጥ ይዘን እንድንዞር መልካቸውን በሳንቲም ላይ ያትሙት ነበር። ይሁን እንጂ መልካቸውን ለዘላለም የሚያጋንን ሐውልት የማስገንባት እድል እያላቸው አላደረጉትም። የመሪ ምስል አምልኮ የዘመናችን ልዩ ክስተት ይመስለኛል። ባክሱም ከተማ፤ "ታሪክን የመለሰ ጀግና" ከሚለው ግብዳ ፖስተር ጀምሮ ሳር ቅጠሉ የመለስ ዜናዊ ፎቶ ነው። ከመሌ ፎቶ ቀጥሎ፤ ባንድ እጁ መስቀልን ገትሮ ይዞ በሌላ እጁ ዳዊት የሚደግም ቄስ ምስል በሁለተኛነት ይመራል። ይሄ ከሻይ ቤት እስከ አሉላ አባነጋ አየር ማረፍያ ድረስ የተንሰነሰ ቄስ ማን ይሆን? የመለስ ዜናዊ ንስሀ አባት ይሆን?

ላሊበላ ታዋቂ ሰዎችን ማፍራቷን አላቆመችም። ከነዚህ አንዱ በምርጫ ዘጠና ሰባት መባቻ ጀግና የነበረው፤ በምርጫው ዋዜማ ግን "የተገለለ ነቢይ" የሆነው ልደቱ አያሌው ነው። የምርጫ ዘጠና ሰባት ጦስ ልደቱን በሄደበት ያሳድደዋል። ባንድ ወቅት ልደቱ ከጓደኛው ጋር ምግብ ቤት ውስጥ ምሳ በልቶ ጨርሶ እጁን ታጥቦ ወደ ቦታው ይመለሳል። በቦታው የነበረው አንድ ተራቢ ተመጋቢ ብድግ ይልና ወደ ልደቱና ጓደኛው ቀረብ ብሎ፤ "የእጅ መታጠቢያው በየት በኩል ነው?" ይላቸዋል። ልደቱ ተሽቀዳድሞ፤ "በዚህ በኩል" ብሎ በትህትና ይጠቁመዋል። ያን ጊዜ ተራቢው፤ "አንተን አላምንህም። እሱን ነው የጠየቅሁት" ብሎ መለሰ። የፖለቲካ አቋሙን ትተን ልደቱ እንዲህ ዐይነቱን መራራ ንጠመኝ ተጋፍጦ፤ የእሾህ አክሊል ደፍቶ መኖር መቻሉ ያስደንቀኛል።

አባ ብርሃነ ሥላሴም የላሊበላ ሰው መሆናቸውን ሰምቻለሁ። አባ ብርሃን ማለት መንግሥቱ ኃይለማርያም የመጨረሻውን ስብሰባ ባደረገበት ቀን ልክ ልኩን የነገሩት ደፋር የቀይዳማ መነኩሴ ናቸው "የኢትዮጵያን ሕዝብ በደም ባሕር ማግደው ቆስቁሰው፤ የርስዎን አስተዳደር ሕዝብ የማያምንበት ሆኖ ከተገኘ፤ ከኢትዮጵያ አንድነት በኋላ ተወያይተን ርስዎ በወታደርነት ደረጃ ያድራሉ። ወይም ያገልግሎት ዘመንዎ ተቆጥሮ ጡሮታ ይወጣሉ።...ነገር ግን

ባሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያን አምሳ ሚሊዮን ሕዝብ ማግደው፣ ቆስቁሰው፣ በርስዎ ኃላፊነት 16 ዓመት ሙሉ መርተው ሳያረጋጉት፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለሣት ዳርገው ባሁኑ ጊዜ የቴዎድሮስን ጽዋ ከመጠጣት በቀር ሌላ እድል የለዎትም። ይችን እድል እንደማያበላሹ አምናለሁ" ብለው ፊት ለፊት ሲነግሩት በቴቪ. ተመልክተናል።

መንጌና ጓደኞቹ አቡነ ቴዎፍሎስን በገመድ አንቀው ማሰናበታቸውን የሚያውቅ ሰው፣ ያባ ብርሃነሥላሴ መትረፍ የእድል ጉዳይ መሆኑ ይገባዋል። ባገራችን ጀግና ተብሎ የሚዘፈንለት ወይም ሐውልት የሚሠራለት ታጥቆ የሚገድል ብቻ ነው። ባለስልጣኑን ደፍሮ የሚገስጽ ሰው ብርቅ ጀግና መሆኑን መቀበል አለብን። እንዲህ ዐይነት ሰው ሲገኝ የእብነ በረድ ሐውልት እንኳ ባንሠራለት አንዲት አንቀጽ እናስተርፍለት።

## ሲመሽ

ላሊበላ በምሽት ታሳዝናለች። ተራራና ሸለቆ አደላዳዩ ጨለማ ይወርድና ይውጣታል። ጅንኑ የታቦር ተራራ በጽልመት ወቅያኖስ ውስጥ ይሰጥማል። የመንገድ መብራቶች ባንድ ሰፌ ማቅ ላይ የፈሰሱ አብረትሎች መስለው ጭልጭል ይላሉ። ልጆች በጨረቃ ብርሃን፣አቧራ ላይ የሀይላንድ ላስቲክ ጠርሙስ እየሰጉ ይጫወታሉ። ላሊበላ በምሽት ሳያት፣ ወደ አእምሮየ የመጣችው ቬጋስ ናት። ቬጋስ ከአሜሪካ ከተሞች በቁረሰት ማራኪነቷ ግንባር ቀደም ናት። ቬጋስን በምሽት ምን ትመስላለች የሚለውን የሚገልጸት በዘመኑ መሳፍንት ላንዲት ዝነኛ ቆንጆ የተዘፈነ ዘፈን ነው፤

"ከወዴት መጣሽ !
ከወዴት ከወዴት
ፊትሽ ያበራል በሌት"





የቬጋስ ፊት በሌት ያበራል። ገና ካውሮፕላን ሆድ ውስጥ ሆነህ፣ በመስኮት በወፍኛ ስትመለከታት ኮረንቲ ብርሃኗ የኤርታሌን የሣት ኩሬ መስሎ ተንጣሎ ይጠብቅሀል። ከዝያ ምድር ወርደህ ስትቀላቀላት፣ ድርና ማጓ ብርሃን ሆኖ ታገኘዋለህ። ከሀዋ ላይ ተገንጥላ የወደቀች የኮከብ መንደር (ጋላክሲ) ትመስላለች። የቨርጂኒያው ወዳጄ በኀይሉ ዘሪሁን፣ቬጋስን ጎብኝቶ ስመጣ፤

"ቬጋስ እንዴት ናት" ሲለኝ

"ትጣፍጣለች"አልኩት።

"ወትሮም ኀጢአት ጣፋጭ እንደሆነ የታወቀ ነው።" ሲል መለሰልኝ።

ቬጋስ፣ ቢደባባይ ወሲብ የምትቸረችር ሀገር በመሆኗ የኀጢአት ሀገር ትባላለች። ግን ቬጋስን የመሰለ የኀጢአት ሀገር ብርሃን አልብሶ ላሊበላን የመሰለ ቅዱስ ኩተማ በውድማ ጨለማ የሚያዳፍን አምላክ ምንድነው?

ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የላሊበላ የገቢ ምንጭ በማማለል ላይ የተመሠረተ ነው። ላሊበላን የሳመ ምእመን መንግሥተ ሰማያት መግባት ብቻ ሳይሆን፣ እስከሰባት ትውልድ ይማርለታል የሚል ቃልኪዳን አለ። በዚህ የምታምን ሴት ባሏን ጥላ ብቻዋን ገስግሳ ትመጣና

"እዛው ማርልኝ ያንን ግትቻ
ይገፍው እንዳልመጣ የለኝ ማንገቻ" ብላ ትዘፍናለች።

ባል ብቻውን ከመጣ፤

"እዛው ማርልኝ ያችን እሳት
ይግፍት እንዳልመጣ ነገሩ አያደርሳት" በማለት ይዘፍናል።

ቅዱስ ላሊበላም በኒህ ዘፈኖች እየተዝናና በውክልና መማሩን ይቀጥላል። በዚህ ዐይነት ከየማእዘኑ የሚተሙ ምእመናን የሚገኘው ስጦታና የስእለት ንብረት የደብሩ ኢኮኖሚ መሠረት ነበር። አሁን እምነት ሲደበዝዝ፣ ዕውቀት





ሲጨምር፣ የምእመናን ቦታ በቱሪስቶች ተተክቷል። ካንድ ፈረንጅ ቱሪስት በነፍስ ወከፍ አምሳ ዶላር ይገኛል። የገቢውን ትልቅነት መገመት ይቻላል። ታድያ ዶላሩ የት ይገባል? የላሊበላ ኪራይ ሰብሳቢ ማነው? የከተማዋ ደካማ መንገዶችና መናኛ ቤቶች ከተማዋ የዶላሩ ሽታ እንደማይደርሳት ጮክ ብለው ይመሰክራሉ።

በላሊበላ በሀያ ሦስት ዓመታት ውስጥ በመንግሥት የተገነባ ነገር ካለ የመቀላ ጀግኖች ሆስፒታል ነው። በመጀመርያ የፊደል ግድፈት መስሎኝ "የመቅደላ ጀግኖች መታሰቢያ ሆስፒታል" በሚል አነበብሁት። ወድያው ግን፣ መታሰቢያው ለገብርየና ለቴዎድሮስ ሳይሆን ኢዮብና ዘርጋው ለተባሉ የኢህዴን ጀግኖች መሆኑ ተነገረኝ። የኒህ ጀግኖች መስዋእትነት በፓርቲያቸው ስም ላይ የተገለጸውን ዲሞክራሲ ማስገኘት አልቻለም። ያም ሆኖ ተቃውሟቸውን በሰላማዊ መንገድ የሚገልጹ ዜጎች በፖሊስ ተደብድበው ሲቆስሉ የሚታከሙበት አሪፍ ሆስፒታል ለማስገንባት ችለዋል።

ላሊበላን ልሰናበት አንድ ቀን ሲቀረኝ፣ ከላሊበላ ወዳጆቼ ጋር ከአሸትን ተራራ እግር ሥር ከሚገኘው አደባባይ ላይ ቆመን፣ እንደ ዝሀ ዘጊ ብቻውን የሚመላለሰውን የከተማይቱ ብርቅ ባጃጅ እንጠብቃለን። ድንገት ባቅራቢያው ካለው ጣቢያ ሁለት ፖሊሶች ወጥተው መንገዱ ዳር ወደ ተኙት የጎዳና አዳሪ ልጆች ሲራመዱ አየሁ። አንደኛው ፖሊስ፣ አንዱን ብላቴና ማጅራቱን ጨምድዶ ካስነሳው በኋላ በከስክስ ጫማ ረገጠው። ልጁ እያለቀሰና፣ እያነከሰ ለመሮጥ ሲሞክር ፖሊሱ እየተከተለ ይነርተዋል። ልጁ ምን ቢያደርገው ነው ያልጠና ሰውነቱን ጉቶ እንደ እንቁላል የሚጨፈልቅ በሚመስል ከስከሱ የሚረግጠው? ለነገሩ ልጁ ምንም ቢሠራ ፖሊሱ የመደብደብ መብት አልነበረውም። የማደርገው ቢቸግረኝ፣ ሞባይሌን ካሜራ አመቻችቼ ወደ ፖሊሶች አነጣጠርሁ። ለወገኑ ጥቃት የሚቆረቆር፣ በምኒሽር ፋንታ ካሜራ አልሞ የሚተኩስ አበጀ በለው መሆኔ ነው።

አጠገቤ ከቆሙት ወጣቶች መካከል አንዱ አስጠነቀቀኝ፤

"ተው! ታሳፍሰናለህ!! አንተ ብትታሠር ደራሲያን ማኅበር ይደርስልሀል። እኛ ግን ጊዮርጊስ እስኪደርስልን መሰቃየታችን አይቀርም"





እኔ ብታሠር የደራሲያን ማኀበር እንደማይደርስልኝ ትውስ አለኝና ሞባይሌን ወደ ኪሴ መለስኩት። የሚደበደበውን ልጅ እሪታ ከጀርባየ አድርጌ ወደ ባጃጄ ገባሁ።

ቀጣይዋን ምራቂ ማስታወሻ የጨመርኳት ላሊበላን ተሰናብቸ አዲስአበባ ኩተመለስሁ በኋላ ነው።

በገድለ ላሊበላ ውስጥ አንድ ቦታ ላይ፣ ላሊበላ ሕንጻዎችን ለማሳነጽ በተነሣበት ጊዜ ከቦታው የሚነሡ ሰዎች ተገቢውን ካሳ እንደተከፈላቸው፣ እንዲሁም ሠራተኞች ለላባቸው ዋጋ የሚሆን ደመወዝ ይቆረጥላቸው እንደነበር ተጽፎ አንብቢያለሁ። ገድለ ላሊበላ ንጉሡ ከሞተ ከብዙ ዘመን በኋላ የተጻፈ በመሆኑ፣ የዚህን ታሪክ አስተማማኝነት ማረጋገጥ አይቻልም። የፈጠራ ድርሰት አድርገን ብንወስደውም ዋጋው አያንስም። ጸሐፊው መጽሐፉ ውስጥ ያካተተው፣ ለተፈናቃዮች ተገቢ የካሳ ክፍያ መከፈልና ሠራኞችን በደመወዝ ማኖር ከበጎ ንጉሥ የሚጠበቅ በጎ ተግባር አድርጎ ቢቀበለው ነው። ብዙዎቹ የጥንት ነገሥታት የሚገዙትን ሀገር እንደግል ርስታቸው ሕዝቡን ደግሞ እንደሚነዱት ከብታቸው አድርገው ስለሚቆጥሩት ባንድ ቦታ የሰፈረን ሕዝብ "ተነሥና ውጣ!" ብለው የማባረር ፍጹም ሥልጣን ነበራቸው። በዚህ ሚዛን ስንመዝነው፣ ላሊበላ ለባላገሮች ተገቢ የካሳ ክፍያ የመከፈሉ ታሪክ ተፈጽሞ ከሆነ ከሕንጻው የማይተናነስ አድናቆት ይገባዋል ባይ ነኝ። የገድል ጸሐፊው ፈጠራ ከሆነ ደግሞ አሪፍ የሩቅ ሐሳብ (Ideal) ነው። የሩቅ ሐሳብ ገና ያልተደረሰበት ምናለ ቢደረስኩበት እያሰኘ የሚያጓጓ ሐሳብ ነው። አዲስ አበባ እየፈረሰች ስትገነባ፣ ገጠሩን እየገፋች ወደ ጎን ስትሰፋ፣ በዚህ ላሊበላዊ መንፈስ ላይ እንዳልደረሰች ማየት ያሳዝናል። መዲናይቱ ወደፊት በተራመደች ቁጥር በመንኮራኩር እግሯ የድኻ ሕይወት ትድጣለች።

# ከቸርችል ጎዳና ወደ ቸርችል ደመና

ነይ ነይ በዳመና
ነይ ነይ በዳመና
ዱሩን ጥሰ፣ ሣሩን አጭዶ፣ ባወጣው ጎዳና
ነይ ነይ በዳመና

(የፍታሒ ንጉሤ)

የተሣፈርንበት አውሮፕላን ምድሪቱን ሲለቅ ዐይኔን ጨፈንሁ። የከፍታ ፍርሃት አለብኝ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የዕርገት መኪና (ሊፍት) ለመሣፈር አልደፍርም ነበር። የሦስተኛ ዓመት የሳይኮሎጂ ተማሪ እያለሁ The future of an illusion የተባለውን የሲግመንድ ፍሮይድን መፅሐፍ አንብቤና ከሃይማኖት ጋር ፍቺ ፈፀምኩ። ይሁን እንጂ አውሮፕላን ላይ በወጣሁ ቁጥር ለአጭር ጊዜ ሃይማኖተኛ እሆናለሁ። አውሮፕላኑ ሰማይ ላይ ሲደላደል የበረራ አስተናጋጇ ብቅ አለችና አደጋ ቢፈጠር ልናደርገው የሚገባንን ጥንቃቄ ታብራራልን ጀመር። ይህንን የጉዞ እድል ያገኘሁበትን ቀን በልቤ ረገምሁ።





እንግዲህ ምን ይደረግ? ይቺን ዳመና አሳልፋችሁ አውርዱኝ አይባል ነገር!! "አውሮፕላኑ በባሕር ላይ እንዲያርፍ ከተገደደ ከወንበርዎ ሥር ያለውን መንሣፈፊያ ትጥቅ እንዲህ አድርገው ይልበሱት። ከለበሱትም በኋላ እዚህ ጋ የሚታየውን ከር በተደጋጋሚ ይሳቡት። ያኔ ከረጢቱ በአየር ይሞላል" አለች፣ አስተናጋጇ።

ወይ አበሳ! ወይ ቀን አያውቁ! ወይ መንሣፈፊያ ከረጢት!

ለመሆኑ በአደጋ ሠዓት ከወንበሬ ሥር መንሣፈፊያ ከረጢት መኖር አለመኖሩን ይቅርና፣ ወንበር ላይ ልቀመጥ ጉቶ ላይ እንዴት ትዝ ሊለኝ ይችላል? ሰው አለቅጥ ሲደነግጥ እንዲህ ያለውን የጥንቃቄ ዝርዝር ይቅርና በሽንት ቤት እና በሱሪው መካከል ያለውን ልዩነት እንኳ ይረሣዋል። ለዚህ ነው ብዙ ድንጉጦች በአደጋ ሠዓት ሽንታቸውን ለሱሪያቸው የሚያስረክቡት። አሁን አስተናጋጇ የምታቀርበውን የአደጋ ጥንቃቄ ተግባራዊ አድርጎ የዳነ ሰው ካለ ጀምስ ቦንድ መሆን አለበት። እኔ የበረራ አስተናጋጅዋን ብሆን ኖሮ የሚከተለውን ማለቴ አይቀርም ነበር። "ክቡራን መንገደኞቻችን አውሮፕላኑ ድንገተኛ አደጋ ከገጠመው በወንበርዎ ሥር የፀሎት መፅሐፍ ስላለ ያንን አውጥተው፤ አጠር ያለ ፀሎት መርጠው ይድገሙ።"

ትዝ ይለኛል፣ በመጋቢት ማጠናቀቂያ ላይ እንደ ገጠር ሎንቺና የሚንገጫገጭ አውሮፕላን ተሣፍሬ ወደ ባሕር ዳር ስበር እንቅልፍ ሸለብ ያደርገኛል። በሕልሜ ኪፓይለቱ ክፍል፣ በማጉያ የሚመጣ ድምፅ "ክቡራንና ክቡራት ደንበኞቻችን በአሁኑ ጊዜ ከባሕር ጠለል በላይ በሁለት ሺህ ሜትር ላይ እየበረርን ነው። ይሁን እንጂ በድንገት የአውሮፕላኑ ሞተር ስለጠፋብን በከባድ ጭንቀት ላይ እንገኛለን። ስለዚህ ካሁኗ ደቂቃ ጀምሮ ሞባይላችሁን ከፍታችሁ ለቤተሰቦቻችሁ የስንብት ቃል ወይም ኑዛዜ ማስተላለፍ እንደምትችሉ ስገልፅ ሐዘን ይሰማኛል" ይላል። ወዲያው የአውሮፕላኑ ሆድ በሽብር ይታመሣል። ሽንትና እንባ ተቀላቅሎ ይፈሣል። ከጥቂት ትርምስ በኋላ ፓይለቱ "ክቡራንና ክቡራት ደንበኞቻችን የጠፋውን ሞተር ካፖርት ኪሴ ውስጥ ስላገኘሁት ተረጋጉ። በነገራችን ላይ አፕሪል ፉልን ምክንያት በማድረግ ያዝናናኋችሁ





ካፒቴን ጉብረመስቀል ነኝ። መልካም በረራ" ይልና ይስቃል። ከዚህ ሕልም በኋላ አውሮፕላን ላይ ላለመተኛት ወሰንኩ።

ለበራራ ፍራቴ መፍትሄ እንዲፈልጉልኝ አንዳንድ ትልልቅ ሰዎችን አማክርያለሁ። ከኒህ ትልልቅ ሰዎች አንዱ ኮሎኔል ብርሃኑ ነበር። (ኮሎኔል ብርሃኑ የቀድሞው መንግሥት ተዋጊ-አውሮፕላን አብራሪ ነበር። ኢህአዴግ ሥልጣን ሲይዝ አስሮ ካከራረመው በኋላ፣ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ፈትቶ እንደገና ፈትኖ ወደ ሥራው መለሰው። ኮሎኔሉ በእንግሊዝ ኤምባሲ አካባቢ በሚገኘው አፓርትመንቱ እኔና ጋዜጠኛ አንተነህ ይግዛውን ጋብዞን፣ ተፈትኖ ያለፈበትን የበረራ ቪድዮ አሳየን። አውሮፕላኒቱን ዘና ብሎ ዳመና ላይ ሲጋልባት ሳይ ራሴን ታዘብኩት። ከዚህ በኋላ አውሮፕላን ላይ ስወጣ የኮሎኔል ብርሃኑን የተዝናና ፊት እያስታወስኩ አሞቴን ኮስተር አደርገዋለሁ ብየ ቃልገባሁ።

ከጥቂት ወራት በኋላ ጦር መሣሪያና ጥቂት ሰዎችን አሳፍሮ በመነሣት ላይ ያለ አውሮፕላን ሶማሌ ውስጥ ተከሰከሰ። ተሳፋሪዎችና አውሮፕላን ነጂው በሰው ሀገር ወደ አመድነትና ጭስነት ተቀየሩ። ያንን አውሮፕላን ይነዳው የነበረው ኮሎኔል ብርሃኑ መሆኑን በሬድዮ ስሰማ ምን ልበል? ለጥቂት ጊዜ አንሠራርታ የነበረች መረጋጋቴ የኮሎኔሉን አውሮፕላን ተከትላ ተከስከሰች።

የበረራ አስተናጋጇ በአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ አስቦኪታኝ ወደ ማጀት ስትገባ ወደ ግራዬ ዞር አልሁ። በጢም ቁጥቋጦ የተሸሸገ ተሣፋሪ አጠገቤ ተቀምጧል።

ኢድሜ ለቢንላደን! ጢማም ሰው ባየሁ ቁጥር የሚቃጠል ሕንፃ አብሬ አያለሁ። ጢምና ነውጥ ተቆራኝተው ታዩኝ። በዓለማችን ላይ የተፈራረቁ ነውጠኞች ወይም የነውጥ ሰበቦች ጢማም ወይም ሙስታሻም ሲሆኑ፣ ሰላማዊ ሰዎች ደግሞ ልጩዎች ናቸው። የማሕታማ ጋንዲን፣ የማርቲን ሉተር ኪንግን እና የማንዴላን ጢም አልባ አገጭ ይመለከቷል። ስልጣኔ ማለት ተፈጥሮን መከርከም ነው። ጢሙን መግታት የማይችል ሰው ምናልባት ደም ፍላቱንም መግታት አይችል ይሆናል። ጢማሙን ነውጠኛ ጢሙ-በራውን ደግሞ ሰላማዊ የሚያደርገው ምደባዬ፣ ከአጉል እምነት የሚጠጋ ሐሳብ መሆኑ ገብቶኛል። ቢሆንም አእምሮዬ እንዳይቦዝን አገልግሎኛል። ግን ብዙ አልቆየም።





ሐሳቤ ሲያልቅ ሰውዬውን ደግሜ ተመለከትሁት። እጅግ ጠብደል ከመሆኑ የተነሣ ያለ ምንም የጦር መሣሪያ በጥፊና በእርግጫ ብቻ አውሮፕላኑን መጥለፍ የሚችል ነው። በአይኔ ቁራኛ እሾፈው ጀመር። ትንሽ ቆይቶ ብድግ አለና ከፓይለቶቹ ክፍል አጠገብ በሚገኘው ሽንት ቤት ውስጥ ገብቶ ሰነበተ። ኧረ ይሄ ነገር አላማረኝም።

ሰውዬው ኑሮውን ነው እንዴ የሚፀዳዳው? ሽንት ቤቱን ለብቻው ነጥሎ ሳይጠልፈው አልቀረም። 'Ladies and gentlemen the toilet has been hijacked! Please remain seated' የሚል ማሳሰቢያ መጠበቅ ጀመርሁ።

አውሮፕላኑ የኔን ሥጋት እያስተባበለ ካርቱምን አልፎ ካይሮን ቁልቁል ገላምጦ ሜዴትራኒያንን ማቋረጥ ጀመረ። ዞር ዞር ስል ጥቂት ተሣፋሪዎች በንባብ ተጠምደዋል።አንድ አበሻ ተሳፋሪ ቀይ ሽፋን ያለው መጸሐፍቅዱስ ገልጦ ያነብባል።

እኔም የገዛ ሐሳቤን ማንበብ ጀመርሁ።

አውሮፕላን የሰው ልጅ የመብረር ምኞት ያስገኘው የቴክኖሎጂ ፍሬ ነው። የጥንት ኢትዮጵያውያን የመብረር አምሮታቸውን በሥዕልና በተረት ተወጥተውታል።

ባህላዊ ሥዕላችንን ብታዩ በክንፍ የተሞላ ሆኖ ታገኙታላችሁ። ዝነኛው የስክንድስ ተረትም እዚህ ላይ ሊነሣ ይችላል። ከእለታት አንድ ቀን እስክንድስ የተባለ ጀግና፣ ፈረስና ንሥርን አዳቅሎ (ለተረት ምን ይሣነዋል!) የሚበር ሥጋ በል ፍጡር አስገኘ። እስክንድስ በራሪው ፈረስ ላይ ይወጣና የሥጋ ብልት በሜንጦ ይዞ በፈረሱ አፍ ግድም ያንጠለጥለዋል። በራሪው ፈረስ ሥጋውን አገኛለሁ እያለ እመር ሲል ምድሪቱን ለቅቆ ወደ ሰማይ ይወጣል። ተረቱ ወደ ገሀድ ሲተረጐም የእስክንድስ ፈረስ አውሮፕላን፣ የሜንጦው ሥጋ ያውሮፕላኑ ሞተር ይሆናል።

አባቶቻችን (እናቶቻችንም) አስደናቂ ምናብ እንደነበራቸው አያጠራጥርም። የምናባቸውን ሥዕል ወደ እውን ለመቀየር ግን ድፍረት የነበራቸው

አይመስልም። ምናልባትም ትሕትና ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ አድርጓቸው ይሆናል። በዳመና ላይ የመጋለብ መብት ያላቸው መላእክት እና እንደ ኤልያስ ያሉ መላእክት- አከል ቅዱሳን ብቻ ናቸው ብለው የታቀቡ መሰለኝ። "እልበር እንዳሞራ ሰው አርጐ ፈጥሮኛል" የሚለው ዘፈን ሁኔታውን በደንብ ይገልጠዋል።

ሰው ራሱን በአሞራ አምሳል እንደገና መፍጠር እንደሚችል የተገለጠለት ዳቪንቺ ግን የበረራ መኪናዎችን ነደፈ። እንሆ እኔም አባቶቻችን በአለሙት፣ የራይት ወንድማማቾች በተረገሙት የእስክድስ ፈረስ ላይ ተፈናጥጬ ወደ ሀገረ እንግሊዝ ለመጋለብ በቃሁ።

አውሮፕላን ወደ አገራችን በገባ ሰሞን ሕዝቡ እንዲሳፈር ማሳመን ቀላል አልነበረም። የዛሬ ዘጠና ዓመት አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ለቅስቀሳ የፃፈውን፣ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ ማንበቤ ትዝ አለኝ።

"በድፍን አውሮፓ" ይላል አፈወርቅ፣ "በድፍን አውሮፓ እንኳን ወንዶች ሴቶች ሳይቀሩ ራሳቸው እየነዱ በዚህ በአይሮፕላን ሀገር በሀገር ሲሮጡ ሲራወጡ ይኖራሉ። ምንም አያገኛቸውም።

"አሁን በቅርቡ ያገራችን ወይዘሮ የነጋድራስ መኮንን ባለቤት ወይዘሮ ዘውዲቱ በዚሁ በአይሮፕላን መሄዳቸውን ብርሃንና ሰላም አስታውቆናል። በአማሪካ ሀገር ገረዶች ሳይቀሩ ማለዳ ማለዳ ለጌቶቻቸው የሚገዙትን የለት ምግብ ባገልግላቸው ቆልፈው ይዘው ታንዱ ገቢአ ወደ አንዱ እየሳቁ እየተሳለቁ በዚህ በሰማይ መርከብ ሲሄዱ እንሞታለን ብለው ምንም አይፈሩ።

"በአውሮፓ ሀገር በየከተማውና በየተራራው ሺህ የሺህ ኤሮፕላን እንዳንበጣ አየሩን እያላበሰ ነፋስና ዳመናውን እየቀደደ ሲራወጥ ይውላል። እንደ ብዛቱ መጠን ግን ሞት የለበትም። አያስፈራም። ከሺህ አንድ ቀን አንዱ ቢወድቅና ሰው ቢሞት አያስደንቅም። ስለምን ሞት ጉግሥ ሲጫወቱ ፈረስ እየተንደላቀፈ፣ ፈረሰኛ እየወደቀ ይሞታል ይሄም ይሄን አከል ነው።"





በአፈወርቅ ጽሑፍ ውስጥ ያውሮፕላን ኢትዮጵያዊ ስሙ "የሰማይ መርከብ" እንደነበር እንረዳለን። ስያሜው በዘፈቀደ የወጣ አይመስልም። አባቶቻችን በአየር ላይ ባሕር አለ ብለው ያምኑ ነበር። "አንዱ እጅ ውሃ ከጠፈር በላይ ተሰቀለ፤ ስሙንም ሀኖስ አለው" እንዲል መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት። በአየር ላይ ባሕር ካለ አውሮፕላን የሰማይ መርከብ መሆን አለበት።

በጊዜው ወይዘሮ ዘውዲቱ በአውሮፕላን ላይ ለመሳፈር መድፈራቸው ለጋዜጣ የሚበቃ ክስተት ኖሯል። ይህም በወቅቱ በአውሮፓ ስልጣኔ እና በኢትዮጵያ ውጥን ስልጣኔ መካከል የነበረውን መራራቅ ያሳየናል። በአውሮፓ አውሮፕላን የእለት ተእለት ልምድ በሆነበት በዚያን ዘመን፣ በእኛ ሀገር በመንኮራኩር የመምጠቅን ያክል ትንግርት ነበር። የአፈወርቅ ዓላማ ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ አውሮፕላን ላይ እንዲወጣ ማደፋፈር ነው። ከጠላት ጋር የመተናነቅ ድፍረት እና ከአዲስ መሺን ጋር የመግባባት ድፍረት ለየቅል መሆናቸው የተገለጠለት አይመስልም።

አፈወርቅ በቅስቀሳ ጽሑፉ ውስጥ፣ "ከሺህ አንድ ቢወድቅ እንኳ" ብሎ እንደገና አስቦካኝ።

ይሄ አውሮፕላን ከሺህ አንዱ አለመሆኑን በምን ላውቅ እችላለሁ? አፈወርቅ ሞትን ቢያናንቅ አይገርመኝም። ይሄንን በሚጽፍበት ጊዜ እድሜ ጠግቧል ። ኑሮን ካጤ ምኒልክ ቤተመንግሥት እስከ አውሮፓ ድረስ አጣጥሞታል። እኔ ግን ገና ዘልየ ያልጠገብሁ ጎረምሳ ነኝ።

ከወንበሬ ጋር የተቆራኘሁበትን ቀበቶ ፈታሁና እየተንገዳገድሁ የበረራ አስተናጋጆች ምግብ ወደ ሚያበስሉበት ያውሮፕላኑ ማጀት ሄጄ የበሩን መጋረጃ ገልጬ ገባሁ። ሁለት ቆንጃጅት የበረራ አስተናጋጆች ከምድጃቸው ላይ ቀና ብለው በግርምት ተመለከቱኝ።

"ትርፍ ፓራሹት ይኖራችኋል?" አልኳቸው።

ሲስቁልኝ ጊዜ ፍርሃቴ ጥሎኝ ጠፋ።





ከዚያ እንድቀመጥ ጋብዘውኝ፣ የክት ምግብና መጠጥ አቅርበውልኝ እንደ ጋዳፊ በቆንጃጅት ታጅቤ የሮማን ሰማይ አለፍሁ። ትንሽ ቆይቶ ያውሮፕላኑ ምክትል ነጂ ያለሁበት ድረስ መጥቶ የምፈልገው ነገር እንዲዘጋጅልኝ አሳሰበ። በርግጥ የምፈልገው ካውሮፕላኑ መውረድ ነበር።

እውነት ለመናገር ያውሮፕላኑ ቤተሰቦች ከሁለት ሳምንታት በፊት የኢሚግሬሽን ዘበኛ ያደረሰብኝን በደል ካሱኝ።

ትዝ ይለኛል። የይለፍ ጦማሬን (ፓስፖርቴን) ለማሳደስ ኢሚግሬሽን ገስግሼ ብሄድ፣ የደጅ ጠኚው ሰልፍ አሥር ቦታ ተጠማዞ የኮንሰን እርሻ መስሎ ጠበቀኝ። እውን ይሄ ሁሉ ሠልፍ የፓስፖርት ነው ወይስ ኢሚግሬሽን ስኳርና ዘይት ማደል ጀምሯል? በማለት እያጉተመተምሁ አጠር ያለውን ሠልፍ መርጬ ቆምሁ።

ወድያው ግን ከየት መጣ ያላልኩት፣ በአንገቱ ላይ የታይሰን ፊት፣ በትከሻው ላይ የተርምኔተር ክንድ የተገጠመለት ዘበኛ እንደ በቆሎ በገዛ ኮቴ አንጠልጥሎ ቢወረውረኝ በአካባቢው በሚገኝ የጉልት አምባሻ ላይ ባፍጢሜ ተደፋሁ። የዐረብ መንደገኛ ሁላ ለጊዜው ትካዜውን ረስቶ ባውዳደቄ ሳቀ።

ለንደን ገባሁ።

ለንደን እንደገባሁ፣ በመጀመሪያ ያደረግሁት የፊደል ገበታ የሠፈረበት ካናቴራ ለብሼ ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ በመንሸራሸር አገሬን ማስተዋወቅ ነበር። ትንሽ እንደቆየሁ ግን ባለፊደል ካናቴራ ቀርቶ የቄስ ትምህርት ቤት ተሸክሜ ብዞር እንኳ ትኩረት እንደማላገኝ ገባኝ። በርግጥ አንድ ሁለት ፈረንጆች ዞር ዞር እያሉ ባድናቆት ተመልክተውኛል። ያድናቆታቸው ምንጭ ግን፣ "እንዴት በዚህ አጥንትን በሚቆረጥም ብርድ ካናቴራ ለብሶ ይወጣል!" የሚል እንደሆነ ጠርጥሬያለሁ። ለንደን ውስጥ ዐይን ማግኘት በጣም ብርቅ ነው። በዚያው መጠን ዞር ብሎ ከማያያቸው ሕዝብ ጋር እልህ የተጋቡ የሚመስሉ፣ ለመታየት ተግተው የሚሠሩ ሰዎች አሉ። ከላይ እስከ ታች በንቅሳት ተዥጎርጉሮ የጥምቀት ሽመል የሚመስል ወደላ ፈረንጅ ተመልክቻለሁ። ፊቷ ላይ አራት ትልልቅ ቀለበት ደርድራ ጽናጽል የመሰለች ሴትዮ ተመልክቻለሁ። በዚህ





ማኸል የኔ ካናቴራ ብርድ እንጂ ትኩረት እንደማትስብ ስገነዘብ ሆቴሌ ገብቼ ካፖርት ደረብሁ።

ለንደን እንደ ገባሁ ራሴን ከብልቃጥ ወደ ባሕር የተሸጋገረ አሣ አድርጌ ቆጠርሁት። አዲስ አበባ ውስጥ አንድ ቦታ ከጠፋኝ የመንደሩ ሰው፣ "ደርሰሃል ከስልክ ግንዱ ወደ ግራ እጥፍ ስትል ታገኘዋለህ!" እያለ ተግቶ ይመራኛል። በለንደን የገጠመኝ ግን እገሬ ማሪኝ የሚያስብል ነው። እንዴ ሁሉ ነገር የዐይን ዐዋጅ ሆኖብኝ ግራና ቀኙን እየሾፍሁ ስገሰግስ፣ ሳላውቀው ከሆቴሌ በጣም ርቄ ኖሮ መመለሻው ግራ ገባኝ። ወደ አንድ መጽሐፍት ሱቅ ገብቼ በይሉኝታ ውድ መጽሐፍ ገዝቼ ሳበቃ፣ ሻጩን Travel Lodge የተባለው ሆቴል የት እንደሚገኝ ጠየኩት። ሻጩ ምንም ሳይል ከመሳቢያው ውስጥ እንደ ጃክሰን ፓሎክ የአብስትራክት ሥዕል የተወሳሰበ ካርታ አውጥቶ አቀበለኝ። በካርታው ላይ ለግማሽ ሰዓት ያክል እንደ ምሥር ለቃሚ አቀርቅሬ ቀና ስል ዞረብኝ። የሆቴሌን አድራሻ ማግኘት ቀርቶ የገባሁበት ሱቅ በር ራሱ ጠፋኝ።

"የሸዋ ክፍለ ሀገርን በሰሜን ወሎ፣ በደቡብ ሲዳሞ ያዋስኑታል" ከሚል ያለፈ የካርታ ንባብ ያላስተማሩኝን የጥንት መምህሮቼን በልቤ እየረገምኩ፣ እንደወጣሁ መቅረቴን በስልክ ለወዳጆቼ አስታወቅሁ።

በለንደን ባቡሩ፣ አውቶብሱ፣ ፈረንጁ ሁሉም በተቀጠረበት ሰዓት ከተፍ ይላል። ባልተቀጠረበት ሰዓት የሚመጣው ዝናባቸው ብቻ ነው። ያገራችን ዝናብ ቢያንስ የተሰጣ ብቅል እስከናስገባ ድረስ ይታገሣል። የለንደኑ ግን ይሉኝታ ቢስ ነው። እኔ በደረስኩበት ወቅት ባውሮፓ ጥቢ ገብቷል። ሴቶቹ እንደ ዓይነ ርግብ ውብታቸውን ሸሽጐባቸው የቆየውን ክረምት ለመበቀል ተገላልጠው የሚወጡበት ወቅት ነው። ልጃገረዲቱ ፀጉሯን ተተኩሣ፣ ግልገል ቀሚሷን ለብሣ፣ ጡቷን እንደ ቸርችል ሐውልት ሁሉ ሰው በሚያየው ቦታ ላይ አቁማ እየተውረገረገች ትወጣለች። ይኼኔ ከጠራ ሰማይ ላይ አድፍጦ የቆየ ባለጌ ዝናብ፣ እንደ ወፍ አይነምድር ፺ ብሎ ከላይ እስከታች ያለብሳታል። እየተነጫነጨች ጥግ ለመያዝ ትገደዳለች።

ከዝናባቸው ቀጥሎ ብሽቅ ሆኖ ያገኘሁት ቁርሣቸው ነው። አንድ እፍኝ የባቄላ ንፍሮ፣ አንድ ጭልፋ እንቁላል ጥብስ እና አንድ ሉብ ያለ ድፍን ቲማቲም

ካቀረቡልኝ በኋላ፣ ከምግቡ ጋር የማይመጣጠን ደንዳና ፈገግታ በግ አርገው enjoy your breakfast ይሉኛል። እንደሰማሁት ከሆነ እንግሊዞች የራሳቸውን ቁርስ አይወዱትም። ታሪክ መሥራት ብቻ ሳይሆን፣ ቁርስ መሥራትም እንችላለን ለማለት ያህል ንፍሮአቸውን ለኔ ካቀረቡ በኋላ ለራሳቸው በጓሮ በር በኩል ወደ ጣልያን ሬስቶራንት ጐራ እንደሚሉ ገምትሁ።

ሁሌም በቁርስ ሰዓት ሹካና ቢላዋዬን አመሳቅዬ ሰሀኔ ላይ እንዳቀረቀርሁ ትዝ የሚለኝ "ድኸነት ጠፍንጐ ይዞን ነውንጂ አበላሉንስ እናውቅበት ነበር" የሚለውን የጊዮን ዓለምሰገድን አባባል ነው። (ጊዮን ባንድ ክረምት ለጓደኞቹ ስለ በቆሎ አጠባበስ ማብራሪያ ይሰጣል፣ "አሁን አንድ ጥሩ በቆሎ ቢገኝ ትሸለቅቀውና ወተት ትቀባዋለህ፤ ከዚያ ትንሽ ማር ታልሰዋለህ። ትቀጥልና የተፈጨ ጨው ነስነስ፣ ነስነስ ታደርግበታለህ፤ ከዚያ በወይራ ፍም ላይ ታገላብጠዋለህ። ተወኝ ባክህ ወንድሜ ! ድኸነት ጠፍንጐ ይዞን ነውንጂ አበላሉንስ እናውቅበት ነበር" ሲል ተከዘ) ።

የመቅመስ እድል ባይኖረኝም እንግሊዞች ሹካ የሚያስቀረጥም የጥንቸል ሥጋ ጥብስ እንደሚሠሩ ሰምቻለሁ። የጥንቸል ሥጋ ጣዕሙ ከሽን ብላ እንደተሠራች ዶሮ ነው ብሎኛል አንዱ። ቬጅተርያን ባልሆን ኖሮ የጥንቸል ሙብልን ሙብላት ለኢትዮጵያ በማስተዋወቅ፤ በምሰብ ታሪክ ውስጥ ስሜን እተክል ነበር። ዛሬ ኢትዮጵያዊ የሆኑ መብሎች ባንድ ወቅት በእንግድነት የገቡ ናቸው። አሾካዶ መብላትም ባንድ ወቅት ኢትዮጵያዊ ባህል አልነበረም። እናቶቻችን ብዙ የጥራጥሬና የፍራፍሬ ዓይነቶችን ከሌሎች ሕዝቦች ወርሰዋል። ምሥርን ከግብፃውያን፣ ቲማቲም ከጣልያኖች ተቀብለዋል። አሾካዶ ቀይ ባሕርን የተሻገረው በልጅ ኢያሱ ዘመን በበጀሮንድ ተክለሐዋርያት በርሣ ነው።

ከብርቱካን ጋር ያስተዋወቁን የፖርቹጋል ቄሶች ናቸው ይባላል። የጥንቱ አበሻ ፖርቹጋል ለማለት ብርቱጋል ይል ነበር። ብርቱካን ከዚያ የወጣ ቃል ነው ሲባል ሰማሁ ልበል? በቆሎ ዛሬ ቤተኛ ቢመስልም በቅርብ መቶ ዓመታት ከምድረ አሜሪካ የመጣ መፃተኛ ነው ይባላል። የፍታሄ ንጉሤ፣ "ማሽላና ስንዴ ባንድ ላይ ስንቆላ፣ እያረረ ሳቀ የባሕር ማሽላ" ያሉት አለነገር አይደለም። በቆሎ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ፣ "የባሕር ማሽላ" በሚል የእንግድነት ስሙ ይታወቅ





ነበር። በሁሉም ረገድ ስናያት ኢትዮጵያ፣ "በጐደለ ሙላ" ስልት የተፈጠረች ሀገር ናት።

አባቶቻችን አዳዲስ ፍራፍሬና ጥራጥሬ ከውጭ ለመቀበል ፈጣን የሆኑትን ያህል የሥጋ ምርጫዎቻቸውን ለማብዛት አልጣሩም። የዚህ ምክንያት በባህላችን ላይ የገነነው ኦሬታዊነት ይመስለኛል።

ከኦሪት በፊት የነበረችው ኢትዮጵያ ሰፋ ያለ የሥጋ ምርጫ እንደነበራት የምናውቀው የሙሴ ድምጽ በማይደርስበት ቦታ ተሸሽገው የኖሩ፣ እንደ ነገደ ወይጦ ያሉ ጥንታዊ ሕዝቦችን አመጋገብ ስንመለከት ነው። ብዙዎቻችን እንደምናውቀው ሙሴ እንስሳትን እርኩስና ቅዱስ ብሎ መድቧል። እንደ ሙሴ ምደባ ጥንቸል የሚያመሰኳ እንስሳ ቢሆንም ሸሆናው ክፍት ስላልሆነ እርኩስ ነው። እናም ልንመገበው አይገባም። ዘመናይ የእንስሳት ተመራማሪዎች ጥንቸልን ቀርበው ሲመለከቱት ሙሴ እንደ ተሳሳተ ገባቸው። ለካስ ጥንቸል አያመሰኳም።

ወደድንም ጠላንም የሙሴ የሥጋ ምድባ የአመጋገብ ባህላችንን ለሺህ ዓመታት ያህል መምራት ችሏል። ሥጋን ስናስብ አስቀድሞ ወደ ሐሳባችን የሚመጣው፣ ገበሬ ሲሆን፣ "ገ" የቀረው በሬያችን ነው።

አንዲት ላም አንድ ጥጃ ለመስጠት 286 ቀን ያላነሰ ጊዜ ታስጠብቀናለች።

አንዲት ጥንቸል ግን ከባለቤቷ ጋር በተሣረረች በሰላሳ ቀኗ አንድ ደርዘን ግልገሎች ለእንግሊዞ አርብቶ አደር ታበረክታለች። የጥንቸል ግልገል እንደ ሰው ልጅ ጡጦ አጉርሱኝ አይል፣ የምሳ እቃዬን ሙሉልኝ አይል በተወለደ በአሥራ አራት ቀኑ በግጦሽ ራሱን ይችላል። በተወለደ ባንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለአቅመ መሶብ ይደርሳል።

ጥቂት ለፍቶ ብዙ ሥጋ ማምረት የሚፈልግ ሰው ነገሩን ቢያጤነው ጥሩ ነው።

ብሪትሽ ሙዚየም የተባለውን ከመጎብኘቴ በፊት፣ የብሪትሽን ሙዚየም ልዩ የሚያደርገው በቴዎድሮስ ፍጻሜ ላይ ከመቅደላ የተዘረፉ መጻሕፍትን መያዙ





ይመስለኝ ነበር። ጉብኙ ላይ እንደተሳሳትሁ ገባኝ። እንግሊዞች ከኢራንና ከግብጽ ከዘረፏት ሰፍር ቁጥር የለሽ ቅርስ ጋር ሲመዛዘን ከኢትዮጵያ የተወሰደው ቅርስ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። የፈርኦኖች ግዙፍ ሐውልቶችና የፋርስ ነገሥታት በራሪ እንስሳ ምስሎች በምን ተአምር ተጓጉዘው እዚያ እንደደረሱ ማሰብ ያደክማል። እንግሊዞች አቅም አጥሯቸው ነው እንጂ ስፊኒክስን ወይም ትልቁን ፒላሜት ነቅለው ወደ ሎንደን ቢያሻግሩት የሚጠሉ አይመስሉም። ታድያ ያንን ሁሉ የተዘረፈ ንብረት ለዓለም ሲያስጎበኙት በኩራት ነው።

አንድ ወዳጄ እንግሊዝ ደርሼ ያለማየሁ ቴዎድሮስን መቃብርና የመቅደላ መጻሕፍትን ሳልጎበኝ ብመለስ እንደሚቀየመኝ አስጠንቅቆኝ ነበር። ባጠጣ ባወርድ፤ የዓለማየሁ ቴዎድሮስን መቃብር የምጎበኝበት ምክንያት አልታይህ አለኝ። ዓለማየሁ ባጋጣሚ የንጉሥ ልጅ ከመሆኑ ውጭ ለምርመራ ወይም ለጉብኝት የሚጋብዝ ምንም ብርቅ ነገር አጣሁበት። ይልቅስ ለኔ ከመቅደላ የተዘረፉ መጽሐፎችን መጎብኘት የተሻለ ትርጉም ነበረው። እያሌ መጻሕፍት በመስታወታማ ሳንዱቅ ውስጥ በምቾት ተቀምጠዋል። ለማንበብ የፈለገ ብራናውን ሳይነካ መስታወቱን እንደ ወረቀት እየገለጠ ማንበብ ወይም ሥዕሎቹን መመልከት ይችላል። ብዙዎቹ የተሰረቁ ጥንታዊ መጻሕፍት በማተሚያ ቤት ተባዝተው ተተርጉመው ይጠናሉ፤ ይመረመራሉ። ስለዚህ፣ የኢትዮጵያ ንብረት መሆናቸው ቢቀርም በስልጡን ሌባ እጅ መግባታቸው ያጽናናል።

አሁን ደግሞ ስለለንደን እርፍና ልናገር። ለንደን የምር ስልጡን ሀገር ናት። እንደ ስልጡን አገሮች ሁሉ በውስጧ ላሉት ሁሉ ነፃነት እና ዕድል እንደ ቢጤይቱ ትሰጣለች። ጳውሎስ ኞኞ ባንድ ወቅት፣ "ነፃነት ማለት የሌላውን ነፃነት ሳይነኩ ነፃ መሆን ነው" ብሎ የፃፈውን በመዲናይቱ ቆይታዬ ተገንዝቤዋለሁ።

ዕድል መስጠት የሚለውን ሐረግ የሚያብራራልኝ ገጠመኝ ልጥቀስ። አንድ ቀን፣ እኔና አንጋፋው ደራሲ ጃርሶ ኪሩቤል ወደ ማዕከላዊ ለንደን የሚወስደንን





ባቡር እንጠብቃለን። በባቡሩ ጣቢያው አጠገብ የሕዝብ የጋራ ንብረት የሆነ ፒያኖ ተቀምጧል፡

ችሎታ አለኝ የሚል ሁሉ መጥቶ ችሎታውን ሊያሳይ ይችላል። እኛ በጥበቃ ላይ በነበርንበት ጊዜ አንዲት ባለወርቃማ ፀጉር ሴትዮ ከዋናው መንገዱ ተዘንጥላ መጣችና ዘንቢሏን አስቀምጣ፣ ቀሚሷን ሰብሰብ አድርጋ ከፒያኖው ፊት ለፊት ተቀመጠች። የኖታ ደብተሮችን ገለጥ ገለጥ እያደረገች አንድ ዜማ ተጫወተች። ስትጨርስ፣ ዘንቢሏን ብድግ አድርጋ ያቋረጠችውን መንገድ ቀጠለች። ባቡር ጠባቂው ሁሉ ሞቅ ባለ ጭብጨባ ሸኛት። እኔ "አንድ አለብሽ" የሚል ዘፈን ስጠጣ ስላደግሁ ረቂቅ ሙዚቃ የሚመዝን ጆሮ የለኝም። ጃርሶ ግን ዐይኖቹን ጨፍኖ፣ አንገቱን ወደ ፒያኖው አቅጣጫ ዘመም አርጐ፣ ጉብስማ ረጅም ጢሙን እየዳበሰ ሲያዳምጥ ነበር። ጃርሶ ከደራሲነቱ ያልተናነሰ የረቂቅ የሙዚቃ ቀማሪነት ችሎታ ባለቤት መሆኑን ስለምሰማ፣

"እንዴት ነው?" ስል ጠየኩት።

"ግሩም አድርጋ ትጫወታለች" አለ።

አገሬ ከተመለስሁ በኋላ ላንዱ ተራቢ ጓደኛዬ ይህንን ገጠመኝ አወጋሁትና፤

"ገንዘብ ቢኖረኝ አንድ ፒያኖ ገዝቼ ማከል ፒያሳ አስቀምጠው ነበር። ችሎታ ኖሯቸው ዕድሉን ያላገኙ ያገሬ ልጆች ይጫወቱበታል" አልሁት።

"የማይሆን ነገር ነው!" አለኝ ጓደኛዬ

"ምነው?" አልሁት።

"ጠዋት ማከል ፒያሳ ያስቀመጥከውን ፒያኖ፣ ከሠዓት መርካቶ ልታገኘው ትችላለህ!"


ሳልረሳው ስለጃርሶ ትንሽ ልበል። ጃርሶን ለመጀመርያ ጊዜ የተዋወቅሁት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ በጀርመን ሬድዮ በኩል ነው። በሬድዮው ላይ የሚያቀርባቸው ትረካዎች ለኔ ዝም ብለው ትረካዎች አልነበሩም። አንድ

አረጋዊ ሽማግሌ ራሴን እየዳበሰ ተረት የሚያወራኝ ያህል ነበር የሚሰማኝ። አፈሩን ገለባ ያድርግለትና አብርሃም ረታ ዓለሙ እኔና እንዳለጌታ ከበደ ቤቱ ጎራ ባልን ቁጥር የጃርሶን፣ "የድንጋይ ዳቦ ዘመን" የሚለውን ትረካ በቴፕ ይጋብዘን ነበር። የአባቴንና የዘመን እኩዮቼን የልጅነት ጊዜ ሙሉ ሥዕል ማግኘት የቻልኩት በጃርሶ ተረኮች አማካኝነት ነው።

ለንደን ስንገናኝ፣ ጃርሶ ከጠበቅሁት በላይ ከተለመደው የአኗኗር ዘይቤ የወጣ ሰው ሆኖ አገኘሁት። መልኩ በቀላሉ የሚረሳ አይደለም። ከአቡነ ጳውሎስና ከስብሃት ገብረእግዚአብሔር የተውጣጣ የሚመስል ፊት አለው። ገብስማ ጺሙ በጣም ከመረዘሙ የተነሣ መሬት እንዳይጠርግበት እየጎነጎነ ወደላይ ቀልብሶታል። አከራሬ አይሁዶች የሚያደርጉት ዐይነት ጥቁር ከብ ባርኔጣ ያደርጋል። በደመናም ይሁን በጸሀይ ወፍራም ጥቁር ካፖርት ይደርባል። የሸጉጥ ሰገባ በምትመስል የቆዳ ማኅደር ውስጥ ሻጥ አድርጎ ይዟት የሚዞር የማስታወሻ ደብተሩ አትረሳኝም ። በማስታወሻ ደብተሩ ላይ በቁም ጽሑፍ የተጻፉ ምስጢራዊ ስሞችና ምልክቶች ሰፍረዋል። ጃርሶ ረቂቅ ምርምር ላይ እንደተሰማራ ገልጾ ስለምርምሩ ሊያስረዳኝ ሞከረ፣ አልገባኝም። ጃርሶ ቀርጾ ለማስቀረት የሚያጓጓ ፊት ቢኖረውም ፎቶ መነሣት እርሙ ነው። መንፈሴ አይፈድቅም ዐይነት ነገር ይላል። የካሜራ ዐይን እንደቡዳ ዐይን ይፈራል። ድሮ ምናልባት በቅርብ ከሚከተለው እምነት ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም። ድሮ በወጣትነቱ ኢአማኒ ነበር። አሁን በእግዜር አጥብቆ ከማመኑም በላይ ምኩራብ ይስማል።







በሌላ ቀን የቴምዝን ወንዝ ድልድይ ሳቋርጥ አንድ የፈረንጅ ለማኝ አየሁ። (በነገራችን ላይ የተጋባዥ ገጣሚያን ጊዜያዊ ሠፈር የተመሠረተው ከለንደን ኩራቶች አንዱ በሆነው ቴምዝ ወንዝ ዳርቻ ላይ ነው። ቴምዝ ቅልጥ ባለ ከተማ እምብርት ማኸል የሚፈስ በመሆኑ ጀልባዎች ከመኪናዎቹ ጋር እየተጋፉ ይሄዱበታል። እኔ ያባይ ልጅ፣ እኔ ያዋሽ ልጅ፣ እኔ የተከዜ ልጅ፣ እኔ የባሮ ልጅ፣ ቴምዝ ወንዝ ነው ብዬ ለመቀበል ብዙ ጊዜ ወሰደብኝ። እንድ ወንዝ ሐቀኛ ወንዝ የሚሆነው ከራስጌው ውሃ የምትቀዳ ሴት፣ ከግርጌው ውሃ የሚጠጣ ወይፈን ሲያካትት ነው። እንግዲህ ይሄ የገጠር ልጅነቴ ወይም ያፈ.ወርቅ ተክሌ ሥዕል ተፅእኖ ያመጣው ሳይሆን አይቀርም።

ታዲያ አንድ ቀን የቴምዝን ድልድይ ሳቋርጥ አንድ የፈረንጅ ለማኝ አገኘሁ። ከእግሩ ሥር አሮጌ ጊታር አጋድሞ፣ የልመና ሰሌዳ ደረቱ ላይ አንጠልጥሎ ሳየው ገረመኝ። ወደ ፈረንጁ ለማኝ ቀርቤ እንደ ሁዳዴ አውራ ዶሮ ጅንን ብዬ፣ አንድ ባውንድ ወረወርኩለት። ለካ እንደ ሀገሬ ሁሉ ስልጡንና ሀብታም





የሆኑ ሀገሮችም ከተመጽዋቾች ነጻ አይደሉም። የምንለያየው በብዛታችንና በምጽዋት አጠያየቅ ስልታችን ነው። የፈረንጅ ለማኝ በተቻለ መጠን አዝናንቶ ለመቀበል ይሞክራል። የኤሌክትሪክ ጊታሩንና አነስተኛ ጄኔሬተሩን ይዞ ይሰማራል። በገጽታው ብዙ የተጎሳቆለና ሆድ የባሰው አይደለም። ከእለት እንጀራው በላይ ለእለት ቢራው የሚጨነቅ ነው። "No bulshit i need some bucks for beer፣ ለቢራ ትንሽ ፍራንክ ጣልጣል አርጉልኝ ፤ የምሬን ነው" የሚል ሰሌዳ ከፊቱ አኑሮ፣ አልፎ ሂያጁን በኩራት የሚገረምም ፈረንጅ ለማኝ ማየት ብርቅ አይደለም። ጮሆ ከመለመን ይልቅ አጭር የጽሑፍ መልክት አንገት ላይ ሰቅሎ መዘዋወር የተለመደ ነው። እንደምናውቀው፣ ያገራችን ለማኝ ከማዝናናት ወደ ማሳዘን ያዘነብላል። ሳር ቅጠሉ ሐዘን በሆነበት ሀገር ውስጥ የሰውን አንጀት በቀላሉ መብላት ስለማይቻል ለማኞች በምስኪንነት አንደኛ ለመውጣት ይሽቀዳደማሉ። አንዳንዶች የሚያደርጉት ከማራራት ይልቅ መፈጠርህን እንድጠላ የሚያደርግ ነው። ወደ ኪስህ እንድትገባ ሳይሆን ወደ ቤትህ ሮጠህ እንድትገባ የሚያስገድድ ብዙ ዘግናኝ የልመና ዘይቤ አለ። የሆነ ጊዜ ላይ፣ ሀያሁለት ማዞርያ ጎላጉል ሕንጻ ፊት ለፊት ፣ አንድ ለማኝ የእግረኛውን መንገድ ዘግቶ ተኝቶ አካባቢውን ባስፈሪ እሪታ ሲያደበላልቀው ይውል እንደነበር ትዝ ይለኛል። ሰውየው ከልመና ይልቅ አመጽ ላይ የተሰማራ ይመስላል። እሪታውን "እኔን እየራበኝማ እናንተ ዘና ብላችሁ አትኖሯትም" የሚል ያቋም መግለጫ አድርጌ ነው የተረጎምኩት።

የለንደን ጉብኝት ትረካዬን በቀጣይ አንቀጾች ብደመድመው ይሻላል። "አንድ ወር ቆይቶ ዓመት ሊያወራ ነው?" የሚል ሀሜት ያሲጋኛል። ለነገሩ ምን ይገርማል! ሳሙኤል ጆንሰን የተባለው የእንግሊዝ ደራሲ ኢትዮጵያን ሳያይ ስለኢትዮጵያ ከመቶ ገፆች በላይ ድርሥት ፅፎ የለ። ፈረንጅ ያበሻን ረጅም ስም መጥራት ይከብደዋል። ሳሙኤል ጆንሰን፣ "ራስ ስዕለ ክርስቶስ" እሳለሁ ብሎ የድርሥቱን ዋና ገፀባሕርይ "ራሴላስ" ብሎ ጠራው።

በፈረንጅ በኩል የመጣውን ሁሉ እንደትልቅና እንደቅዱስ የሚቆጥሩ አንዳንድ ያገራችን ወላጆች ልጆቻቸውን፣ "ራሴላስ" ብለው ይጠራሉ። ተማሪ እያለን አጠገባችን ከተቀመጠ ተማሪ ፈተና ስንቀዳ ሥርዝ ድርዙን አብረን እንደምንቀዳው ማለት ነው።





ለንደን ኑሮ እሣት ነው። አውሮፕላን ከወረድሁ ጊዜ ጀምሮ በየርምጃው ኪሴን ሲቀልለኝ ይሰማኝ ነበር። የሆቴሌ ኮምፒውተር የሃያ ደቂቃ ኢንተርኔት አገልግሎት ለመሥጠት አንድ ባውንድ እንዳጎርሠው ጠየቀኝ። በየርምጃው ከፈል ነው! ከፈል ነው! ከፈል ነው። የእንግሊዝ የሾላ ዛፍ በግንዱ ቀዳዳ ሳንቲም ካልተጨመረለት ፍሬውን አይጥልም። ኪጋነንሁ ላይቀር ይሄን ልጨምር። መላው ለንደን በብላሽ መስጠት የማያውቅ አንድ ትልቅ የመክፈያ ከልል Pay Zone ነው።

የኑሮውን እሣትነት እንስቼ ሳማርር የሰማ አንድ የለንደን ኗሪ አበሻ እንዲህ አለኝ፡ "ይገርምሃል። በለንደን አንድ ፓኬት ኮንደም አራት ፓውንድ ነው። በዚህ ዋጋ አዲስ አበባ ካዛንቺስ ሴት መግዛት ይቻላል።"

ለንደን በገባሁ ጥቂት ቀናት በኋላ የጥንቱ እሲቃዬ ዐቢይ ተከለማርያም ከሚማርበት ኦክስፎርድ በባቡር እየሠገረ መጣና፣ "ምን እንዳስጎበኝህ ትፈልጋለህ?" ሲል ጠየቀኝ። ብሪትሽ ሙዚየም ውሰደኝ እንድለው ጠብቆ ይሆናል። ምሣ ሠዓት ስለነበር በቅርብ የሚገኝ የአበሻ ሬስቶራንት እንዲያስጎበኘኝ ለመንሁት። በዳቦሣ በር የሚከፍት፣ "እይስተር" የተባለ ትኬት ገዛልኝና ሜትሮ ባቡር ውስጥ ይዞኝ ገባ። እንግሊዞች ባቡር ይተኩሣሉ እንጂ ባቡር ይነዳሉ አልልም። ተተኩሠን እንደ እርሣሥ ቀጣዩ ፌርማታ ላይ ወደቅን። ጉች ጉች ካለ ጡት ቀጥሎ ብዙ የተዘፈነለት ጥንታዊ ባቡራችን ትዝ አለኝና ፈገግ አልሁ።

ባቡራቸው ተንቀሳቃሽ ቤተመጻሕፍት ይመስላል። ምድረ ፈረንጅ በየጋዜጣው ላይ ተደፍቷል። ውጭ ሀገር ቆይተው የመጡ ሰዎች በየጋዜጣው፣ "ፈረንጆች በጣም አንባቢ ናቸው፤ ባቡር ውስጥ የማያነብ ሰው ካለ ጥቁር መሆን አለበት"፣ በማለት የሚያወሩትን እሰማ ነበር። ያገሬ ባላገር ሲተርት፣ "ወሬ ቢነግሩህ፣ ሐሳብ ጨምርበት" ይላል። እስቲ በዚህ ወሬ ላይ ትንሽ ሐሳብ እንጨምርበት። እውነት ነው ፈረንጆች ያነብባሉ። ንባባቸው በጎጎል Dead Souls ድርሠት ውስጥ የሚገኘው ፔትሮቫ የተባለ ገፀ ባሕርይ እንደሚደርገው ዐይነት ፍዝ ንባብ ይመስላል። ከማወቅ ፍላጎት ሳይሆን ከብርቱ ብቸኝነት የመነጨ ነው። ጥግ ላይ ቆሞ ከማፏጨት የላቀ ትርጉም የለውም። ባገራቸው

ልማድ መሠረት ከማያውቁት ሰው ጋር ለማውራት አይደፍሩም። ስለዚህ ከሚያውቁት ጋዜጣ ጋር ለማውራት ይገደዳሉ። በግዕዝ፣ "ንባብ" የሚለው ቃል፣ "መነጋገር" የሚል ትርጉም አለው። መጽሐፍ አነበበ ማለት ከመጽሐፉ ጋር ተነጋገረ ማለት ኖሯል። ጥቁሩ ስደተኛ አብዛኛውን ጊዜ ብቻውን አይወጣም። ወይ ዘመድ ወይ ሀገር አላማጅ ጓደኛ አጠገቡ ይኖራል። እናም ከወረቀት ጋር ሳይሆን ከሕያው ወንድሙ ጋር ይነጋገራል።

ስለዚህ ፈረንጅ ተሣፋሪዎችን ባንባቢነታቸው ማድነቅ ጥቁር ተሣፋሪዎችን ባለማንበባቸው መናቅ ትክክል አይደለም። ለምሳሌ አንድ ቀን ወደ ማንቸስተር በሚወስደው ባቡር ውስጥ የማያነብ ተሣፋሪ እኔ ብቻ ነበርኩ። ባነብ ኖሮ በመስኮት በኩል ያየኋቸው ብዙ ድንቅ ትዕይንቶች ያመልጡኝ ነበር። ለምሳሌ የሐብታም አፀድ የመሰለ መካነ መቃብር አየሁ። እጅግ ብሩህ ንፁህ በሆነ አረንጓዴ መስክ ላይ ነጫጭ ሰሌዳዎች እንደ ፈንድሻ ተበትነዋል። እንዲህ ያማረ መቃብር ቢኖረን ኖሮ ሙታንን ደረት እየመታን ሳይሆን ከበሮ እየመታን እንሸኛቸው ነበር። በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ ጫፍ ላይ በሚገኝ አንድ ደብር ጓሮ ለቀብር ተገኝሁ። በየመቃብሩ ማኸል ላይ የተነሰነሰውን አይነምድር ላለመርገጥ፣ እንደፈንጅ አምካኝ በጥንቃቄ መራመድ ነበረብኝ። ምን ማድረግ ይቻላል? ያለኝ አማራጭ ኢትዮጵያ ውስጥ ኖሬ እንግሊዝ ውስጥ መሞት ነው።

*****

አንዳንዴ፣ "አገሬ" የተባለውን ገብረክርስቶስ ደስታን ግጥም አነብ አነብና

"አገሬ ቆላ ነው ደጋ ወይና ደጋ፤
እዚያ ብርሃን አለ ሌሊቱ ሲነጋ"

የሚሉት መስመሮች ላይ ሲደርስ ግራ እጋባለሁ። በተለይ የመጨረሻው መስመር ተራ ይሆንብኛል።





"እዚያ ብርሃን አለ ሌሊቱ ሲነጋ" የሚለው ሐሳብ ምን የሚገርም ነገር ኖሮት የገብሬን ልብ ማረከ እላለሁ።

ለንደን ስንበትበት ስል ግን ተራ የነበረው የገብሬ ግጥም ሳይሆን፣ የእኔ ችኩል ግምገማ መሆኑ ገባኝ። ገብሬ እኒያን ስንኞች የደረሳቸው ጀርመን ኮሎኝ ውስጥ በስደት ሳለ ነው። ሲነጋም በሚጨልምበት ወቅት ውስጥ ሆኖ ነው።

በእኛ ሀገር ንጋትና ብርሃን፣ ሌሊትና ጨለማ የማይነጣጠሉበት ውል አላቸው። አውሮፓ ስንገባ ይህ ውል ይፈርሣል። ባገራችን እንደ ተራ ነገር የቆጠርነው የንጋት ብርሃን በሰው ሀገር ተቀምጠን ስናስበው እንደ ሉል የከበረ ሆኖ ይታየናል። "እዚያ ብርሃን አለ ሌሊቱ ሲነጋ" የሚለው የገብረክርስቶስ መስመር ትልቅ ትርጉም ይዞ ብቅ የሚለው ይኸኔ ነው።

በለንደን የሚኖሩ አበሾች በሥራ ሰዓት ሸንጣቸውን ገትረው ይዝናናሉ። በእረፍት ሠዓት ደሞ ሌላ ነገር ገትረው ይዝናናሉ። ከዋና ዋና መዝናኛዎች አንዱ ጫት ነው። እነ ገለምሶ የቪዛ ደጅ ጥናት ሳያጉላላቸው ቀድመውኝ ባሕር ተሻግረው አገኘኋቸው። ዝነኛው ማሙዬ ጫት ቤት ውስጥ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ተደባልቀው ተቀምጠው ቅጠሉን ከወሬው ጋር ያደቁታል። በአንድነት መኖር ያልቻሉት ወንድሞቻችን ባንድነት መቃም አላስቸገራቸውም። ይህንን ስመለከት፡-

"ድንበር ቢለያችሁ
ሱስ አገናኛችሁ"

በማለት በልቤ አንጎራጎርሁ። በአወዛጋቢው የኢትዮ ኤርትራ ድንበር ላይም በተመድ ድጋፍ ጫት ቤት እንዲከፈት ተመኘሁ። ከባሩድ ጭስ ወደ ሺሻ ጭስ መሸጋገር በራሱ እድገት ነው።

በለንደን ያገኘኋቸውን አበሾች ውለታ በሌላ ጊዜ እፅፋለሁ። እለዚያም ለባለውለታዎቼ የምሥጋና ድብዳቤ እፅፋለሁ። ብዙዎቹ በጣም ቅኖችና ብሩሆች ናቸው ማለት እችላለሁ። ታዲያ እንደ ርግብ ብሩህ የሆኑ ያሉትን ያህል እንደ አይነርግብ የጨለሙም ይኖራሉ። ዛሬ ባዲስ አበባ፣ መደባደብን





በውቤ በረሃ ጊዜ የቀረ አራዳነት አድርገን በምንቆጥርበት ሰአት፣ የተፈነከተ ሰው ስናይ፣ "ከማን ጋር ተጋጨህ" ሳይሆን "ከምን ጋር ተጋጨህ" በምንልበት ሰአት፣ በለንደን ምግብ ቤቶችን በአምባጓሮ የሚቀወጡ ጉልቤዎች ሞልተዋል። የአገሩ ሕግ የጦር መሣሪያ መታጠቅን አይፈቅድም። ጉልቤው ስደተኛ ግን የቢራ ጠርሙሱን ወደ ጦር መሳሪያ ለመቀየር አልተቸገረም።

ጥቂት የአበሻ ሬስቶራንት ባለቤቶች ጠቡን ከማስቀረት የጦር መሣሪያውን ማስቀረት ይቀልላል ብለው፣ የብርጭቆ ጠርሙሶችን በላስቲክ መጠጫዎች ተኳቸው። ይሄ ለውጥ ብዙ ሰላማዊ ጠጭዎችን አላስደሰተም። "ውስኪ በፖፖ እየቀረበልኝ እንዴት እንድዝናና ትጠብቃለህ?" ብሎኛል አንዱ የተማረረ።

አንድ ቀን ከማራቶን ምግብ ቤት ፊትለፊት በሚገኝ ጉዳና ላይ አበሾቹ ለሁለት ተቧድነው፣ ሲከታከቱ የሚያሳይ የሞባይል ቪዲዮ ተመለከትሁ። አንዱ ሌላውን በከዘራ ሲያባርረው ያየሁ ስለመሰለኝ፣ "ከዘራውን ከየት አገኘው?" ብዬ ባለ ቪድዮውን ጠየኩት። "እንጃባቱ! ከብሪቲሽ ሙዚየም ሰርቆት ይሆናል!" የሚል መልስ ቀረበልኝ።

ሓይድ ፓርክ የተባለ ሰፈር ዐርፌ ነበር። ከሆቴሉ ፊትለፊት ካለው አስፋልት ተሻግሮ የቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን ይገኛል። ደጃፉ ላይ ያለው ጽሑፍ ባይነግረኝ ኖሮ ቤተክርስትያን መሆኑን ማወቅ አልችልም ነበር። ደብሩን በከበቡት ርጥብ ዛፎች ላይ አዋፋት ይቀድሳሉ፤ የቀሳውስት ድምጥም ሆነ ዳና ግን አይሰማም።

ባገራችን እያደር የሚጎመራው ሃይማኖት አውሮፓ ውስጥ እለት በእለት አቅሙ እየተሟጠጠ ነው። ገዳማት ጥንታዊ ከሆኑ ወደ ቤተመዘክርነት፣ዘመናዊ ከሆኑ ደሞ ወደ ቤተ ዳንኪራነት ይቀየራሉ። በሌሎች ያውሮፓ ከተሞችም እግዜር ደብዛው እየጠፋ ነው። አምስተርዳም ውስጥ ዳም ተብሎ በሚጠራው አደባባይ አካባቢ ብዙ ጥንታዊ ቤተክርስትያኖች በየተወሰነ ምእራፍ ርቀት ቆመው ይታያሉ። ሰዎች እንደ ታቦት እጃቢ ትከሻ ለትከሻ እየተጋፉ የሚተምሙት ወደ ቅዳሴ ሳይሆን በቤተክርስያኖችን ተጎራብተው የቆሙትን መስታወታማ የሸሌ ሱቆች ለመጎብኘት ነው። በዳም አደባባይ እግር ጥሎህ





ስትራመድ አፍንጫህን የሚያውደው የሀሺሽ ጠረን እንጂ የቤተመቅደስ እጣን አይደለም።

ምንም እንኳ ሙልጭ ያልሁ ኢአማኒ ብሆንም፣ የእምነት ምልክቶች በሌሉበት ማኅበረሰብ ውስጥ መኖር አሰልቺና ጣእም አልባ መሆኑን ለመረዳት ብዙ ጊዜ አልፈጀብኝም።

# የጎበና ቅኝት

"እጥንቱን ልልቀመው፤ መቃብር ቆፍሬ
ጎበናን ተሸዋ፤ አሉላን ተትግሬ
አሉላን ለጥይት፤ ጎበናን ለጭሬ
አሉላ ሴት ልጁን፤ ጥይት ሲያስተኩስ
ጎበና ሴት ልጁን፤ ሲያስተምር ፈረስ
አገሬ ተባብራ፤ ካረገጠች ርካብ
ነገራችን ሁሉ፤ የምቧይ ካብ
የምቧይ ካብ
ትምርት እንዲስፋፋ፤ ጉልበት እንዲጠና
አራቱ ጉባኤ ይዘርጉልንና
ጎበና ከፈረስህ ጋር ተነሥ እንደገና
ተነሥ እንደገና"

(ቀኝጌታ ዮፍታሄ ንጉሤ)





## ስኬትና ሹመት

ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ በነበረበት ወቅት ለመጀመርያ ጊዜ የራስነት ማእረግ ያቀዳጀው ለሁለት ሰዎች ነው። የመጀመርያው ተሿሚ የንጉሥ ሣሕለሥላሴ ልጅ ዳርጌ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሸዋ ነጋሢነት ዘር የሌለው ጎበና ዳጬ ነው። የዚያን ዘመኑ የራስነት ማእረግ ከዛሬው ጄኔራልነት ሹመት ጋር ይተካከላል። ለሁለቱ መኳንንት ሹመቱ የተሰጠው በሰሜን ሸዋ ከፍለሀገር ደብረብርሃን ላይ ሲሆን፣ የሹመት አሰጣጡ ስነሥርዓት በመንፈሳዊና ዓለማዊ ትርኢት የደመቀ እንደነበረ ተመስክሮለታል።

ለዝርዝሩ አለቃ አጽሜ፤

"በ1871 ዓ.ም. በዘመነ ሉቃስ በወርኃ ጥቅምት የሸዋ ሰው ካህናቱም ሁሉ በከተት ልቼ ከከተማው ተሰበሰበ። በየመንደሩ ለሹል የደረሰ ወንድ ልጅ እስከሽማግሌው አንድ አልቀረም። ሁሉም በከተት ተሰብስቦ በገባ ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ ከልቼ ተነሥተው ደብረ ብርሃን ወርደው አደሩ። ከዚያ ከሥላሴ ቤተክርስትያን ከፀጼ ዮሀንስ የተቀበሉትን ዘውድ ሲጭኑ፣ (ምኒልክ ከቤተክርስትያን ሲወጡ ዘውድ ጭነው ነበር) ከሺህ የሚበልጡ ቀሳውስት በዙርያቸው እጣን እያጠኑ፣ ካህናቱ ደብተሮች በፊታቸው እየረገጡ፣ ወታደሩ እየጨፈረ፣ የደጃች ጎበና ሠራዊት የመላ ትሎማ (ኦሮሞ) በፈረስ ጉግስ እየተጫወተ፣ በቀኝና በግራ ሆኖ እየጋለበ፣ ሴቱ እልል እያለ፣ ከደብረብርሃን ጀምሮ እስከ ልቼ፣ እስከ ቦሎ ወርቄ፣ እስከ ሳርያ በሠራዊት ተመላ። ሜዳው ሁሉ ጠቦ ነበረ። ንጉሡም ህዝቡም በደስታ በክብር ልቼ ገቡ። ታላቅ በአል ተደረገ። ታላቅ ምሳ ተሰናዳ። ከምሳ በፊት ራስነት ለራስ ዳርጌና ለራስ ጎበና ተሰጠ።"

ሹመቱ ባንድ በኩል፣ ሁለቱን ዋና ዋና ብሔረሰቦች የሚወክሉ ተዋጊዎች ተመጣጣኝ ሥልጣን የተጎናጸፉበት፣ በሌላ በኩል የዐማራና የኦሮሞ ባህል ትርኢቶች ባንድ መድረክ ላይ የቀረበበት፣ የኅብረብሄራዊ ሀገር መሠረት የተጣለበት አጋጣሚ ነበር ማለት ይቻላል።





ጎበና ከእቶኑት ማእረግ ተነሥቶ ባጭር ጊዜ ከንጉሥ ሣሕለሥላሴ ወንድም ተካከሎ እንዲቆም ያደረገው አስደናቂ የሆነው የአዋጊነትና የተዋጊነት ችሎታው መሆኑ ብዙዎችን ያስማማል። ዛሬ አዲስ አበባ በሚል ስም የምናውቀው ክልል ውስጥ ይኖሩ የነበሩትን፣ ለሸዋ መርድ አዝማቾች ሳይደፈሩ የቆዩትን ፊንፊኔ፣ ግምቢቹ፣ ገላን፣ ሜጫ፣ በቾና ጉለሌ የተባሉ ጎሳዎችን አስገብሯል። እኒህ የኦሮሞ ጎሳዎች ለብዙ ዘመን ያከል ባስገባሪዎች ሳይንበረከኩ በመቆየታቸው ከጎበና በቀር ማንም አያሸንፋቸው ተብሎ ይታመን ነበር። እናም በገበሩ ማግስት ካስገባሪው ወገን የቆመ አዝማሪ፤

"እመ ሠላሳ ቀን፣ ጎበና ባይጸና፤
ይካፈሉን ነበር፣ እነ ቱፋ ሙና" ብሎ አዝምሯል።

"እመ ሰላሳ ቀን" ማለቱ ፊታ'ኙ ጦርነቱ የፈጀውን ጊዜ ለመግለጽ መሰለኝ። ባዝማሪው ግጥም መዝጊያ ላይ የተጠቀሰው "ቱፋ" በወቅቱ ይፈሩ ከነበሩት የአብቹ ባላባቶች ፤ማንባር ቀደሙ ነበር። ጎበና በማስቀጠል ወደ ደቡብ ምእራብ ዘምቶ ጉማን፣ ኖኖን ጌራን፣ ጅማን፣ ወሊጋንና ከፋን በዱላና በመላ ለማስገበር ችሏል። ሰላሌና ጨቦ በጎበና ፈረስ አማካኝነት የኢትዮጵያ አካል ሆነዋል። ጎበና ያስገበራቸው የንጉሥ ግዛቶች ባጠቃላይ ሰባት ይደርሳሉ። በዘመኑ የነበረ አንድ የፈረንሳይ መንገደኛ እንደመሰከረው ታፍሮና ተፈርቶ የኖረውን ኀይለኛውን የከፋን ግዛት ጨምሮ አብዛኛውን የደቡብ ምእራብ ክፍል አስገብሮ ለምኒልክ ያስረከበው ጎበና ነው።







እንጦጦ ለጎበና ስትገብር ይህን ትመስል ነበር

የጎበናን አስደናቂ ስኬት በማስመልከት ፣ በምኒልክ ሠራዊት ውስጥ ወዶ-ገብ የነበረ አንድ የሩስያ ወታደር የጎበናን ጥሮተኛ ወታደሮች አናጋግሮ ባሠፈረው ማስታወሻ፤

"ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ አበሻ ፈረሱን በአዋሽ ወንዝ ውሃ ቢያጠጣ እንደ ብርቅ ጀብድ ይታይለት ነበር። ይሁን እንጂ በተከበረው በምኒልክ የጦር መሪ በራስ ጎበና ተደጋጋሚ ምት የጀግናው ብሔረሰብ ምከታ ሊሰበር ቻለ። ራስ ጎበና የሸዋ ሰው ሲሆን በአባቱ ኦሮሞ በእናቱ ዐማራ ነው። ምርጥ የሚባሉ ተዋጊዎች በሥሩ ይሰባሰባሉ። ራስ ጎበና ባለበት ቦታ ሁሉ ወረራና ድል ይኖራል። ራስ ጎበና ሲያውጅ በአሥር ሺህ የሚቆጠሩ ተዋጊዎች ጥሪውን ሰምተው በሥሩ ይሰለፋሉ። ሜዳ ላይ ይህ የተከበረ ራስ ድካምና ፍርሃት አያውቅም። የራስ ጎበና ዘመን የፈረሰኝነት የውጊያ ስልት ያበበበት ዘመን ነው። በወቅቱ የንፍጥ ውጊያ ብዙ አይታወቅም ነበር። ጦር፣ ብርቱ ፈረስ፣ የወረራ ፍጥነት እንዲሁም የሠራዊት ቁጥር ብልጫ የጎበና ድል መሠረቶች ነበሩ።

የጎበና የውጊያ ስልት፣ 'ሂድና በለው' በሚለው በሚወደው ቃል ሊጠቃለል ይችላል።"[5] ብሏል፡፡

አንዳንድ ሰዎች የማስገበሩ ዘመቻ በልኡላዊነትና በሰላም በሚኖሩ ብሔረሰቦች ላይ አስከፊ ውርደትና ጭቆና እንዳስከተለ አድርገው በማቅረብ አላስፈላጊ ቁጭት ይፈበርካሉ። ርግጥ ነው፤ የማስገበር ዘመቻው ነውጠኛ እንደነበረ አይካድም። ቢሆንም ነውጡን ለመጀመርያ ጊዜ ወደ ብሔር ብሔረሰቦች ያስገባው ጎበና ወይም ምኒልክ አልነበረም። ባስገባሪው ኀይል የተጠቃለሉ ግዛቶች ሉብቻቸው በሚኖሩበት ወቅት ለሰላምና ሉብልጽግና የተመቸ ያገር አስተዳደር ዘይቤ አልነበራቸውም፡፡ ግዛቶቹ ከመገበራቸው በፊት በጎሳ ጦርነት እርስ በርስ የሚታመሱ የጎረቤቶቻቸውን ርስት የሚቀሙና ባርያ የሚፈነግሉም ነበሩ። ጉማ፣ ካካ እና ጂማ የተባሉት የኦሮሞ ግዛቶች ከጎበና የማስገበር ዘመቻው ብዙ ዓመታት አስቀድሞ የገዳ ዲሞክራሲያቸውን አፍርሰው በፈላጭ ቆራጭ ሱልጣኖች ሥር ይተዳደሩ ነበር። በጨካኝ የወንጀለኛ መቅጫ ህጋቸው እንዲሁም በማያፈናፍን የጭቆና መዋቅራቸው የሚታሙም ነበሩ። ለምሳሌ በቴዎድሮስ ዘመን መግቢያ ላይ ደቡብ ኢትዮጵያን ያጠናው ቻርለስ ቤከ. ጉማን ጨምሮ በጊዜው ነጻ ስለነበሩት የጊቤ ግዛቶች ጽፏል። እንደ እሱ ትዝብት ከሆነ የጉማ ሕዝብ ከሌሎች ሀገር ሕዝቦች በከፋ መልኩ በባርነት ቀንበር ሥር ወድቆ የሚማቅቅ ነበር። ጨካኙ የጉማው ንጉሥ አንድ ሰው በፈጸመው እዚህ ግባ በማይባል ጥፋት ምክንያት መላውን ቤተሰቡን በባርነት የመሸጥ ልማድ ነበረው።[6]

[5] From Entoto to the River Barro – [Alexander Bulatovich Trans; Richard Seltizer] (Page 184)

[6] 'The inhabitants of Guma were more than those of any other country doomed to slavery; as thier sovereign, who has the character of extreme severity, is in the habit of selling whole family for offences –sometimes of the most trifling nature-commited by a single individual'- Countries On South Of Abyssinia [Dr Beke] (Page 259)





በከፋ አንድ ሰው በጥንቆላና ከተወነጀለ ከነቤተሰቡ ይቃጠል ነበር። የከፋው ንጉሥ ምግቡን በእጁ ቆርሶ መብላትን እንደውርደት ስለሚቆጥረው አጉራሽ ሎሌ ነበረው። አጉራሹ ባርያ ንጉሡን ከማጉረስ በቀር ሌላ የሕይወት ተእልኮ ስላልነበረው ንጉሡን የሚያጎርስበትን እጁን በከረጢት ጠቅልሎ የመኖር ግዴታ ነበረበት። በንጉሡ ዐይን ይህ ሎሌ ፤ሰው ሳይሆን ተንቀሳቃሽ ማንካ ነበር ማለት ይቻላል። ስለዚህ በኒያ ግዛቶች ውስጥ ሲኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ነጻነታቸውንና ሰላማቸውን በጎበና -ምኒልክ እንደተቀሙ ሊቆጠር አይገባም። ሲጀመር ከሰላምና ከነጻነት ጋራ ሙች ይተዋወቁና ።

የጎበና የማስገበር ዘመቻ ባካባቢው የተሻለ መረጋጋት ከማምጣቱ በላይ፣ ባካባቢው ያሉ ትንንሽ አገሮች ትልቅ ሀገር ሆነው ለትልቅ ዓላማ እንዲሰለፉ አድርጓቸዋል።

በብሔርተኞች ጎራ ያሉ አንዳንድ ጸሐፊዎች ምኒልክ ጎበናን ተጠቅሞ ጣለው እንጂ ከስኬቱ ጋር የሚመጣጠን ክብር አልሰጠውም የሚል ክስ ያቀርባሉ። እውነታው ግን ከዚህ ይለያል። ምኒልክ ከመኳንንቱ መካከል አንቱ ብሎ የሚጠራው ጎበናን ብቻ እንደነበር የሩስያው ወዶ ገብ ወታደር ቡላቶቪቹ ነግሮናል። አንቱታው የይስሙላ አልነበረም፡፡ የሸዋው ንጉሥ ጎበናን በተሟላ ክብር "የከፋ ንጉሥ" በሚል ማእረግ ሊሾመው ተሰናድቶ ነበር።

አንዳንድ ዘመናይ ነቃፊዎቹ እንደሚጽፉት ጎበና የምኒልክን ፈቃድ ለመፈጸም የተቀመጠ የንጉሥ ሎሌ ሳይሆን ራሱን የቻለ ጌታ ነበር። ሰውየው ስለራሱ ያለውን ግምት የገለጸበት የሚከተለውን ደብዳቤውን መመልከት የምለውን ጥሩ አድርጎ የሚያስረዳልኝ ይመስለኛል። ደብዳቤው፣ በርስት ሽምያ ሳቢያ በጎጃሞችና በሸዋዎች መካከል እምባቦ በተባለ ስፍራ ላይ በተደረገ ጦርነት ዋዜማ ለምኒልክ የተጻፈ ነው።

"በንጉሥ ሃብት በእግዚአብሔር ቸርነት አምናም የገበሩልኝ ሰባት ነገሥታት ከፋም ገበረልኝ። ሁሉም ለጥ ብሎ ተገዛልኝ። ነገር ግን ጎጃሞችን ጉማ ላይ ባገኛቸው የተቀበሉትን ግብር የማረኩትን ምርኮ አስጥየ ዳግመኛ አባይን እንዳይሻገሩ አስምየ አስገዝቼ ሰደድኳቸው። በኋላ ግዛታቸውን አፍርሰው ፊጠሙን ጥሰው ራስ በዛብህን ጨምረው ሊወጉኝ መጡ። ስንኳን እነዚህን





ጌታቸውን ንጉሥ ተክለሃይማኖትን ጨምረው ቢመጡ ጉዳየ አይደለም። ወደ ንጉሥ መላኬ አለፈቃዴ ሳትነግረኝ ለምን ተዋጋህ እንዳይሉኝ ነው።"[7] (የሥር መስመር የተጨመረ)

ደብዳቤው ላይ አጽንኦት የተሰጠው መስመር የሚያስረዳው፣ ጎበና ራሱን አስገባሪና ገዥ እንጂ ጉዳይ አስፈጻሚ አድርጎ የሚያይ እንዳልነበረ ነው፡፡

ሶሊሊ የተባለው ፈረንጅ መንገደኛ ደቡብ ኢትዮጵያን የመጎብኘት ፍላጎቱን በገለጸለት ጊዜ ጎበና "በምገዛው ሀገር ሁሉ መሄድ ትችላለህ፣"[8] የሚል ማስተማመኛ ቃል እንደሰጠው ጽፏል። ይህ አገላለጽ የጎበና ሥልጣን የይስሙላ እንዳልነበረ ማስረጃ ይሆናል።

ባገራችን ከትቢያም ይነሣ፣ ከንጉሥ ይወለድ አንድ ሰው በጦር ሜዳ ላይ ብልጫ ካሳየ በሕዝብ ዘንድ ይከበር ነበር። ብዙ ጀግኖች ባዝማሪ ሲወደሱ ኖረዋል። ባለታሪካችን ግን ከመወደስ አልፎ፣ "ጎበና ቅኝት" የሚባል የማሲንቆ ምት ተሰይሞለታል።[9]

ጎበና በዘመኑ በሀብትና በሹመት ከመከበሩም በላይ ሌሎችን የሚያስቀና እድል ገጥሞት ነበር። ምኒልክ የጎበናን ዝምድና አጥብቆ ስለፈለገ ልጁን ሸዋረገድን ለጎበና ልጅ ለወዳጆ ጎበና ኢጋባ። በዚህ የተደሰተው ራስ፣ ለምኒልክ 1300 ፈረሶች፣ 500 በቅሎዎች፣ የዝሆን ጥርስና፣ ወርቅ በጥሎሽ መልክ አበርክቷል። በኔ አስተያየት ይህ ጋብቻ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንድ መልካም ገጽታ ተድርጎ ሊወሰድ ይችላል።

በሀገራችን ከማስገበር ፍላጎትና ከርስት ሽምያ የሚመነጭ የደም መፋሰስ ታሪክ ቢኖርም "ደምህ ከደሜ ጋር አይቀላቀል" የሚያሰኝ ዘረኝነት በፖሊሲ መልክ አልነበረም። ጉዳዩ ቀላል ነገር አለመሆኑን የምንገነዘበው በንጽጽር ስናየው

[7] አለቃ አጽሜ ፤ከባይሩ ተፍላ፤ (ገጽ 726)
[8] P. Soleillet, Explorations éthiopiennes (Page10)
[9] መክብብ ደስታ፤ ያቆ መሰንበት ባልንጀርነት ታሪክ፤ የምሲጋና ግጥም (ገጽ 311)





ነው። ለምሳሌ፣ የጣልያን ፋሺስት ወራሪ ኢትዮጵያን ለአምስት ዓመታት ያክል በብረት ጨብጦ በቆየበት ወቅት ማንኛውም የጣልያን ወታደር ካገር ተወላጅ ጋር እንዳይጋባ የሚከለክል ሕግ አውጥቶ ነበር። ክልከላውን ተላልፎ ዐማራ ወይም የኦሮሞ ሴት ያገባ የአምስት ዓመት እሥር ይፈረድበት ነበር። የምኒልክን አስገባሪነት ታሪክ ከአውሮፓ የቅኝ ግዛት ታሪክ ጋር እቻ ለማድረግ የሚቃጣቸው ሰዎች የሚስቱት ይሄንን ነው።

በዘመናችን የገነነውን የአምባጓሮ ፖለቲካ የሚመኑት የብሔር ፓርቲ ልሂቃን የሚያቀራርቡ ታሪካዊ ክስተቶችን አይተው እንዳላዩ ያልፏቸዋል። አንድ በአብሾ የሰከረ የሜዳ ቂስ፣ "ከጋ...ና ሻንቅላ የተጋባ ገሀነም ይወርዳል" ብሎ "ራእየ ማርያም" ላይ የጣፈውን ስድብ ሺህ ጊዜ በመጥቀስ የነፍጠኛው ሥርዓት ፖሊሲ መገለጫ አድርገው በማቅረብ ምሬትን የሚነዙ ሰዎች፣ የነፍጠኛው ሥርዓት እንዲህ ያለ በጎ ባህል እንደነበረው ሊያስታውሱ ከቶ አይፈቅዱም።

ወዳጆ ጎበናና ሸዋረገድ ምኒልክ ከትዳራቸው ወሰን ሰገድ የተባለ ልጅ አፍርተዋል። ወሰንሰገድ፥ የምኒልክን አልጋ እንዲወርስ ታጭቶ የነበረ ቢሆንም በአሥራ አራት ዓመት እድሜው ስለተቀጨ የታሰበው ሳይሆን ቀረ።



የራስ ጎበና ልጅ እና የምኒልክ ሴት ልጅ ጋብቻ ውጤት የሆነው ወሰንሰገድ ወዳጆ ይህ ነበር።

የጎበናን ያክል በውጭ ሀገር መንገደኞች የተደነቀ ታላቅ ሰው በዘመኑ ያለ አይመስልም። አንሬ አደን የተባለ አሳሽ ከባልደረባው ጋር ሆኖ ራስ ጎበናን ጎብኝቶ ነበር። አሳሹ ከጉብኝቱ በኋላ ባሠፈረው ማስታወሻ ላይ፣





"ራስ ጎበና ከንጉሡ ቀጥሎ ያለው ኃያል ሰው ሲሆን፣ በሃብት መጠን ግን ንጉሡን ይበልጠዋል። የላቀ ሰብእና ያለው ሰው ነው። የብሩህ አእምሮ ባለቤት ነው። ልበሙሉ እና ከአድልኦ ነጻ ነው። በጥቂት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከተራ ወታደርነት ተነሥቶ ወደ ትልቅ ማእረግ ለመውጣት ችሏል።" በማለት ጽፏል።

አሳሹ ከእንጦጦ 35 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኝ ፣ፋሌ በተባለ ሥፍራ የተገነባውን የጎበናን ግቢ ከጎበኘ በኋላ በግርማው ከንጉሥ ቤተመንግሥት እንደማይለይ ይመሰክራል። አሳሹ በወሎየው ካቶሊክ በአባ ዮሀንስ አነጋጋሪነት ከራስ ጎበና ጋር አወጋ። ከጓደኛው ጋር ታላቅ መስተንግዶም ተደረገለት። ሁለቱ ፈረንጆች በከበርቴው ራስ ችሮታ፣ አንድ ሰንጋ ፣ጥቂት በጎች፣ እንጀራና ጠጅ ተበርከቶላቸው ዓለማቸውን ቀጭተዋል።

በጊዜው ወደ ሸዋ የመጡ የውጭ ሀገር መንገደኞች የመኳንንትን መልክ ከተቻለ በፎቶግራፍ ካልተቻለ ደግሞ በርሳስ ንድፍ ለማስቀረት ይሞክሩ ነበር። ደብረ በበኩሌ በይፋ የሚታወቅ የጎበና ፎቶ ወይም ምስል አላጋጠመኝም። ደብረ ሊባኖስ በሚገኘው መካነ መቃብሩ ላይ የሚታየው ፈረስ የሚጋልብ ሽማግሌ ምስል የጎበናን አማናዊ መልክ መወከሉ ያጠራጥራል። በርግጥ የፈረንጅ መንገደኞች ፎቶውን ባያስቀሩልንም ምን እንደሚመስል በጽሑፍ ሊሥሉልን ሞክረዋል። ቢያንቺ የተባለው የጣሊያን መንገደኛ የጎበናን መልክ በአውሮፓዊ መመዘኛ ገምግሞ "መልከ መልካም፣ ከንፈሩ ሳሳ ያለ፣ ራሱ አነስ ያለ፣ በበኩሉ በብርታቱ በሸዋ ተወዳዳሪ የሌለው" በማለት ከቦታል። ገፍልየ ቦረሊ በበኩሉ በብርታቱ በሸዋ ተወዳዳሪ የሌለው" በማለት ከቦታል። ገፍልየ ቦረሊ በበኩሉ ከባለታሪካችን ጋር ከተዋወቀ በኋላ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ እኒህን ቃላት አስፍሯል።

"ጎበና ሰድሳ አልፎታል፤ ፊቱ የደግነት ገጽታ የተላበሰ ነው፤ ጸጉሩን ተላጭቷል። ጃኖ ለብሶ፤ አልጋ ላይ ተቀምጦ ነበር።"

ቦረሊ በሌላ ጊዜ ጎበናን ሲያገኘው፣

"ግምጃ በለበሰ አልጋ ላይ ተቀምጧል። ከፊት ለፊቱ በሞሰብ እንጀራ በቀይና አልጫ ወጥ ቀርቦለታል። በርካታ ቤተሰብ አባላት ከበውታል። ካጠገቡ ሌሎች አምስት ሞሰቦች ተሰይመዋል። እስከ ሰውነታቸው አጋማሽ የተራቆቱ፣





በወገባቸው ዙርያ ሸማ ያገለደሙ ኀልማሶችና ብላቴኖች ጠጅና ጠላ ያሳልፋሉ። ከምግብ በኋላ ራስ ጎበና ስለዘመቻው ገድል በሰፊው አወጋኝ።[10] ብሎ በማስታወሻው አስፍሯል።

## ልደት

"ይታመሳል አሉ ከፋና ቦረና፤
አማን አደሉም ወይ እነ ራስ ጎበና።"

ጎበና የተወለደው ሰሜን ሸዋ ውስጥ በሚገኝ አማን በተባለ ቦታ ነው። የልደት ዘመኑ 1817 መሆኑ ተገምቷል። የጎበና ዘር ማንዘር ከፊት ወደ ኋላ ሲዘረዘር ዳጬ- ወዱን- የሮ- ኩታይ— ገሜ- ዋዩ -አብደላ- ዳጬ- ቦረና መሆኑ ተዘግቧል። የዘር ሐረጉን በቃል አጥንቶ በአለቃ አጥሜ መጽሐፍ ውስጥ እንዲመዘገብ ያደረገው የሥዓሊና ባለቅኔ ገብረክርስቶስ አባት ደብተራ ደስታ ነገዎ መሆኑ ታውቋል።

ጎበና እንደዘመኑ ልማድ ክርስትና ቢነሳም፣ እንደወሎው ራስ አሊ ወይም እንደወሲጋ ባለአባቶች የጥንት ስሙን ትቶ በክርስትና ስሙ አልተጠራም። ብዙ ጊዜ ከሀገር በቀል እምነት ወይም ከእስልምና ወደ ክርስትና የገቡ ሰዎች አዲሱን እምነት ከነባር ምእመናን በላይ አጥብቀው ይይዛሉ። የወረሼኮች አባት የሆነው ትልቁ ራስ አሊ ክርስትና ከተነሣ በኋላ፣ የአባቶቹን አጽም ቆፍሮ አውጥቶ ለማጥመቅ እስከመመኘት ደርሷል ይባላል። የወሊጋው ኩምሳ ሞረዳ፣ ገብረእግዚአብሔር በሚል ስም ክርስትና ከተነሣ በኋላ ባገሩ የሚኖሩትን ቃልቻዎች አላስቆም አላስቀምጥ ብሏቸው ነበር። ፈረንጆች ጀማሪ ዳያቆን ከጳጳስ ይብሳል፣ እንደሚሉት ወይም ያገራችን አረጋውያን፣ "አዲስ አረኛ ከብት አያስተኛ" ብለው እንደሚተርቱት መሆኑ ነው።

[10]ቦረሊ (ገጽ 164)





ጎበና ግን ከላይ ክርስትያን ቢሆንም፣ ውስጥ ውስጡን የዋቄፌታ እምነት ተከታይ ነበር ይባላል። የጎበና ቤተኛ የነበረው ቦረሊ ይህን ታዝቦ በማስታወሻው ሲጽፍ፣[11] (ጎበና) ከአባ ሙዳው ጋር በሥጋ ይዛመዳል ይባላል። ክርስትና ተነሥቷል፤ ይሁን እንጂ ውስጥ ውስጡን በቀድሞው እምነቱ ጸንቶ ቀርቷል" ይላል።

ጎበና በጎረምሳነቱ በውትድርና ማገልገል የጀመረው ከሸዋ መርድ አዝማቾች ሁሉ ባስተዳዳሪነቱ ችሎታው ወደርየለሽ በነበረው በሣሕለሥላሴ ዘመን ላይ እንደሆነ ይነገራል። ሣሕለሥላሴ ከኦሮሞ ጋራ በጋብቻ መዛመዱና አፋን ኦሮሞን ማወቁ ከኦሮሞ ማኸል ምርጥ ተዋጊዎችን ለማፍራት አግዞታል።[12]

የምኒልክን አያት ሣሕለሥላሴን ትክክለኛው የሸዋ ገዥ መድብ ፈጣሪ ብንለው አይበዛበትም። ሣሕለሥላሴ በዘመኑ በፊንፊኔና በእንጦጦ ዙርያ የጥንት ቤተክርስትያን ፍርሥራሾችን እንዲሁም ዝዋይ ላይ የብራና መጻሕፍትን በማግኘቱ "ሸዋ በግራኝ ዘመቻ ጠፍቶ በኦሮሞ የተወረሰ የክርስትያን ሀገር ነው" ብሎ እንዲያምን አድርጎታል። ይህ እምነት "የክርስትያን አባቶቼን ሀገር መልሼ በእጄ ማስገባት አለብኝ" የሚል ምኞት ቀስቅሶበታል። የማቅናት ዘመቻውን ለማድረግ ሲነሳ ከኦሮሞ ባላባቶች ጋር መጋጨት ጀመረ።

አሁን ሳስበው የአዲስ አበባና የአካባቢው ይገባኛል ጥያቄ የተጀመረው በሣሕለሥላሴ ዘመን ላይ ይመስለኛል። የብሔረሰባዊ ራስ ወዳድነት ፖለቲካ እስከቀጠለ ድረስ የርስቱ ሽምያ በመጭው ዘመንም ተቧጥፎ መቀጠሉ አይቀሬ ነው። ድርሻየን ይዠ ልሂድ በሚሉ ተገንጣይ ብሔርተኞች መካከል ብጥብጥ ከሚያስነሱት አካባቢዎች አንዱ የአዲስአበባ ርስት ጉዳይ ይሆናል። ታሪክ

[11]IL se dit proche parent de l'Abba Mouda.Il a embrassé le Christianisme; mais dans son for intérieur, i lest fidéle à sà premiére religion. (P 150)

[12]The king having rode on his mule for considerable time, descends and walks on foot like his people .He speaks the The Galla language pretty well (january 23,1840) Journal

የባለቤትንት ምስክር ሆኖ ይቅረብ እንኳ ቢባል ላንዳችን የሚያዳላ ምስክርነት የሚሰጠን አይመስለኝም።

እኔ ጎበና አካባቢውን በሚያስገብሩበት ወቅት በአዲስአበባ ዙርያ ያሉ መንደሮች ባለሀገሮቹ በብዛት አሮሞዎች ነበሩ። ያም ሆኖ የጥንት የክርስትያን ምልክቶች መገኘታቸው፣ሌሎች የክርስትያን እምነት ተከታይ ህዝቦች ለአካባቢው ባዕድ እንዳልነበሩ የሚያሳይ ነው። በአዲስ አበባ ነባር ሕዝብ ማን ነው? የሚለውን ጥያቄ የተለያዩ ሊቃውንት እንደ ፍላጎታቸው አቅጣጫ ሲመልሱት ደክመዋል። ግን የሚያረካ መልስ ያገኙ አልመሰለኝም። እንዲያው ለነገሩ፣ "ነባር" የሚባል ሕዝብ ከምን ዘመን እስከምን ዘመን የኖረ ነው? የሕዝቦችን አሠፋፈርና የቦታዎችን ስም መመዝገብ የተጀመረው ከሕዝቦች እንቅስቃሴ ታሪክ ዘግይቶ ነው። ዐረብ ፋቂህን የመሳሰሉ የታመኑ የታሪክ መዝጋቢዎች የውጭ ሀገር ሰዎች በመሆናቸው ያካባቢ ስሞችን እንደባላገሮች አድርገው ለመመዝገብ እንዳይችሉ የቋንቋ ገደብ ነበረባቸው። የአረጋውያን የቃል ምስክርነት የተባለውም ምስክርነቱ አያስመካም። ዛሬ ለጥቅም ሲል እንደመጣሉት የሚቀደድ አረጋዊ ሞልቷል። ውሸቱን ተናግሮ ቪላ ቤት መገንባት በተለመደበት ዘመን ውስጥ እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት ማደር ብርቅ ሆኗል።

በዚያ ላይ ሰዎች እንደ ፍላጎታቸው አቅጣጫ ነገሮችን የሚቆለምሙበት የቋንቋ አስማታቸው አይጣል ነው። ለምሳሌ ዝቋላ የሚለውን ቃል ዝ- ቆላ ከሚለው የመጣ ነው ብለው የሚተረጉሙ አሉ። የለም፤ ዝቋላ የሚለው "ጩቋላ" ከሚለው የተገኘ ነው ብሎ በሌላ ወገን የተከራከረም አልጠፋም ። ይህ ሁሉ ደማምረን ስናየው መሬቱ የማን ነው በሚለው ጉዳይ ላይ ደረት የሚያስነፋ ዕውቀት ሊኖረን አይችልም። ስለዚህ፤ እንደየፍላጎታችን አቅጣጫ ግምቶቻችንን ከማቅረብ ውጭ አማራጭ የለንም። እንደሌሎች ያገራችን ከፍሎች ሁሉ አዲስ አበባን በተለያየ ዘመን የተለያዩ ህዝቦችና ባህሎች ተፈራርቀውባታል የሚለው የተሻለ ግምት ሳይሆን አይቀርም። የዘመናችን ጀግና፤ "አንተ መጤ እኔ ባለቤት" እየተባባለ አጭር እድሜውን በብጥብጥ ከሚጨርስ አዲስ አበባን የሁሉም ብሔረሰቦች የጋራ ንብረት አድርጎ ቢቀበል ያዋጣዋል። ባንድ ሀገር ውስጥ እየኖሩ አንዱን ዜጋ ባለቤት፣ ሌላውን ደግሞ





ባዕድ የሚያደርግ የመሬት ሥሪት "እንረስ ካላችሁ ተስማምተን እንረስ/ አይሆንም ካላችሁ ተውት ዳዋ ይልበስ፣" የሚል ቀጭት በተገፋው ወገን ልብ ውስጥ መቀስቀሱ አይቀርም። አዲስአበባን የጋራ ቤት ማድረግ እየተቻለ ወደ ጋራ መቃብርነት መለወጥ ለማንም አይጠቅም።



በማስገበር ዘመቻው ወቅት ከተገኙት ጥንታዊ የሕንጻ ፍራሾች አንዱ ከጀርባ ይታያል። የፎቶው ምንጭ (vers faschoda)





## ጎበና ወደቀ፤ሀገር ተነቀነቀ

ጎበና በታሪክ ውስጥ ያለውን ከፍ ያለ ቦታ ለማሳየት አንዳንድ ክስተቶችን እናስታውስ። ምኒልክ ሀረርን ለማስገበር ሲዘምት ጎበና ከጣይቱ ጋር አልጋ እየጠበቀ በሸገር እንዲቆይ አዞት ነበር። ይህ ሁለት ነገር ያሳያል። አንድም፣ ምኒልክ ለጎበና ዙፋኑን በአደራ ጥሎ የሚያስኬድ እምነት እንደነበረው ያሳያል። አንድም፣ በአካባቢው የገባሮች አመጽ ቢነሣ ከጎበና የተሻለ አክሻፊ የለም ብሎ እንደሚያምን ያሳያል።

ጦርነትን እንደሙያ ሳይሆን እንደ የሕይወት ዘይቤ ይቆጥሩ የነበሩ የጊዜው ጦረኞች የሰላሙን ጊዜ እንዴት ማሳለፍ እንዳለባቸው ባለማወቅ ይቸገሩ ነበር። ስለዚህ የጦር አራራቸውን ለመወጣት ጉግስ በመጫወት ያሳልፋሉ። አንድ ቀን ራስ ጎበና በጉግስ ጨዋታ ላይ እያለ ከፈረስ ወደቀ። በጊዜው ሽምጥ ከሚጋልብ ፈረስ ላይ ወድቆ መትረፍ የቻለ አዛውንት ወይ እድለኛ ነው ወይ ልእለ-ሰብአዊ ብርታት የታደለ መሆን አለበት። ከዚያ በፊት የዳርጌ ጎረምሳ ልጅ ከፈረስ ተፈጥፍጦ ሞቷል። ጎበና ሕይወቱን ባያጣም አለቃ ገብረሥላሴ እንደጻፈው "አጥብቆ ታመመ።"

ቦረሊ እንደተረከው፣ በወቅቱ የኦሮሞ ባላገሮች ራስ ጎበና በወደቀበት ቦታ ደም በማንጠባጠብ ፣የዐማራ ካህናት ደግሞ ድጋም በመድገም፣ ጎበናን የጣለውን ክፉ መንፈስ ለማባረር ተረባርበዋል። ይህ ማኅበራዊ ምላሽ ሰውየው በጊዜው ምን ያህል ተወዳጅ እንደነበረ የሚያሳይ ይመስለኛል።

የጎበና ከፈረስ መውደቅ ባንድ መኮንን ላይ የደረሰ አደጋ ሆኖ የሚያልፍ ሳይሆን አጠቃላይ ሥርአቱን የሚንጥና መሬት የሚያንቀጠቅጥ ክስተት ነበር ማለት ይቻላል። አለቃ ገብረሥላሴ ይህን አስመልክቶ ሲጽፍ "ህዝቡም የንጉሡን ወሬ መጥፋት የራስ ጎበናን መታመም ባየ ጊዜ አገሩ ተናወጠ።" ብሏል።[13] በጊዜው የአገሩ ደህናነት ከምኒልክ ጎበና ደህናነት ጋር መሳ መሆኑን

[13]ታሪክ ዘመን፤ (ገጽ 43)





ያሲቃ አገላለጽ መገንዘብ ይቻላል። በዚያ ቀውጢ ጊዜ ጣይቱ የሕዝቡን ነውጥ ለመቀልበስ እጅግ መለኛ የሆነ እርምጃ ወስዳለች። ቀልጠፍ ብላ በፍልውሃ ዙርያ ቤት ማሠራት ጀመረች። ሕዝቡም አዳዲስ ሕንጻዎችን የመንግሥት ህልውና ማሳያ አድርጎ ስለቆጠራቸው ተረጋግቶ መኖሩን ቀጠለ።

## ሞትና ውርስ

የራስ ጎበናን አሟሟት በተመለከተ ከኦሮሞ ምንጭ የተገኘው እንዲህ ይላል።

"ራስ ጎበና ከዚያ (ከደርቡሽ ዘመቻ) ተመልሰው .. ቤታቸው ገብተው ጥቂት ቀን ሳይቆዩ 'አሰን ወንጀቦ የሚባል ከድቷልና መጥተህ እንድትዘምት' ብለው ዐጼ ምኒልክ ራስ ጎበናን አዘዟቸው ። ላኩባቸው። ራስ ጎበናም ወጥተው ከአሰን ወንጀቦ ገጥመው የራስ ጎበና ሠራዊትም እዚያ ብዙ አለቀ። ራስ ጎበናም አሰን ወንጀቦን ድል አደረጉት። ከዚሁ ካሰን ወንጀቦ ጦርነት ተመልሰው እፋሌ ቤታቸው ገብተው ጥቂት ሳይቆዩ ሞቱ።"[14]

አለቃ አጥሜም ጎበና ከሀሰን ወንጀቦ ዘመቻ በኋላ ወደ እንጦጦ በድል አድራጊነት መመለሱን ከጻፈ በኋላ፣ "በ25 ሰኔ ከቾሎት በኋላ ታመሙ። ራስዎን ሰኞ ማታ። በ27 ረቡእ በሰለስት አረፉ። ደብረሊባኖስ ተቀበሩ።" ብሏል

ጎበና እንጦጦ ላይ ታሞ ሲሞት ምኒልክ ወሎ ቦሩ ውስጥ ነበር።

"ዐጼ ምኒልክ ቦሩ ላይ ሊከርሙ ሳለ ራእይና ህልም የሚያውቅ መነኩሴ ላኩብዎ። ወሎ አይከረሙ። ሀገርዎ ይግቡ። መንግሥትዎም ይፈርሳል ሲል። ስለዚህ ገሰገሱ። ወንጭት ላይ ሲደርሱ የራስ ጎበናን መታመም ሰሙ። ገሥግ

[14]የወሊጋ ታሪክ ሰነዶች፤ (ገጽ 278)

ሲደርሱ ሞትዎን ሰሙ። ንጉሡም፡ መኳንንቱም (ኦሮሞውም) ዐማራውም በራስ ጎበና ሞት አዘኑ። እንጦጦ ከረሙ።"

በዘመናችን ከተፈበረኩ ወፈፍራም ውሸቶች መካከል አንዱ ጎበና በምኒልክ ተመርዞ ተገድሏል የሚለው ነው። ከምርምር ይልቅ አሜትና የሴራ ተረት ለሰፈነበት የአእምሮ ባህላችን እንዲህ አይነቱ ክስ የተለመደ ነው። አንዲት አሜሪካዊት ተመራማሪ፤ "ኢትዮጵያ ውስጥ ሰው በተፈጥሮአዊ መንገድ ይሞታል ብሎ ማሰብ ብርቅ ነው" ያለችው ወድዳ አይደለም። እንዲህ ዐይነት ክስ የሚፈበርኩ ሰዎች ምኒልክ ጎበናን መግደል ምን ይጠቅመዋል? ብለው የሚያስቡ አይመስለኝም። ጎበና በድሜው ፍጻሜ ወቅት ምኒልክ ከሁሉም አስበልጦ የሚመካበት ወዳጅ እንጂ ባላንጣ አልነበረም። ስለሆኑ ምኒልክ የገዛ ቀኝ እጁን ቆርጦ የሚያገኘው የፖለቲካ ፋይዳ ምንድነው?

ጎበና በተፈጥሮአዊ መንገድ ወይም እኛ ባላወቅነው በሽታ ሞቷል። ተመርዞ ሞተ የሚለው በኦሮሞና በዐማራ መካከል የወዳጅነትና የትብብር ታሪክ ነበረ የሚለውን ሀቁታ ለማፍረስ የተፈበረከ የሴራ ትረካ ነው።


ባገር ውስጥ አንድ ወሳኝ ሰው ሲሞት ተተኪ አለው ወይስ የለውም የሚለው ጥያቄ ትውልዱን ያሳስበዋል። "ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ" ያለው አዝማሪ ገበየሁና ባልቻ እኩያ መሆናቸውን ያውቃል። ገበየሁ ጥሎት የሄደውን ዱካ የሚሞላ እግር ያለው ጀግና መኖሩን አውቆም ተጽናንቷል። ጎበና ግን በዘመኑ መስፈርያ ምትክ ወይም እኩያ የተገኘለት አይመስልም። ይህንን ያጤነ አዝማሪ በፍጻሜው ዋዜማ ላይ፤

"የሚሰጡት ቢያጡ፤ ከድፍን አበሻ
ለእስራኤል ሰጡት፤ የጎበናን ጋሻ"

ብሎ ለማንጎራጎር የተገደደው ለዚህ ነው።











# የመጨረሻው ምሳ

## 1

ዳኛው ወደ ችሎቱ አዳራሽ ሲገቡ ሁላችንም ከየመቀመጫችን ብድግ ብለን ተቀበልናቸው። ረጅም ጠይም ቀጭን ባለገብስማ ጸጉር ሽማግሌ ናቸው። እንድንቀመጥ ምልክት ሰጡንና መነጽራቸውን ከሰገባቸው መዘዙ። ከፊት ለፊታቸው እንኳን ተነብቦ፤ ተቃጥሎ የማያልቅ የሚመስል የወረቀት ነዶ ተከምሮ ይታየኛል። እንግዲህ በዛ ነዶ ውስጥ የጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ እጣፋንታ ተሸሽጓል።

ከዳኛው ትይዩ ጉብ ብሎ የሚታየውን ግዙፍ ጠረጴዛ ደገፍ ብሎ ቆሞ ነበር። ፊቱ ላይ የተሣለው ደንታ ቢስነት ከፈራጁ ፊት መቆሙን እንድጠራጠር አደረገኝ። እንዲህ ዓይነቱ ፍርሃት አልባ ፊት ከስንት አንድ የሚገኝ ብርቅ ነገር ነው። ለመሆኑ የጀግና ሥራ መሥራት ቀርቶ ጀግናን የማድነቅ ባህላችን እንኳ ጥሎን እየጠፋ መሆኑን ልብ ብለነዋል? ተመስገን አንድ ልበ ሙሉ መጣጥፍ ጽፎ ባተመ ቁጥር፤ "አይሄዬ ከጀርባው ቆሞ አበጀህ የሚለው ሰው ቢኖር ነው እንጂ እንዲያው ከመሬት ተነሥቶ እንዲህ አይዳፈርም ነበር" እያሉ የሚያሙት ሰዎች መኖራቸውን ያውቅ ነበር። እንዲያውም ከፈራጆች ባልተናነሰ ከነጻ ፕሬሶች ጋዜጠኞች በኩል ከምቀኝነት የመነጨ የብእር ዱላ ሲወርድበት እንደኖረ ከብዙዎቻችን የተሰወረ አይደለም።







"ወዝውዘው ወዝውዘው ጣሉት እንደዝሆን፤
ያው ወደቀላቸው ይበሉት እንደሆን"

የሚለው የጥንት አልቃሽ እንጉርጉሮ ትዝ ይለኛል።

ኩተቀመጥኩበት ወደ ግራ ገልመጥ ብዩ የታዳሚውን እንቅስቃሴ ባይነቁራኛ የሚከታተሉ ፖሊሶችን አይቶ ስመለስ ዳኛው የክስ ጽሁፉን ሲያነቡ አገኘኋቸው። ሐረጎችንና ዐረፍተነገሮችን እየገደፉና እያረሙ በማንበብ ተጠምደዋል። የፍርዱን ጽሑፍ በደንብ ያጠኑት አይመስልም ።

አንድ ሁለት ገጾች እድምጬ ስለሰለቸኝ የተባለውም ነገር ስላላሳመነኝ ዓይኔን ወደጣራው ሰቀልኩ። ኮርኒሱ ላይ በርጥበትና በአድፍ ተሥሎ ከኮሎምበስ

በፊት የነበረውን የዓለም ካርታ የሚመስል ምስል ይታየኛል። እሱም ስለሰለቸኝ በእቅፌ ላይ ያስቀመጥኩትን፤ ሰሞኑን ለገበያ የበቃውን የፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌን "ባሕረ ሐሳብ" የተባለ መጽሐፍ በዘፈቀደ ገልጬ ማየት ጀመርሁ። በመጽሐፉ ውስጥ ያንድ ዘመን ዋና ዋና ክስተቶች በሚከተለው መንገድ ተደርድረዋል።

*-ታህሳስ 1 ፤ የንጉሡ ልጅ አቤቱ ዳዊት አምጾ፤ አዛዥ አትናቴዎስን ገደለው። ጃንደረባውን ጴጥሮስን አስሮ ወሰደው።*

*-ብላቴን ጌታ መልከአ ክርስቶስና ብላቴን ጌታ አይገበዝ ብዙ ሠራዊት ይዘው ዘመቱበት፤ተያዘ።*

*-ታስሮና ድንጋይ ተሸክሞ ሲመጣ እሱንም ልጁንም ወህኒ ሰደዷቸው።*

*-ጥር18፤ አቤቶ ደመ ክርስቶስ ታሰረ። ሰኔ 12 አካሌና አካሌ የሚባሉ መነኮሳት ለእግዝትነ ማርያምና ለመስቀል መስገድ አይገባም የሚል ክህደት በማስጠር ሲያስተምሩ ተይዘው ተመስክሮባቸው ተሰቀሉ።*

*-1674 የጻድቁ ዮሀንስ ዘመነ መንግሥት*

*- 11 አእላፍ ሰገድ ዮሀንስ ነገሡ።*

*-እግዚአብሔር ዮሀንስን ከአርባ አምስት ወንድሞቹ መካከል መርጦት ስመ መንግሥቱ አእላፍ ሰገድ ሆኖ ባባቱ ዙፋን ተቀመጠ። ሆኖም ወንድሞቹ ሁሉ እንዲጠበቁ ወህኒ አስገባቸው።*

ቢታሪካችን ውስጥ ያሉት ቁልፍ ቃላቶች "ታሰረ... ነገሠ... ዘመተ... ተሰቀለ" የሚሉ ብቻ መሆናቸው ገረመኝ። በዚህ ዐይነት መቀጠል ስላቃተኝ እያፏሸኩሁ መጽሐፉን ከደንኩት። ከጥቅምት 1614 ተነሥቼ፤ አያሌ የመስቀያ ዛፎችን ጥሼ፤ የጻድቁ ዮሀንስን ወህኒ ቅጽሮች አልፌ፥ ወደ ጥቅምት 2007 ተመለስኩ። እናም ከፊትለፊቴ የተሰየሙት ዳኛ በተመስገን ደሳለኝ ላይ ሲፈርዱ ደረስኩ።





እስካሁን ሲያነቡት የነበረው የጽሑፍ ዓላማ የተመስገንን ሕገወጥነት በምክንያትና በሕግ አግባብ ለማሳመን መሆኑን ስገምት ገረመኝ። የዘመኔ ፖለቲካ ተስጥኦ አልባ ተዋናዮች የሚጨማለቁበት አሰልቺ ተውኔት መሆኑን እስካሁን እንዴት ሳይገለጥልኝ ቀረ?

የዘመኔ ማለቴ አለምክንያት አይደለም። አባቶቻችን በስልጣናቸው ለሚመጣ ወንድም አይምሬ ነበሩ። ግን ሌላው ቢቀር እውነተኛ መሆናቸው አያጠያይቅም። በንጉሥ ላይ ማመጽ ክልክል ነው የሚል ሕግ ያወጣሉ። ሲወርድ ከመጣው እምነት ማፈንገጥ ወንጀል ነው ብለው ይደነግጋሉ። ይህን ሲጥስ የተገኘውን ሽፍታና መናፍቅ ወደ ወህኒ፤ ባስ ሲልም ወደ መስቀያው ምሶሶ ይገፈትራሉ።

በዘመናችን በጽሑፍ የሠፈረ መንግሥትን የመተቸት መብትን የሚያረጋግጥ ሕግ አለን። ያም ሆኖ፤ይህን ሕግ ተማምኖ የሚጽፍ ሰው ወደ ወህኒ ሲወረወር እናያለን። ወህኒ ቤትን ያስተዳደር እንቆቅልሾች ሁሉ መፍትሄ አድርጎ መውሰድ ከነጻድቁ ዮሀንስ የወረስነው ባህል ቢሆንም በሕግ ስም ማታለል የዘመናችን ጭማሬ ይመስለኛል።

ሕገመንግሥታችን እንደ አክሱም ሐውልት ነው። ያክሱምን ሐውልት ከሩቅ ስታየው በር አለው። ቀረብ ብለህ ስትመለከተው ግን የበር ሥዕል እንጂ በር አይገኝበትም።

ተሜ ይህንን ተውኔታዊ ፍርድ ተቀብሎ ጠረጴዛ ላይ ያስቀመጣትን ኮፍያ ብድግ አድርጎ በፖሊሶች ለመነዳት ተዘጋጀ። ጥቂት ፖሊሶች ተመስገንን አጅበው ወሰደው ፍርድቤቱ ግቢ ውስጥ በሚገኘው አዲስ በረት በሚመስል ቀፎ ውስጥ አስገብተው ቆለፉብት።

ፖሊሶች ጓደኛችንን አጅበው ሲወስዱት እኔና ጋዜጠኛ ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ እንደ መከተልም እንደ መሸሽም እያልን ከኋላው ስንራመድ ነበር። በሞባይሌ ካሜራ ሦስት ጊዜ ያክል ፎቶ ካነሳሁት በኋላ ሞባይሌን ኪሴ ውስጥ ጨመርኩት። ታሪክን በኪሴ ደብቄ ለመውጣት ያደረግሁት ሙከራ ግን ወድያው ከሸፈ።





"ና ወዲህ የሚል ድምጽ ሰማሁ፡"

ፖሊስ ነው። ግማሽ መስታወት ግማሽ ቆርቆሮ ወደሆነች ክፍል ውስጥ አስገባኝና፤

"ለምንድነው ፎቶውን ያነሳከው?"

"የሚፈቀድ መስሎኝ ነው!"

"ህምም የሚፈቀድ መስሎህ?" ፖሊሱ አሽሟጠጠኝ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎች በማጀታቸው የሚያደርጉት ነገር በካሜራ መቅረጽ በሕግ ተፈቅዷል (የጸረሽብር ሕጉ ምስክሬ ነው)፤ ግን ባደባባይ የተገለጠውን በካሜራ ማስቀረት ክልክል ነው። ይህ እንግዲህ ስፍር ቁጥር ከሌላቸው የዘመናችን ግርምቢጦች አንዱ ይመስለኛል።

ከጥቂት ወራት በፊት አዋሳ ውስጥ የቆመውን ያንድ የሲዳማ ጀግና ሐውልት ለማየት ባጃጅ ተሳፍሬ ሄድኩ። ቦታው ስደርስ ከሐውልቱ ጋር አብረው የሚጎበኙ የሚመስሉ ሦስት ፖሊሶች ቁጭ ብለዋል። ሐውልቱ ላይ ካሜራ ሳነጣጥር፤

"ሚን ፈለገህ ነው?" አለኝ አንዱ ፖሊስ በቁጣ።

"ፎቶ ማንሳት አይቻልም?"

ፖሊሱ 'ፎቶ ላንሳ' ሳይሆን 'ሐውልቱን አንስቼ ተሸክሜ ወደ ቤቴ ልሂድ' ያልኩት ያክል በከፉ ዐይን ከገላመጠኝ በኋላ፤

"ኢኛ ኢዚ ምን ሊናረግ የተቀመጥን ይመስልሃል? ጤፋ ከዚ!" ብሎ አንባረቀብኝ፤ እናም ከዚያ ጠፋሁ።

አሁን ደሞ ይሄው ባደባባይ የተገለጠውን ፎቶግራፍ ለማንሳት ስሞክር እጅ ከፍንጅ ተይዣለሁ። ጭጭ ብየ የሚመጣውን መጠባበቅ ጀመርሁ። በዛ ሰአት





ወህኒ መውረድ የሚባል ነገር ታየኝ። ከወህኒው ባሻገር ቶርቸር የሚባል ነገር ወለል ብሎ ታየኝ።

ከጥቂት ወራት በፊት አምስተርዳም ውስጥ በስድተኛ ጋዜጠኞች በማስረሻ ማሞና በደረጀ ሀብተወልድ ጋባዥነት በዳም አደባባይ የሚገኘውን፤ "ቶርቸር ሙዚየም" የሚባለውን የኪነ -ስቃይ ቤተመዘክር ጎበኘሁ። እዚያም ባንድ ወቅት አውሮፓውያን ጉልቤ ጌቶችና ካህናት፤ አመጸኞችንና መናፍቃንን ለማሰቃየትና ለመግደል ሲጠቀሙባቸው የነበሩትን መሣርያዎች ተመለከትሁ። ወንድም ወንድሙን የሚያሰቃይበትን መሣርያ ለመፈልሰፍ እንዲህ መጨነቅ መጠበቡ ገረመኝ። ሰው እንደ ግንድ የሚቆረጥበት መጋዝና ሰው እንደ ብቅል የሚፈጭበት ባለመንኮራኩር ወፍጮ፤ አጠገብ ቆሜ ፎቶ ተነሣሁ። በርግጥ አውሮፓ ውስጥ ቶርቸር፤ ቤተመዘክር ውስጥ የተወረወረ ታሪክ ሲሆን፤ ባገሬ ግን ያዘቦት ዜና ነው።

'Give me my libirty or Death' (ነጻነቴን ወይም ስጡኝ ሞቴን) ያለው የፈረንጅ አርበኛ በጣም የደላው መሆን አለበት። በነጻነትና በሞት መካከል የሚያማርጥ የፖለቲካ ትግል ዕዳው ገብስ ነው። ግን የማሰቃያ መሣርያ ታጥቆ "ነጻነትህን እወስድብሃለሁ፤ ሞትህንም እነፍግሃለሁ፤" የሚል ጉልበተኛ ሲገጥምህ ምን ታረጋለህ?

"አሁን ያነሳከውን ፎቶ ታጠፋለህ አታጠፋም? ሲል ባረቀብኝ ፖሊሱ።

እየተጣደፍኩ ተሜ ከጓደኞቹ ጋር ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፎ ሲሳሳም ያነሣሁትን ፎቶ አጠፋሁ። ቀጠልሁና፤ ግርግሙ ውስጥ የብረት ፍርግርጉን ጨብጦ ያነሣሁትን ፎቶ አጠፋሁ፡

"ቶሎ ቶሎ አጥፋ"

ከመደንገጤ የተነሣ ከሁለት ወር በፊት ላሊበላ ቤተ-ጊወርጊስ ፊትለፊት የተነሣሁትን ፎቶ ሳይቀር አጠፋሁ።

በመጨረሻ ፖሊሱ

"እድለኛ ነህ። ጥሩ ሰው ገጥሞሃል" አለና አሰናበተኝ።

እውነትም እድለኛ ነበርሁ።

## 2

ተመስገን ሰኞ ለፍርድ ሊቀርብ እሁድ ተሲአት ሃያሁለት ማዞርያ የመጨረሻውን ምሳ ለመብላት ተቀጣጠርን። ምርጥ ዘር በተባለው ኮንደሚኒየም ውስጥ ከሚገኘው ከኔ ቤት ተነሥተን፣ መንግሥተሰማያት የመሰለውን የፕሬዚዳንት ግርማን ቤት ታከን አለፍን። ከጥቂት ጊዜ በፊት የልጆች ትምርት ቤት የነበረና ሰሞኑን፣ "መሲ ባርና ካፕል" በሚል ወደ ተለወጠው ታጥፈን፤ እንደንጉሥ ላሊበላ ፊት በንብ የተወረረውን ጠቢያ ጠጅ ቤትን ወደ ግራ ትተን፣ በመንዳት ወደ "ሃፒ ምግብ ቤት" ጎራ አልን።

ተመስገን በጉዲፈቻ የሚያሳድጋቸውን ሁለት ብላቴኖች ያለወትሮው ይዞ መምጣቱን ልብ አልሁ።

በየፊናችን የቀረበልንን እየበላን ስናወራ፣

"ነገ የሚሆነው አይታወቅምና ዘና በል" አልኩት።

"ዘና በል ስትል?"

"ግልጽ ነው። ለምትወዳት ልጅ ደውልና ዓለምህን ቅጭ"

"እንደምታስበው ከውስጥ ዐዋቂ ምንም ስምቻለሁ። ልጆቹን ይዤ የመጣሁት ለዛ ነው። ከምሳ በኋላ እነሱን ሳዝናና ለመዋል አስቢያለሁ። የዛሬው ቀን የነሱ ነው።" ሲል መለሰ።

ዝምታ ነገሠ።





ዝምታውን ለመስበር ብዙ ነገር ቀባጠርኩ። ለምሳሌ የሚከተለውን ቀባጠርኩ።

በዝነኛው ምርጫ ዘጠና ሰባት ሰሞን፣ ከተቃዋሚው ወገን ፕሮፌሰር መስፍን፣ ከገዥው መደብ በኩል ደግሞ እንኳን ተነብቦ ተቃጥሎ የማያልቅ የሚመስል መጽሐፍ ያሳተሙ የነበሩት ፕሮፌሰር ከንፈ. አብርሃ በግንባር ቀደምነት ይጠቀሱ ነበር። በምርጫው ጦስ ፕሮፌሰር መስፍን ተይዘው ወደ እሥርቤት ተነዱ። እሥር ቤት ሲደርሱ የወህኒው ዘበኛ ገና ሲያያቸው በቃርያ ጥፊ አጮላቸው።

ፕሮፌሰር ከምቱ ይልቅ ባንድ ተራ ዘበኛ መመታታቸው አናደ ቸው፣

"አንተ እኔን ትመታኛለህ? አንተ እኔን? አንተ እኔን?" አሉት በንቀት እያዩት።

"ዋይ! ታድያ ሎርስዎን ቦጥፊ ሎመምታት ፕሮፌሰር ከንፈ. አብርሃ ይጠራ እንዴ?" አለ ዘበኛው።

ቀጥዬ ስለ ሻለቃ አድማሴ የሰማሁትን እውነተኛ ታሪክ አጫወትኩት። ሻለቃ አድማሴ በሽግግሩ ዘመን ፓርላማ ውስጥ በለዛቸውና ባወዛጋቢነታቸው የታወቁ ተቃዋሚ ነበሩ።

አንድ ቀን የሆነ አጀንዳ ተነሥቶ ፓርላማው ሲታመስ፣ ከገጠር የመጣ የኢህአዴግ ካድሬ ጠረጴዛው ላይ ተደፍቶ እንቅልፉን ይለጥጣል። በመካከል በጭብጨባ ድምጽ ብንን ይልና እጁን ዘርግቶ ሲንጠራራ፤ አፈ ጉባኤ ዳዊት ዮሀንስ ሰውየው አስተያየት ለመስጠት እጅ ያወጣ መስሎት

"እሺ እዚያ ጋ፣ አምስት ደቂቃ ሰጥቸሃለሁ" ይሉዋል።

ነገሩ ድንገት የሆነበት ካድሬ የሚለው ጠፍቶት ተደነባበረ። ግን ወድያው ከፊት ለፊቱ ሻለቃ አድማሴን ተቀምጠው ሲያያቸው መላ መጣለት። ወድያው ማይኩን አፉ ላይ ደቅኖ





"እህህ... እኔ እንኳ ማለት የፈለግሁት... እህህህ እኔ መናገር የፈለግሁት ... እሁን ሻለቃ አድማሴ የተናገሩት ጸረ-ዲሞክራሲያዊ ስለሆነ ልናወግዘው ይገባል ለማለት ነው" ሲል፣

ሻለቃ አድማሴ ከወንበራቸው ብድግ ብለው እጃቸውን መስቀልኛ ዘርግተው

"የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍረደኝ አሁን ምን ተናገርሁ፣" ብለው ቀወጡት።

አዳራሹ በሳቅ ተናጋ። ሻለቃ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍረደኝ" ሲሉ ይህ የፓርላማ ድራማ በቴቪ ይተላለፋል እንጂ ተቆርጦ ይቀራል የሚል ሥጋት አልነበራቸውም።

ተመስገን ይህን ሰምቶ በሳቅ ሲተባበረኝ ቆየ።

********

ምንም እንኳ ተመስገንን በልበ ሙሉነቱ በታታሪነቱ እና ለጭቁኖች ባለው ልባዊ መቆርቆር ባደንቀውም ስለ አብዮት የሚጽፋቸውን መጣጥፎች አሜን ብየ ተቀብያቸው እንደማላቅ መደበቅ አልሻም። ቆራጡ ወዳጄ ስለአብዮት የነበረውን የተጋነነ እምነት ባሰላሁት ቁጥር ከእውነታው ይርቅብኛል። ለሱ የሚታየው አብዮት መንፈስ በህዝቡ ማኸል አልነበረም። እንደኔ እንደኔ የሕዝብ ቅሬታና ምሬት አለመጠን መጠራቀሙ ብቻ የአብዮት ምጽአት ምልክት ሊሆን አይችልም። ያገሬ ሰው በማያባራ ጭቆና ሥር ለብዙ ዘመናት ስለኖረ የጭቆናን ምሬት የሚያጣፍጥበት የግፍን ቀንበር የሚያቀልበት የስነልቦና ዘይቤ ፈልስፏል። በዚህ ምክንያት ቅሬታና ምሬት የለውጥ ሞተር ሲሆን አይታይም።

እያሌ ያገሬ ሰዎች፣ ለብሔራቸውና ለሃይማኖታቸው ሞትና መከራን ለመጋፈጥ ቁርጠኝነት ሞልቶ የተረፋቸውን ያህል፣ ለዴሞክራሲ የሚደረግ ትግል ደንታ አይሰጣቸውም። ሀገር አቀፍ አብዮት እንዲኖር ሀገር አቀፍ የጋራ መንፈስ ሊኖር ይገባል። ተሜ እኒያን በአብዮት ብሥራት የሰከሩ መጣጥፎችን





በሚያኽጎደጉድበት ወቅት የትብብር መንፈስ ከሙቸውም በላይ የተዳከመበት፤ ሁሉም ሠፈሩን ነጻ ለማውጣት የሚታገልበት ጊዜ ነበር። እና በተሜ ደጅ ውልብ ብሎ የጠፋው አብዮት መች ይመለሳል? ማንም አያውቅም። ኢትዮጵያ ውስጥ እንደብዙዎች ክስተቶች አብዮትም ለነቢያት ትንቢት የሚመች አይደለም። ምናልባት በይርጋ ዱባለ ዘፈን ውስጥ እንደተሣለው ጀግና "ከኋላ ነው ሲሉት ከፊት የሚደርስ" ይሆናል። ተሜ እንደገመተው ሆኖ አብዮት ደጃችን ላይ ቆሞ እያንኳኳ ከሆነ እንኳን ሊበጀን ይሁን ሊፈጀን ማወቅ የሚቻል አይመስለኝም።

ዞሮ ዞሮ አንድ እውነት አለ።

በሥልጣን ያሉ ሰዎች መልካም አስተዳደርን፣ ዲሞክራሲንና የሕዝቦችን የትብብር መንፈስ በጨዋና በሰከነ መንፈስ የማደስ እድል እያላቸው የለውጥን ነቢያትን አስረው አይዘልቁትም። አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ ባንድ ወቅት፤ "ሙቼም ለውጥ የፍጥረት ሕግ ስለሆነ ዛሬ ባይሆን ነገ ለውጥ መምጣቱ አይቀርም። ጥያቄው፣ ለውጥ በሰላም? ወይስ ለውጥ በደም? ፣ ስለሆነና ለውጥ በሰላም ሊሆን ሲችል በደም እስኪሆን መጠበቅ ሁሉን ከመጉዳት በቀር ማንንም ስለማይጠቅም፤ ለውጥ በሰላም የሚሆንበትን መንገድ አሁን፤ ጊዜው ሳያልፍ ማበጀት አስፈላጊ ነው"[3] ያሉትን ጆሮ ያለው ይስማ!

ከተመስገን ጋር እያወጋን አሻግሬ ተመለከትሁ። ልጆቹ ፈንጥር ብሎ በሚገኘው ጠረጴዛ ዙርያ ቶማስ ከተባለው ሾፌሩ ጋር ሆነው እየተሳሳቁ ምሳቸውን ይበላሉ። ለልጅ ይታየዋል ቢባልም ነገ ሁለተኛውን አባታቸውን እንደሚነጠቁ የታያቸው አይመስልም።

በማግስቱ ሰኞ፣ በፍርዱ ቀን፣ የቀጠሮው ሰአት እስኪደርስ በረጃጅም ሳሮች ተውጦ ወራሽ የሌለው የሙት ቤት ወደሚመስለው የፍርድቤቱ መዝናኛ ከቡብ ጎራ አልን። ቅጣቱ ከዛ ይጀምር ይመስል ሻይም ሆነ ቡና እንደሌለ ተነገረን።

[3]ኢትዮጵያ ምን አይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል? (መቅድም)

ግቢውን የወረረው ዳዋ ከዝምታው ጋር ተባብሮ ስለተጫጫነኝ እፌ ያመጣልኝን ወረወርኩ።

"ፕሮፌሥር ጋ መች ትወስደኛለህ? የግርማቸው ተክለሐዋርያትን ያልታተመ ግለታሪክ እንደሚያውሱኝ ቃል ገብተውልኛል"

"ሮብ እንሄዳለን" አለኝ።

የቂል ጥያቄ ጠይቄ የዋህ ሰው መልስ አገኘሁ ልበል? ከጥቂት ዓመታት በፊት ያነበብኩት "መልካሙ ወታደር ሺቬክ" የተባለ በቼክ ደራሲ የተጻፈ የፌዝ ልቦለድ ትዝ አለኝ። በመጽሐፉ አንድ ምእራፍ ውስጥ ሁለት ወታደሮች ወደጦር ሜዳ ሲቃረቡ፣ "ከጦርነቱ በኋላ አዛች የምናውቃት ቤት እንገናኝና አንድ ሁለት እንላለን" ብለው ሲቀጣጠሩ አንብቤ እየተከዝኩ ስቂያለሁ። ተስፋ የሚባለው አስማት ግዙፍ ሥጋቶችን የሚደመስስበት ጉልበት አለው።

"ረቡእ እንሄዳለን" የሚለው የተሜ መልስ ገረመኝ። ወደ ወህኒ እንደሚወርድ ርግጠኛ የሆነው ሰውየ ልብ ውስጥ "ማን ያውቃል በነጻ ልሰናበትም እችላለሁ" የሚል የተስፋ ቁራጭ ጨርሶ እንዳልጠፋ ገባኝ።

ግና ምን ይገርማል። ነጻነት የሚባለው ነገር እጅግ ብርቅ እንደሆነ እስካወቅን ድረስ፣ በሰው ልጅ መሠረታዊ ጥሩነት እስከተማመን ድረስ፤ እንዲህ ዓይነቱ ተስፋ ጥሎን አይጠፋም። በዓሉ ግርማም ብሎታል፤ *ተስፋ ሌድርግ ተስፋ በሌለበት ቦታም ቢሆን። ኦሮማይ!*

ሐምሌ 2007





# ሦስቱ ኤልሻዳዮች

አለቃ ተክለኢየሱስ ዋቅጅራ "ከዚህ ቀደም ትልቁ ጠብ በዚህ ዓለም በርስት፣ በከብት፣ በሴት ነው" ይላሉ። በአለቃ የግጭት ምንጭ ንድፈ ሐሳብ 'Social Conflict Theory' መሠረት የሰው ልጆች ዋና ዋና የግጭት ምንጭ፤ ርስት ለማስፋት፤ ከብት ለመሰብሰብና ሴት ለመወሰብ የሚደረገው የሞት ሽረት ትግል ነው። ከብት የሚለው ቃል ቀስበቀስ ሀብት ለሚለው ቃል ምንጭ ሆኗል።[16] ሀብታም የሚለው ቃል "ከብታም" ከሚለው ወጥቷል። አካበተ የሚለው ቃልም ምንጩ ከብት የሚለው ስም መሰለኝ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን አስተምህሮ መሠረት አቤልና ቃየል የተጋደሉት በሴት ምክንያት ነው። ሲቃውንት ከጻፉት ልጥቀስ፤

"ሄዋን መንታ መንታ እያደረገች ወልዳለች። የወለደችውም እሥራምስት ጊዜ ነው ቢሉ ሠላሳ ይሆናሉ። ሠላሳ ጊዜ ነው ቢሉ ስድሳ ይሆናሉ። ቃየልና ሉድ አቤልና አቅሌማ መንትያዎች ናቸው። አካለ መጠን በደረሰ ጊዜ አዳም ሄዋንን

[16]Isenberg; Amharic grammar, (page 170)





ጠርቶ ኦ ሄዋን ልጆችሽ አደጉ እናጋባቸው አላት። እርስዋም ይሁን እሺ አለችው። አዳምም እህትና ወንድም አይጋቡ የምትል ሕግ እንድትሠራ በሕገ ልቡና ተገልጦለት ያራራቅሁ መስሎት የቃየልን መንትያ ለአቤል የአቤልን መንትያ ለቃየል ትሁን አለ። ... ሉድ መልከ ከደም ግባት እስተካከላ የያዘች ናት። አቅሌማ አይነ መጫማጫ ጸጉረ ላሁጫ ናት። አዳምም ይህን ሰምቶ መስዋእት ሠውና መሥዋእቱን የተቀበለለት ሉድን ያግባ አለ። አቤል እግዚአብሔር ንጹህ ባሕርይ ነው፤ ንጹህ ነገር ይወዳል ብሎ ጠጉሩ ያላረረውን የሰባውን ሰዋ። መስዋእቱን ሠዋ። መስዋእቱን ተቀበለለት። ቃየል ግን እግዚአብሔር ይበላው ይመስል ብሎ ያልተለቀመውን መስዋእቱን ሠዋ። ሳይቀበልለት ቀረ። እያዘነ ሲሄድ ሰይጣን ከመንገድ ቆይቶ ኦ አዛል ብእሲ ምንት ያስተክዘከ (ምን ያስተክዝሃል?) አለው። እኔ ያላዘንሁ ማን ይዘን አባቴ ቢያዳላ በእኔ እግዚአብሔር ቢያዳላ በእኔ አለው። ወንድምህን አትገድለውምን ሁለቱስ ለማን ይሆናሉ አለው። ለካ እንዲህ ያለም ነገር አለ ብሎ ከዚህ እብንት ተነሥቶ ገድሎታል።"[17]

እኔ በፈንታየ የአንድምታ ትርጓሜውን ስተረጉመው ይህን ይመስላል። አንድምታው የጥንታዊው የኅብረተሰብ ባሕርይ ነጸብራቅ ነው። እግዜሩ፣ ውድ ጥሎሽ ለሚያቀርብ ሰው ቆንጆ ልጁን የሚድር ሀብታም ሰው ይመስላል። ቃየል በቅናት ወይም በከሸፈ ፍቅር ምኞት ምክንያት ወንጀል የፈጸመ ወንዶች ምሳሌ ነው።

ከላይ ከላይ ስታየው ለሴት የሚደረገው ትግል ዝምብሎ በሽፍድት ምክንያት የሚመጣ ይመስላል። የነገሩን ምንጭ ስትምሰው ግን ለሴት የሚደረገው ፍልምያ ዝርያን ማስቀጠል ከሚደረገው ተፈጥሮአዊ ትግል ጋር የተቆራኘ ሆኖ ታገኘዋለህ። በጥንት ጊዜ ጉልበት ያለው ሁሉ ጉልበቱን ተጠቅሞ ቆንጆጅትን ያከማች ነበር። ባገራችን ባንድ ሚስት የተወሰነ ንጉሥ ወይም ጌታ ማግኘት ይከብዳል። ጥንታዊ ባለጉልበቶች ሚስቶቻቸውን የሚጠብቁላቸውን ወንዶችን ቆላ ይቆርጡ ነበር። ይህ ለምን ሆነ ብለህ አትገረም። በሌላው ኪሳራ የራሳችንን ዝርያ የማስቀጠል ፍላጎት በተፈጥሮ የተጫነብን ዝንባሌ ነው።

[17]መጽሀፈ ብሉያት ፤አንድምታ ትርጓሜ፤ (ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት)





ጥንታዊ ጌቶች ይህንን ዝንባሌ ለራሳቸው እንዲመቻቸው አድርገው ደንብ አበጅተውለታል። ደግነቱ ፤ሥልጣኔ እንዲህ ዓይነቱን የተፈጥሮ ዝንባሌ እየገራ ልክ ያስገባዋል።

ለርስት፣ ለከብትና ለሴት የሚደረገው ፍልምያ በሦስት ወሳኝ መሣርያዎች አማካኝነት ተካሂዷል። እኒህን ሦስት መሣርያዎች ሦስቱ ኤልሻዳዮች እላቸዋለሁ። ኤልሻዳይ ማለት ሁሉን ቻይ ማለት ሲሆን ለእግዜር የሚነገር ቅጽል እንደሆነ ይታወቃል። በታሪካችን ውስጥ አምላክ- አከል ዐቅም የነበራቸው ሦስት ኀይሎች ነበሩ። እነሱም፤ ግዝት ጠመንጃና ገንዘብ ናቸው።

## ግዝት

ብዙዎቻችን እንደምናውቀው ኢትዮጵያ የክርስትና ሀገር ነበረች። እስልምናና ሌሎች አገር በቀል እምነቶች እንደነበሩ ዘንግቼ አይደለም። የማእከላዊ መንግሥትን ሥልጣን ይዘውሩ የነበሩት ኀይለኞች ባብዛኛው ክርስትያኖች እንደነበሩ ማስታወሴ ነው። መንፈሳዊ ባለስልጣኖች ከዓለማዊ ባለስልጣኖች የሚበልጥ እንጂ የማያንስ ጉልበት ነበራቸው። የጉልበታቸው ምንጭ ግዝት ይባላል። አንድ ፍሬ ሽንብራ የሚያክል ቄስ ባንዲት ቃል "እሠርሁ ፈታሁ" እያለ ሀገር ሊያምስ ይችላል። መኖር ማለት አሜን አሜን ማለት በሆነበት በዚያ ዘመን ከሞት በላይ ግዝት ያስፈራ ነበር። ምክንያቱም ግዝት ማለት በምድርም በሰማይም መታሠር ማለት ነው።

ርግጥ ነው፤ መልካም መንፈሳዊ መሪዎች ይህንን ስልጣናቸውን ለመልካም ነገር ተጠቅመውበታል። አምባገንኖችን ለመገሰጽ ተገልግለውበታል። ግፈኞችን ገስጸውበታል። ፈራ ተባ የሚሉትን አበረታተውበታል። እንደ አቡነ ማቴዎስ ያሉ የሚሠሩትን የሚያውቁ ሊቃነ ጳጳሳት የኢትዮጵያ ወታደሮች፤ ከጦር ሜዳ እንዳይሸሹ በግዝት ገድበዋቸዋል።

ሎርድ አክተን የተባለ አሜሪካዊ ጸሀፊ፣ "ገደብ የለሽ ሥልጣን ያለገደብ ያባልጋል" ይላል። አባባሉ በዘመን የተፈተነ ሀቅ ነው። በጥንት ኢትዮጵያ የመገዘትን ሥልጣን ይዘው ያለገደብ ከባለጉ የሃይማኖት ባለስልጣኖች መካከል እንደ ምሳሌ የሚጠቀሰው አቃቤ ሰአት አባ ሰላማ ይባላል። ዝነኛው መንገደኛ ያቆበ ብሩስ ስለዚህ ሰውየ ሲነግረን "(ሰላማ) በቤተክርስትያን በሦስተኛ እርከን ሥልጣን አለው። በጣም ሁብታምና በጣም እኩይ ሰው ነው። በጎንደር ውስጥ ከሰባ በላይ ቅምጦች እንዳሉት ይነገራል። ሴት የሚያማልልበት መንገድ የተማላዮችን ብዛት ያክል ያስደንቃል። አንዲትን ሴት በሬለገ ቁጥር በግዝት ያስፈራራታል" ይላል።

የግዝት ኀይል በዘመን ብዛት ቀንሷል። የእምነት መሠረቶች እየተረቱ፣ የጉልበት መሠረቶች እየበረቱ ሲሄዱ ኀያላን መንፈሳዊ አባቶችን በጠመንጃ አስፈራርተው ተቀናቃኞቻቸውን እንዲገዝቱ እስከማስገደድ ደርሰዋል።

## ጠመንጃ

ከእለታት አንድ ቀን የነገሮች ሁሉ መስፈርያ ጠመንጃ ነበር። ጠመንጃ ያለው ማምረት አይጠበቅበትም። ሌላው ያመረተውን ይዘርፋል። ሌላው ያካበተውን ይወስዳል። ሌላው ያደለበውን ይነዳል። ከሴቶች ሁሉ ቆንጆይቱን መርጦ ከስመረለት በውድ፣ ከጠመመበት በግድ ያገባል። የሰው ሚስትም ይነጥቃል።

የጠመንጃ መንፈስ ብርቱ ከመሆኑ የተነሣ የማማለል ስነልቦናን ሳይቀር መቆጣጠር ችሎ ነበር። የዚያ ዘመን ሴቶች ባለጠመንጃ የሚያማልላቸው፣ ገዳይ የሚያሻፍዳቸው ሆነው በዘመን መንፈስ ተቃኝተዋል።

"አልቢን የያዘ ሰው፣ ይሁነኝ ውሽማ
መውዜር አይገዛም ወይ፤ ባሌ እንዲሆንማ"





ብሉው የሚዘፍኑ ሆነዋል። እነ መውዜር ዛሬ እንዲህ ቀን ጥሏቸው ሙዚየም ውስጥ ሳይወረወሩ፣ የክብር፣ የሀብት የደህናንትና የፍቅር ምንጭ ነበሩ።

እነ መውዜር ከገንዘብ በላይ በገነኑበት ዘመን ሀብት ዋስትና አልነበረውም። አሊቃ አጥሜ እንዲህ ባለው ዘመን፣ የንብረትን መቅኖቢስነት ሲገልጹ፣ "ያገኘ ምን አገኘ ያጣስ ምን አጣ" ብለዋል። ሀብታሙ ሰው ባንድ ጀንበር ሀብቱን አጥቶ ስለሚያድር ሀብት አይኮራም ነበር። እንዲሁም መናጢው ድሃ ባንድ ጀንበር ከበርቴ ሆኖ ሊያድር የሚችልበት እድል ነበረው።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመናዊ ወታደር እስኪያቋቁሙ ድረስ የኢትዮጵያ ወታደር የኢትዮጵያን ባላገር እየዘረፈ ይበላ ነበር። ጠመንጃ ሁሉን አድራጊ፣ ኤልሻዳይ በነበረበት ዘመን ውትድርና የሙያዎች ሁሉ ቁንጮ ሆኖ ተቆጥሯል። ለምን? አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ጥያቄያችንን ሲመልስ፣ "አበሻ ለመኖር አንድ የሚሻለው ነገር ወታደር መሆን ብቻ ነው። እሄው መሆኑ እውነት ደስ ያለ ትዳር (ኑሮ) ለማግኘት አይደለም። ነገር ግን ሲዘረፉና ሲገፈፉ ከመኖር ሌላውን ሲዘርፉና ሲገፉ መኖር ይሻላል ለማለት ነው[18] ብሎ ጽፏል።

ባላገሩም እድሉን ሲያገኝ ጦርነት በፈጠረለት ቀዳዳ ገብቶ ከዘርፍያው ሲሳይ ይሳተፋል። ተክለኢየሱስ ዋቅጅራ፣ መይሳው ካሳ የራስ አሊን ጦር አሸንፎ በደጋ ዳሞት በኩል ሲመለስ ያጋጠመውን ሲተርኩልን፤

"የደጋ ዳሞት ገበሬ እርሻውንና ቆፋሮውን ትቶ በማቅና በሚስቱ ወስፌ በአምጃ በትር ሰክቶ ፈረስና በቅሎ እየፈለመ ሲማርክ ከቆሰለ ሠራዊት ገንዘብ ሲቀማ እየፋነነ ወጣ። የጎሹን ደመኛ ያሊን ወደረኛ ትሰደዋለህ ብሎ ብዙ ሰው ገደለ። የዚህን ጊዜ ደጃች ካሳ ሰገድ ከሚባል ሀገር ሰፈር አድርጎ ወገን ሰቀቀበት። በፈረስና በበቅሎ ርስበርሱ ሲጣላ ዙርያውን ኩበቦ በነፍጥና በነፍጠኛ አስገደለው። ከዚህ ወዲህ ባልዋ ሄዶ የሞተባት ስታለቅስ፤

[18]Ghevre Jesus Afevork; Guide du voyageur en Abyssinie: (Page 285)





'እመጣለሁ ብሎ፣ የካሳን ፈረስ
ሳያርመው ሞተ ፥የዘራውን ጉብስ' አለች ይላሉ።"

ከላይ እንዳየነው ገበሬው እርሻውንና ቁፋሮውን ጥሎ፣ ከወስፌና ከአምጃ እንጨት የተሠራ ጦሩን አንግቦ የወጣው ለነጻነት ትግል ሳይሆን በቅሎና ፈረስ እየፈለመ ሊማርክ ነው። መፈለም የምትለዋ ቃል ዘመን ከጥቅም ውጭ ካደረጋቸው ቃላት አንዷ ናት። አንድ የጠላት ፈረስ ጦር ሜዳ ላይ ቆሞ ሲገኝ ብዙ ማራኪዎች ይሻሙታል። ቀድሞ ሮጦ የነካው "ፈለመው" ይባልና ምርኮው ይጸድቅለታል። ውሃ ለቀደመ ግዳይ ለፈለመ ይባል ነበር። የምርኮ ሽምያ ብርቱወና ፈጣኑ ብዙ የሚሰበስብበት፣ ደከም ያለው ባዶ እጁን የሚቀርበት ስለሆን በተሻሚዎች መካከል አምባጓሮ መከሰቱ አልቀረም። እየፋነነ ሲል ፋኖነቱን ለመግለጽ ነው። ሳይታዘዝ በፃኞቱ እየተገፋ የሚዘምት ባላገር ፋኖ ተብሎ ይጠራ ነበር።

በጊዜው ዝርፍያ ነውር ሳይሆን ሁሉም ዜጋ ፈረቃ ጠብቆ የሚሳተፍበት ደንብ ነበር ማለት ይቻላል።

መሣርያ የክብርና የሀብት ምንጭ በሆነበት ዘመን ላይ፣ ወታደር የተከበረ ሰው ሲሆን፣ ሰራራ ነጋዴ እና የኢደጥበብ ሠራተኛ የተናቁ ቢሆኑ አይገርምም።

## ዘመነ ገንዘብ

ቀስበቀስ የጦር መሳርያ በግለሰቦች እጅ እየወጣ በመንግሥት እጅ መጠራቀም ጀመረ። ጦርነት እየቀነሰ ሰላም እየነገሠ መጣ። ከጦር ሠፈሮች ይልቅ ባንኮች መበራከት ጀመሩ። ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፍልስፍና ተወለደ። ብር በቁምነገር ተወሰደ። ግብር ማብላት ቀርቶ ሆቴል መከፈት ተለመደ። እንጀራ የሚሰጥ መሆኑ ቀርቶ የሚሸጥ ሆነ። እነ እቴጌ ጣይቱ የግብር ድንኳቸውን አፍርሰው





ሆቴል ከፈቱ። ከለውጡ ጋር መራመድ ያቃተው ሁላ እሮጌ በገናውን ድር ከለበሰ ግድግዳው ላይ አውርዶ

"እቴጌ ጣይቱ እጅግ ተዋረደች፣
ሁቴሏን አቁማ እንጀራ ነገደች" እያለ አዘነ።

እየሰነበተ ቁርጡን ሲያውቅ ግን "እያለህ ካልሆነ ከሌለህ የለህም" ብሎ ዘፈነ። ገንዘብ ያለው ሰው ጠመንጃ ሳይሆን ባለጠመንጃ መግዛት ቻለ። "ወይ ጉዴ ላግባሽ አለኝ ነጋዴ" የሚለው ቀርቶ "መልበስ አረንጓዴ ማግባት ነው ነጋዴ" ተብሎ ተቀነቀነ። በዘመነ መውዜር የሰርግ ዘፈን በግዳይ ላይ ያጠነጠነ ነበር። በዘመነ ብር "ኧረ ሚዜው ደኻ ነው ሽቶው ውሃ ነው" ተብሎ ተዜመ። ወላጅ ልጁን በኢኮኖሚ ዙርያ የሚያጠነጥን ስም ሰየመ። እነ ሽፈራው ቀርተው እነ ብሩ እነ ሚሊዮን መጡ። ካርል ማርክስ የተባለው ሊቅ ገንዘብ በቡርዥዋ ሥርአተ ማኅበር ውስጥ ያለውን አስማት ባብራራበት ሐተታው፣ "(በቡርዣ ሥርዓት ውስጥ) ገንዘብ የመልካም ነገሮች ሁሉ ቁንጮ ነው። ስለዚህ ባለ ገንዘቡ መልካም ሆኖ ይታያል" ብሎ ጽፏል።

ማርክስን ከነመፈጠሩ የማያውቁት አባቶቻችንም "ያለው ማማሩ ከነነውሩ" በማለት የገንዘብን ተአምር አሳምረው ገልጠውታል። ሁብታም ሰው ወራዳ ሕይወት ቢኖርም የገንዘብ አቅም ባይናችን ፊት ክቡር ሆኖ እንዲቆም ያደርገዋል። እናም "የገንዘብ ደግነቱ ታስሮ ማስፈታቱ" ተብሏል። ገንዘብ ነውረኛውን ክቡር፣ እስረኛውን ነጻ የማድረግ ሀቅም እንዳለው ተደርሶበታል።

ዛሬ ገንዘብ ሰዎችን የማያደርጋቸው ነገር የለም። ሰዎችም ለገንዘብ ሲሉ የማይሆኑት ነገር የለም። የይሉኝታን የስነምግባርን አጥር የገንዘብን ፈተና የመገደብ አቅም የላቸውም። ጥንት ወተትና ቅቤ በስጦታና በችሮታ እንጂ በሽያጭ የሚቀርቡ ነገሮች አልነበሩም። ዛሬ ሰዎች ለገንዘብ ሲሉ የገማ መግዝ ቅቤ ነው ብለው ይሸጣሉ። መንገደኛ ተቀብሎ በብላሽ ማሳደር የተለመደ ነበር። ዛሬ ሰዎች መንገደኛውን ተቀብለው ገድለው ኩላሊቱን የሚሸጡበት ዘመን ላይ ደርሰናል። የተፈጥሮ ውበታቸውን ሸጠው ሰው ሠራሽ መዋብያ ይገዛሉ፤ ድንግልናቸውን ይሸጣሉ፤ ወላቆች ጥርስ ይገዛሉ፤ ተካዞች ሳቅ

ይከራያሉ፤ መላጦች ጸጉር ይሸምታሉ፤ ጃንደረቦች ሙርጥ ይገዛሉ። ገንዘብ ይኑር እንጂ አሮጊቶች ጨምዳዳ ቆዳቸውን አስገፍፈው የኮረዳ ልስልስ ገላ ይለብሳሉ። ሰዎች እንቅልፋቸውን ጨቁነው ባፈሩት ገንዘብ የእንቅልፍ ክኒን ይሸምታሉ። ከየትኛውም ስኬት ጀርባ ከየትኛውም ውድቀት ጀርባ ከየትኛውም ቀውስ ጀርባ ከየትኛው ሰላም ጀርባ ኤልሻዳይ ገንዘብ ቆሟል።

ያም ሆኖ፤ አቤቱ የእለት መቆ ብራችንን አትንፈገን!





# ስምና ማንነት

ከብዙ መነፋፈቅ በኋላ ካባቴ ታናሽ ወንድም፤ ካቶ አማረ በዳዳ ጋር ተገናኝተን አራት ኪሎ በሚገኘው ሮሚና ምግብ ቤት ምሳ በላን።

አማረ ቢፈችሁ ቀላል ሰው እንዳይመስላችሁ፤ ከስድሳ ስድስት አብዮት ትንሽ ቀደም ብሎ በዩንቨርሲቲ ኮሌጅ በታሪክ ትምርት ዘርፍ በዲግሪ ተመርቋል። በአብዮት ማግስት በኢሀአፓ አባልነት ተመልምሎ፤ በዚሁ ጦስ ተይዞ ዓለም በቃኝ አምስት ዓመት ታስሯል። እነ ማርታ ኩምሳ፣ ጌታቸው ኩምሳና ገነት ዘውዴ አብሮ ታሳሪዎቹ ነበሩ። ደራሲ ግርማይ አብርሃ በእሥር ቤት ማስታወሻው ላይ እንደጠቀሰው አማረ በእሥር ቤት ቆይታው እሥረኞችን በነጻ የማስተማር አገልግሎት ከሚሰጡ ታራሚዎች አንዱ ነበር።[19]

[19] ግርማይ አብርሃ፤ የሚያነቡ እግሮች፤ ገጽ 195





እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምርያ ያዲሳባ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሠራ ቆይቷል። አዲሳባ ዩንቨርሲቲ በምማርበት ወቅት የሻይ መጠጫ የሚቆርጥልኝ አማረ ነበር።

አባቴና አማረ ያንድ አባት ያንድ እናት ቢሆኑም በመልክና በእጣ ፈንታ የተለያዩ ነበሩ። አባቴ የቀይ ዳማ ሲሆን አማረ ከስል ያለ ጥቁር ነው። ወንድማማቾቹ የሚጋሩት አንድ ምልክት ቢኖር፣ ከጥቁር ጸጉራቸው ማኽል እንደባትሪ ቦግ ብሎ የሚታየው ሽበታቸው ነበር። ከአማረ በተቃራኒ አባቴ ለፖለቲካ ያለው ስሜት በጣም የቀዘቀዘ ነው። አማረ የቢሮ ሰው ሲሆን፣ አባቴ የተፈጥሮ ሰው ነው። ከትምርት ቤት ውጭ ያለውን ጊዜውን ያሳለፈው ከልጆቹ የማያንስ ፍቅርና ጊዜ ለሚሰጣቸው የጓሮ አትክልቱ ነበር ማለት ይቻላል።

በድህረ ምሳ ጨዋታ ላይ የዘመዳ-ዝማድ ጉዳይ ስናነሳ ስንጥል ቆይተን ልንሰነባበት ስንል፣

"እስቲ ያባቴን የትውልድ ሐረግ ጻፍና ስጠኝ" አልኩት።

"ምን አሳሰበህ" አለኝ በዋዛ።

"እንዴት አያሳስበኝ፤ አባታዊነትን የሚያጋንን ማኅበረሰብ አባል ነኝ። አንድ ሰው ፍቅሩን ለመግለጽ "እንዲያው ምናባቴ ላርግህ" በሚልበት፤ ጠላቱ ከፉ እንደገጠመው ሲሰማ፣ "የታባቱ" ብሎ፣ በሚፈነጥዝበት ግራ ሲገባው፣ "ምናባቱ" እያለ በሚያጉተመትምበት ሀገር ውስጥ የምኖር ነኝ። አባት የነገሮች ሁሉ መስፈርያ ሆኖ በሚቀርብበት ማኅበረሰብ ውስጥ ስለአባቴ ማንነት ለማወቅ ብጥር ምን ይገርማል?"

በግርምት ለጥቂት ጊዜ አተኩሮ ሲያየኝ ከቆየ በኋላ ወደ መኪናው ውስጥ ይዞኝ ገባ። ከዚያ ከመኪና እረኛዋ (ከፓርኪንግ ሠራተኛዋ) እስክሪብቶ ተውሶ፣ በቢጫ ማስታወሻ ደብተሩ ውስጥ አንድ ቅጠል ገንጥሎ የሚከተለውን ጻፈልኝ፤

በዕውቀቱ ሥዩም-በዳዳ-ደስታ-ወየሳ





"ይሄው ነው?"

"እኔ የማውቀው እስከዚህ ድረስ ያለውን ነው፤ ሌላውን ደሞ የሁላችን ታላቅ የሆነችውን አበራሽን ጠይቃት"

ትንሽ አሰብ አድርጌ፤

"አባታችን አባቱ በዳዳ ተብሎ እንደሚጠራ ነፍስ ስናውቅ ጀምሮ ይነግረን ነበር። ግን በመሰለ ለምን እንደሚጠራ ጠይቀነው አናውቅም። ለምንድነው አባታችን በመሰለ የሚጠራው?"

አማረ ማብራራት ጀመረ። ማብራሪያውን ላንባቢዎቼ እንዲያመች አድርጌ ሳሳጥረው ይህንን ይመስላል።

አቶ በዳዳ የተባለ ገበሬ ነበረ። የወላጆቹ መነሻ ድሮ ጂባትና ሜጫ ይባል በነበረው አሁን አምቦ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ቢሆንም እርሱ ጋርዱላ ወደተባለ ሀገር ወርዶ ኖሯል። ወይዘሮ ሙሉነሽን አግብቶ ሥዩምን ጨምሮ ወንድና ሴት ልጆችን ይወልዳል። ሥዩም በዳዳ አምስት ዓመት አካባቢ ሲሆነው፣ አባቱን በሞት ይነጠቃል። እናቱ ወይዘሮ ሙሉነሽ ልጆቿን ለማስተዳደር ትቸገራለች። በዚህ ጊዜ ወይዘሮ ሙሉነሽ ከመጀመርያ ባሏ የምትወልደው መሰለ የተባለ ልጇ በፈጥኖ ደራሽነት ከተፍ ይልና፤ አባቴን እና በለጠ የተባለውን ወንድሙን ይወስዳል። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ አቶ መሰለ ባደራ የተረከበውን ብላቴና ሥዩም መሰለ በሚል ስም ትምርት ቤት ያስመዘግበዋል። በዚህ ዓይነት አባቴ መጀመርያ አባቱን፣ ቀጥሎ ያባቱን ስም ያጣል።

"ሙቸም አባቴ በልጅነቱን ስሙን የመምረጥ መብት አልነበረውም። መሰለ ይሄን ያደረገው በዘመኑ ፖለቲካ ጫና ነው ወይስ በሕያውነት ፍላጎት ተገፍቶ ነው?" ስል ጠየቅሁት፤ አማረን።

አማረ ፈገግ ከማለት ውጭ ለጥያቄየ ቀጥተኛ መልስ አልሰጠኝም። ትንሽ ቆየና እንደቀልድ እያረገ መለሰልኝ፤

"እስቲ አባትህን ጠይቀው፣ አለበለዚያ ደግሞ እስቲ አለታ ወንዶ ብቅ ብለህ ራሱን መስለን ጠይቀው። በጣም እያረጀ ነው። ዘጠና ዓመት ሳይሞላው ይቀራል ብለህ ነው? አማረ መንገዱንም ለድርሰትህ የሚጠቅም ብዙ ታሪክ ሊያጫውትህ ይችላል።"

እስከምፈልገው ቦታ አድርሶኝ ከመኪናው ልወርድ ስል አማረ ማስጠንቀቂያ ቃና በተላበሰ ድምጽ የሚከተለውን ጨመረልኝ።

"ስለ ዘርና ሃይማኖት በመጻፍና በመከራከር ጉልበትህንና ጊዜህን እንደማትጨርስ ተስፋ አደርጋለሁ። ሰዎች በውይይት የሚግባቡበት ዘመን እስኪመጣ አርፈህ ግጥምህን ብትጽፍ ይሻላል። ከቻልክ ዓለማቀፍ ጸሃፊ ለመሆን ሞክር"

ምክር የማልሰማ ልጅ መሆኔ እንሆ በዚህ ጽሑፍ ተረጋገጠ።

ካንቴ ጋር በዚህ መንገድ ከተሰነባበትን ከጥቂት ሳምንት በኋላ ያባቴን አሳዳጊ አቶ መስለን ለመጎብኘት ወደ አለታ ወንዶ ተሳፈርሁ። መስለን ሳገኘው በጣም አርጅቷል። ይሁን እንጂ ጨዋታ ሲጀምር ነገሮችን ትናንት የተደረጉ ያክል ጥርት አድርጎ ያስታውሳል። ከመስለ ጋር ስለ አካባቢው ወንዞና ሸለቆ ስሞች እንዲሁም ሁለታችንንም ስለማይመለከቱን ብዙ ነገሮች ስናወጋ አድረን ልንሰነባበት ሲሸኘኝ ካዲስ አበባ ይገፎው የመጣሁትን ጥያቄ ለመጠየቅ እንዳለብኝ ገባኝ። ግን በድንገት እንደመርዶ ነጋሪ ልቤ በፍጥነት ይመታ ጀመር።

"አንድ ነገር ልጠይቅህ ነበር" አልሁት፤ ድምጼን ምን እንዳጎረነነው አላውቅም።

"እሺ"

"እህ ያባቴ ..." አፌ ጣውላ ሆነብኝ። ለምንድነው አባቴ በስምህ እንዲጠራ ያደረግከው የሚለው ጥያቄ ተገቢነት አጠራጠረኝ። ለካ ወቀሳ እንጂ ጥያቄ





አልነበረም ይገፎ የመጣሁት። ለመሆኑ ምን ብሎ እንዲመልስልኝ ነው የምፈልገው? የመጣሁት ማንነትን ፍለጋ ነው ነገር ፍለጋ?

"ያባትህ ምን?" አለኝ።

"ያባቴ ማስታወሻ፣ የሆነ ነገር ካለህ እንድትሰጠኝ ፈልጌ ነበር" አልሁ አፌ እንዳመጣልኝ ።

መስለ ወደ ጓዳ ገባና ትንሽ ቆይቶ አቧራ የለበሰ ካኪ ፖስታ ይዞ ተመለሰ። አባቴ የተማረባቸውን ሁለት የትምርት ውጤት መግለጫ ካርዶችና አንድ የወጣትነቱን ፎቶግራፍ ሰጠኝ። ያንን ቦርሳዩ ውስጥ ወርውሬ ወደ አዲስአበባ ተመለስሁ።

የዚያን ሰሞን የፋሲካን በዓል ከቤተሰብ ጋር ለማክበር ወደ ትውልድ መንደሬ ማንኩሳ ወረድሁ። እጋጣሚውን ተጠቅሜ፣ ከሥዩም መሰለንት ወደ ሥዩም በዳዳንት ያልተመለሰበትን ምክንያት እንዲነግረኝ አባቴን ጠየኩት።

"መስለ በጊዜው በሱ ስም እንድጠራ ፈልጓል። እኔ ደሞ የውሲታው ባለዕዳ ነኝ። ስሙን ፍቁ ላስቀይመው አልፈለግሁም። የሱን ስም መፋቅ ውሲታውን መግፋት ይሆናል" ሲል፣ መለሰ።

አስከተልሁና፣ ሥዩም መሰለ የሚለውን ስም ይዞ አባይ መሻገሩ ለተቀባይነቱ ጠቅሞት እንደሆነ ጠየኩት። ይህን ጊዜ፣ ጭውውታችንን ስትሰማ የቆየችው የእናታችን እህት ወይዘሮ ዓለምላንች ከበደ በጣም ተቆጣች።

"ምን ማለትህ ነው እያና፣ (የእናቴ ዘመዶች የሚጠሩኝ "እያና" ብለው ነው)፤ ወረሞ በጎጃም ንጉሥ ነው፤ መኳንንት ነው፤ የተከበረ ነው። ደሞ ገና ሞሳ ሞሳ (ትንንሽ) ልጆች እያለን ሳለን በየሰርጉ ምን እያልን እንደምንዘፍን ብታውቅ እንዲህ አትልም ነበር"

"ምን እያላችሁ ትዘፍኑ ነበር?"





"ብቻ ዐማራ ኣይደለም ጋ* ቅልቅል
አንጠልጥሎት ሄደ ልቤን እንደ ቅል

ብለን እንዘፍን ነበር። እሷም (ወደ እናቴ እየጠቆመች) ይሄን ዘፍና ነው የወሰደችው።"


አሁን ሳስበው፣ ኦሮሞ በጎጃም "መኳንንት" የመሆኑ ጉዳይ በሰነዶች የተረጋገጠ ታሪክ ነው። ጎጃም የሚገኙ ብዙ ሥፍራዎች መካካከል ባሶ ሊበን፣ ጃጋ፣ ጃዊ፣ ቡሬ፣ ሶማ፣ ዲማ፣ ኢልማና ዴንሳ፣ ሜጫ የተባሉት በኦሮሞ አቅኝዎች የተሰየሙ ሥፍራዎች ናቸው። ከተወለድሁት ቤት ግርጌ የሚንቆረቆረው ቀይ አቧራዩን ከእግሬ ላይ ያስለቀቅሁበትን ደቦሆላ የተባለው ወንዝ የዐማርኛም ሆነ የግእዝ ትርጉም እንዳለው ለማረጋገጥ ሞክሬ አልተሳካልኝም። ለካ ደቦላ በኦሮምኛ daboolaa "የተከደነ" ማለት ኑሯል።

የመጀመርያው የጎጃም ጌቶች አባት ኢቢዶ የሚባል የበረና ኦሮሞ መሆኑ በታሪክ ሰነዶች ተጠቅሷል። ይህ ሰው ከወሎ ከብት እየነዳ ወደ ጎጃም ከገባ በኋላ፣ ለጎጃም ሥርወ መንግሥት መሠረት ጣለ። ከታወቁት የጎጃም መሣፍንት መካከል የዘመነ መሣፍንቱ ደጃዝማች ጎሹ በዘር ኦሮሞ ቢሆንም የኦሮሞንና የዐማራን ባህል እኩል በማክበር ይታወቅ ነበር።[20] ኦሮምኛን፣ ዐማርኛንና ግእዝን አዛንቆ የጻፈው ደብዳቤ ደርሶናል ።

[20]'Goshu Zaudie, Dejazimach (or Duke) of Gojjam, a prince whose friendship and protection i enjoyed during my stay in the country .By descent he is a Galla of Amaru.' (Charles Beke.)







ልጆቹንም ኤሊምቱ፣ ዶሪ፣ ተሰማ እያለ ሰይሟል። ቀስበቀስ ወራሾቹ በገባሪው ሀገር ባህል ተውጠዋል። የጎሹ የልጅ ልጅ አዳል ተሰማ (በኋላ ንጉሥ ተክለሃይማኖት) ከዐማርኛ በቀር የሚናገረው ቋንቋ አልነበረም። እና ባንድ ወቅት ወደ ወለጋ ለመሻገር ሲዩቅድ ጸሐፌ ትእዛዙን ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራን፣ "ኦሮምኛ እንዳይጠፋህ ዘመዶችህን ታሳምንልኛለህ" ብሎ እስከመማጸን ደርሷል። ውዳሴ ማርያም በሊቁ በአሲታ ተገኝ አማካኝነት ከግእዝ ወደ ኦሮምኛ የተተረጎመው በንጉሥ ተክለሃይማኖት ድጋፍ ነው።

አንድ ሰው በእንግድነት ወደ አንድ ከልል ገብቶ መኖር ብቻ ሳይሆን መግዛትና መንዳት የሚችልባት ሀገር ነበረች ኢትዮጵያ።

አንዳንድ ሰዎች ሕያው ለመሆን ካላቸው ፍላጎት የተነሣ ያሳደጉት ልጅ በስማቸው እንዲጠራ ያደርጋሉ። ልጅ ላደገበት የሚከፍለው ዋጋ የአሳዳጊውን ስም መሸከም ነው። ሙሉቀን ታምሩ፣ ድምጻዊ ሙሉቀን መለሰ የሆነው በዚህ መንገድ ነው። እንዲሁም ዝነኛው የግራ ፖለቲከኛ ብርሃን መስቀል ረዳ ባሳዳጊው (በእናቱ አባት ስም) ተሰይሟል።

ሌሎች ደግሞ በገዛ ፈቃዳቸው፣ መወሊድ ቋንቋ ነው ብለው አሳዳጊያቸውን ባባታቸው ቦታ ይሾማሉ። ኪዳነወልድ ክፍሌ የተባለው የቋንቋ ሊቅ አባቱን ትቶ ክፍለጊዮጊስ በተባለው መምህሩ ስም መጠራት መርጧል።

አቶ መሰለ፤ ሥዩም በዳዳን ሥዩም መሰለ ብሎ እንደሰየመው ሁሉ የወንድሙን የበሰጠ በዳዳን ስም ደግሞ በሰጠ ተሰማ ብሎ አስቀይሮታል።

ይህ እንግዲህ ከዘመኑ መንፈስ የመነጨ ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት አይከፋም። ብዙ ያባቴ የዘመን ጓዶች ስማቸውን በዚህ መንገድ እንዲቀይሩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጫና ነበረባቸው። ፈቂዶ አዚዝ የተባለ ተማሪ ፈቃደ አዘዘ እንደ ተባለ አውቃለሁ። ላጺሶ ደልቦም ከዛሬ ጀምሮ ጌታሁን ነህ ተብሏል። የቀድሞው እሊቃየ የዐቢይ አባት "ተክለማርያም" ተብለው ከመጠመቃቸው በፊት ቂጤሳ ተብለው ይጠሩ እንደነበር ሰምቻለሁ።





የማኅበረሰብን ለውጥ የሚከታተሉ የዚያ ዘመን ደራሲያን ይህን ጉዳይ አይተው እንዳላየ አላለፉትም። ለአብነት፣ አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ የልምዣት በተባለው ልቦለድ ድርሰቱ ነካ አድርጎታል።

የዚህን ወፍራም ልቦለዱን ምእራፍ ሀያ ስምንትን የሚከፍተው በሚከተለው አንቀጽ ነው፡-

"ተፈራ ሉል ሰገድ የደጃዝማች ሉልሰገድ ከንፈ ያከስታቸው የልጅ ልጅ ነበር። አባቱ ሜጫ ውስጥ አቶ ገለታ የሚባሉ የ(ኦሮሞ) ባላባት ነበሩ። እሱም እንደተወለደ ስሙ ዳባ ነበር። ኋላ ግን ለትምህርት አዲስአበባ እንደመጣ ዳባ መባሉን ትቶ ተፈራ ተባለ።"

በቀኃሥ ጊዜ በተማሪ ቤቶች አማካኝነት ሲደረግ የነበረው ስም የማስመጥ ዘመቻ ከዚያ ቀደም ከነበረው ጋር በዓላማ በጣም ይለያያል። በቀደሙት ንጉሠ ነገሥታት ዘመን የማእከላዊው መንግሥት ርእዮተ ዓለም ክርስትና ነበር። ክርስትና መነሣት የሙሉ ዜግነት መሥፈርት ነበር ሊባል ይችላል። የስም ለውጡ በዋናነት ከጥምቀት ልጅነት ጋር የተያያዘ ነበር። ሳውል የተባለ ይሁዲ ወደ ክርስትና ሲመጣ አሮጌ ስሙን ካሮጌ እምነቱ ጋራ አራግፎ ጳውሎስ የሚል አዲስ ስም እንደተቀበለ በሀዋርያት ሥራ መጽሐፍ ተተርኮልናል።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ሃዋርያት ይህንን ፈለግ ተከትለው የሚያጠምቋቸውን ሰዎች ስም ይቀይሩ ነበር። ለምሳሌ የአቡነ ተክለሃይማኖት ደቀመዝሙር የነበረው አቡነ አኖሬዎስ ከሙገር ተነሥቶ ወረብ የሚባል ሀገር ሲደርስ የወረብ ነዋሪዎች በቅድመ ክርስትና እምነት ሲኖሩ አገኟቸው። መነኩሴው በማጥመቅ ዘመቻ ወቅት የሚገጥመውን ፈተና ገምቶ ሲያመነታ ቤራግባን የተባለ ሹም ሊተባበረው ቃል ይገባለታል። ሹሙ ከህዝቡ ቀድሞ ክርስትናን የተቀበለበትን መንገድ ለአቡኑ ሲተርክለት እንዲህ ይላል፤

"ወእሐተ እለት ሖርሁ ኀበ አሃዱ ካህን ወነገርክዎ ኩሎ እምጥንቱ እስከ ተፍጻሜቱ ወውእቱኒ ወሀበኒ ንስሐ። ወይቤለኒ ኢይኩን ስምከ ቤራግባን አላ ትሰመይ ዘካርያስ ወስመ እምከ መርኬዛ ውብእሲትከ ማርያም ዘመዳ ወስመ አኃዊከ አብርሃም"





ትርጉሙ ፤

"አንድ ቀን ወደ አንዱ ካህን ሄጄ (ታሪኬን) ከጅማሬው እስተ ፍጻሜው አጫወትኩት። እሱም ንስሀ ሰጠኝ። ስምህ ዘካርያስ ይባል እንጂ ቤራግባን ተብለህ አትጠራ፤ የእናትህ ስም መርኬዛ የሚስትህ ስም ማርያም ዘመዳ የወንድምህ ስም አብርሃም ይሁን አለኝ" የሚል ነው።

በዚህ ዓይነት፣ ዮሐንስ አራተኛ የወሎውን ባላባት መሀመድን ክርስትና ሲያነሱ ራስ ሚካኤል አስኝተዋቸዋል። ባክሱም ሙዚየም ፣ በመስታወት ሳንዱቅ ውስጥ ተቀምጦ የተመለከትኩት ወርቅ ለበስ ከበሮ፣ "ራስ ሚካኤል ወልዱ ለዮሐንስ"፣ የሚል ጽፈት ተንቅሷል። እንዲሁም፣ ሐብተጊዮርጊስ፣ ገብረእግዚአብሔር፣ ተክለኢየሱስ፣ ቆሲ፣ ኩምሳ፣ ነገሮ የተባሉ ስሞቻቸውን የተውበት መንፈስ ይህ ነው።

"እልተተከለም ወይ ታቦት ባገራችሁ
ቡልቡላ ድጉማ ነጃራ ስማችሁ"

የሚለው የጥንት ዘፈን የሚጠቁመው በዚያ ዘመን የነበረው የስም ቅያሬ በዋናነት የእምነት ጣጣ ያመጣው መሆኑን ነው። ሽግግሩ ከአረሚ (ፔገን) ስም ወደ ክርስትና ስም የተደረገ ሽግግር ነው።

ነገሩ በተነሣ ቁጥር ቤተክህነትን ብቻ ነጥለው የሚወቅሱ ሰዎች ያጋጥሙኛል፣ ተገቢ አይደለም። እስልምናምኮ የትውልድ ስምን አስቀይሯል። ቀዳማዊ አባ ጅፋር መሀመድ ኢብን ዳውድ የሚለውን ስም የተረከቡት ከሰለሙ በኋላ ነበር። ትሪንግሀም እስልምና በኢትዮጵያ በተባለ መጽሐፉ እንደነገረን የቅድመ እስልምና ስማቸው ቱሉ ነው። ቾቾ የተባለ የጣልያን መንገደኛ በጊቤ ኦሮሞዎች ማኸል ኖሮ በጻፈው ማስታወሻ እስልምና ወደዚህ ሀገር ከገባ በኋላ ብዙ ገባርና ባርያ ኦሮሞዎች ሙስጠፋ፣ አሊ፣ ሙሳ፣ አቡበከር፣ በመሳሰሉ የቁርአንን ስሞች መጠራት ጀመሩ ይላል።

በዘመነ ምኒልክ በእምነት ጫና ስምን መቀየር የተለመደ ቢሆንም፣ ለመሾምና ለመሸለም ግዴታ አልነበረም። ወላጆቻቸው በሰጧቸው ስም በይፋ እየተጠሩ





ትልቅ ሥልጣን ላይ መውጣት የቻሉ ሹማምንት ነበሩ። ከነሀ መካከል ራስ ጎበና ዳጨ፣ የልፍኝ አስከልካዩ ፊታውራሪ ኢብሳ፣ የንጉሡ ገንዘብ ጠባቂ ባልቻ ሳፎ፣ በጣልያንና በሩስያ የኢትዮጵያ ልኡክ የነበረው ገነሜ እና የአድዋ ሰማእት ፊታውራሪ ጫጫ ይጠቀሳሉ።

በኃይለሥላሴ ዘመን ይደረግ የነበረው ከዚህ ይለያል። በዘመኑ የከፍለ ሃገር ባላባቶች የባላባትነታቸውን ሥልጣን ተነጠቁ። ሥልጣን በማእከላዊ መንግሥት እጅ ተጠቀለለ። ገና በመዳህ ላይ ያለውን የኢትዮጵያን አንድነት አላቅሙ እንዲሰግር የማድረግ ዘመቻ ተጧጧፈ። ኃይለሥላሴ ሹማምንት የራሱን እድገት ደረጃ ጠብቆ ቀስበቀስ ሊመጣ የሚገባውን ያገር አንድነት፣ በዘመናቸው ጠፍጥፈው ሊሰሩት ፈለጉ። ስም ለመለወጥ የሃይማኖት ለውጥ ሰበብ መሆኑ ቀረ። በዐማርኛ ትርጉም ያለው ስም መያዝ በከተሞች ደንበኛ የኑሮ ዘይቤ ሆኖ ቀረበ። ዳባ ገለታ የሚል ስም ይዞ ከቤቱ ወጥቶ ተፈራ ሉልሰገድ ሆኖ የሚመለስ ትውልድ የተፈጠረው በዚህ አግባብ ነው።

ደርግ እንዲህ አይነቱ ዘመቻ የፈጠረውን ብሄራዊ ቅሬታ በመረዳት አንዳንድ ገንቢ ርምጃዎችን ወስዷል። እኔ በተማርኩባቸው የዐማርኛ ማስተማርያ መጽሐፎች ላይ የብሔረሰብ ስሞችን ለአረፍተነገር መልመጃ በማድረግ እንዲለመዱ ለማደረግ በጎ ጥረት አድርጓል።

በታሪካችን የተከሰቱት እንዲህ ዐይነት ነገሮች ልንማማርባቸው እንጂ የተበዳይነት ፖለቲካ ማካሄጃ ልናደርጋቸው አይገባም። ይህንን የሌሎችን ስምና ባህል መዋጥ ክስተት መነሻ በማድረግ የራሳቸውን የፖለቲካ አጀንዳ ማራመጃ ሊያደርጉት የሞከሩ ሰዎችን እናያለን። በተለይ የሻእቢያ ምሁራን በዚህ ቀዳሚ ናቸው። እኒህ ምሁራን ስም ማስመጥ በዋናነት እምነትን መሠረት ያደረገና በሁሉም ሀገር የደረሰ ሁሉንም ያካተተ ሆኖ ሳለ፣ "ያማራው ገዥ መደብ"ን እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንን ብቻ ተጠያቂ አድርገው ሊያቀርቡ ሞክረዋል። እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው። እኒህ የሻእቢያ ሊቃውንት፣ ፕሮቴስታንቶች በኤርትራ የነበሩ ሙስሊሞችን ሲያጠምቁ ስማቸውንም አብረው መቀየራቸውን አይነግሩንም። የስም ለውጡ እጣ ከወደቀባቸው ኤርትራውያን መካከል የቴዎድሮስ አማካሪና አስተርጓሚ ለመሆን የበቃው

ሳሙኤል ጊወርጊስ አንድ ምሳሌ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል። ይህ ሰው ወደ ክርስትና ከመግባቱ በፊት የሳሆ ብሔረሰብ ተወላጅና የሼክ ልጅ ነበር። ሳሙኤል ጊዮርጊስ በሚል ከነአባቱ ስሙን ቀይሮ ያጠመቀውም የእንግሊዙ ጴንጤ ኢዘንበርግ መሆኑን ቻርለስ ቤኪ ነግሮናል።

ፕሮፌሰር አስመሮም ሁለቱን የኢትዮጵያ አውራ ብሔረሰቦች ከወንድማማችነት ይልቅ በበላጋራነት ስሎ በማቅረብ የታወቀ ጸሀፊ ነው። አስመሮም ባንድ ጽሁፉ ላይ ዐማራና የኦሮሞ ሌላውን የሚውጡበትን መንገድ ያወዳድርና የሚከተለውን ፍርድ ይሰጣል።

"ኦሮሞዎች ሌሎችን ሕዝቦች ሲውጡ ከሌሎች ለሚያገኙት እሴት እውቅና ሲሰጡ ዐማሮች ግን ዕውቅና የሚሰጡበት ጊዜ እምብዛም ነው። ለምሳሌ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የኦሮሞ የዘር ሐረግ ከሕይወት ታሪካቸውም ሆነ ከግለ ታሪካቸው ሙሉ በሙሉ ይፋቅ ነበር። የሸዋ ሥርወ መንግሥት አባላት ጠላቶቻቸውን ካስገበሩና ካጠመቁ በኋላ የማግባት ልምድ ነበራቸው። ይህ ሐቅ ባንድ ክፍለ ዘመን ውስጥ ከዘር ሐረግ ተሰርዟል። የተጠመቀው ሁሉ ስሙን ብቻ ሳይሆን፣ የወላጆቹን ስም ሳይቀር እንዲለውጥ ይገደድ ነበር"[21]

እስቲ የፕሮፌሰር አስመሮም ለገሰን አንቀጽ አንድ ሁለት ነጥቦች አንስቶ ልመዝነው።

[21]Whereas the Oromo assimilate other populations and culturally recognize thier indebtedness to those they have assimilated ,Amhara rarely make any such recognition .For example ,Emperor Haile Selasse's Oromo ancestory was completely scrubbed from his biography and autobiography .The Shoan dynasty was in the habit of Marrying thier enemies after they had conquered and babtized them .Within one generation ,that fact was deleted from the genealogy .The assimile changed not only his name but the names of of his parents as well. (Oromo Democracy ,p7)





## አንድ፥

ሲጀምር አስመሮምና ቢጤዎቹ የማጥመቅና ገባሩን ባህል በጌታው ባህል የመዋጥ ፖሊሲ (Assimilation) የዐማሮች እና የኦሮሞዎች ጉዳይ ብቻ አድርገው ሊያቀርቡት መሞከራቸው ስህተት ነው። ባህልን በባህል ማስገበር የማንኛውም ገናና ሥርዓት ባሕርይ ነው እንጅ የተወሰኑ ብሔሮች ባሕርይ አልነበረም። ንጉሠ ነገሥት ዮሀንስ በዘመቻ ቅማንቶችንና የወሎ ኦሮሞዎችን በክርስትና አጥምቀው ማንነታቸውን ጨፍልቀውባቸዋል።

ከተነሣ ላይቀር ዐማርኛ ብቸኛ የኢትዮጵያ ቋንቋ እንዲሆን አጥብቀው ሲወተውቱ ከነበሩት ምሁራን ግንባር ቀደሙ ኤርትራዊው በእምነት ገብረእምላክ መሆናቸውን "ያንድ ቋንቋ እድገት" የሚለው መጽሐፋቸውን ያነበበ ሁሉ ይረዳዋል። በብዙ መንገድ የማደንቃቸው የሀማሴኑ ገብረእግዚአብሔር ጊላማርያም፣ "ሁሉም እንዳባቱ ይደር" የሚለውንና ለዘብተኛ የምኒልክ የሃይማኖት ፖሊሲ በመቃወም ብሔረሰቦች በነባር እምነታቸው እንዲኖሩ መደረጉን ባገራችን ብርሃን እንዳይወጣ የሚያደርግ ተግባር ብለው አጣጥለውት ነበር። እኒህ ሰው በሚኒልክ ዘመን ባሳተሙት የስብከት መጽሀፋቸው፤

"አሁንም እስላሙ፣ ኦሮሞው፣ ፈላሻው፣ አረሜኑ፣ ወይጦው እያባቱ እያስተማረ ከክርስትያን ሃይማኖት እጅግ የራቀ የረከሰ(ን)ም መሆኑን እያወቁ ተወው ያስተምር እያሉ ትተውታል...." በማለት ከወቀሱ በኋላ፤

"አባቶቻችን በሃኬት እንቅልፍ ተኝተው ሃይማኖታችነን እንዲያጠፉ ባገራችን ብርሃን እንዳይወጣም እስላሙና ፈላሻው ኦሮሞው ሻንቅላው ከንቱ ሃይማኖት እያስተማሩ ዝም አሏቸው።"[22]

[22]እዋጅ እንዲበጅ ፤(ገጽ 65)





በማለት የተሰማቸውን ቁጭት ገልጸዋል። ዛሬ ምኒልክና ኀይለ ሥላሴ የብሔሮችን ማንነት መጨፍለቃቸውን ተርከው የማይጠግቡት አስመሮምና ቢጤዎቹ እኒህን ነገሥታት መጨፍለቂያ ድንጋዩን ሲያቀብሏቸው ስለነበሩት የመረብ ምላሽ ሊቃውንት የሚነግሩን የለም።

## ሁለት፥

ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የኦሮሞ ዘር- ሐረጋቸውን አስፍቀዋል ይላል አስመሮም ለገሰ። እውነት ነውን? እስቲ ዶሴው ይውጣና ይፈተሽ። ቀዳማዊ ኀይለሥላሴ በሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ከቤተመንግሥት ጸሐፊዎች አንዱ የሆነው፣ ማህተመ ሥላሴ ወልደመስቀል ቼ በለው በተሰኘው የመኳንንት አጫጭር የሕይወት ታሪኮችን በያዘው መጽሐፉ፣ ስለራስ መኮንን ሲጽፍ የሚከተለውን አስፍሯል፤ "መኮንን ወልደሚካኤል ... እባታቸው የዶባው ስመጥር ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ጉዲሳ ናቸው።"[23]

ኀሩይ ወልደ ሥላሴም የሕይወት ታሪክ በተባለው መጽሐፉ የተፈሪን አባት ጉዲሳ ወልደሚካኤል እንደሆነ ጽፏል። ኀይለ ሥላሴ ከኦሮሞ መወለዱን የሚያስፍቅ ከሆነ፣ ለምን በዘመነ መንግሥቱ የተጻፉትን እኒህን መጻሕፍት ይሁንታ ሰጥቶ እንዲታተሙ አደረገ?

ርግጥ ነው፤በኀይለስላሤ ዘመን ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው ስምን የማስመጥ ዘመቻ ባጼው ዘመዶች ላይ ሳይቀር አሻራውን አሳርፏል:: እዚህ ላይ የተፈሪ እኅት ልጅ የሆነውን ፊታውራሪ ቢራቱን ማንሳት ይቻላል። ቢራቱ የራስ መኮንን ታላቅ ወንድም የደጃች ሃይለማርያም ልጅ ሲሆን በራስ መኮንን ቤት አድጓል። ራስ መኮንን ከውጫሌ ውል በኋላ ወደ ጣልያን ልኡካንን ይዞ ሲሄድ ቢራቱ አብሮ የመሄድ እድል ገጥሞት ነበር። አፈወርቅ ገብረእየሱስ

[23]ቼ በለው ፤(ገጽ 69)





በሮም ጉብኝት ዘገባው ለልኡካኑ ከብር ተተኩሰውን መድፍ ቀልሀ ሲያዳንቅ "ከሐውልት የሚበሳልጥ መድፍ ሲተኩሱና በዙርያው ያለ ሰው መሬቱ እየተንቀጠቀጠ ሲወድቅ አዩ ተገረሙ ፤ተደነቁ። የመድፉ ጥይት ብቻ ከፊታውራሪ ቢራቱ (ዛሬ ደጃች ተብሏል) ቁመት ስንዝር ተጋት በለጠ" ይላል። [24]

ይህ ከንጉሥ እምቤርቶ የመድፍ ጥይት ስንዝር ተጋት የሚያንስ ሰውየ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዳጃዝማችነት ማእረግ ሲያገኝ ከ "ቢራቱ" ወደ "ብሩ" ተቀይሯል።[25]

## ሦስት፥

የዘር ሀረግን ዐውቀው በድፍረት፣ ሳያውቁ በስህተት የሚቀይሩና የሚሰርዙ መኖራቸው አይካድም። ግን በዐማራው ብቻ ሳይሆን በኦሮሞውም ሁፊርም ይደረግ ነበር። እዚህ ላይ፣የኦሮሞ ሊቃውንት ጽፈውት የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ካሳተመው መጽሐፍ የሚከተለውን ማስረጃ እንድጠቅስ ይፈቀድልኝ፡፡

"በኦሮሞ ሞጋሳ ባህል ሥርዓት <u>ወደ ኦሮሞነት የተለወጠ ግለሰብ</u> ወይም ጎሳ የዘር ሐረጉን ሲቆጥር በኦሮሞ እንጂ <u>በወለዱት ቤተሰብ ወይም ሕዝብ ዘር አይደለም</u>" (ሰረዞች የተጨመሩ)[26]

ይህ አንቀጽ ግልጽ ቢሆንም የበለጠ የሚያብራራው ምሳሌ ላምጣ ። አቦ ኢብሳ የተባለ ሰውየ ግርማ ከበደ የተባለ ልጅ በሞጋሳ ተቀበለ እንበል። ታድያ ግርማ የወላጅ አባቱን ስም ወድያ ጥሎ ግርማ ኢብሳ ተብሎ ሊጠራ ይገደዳል ማለት ነው። ነገሩ ግን በዚህ አያበቃም። የግርማ ዘር ማንዘር ከትውስታ ተደምስሶ ባቶ ኢብሳ የዘር ሐረግ ይተካል ማለት ነው። በሞጋሳ ወደ

[24]አጼ ሚኒልክ ፤ (ገጽ 70)

[25] ቼ በለው፤ (ገጽ 37)

[26]የኦሮሞ ታሪክ እስከ አሥራስድስተኛው ክፍለዘመን (ገጽ 116)

ኦሮሞ የተቀየሩ ህዝቦች በዚህ መንገድ ተውጠዋል፤ ተለውጠዋል። በጉዲፈቻ አባት አድገው በታሪክ ትልቅ ቦታ ከደረሱ ሰዎች አንዱ የወሊጋው መስፍን ጆቴ ይገኝበታል። የጆቴ እናት ከዐማራ ባሏ ጋር ከተለያየች በኋላ የሌቃ ኦሮሞ ስታገባ ጆቴም በጉዲፈቻ ወደ ኦሮሞነት መለወጡ ተወስቷል።[27]

እዚህ ላይ ዜግነት እንጂ የብሔረሰብ ማንነት አይለወጥም እያሉ በልበ ሙሉነት ለሚጽፉ ሰዎች ከዚህ የተሻለ ማስተባበያ የሚገኝ አይመስለኝም፤ "ወደ ኦሮሞነት የተለወጠ ግለሰብ" የሚለው ሐረግ የብሔረሰብ ማንነት ለለውጥ የተጋለጠ ለመሆኑ ማስረጃ አይደለምን? ለነገሩ እንዲያውም እንዲያው ልፋ ቢለን ነው እንጂ፣ የዜግነታችን እንጂ ዘራችን ግልጽ አይደለም።

ወደ ማሳረጊያየ እየደረስሁ ነው።

የቤተሰቤና የጉብረተሰቤ ላይ ባደረኩት መጠነኛ ጥናት፤ ግለሰቦች የገዛ ማንነታቸው ጌቶች እንዳልነበሩ ተረድቻለሁ። የግለሰቦች ማንነት ከበላይ ባሉ አሳዳጊዎችና አስጠጊዎች ፍላጎት ሲወሰንኖሯል። የተለያዩ ባህሎችን ባንድ በገና ውስጥ እንደተወጠሩ አውታሮች ማስተናገድ በማይታወቅበት ጥንታዊ ማኅበረሰብ ውስጥ ግለሰቦች የገናና ባህሎችን (የሞጋሳንየ ጥምቀት) ምልክት አሜን ብለው ከመቀበል ያለፈ ምርጫ አልነበራቸውም።

[27]Studies of the Oromo of Wallaga, by Lamert Bratels: Journal of Ethiopian study, (p 146).





# ስለ ገብረእግዚአብሔር

የታመነው ባንዳ፤

ታህሳስ 14፤ 1894

ደጃች ባህታ ሀጎስ የተባለ የአካለ ጉዛይ ተወላጅ ሹምባሽ፣ ሰገይኒቲ በሚገኘው የአንድ ጣልያንያዊ መኮንን ቤት ውስጥ ከወንድሙ ጋር ተጋብዞ ይጠጣል። ባህታ በጊዜው በኤርትራ ይኖሩ ከነበሩ ለጣልያን የገበሩ ሹሞች አንዱ ተደርጎ ስለሚቆጠር ቀጥሎ የተከሰተውን ጀብደኛ ርምጃ ይወስዳል ብሎ የሚጠረጥረው አልነበረም።

ባህታና ወንድሙ ድንገት ተጠቃቅሰው ከወንበራቸው ብድግ ብድግ ካሉ በኋላ የቤቱን ባለቤት መቶ አለቃ ሳንጎኒቲን አንቀው ይዘው ወለሉ ላይ ጣሉት። መቶ አለቃው በደረሰው ነገር ቢደናገጥም ራሱን ለመከላከል ትንሽ ተፍጨረጨረ። አልሆነለትም። ባህታ መኮንኑን ወለሉ ላይ ጥሎ በጉልበቱ ደረቱ ላይ ቆመበት። መኮንኑ ከታች ሆኖ "እግዜር ይቀጣሃል፤ኢጣልያ ታላቅ ናት" ብሎ ፎከረ። ባህታ ሀጎስ፤ "ኢትዮጵያ የበለጠች ታላቅ ናት" ብሎ መለስለትና አሠረው።





ባህታ መኮንኑን እና አስተርጓሚውን አሥሮ ወደ ራስ መንገሻ ወስደው እንዲያስረክቧቸው ሎሌዎችን ካዘዘ በኋላ ማመጹን አስታወቀ።

በማግስቱ ማርሻል ቶሊዚ በሚባል የጦር አዝማች የሚመራ ጦር ባህታን ከነጭፍሮቹ ከበበው።


ባህታ ከትግራዩ ራስ መንገሻም ሆነ ከሸዋው ምኒልክ ደጋፊ ጦር ይመጣልኛል በሚል ተስፋ ቢጠብቅም ብቅ የሚል ጠፋ። በመጨረሻ ከጥቂት ታማኝ ወታደሮቹ ጋር ሆኖ ከኃይለኛ ጠላቱ ጋር ተፋለመ። የጎልያድና የዳዊት ግብግቡ በጎልያድ አሸናፊነት ተጠናቀቀ። ሦስት ሰአት ከፈጀ መታኮስ በኋላ የአካለ ጉዛዩ ጅግና በጥይት ተመትቶ ወደቀ።



ብላታ ገብረእግዚአብሔር







ብላታ ሀጎስ

ማጆር ቶዜሊ የባህታ አስከሬን ለሕዝብ መቀጣጫ ይሆን ዘንድ ሳይቀበር አደባባይ ላይ እንዲሰጣ አዘዘ። እስከ አድዋ ጦርነት ድረስ፤ "ጣልያን ታላቅ ናት" የሚለው የጣልያኑ መኮንን ሽለላ የማይስተባበል ሀቅ መስሎ ቆየ።

ኤርትራ በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰች ማግስት የኢትዮጵያ ብሔርተኛ ጸሀፊዎች የመረብ ምላሽ ጀግኖችን ገድል በማውሳት ተጠምደው ነበር። ለዋቢነት፤ ጸጋዬ ገብረመድህን "ዘርአይ ደረስ በሮም አደባባይ" በተባለው መነባነቡ፤

"...የባህታ ሀጎስ አጽም ይመስክር
ያየደገኛው ወንድ የአካለ ጉዛዩ ነብር
ይመስክር የህላይ ምድር
የነሳንንቲ ጌታ "ጣልያን ኀያል" ናት ብሎ ሲል
የኢትዮጵያን የበላይነት በቡጢ ከንትሮ የሚያስምል፤" ይላል።

ባህታ ሀጎስ የጣልያኑን መኮንን ወለል ላይ ጥሎ የኢትዮጵያን የበላይነት፣ "በቡጢ ከንትሮ" ለማስማል በሚቃጣበት በዚያ ቀውጢ ሰአት ገብረእግዚአብሔር የተባለ ጎረምሳ ቁጭ ብሎ ይህን ጉድ ይመለከት ነበር። ገብረእግዚአብሔር የሀማሴን ተወላጅ ሲሆን ካፒቴን ቤኒት በተባለ ጣልያንዊ መኮንን ቤት አድጓል። ካፒቴኑ ከሞተ በኋላ ደግሞ የመቶ አሊቃ ሳንጎኔቲ ወደተባለ መኮንን ተጠግቶ ባስተርጓሚነት ሲያገለግል ቆይቷል። በግብግቡ ወቅት ገብረእግዚአብሔር ከወንዙ ልጆች ጋር በማበር ፈንታ መኮንኑን ከጥቃት ለመከላከል መርጧል። ጌታውን ታግሎ ማስጣል እንደማይችል ሲረዳ ባህታ ሀጎስን በወቀሳ ያጣድፈው ጀመር። ሁለቱ ሰዎች የተለዋወጡትን መወቃቀስ የዘመኑ አፍቃሬ ጣልያን ዘጋቢ ፖል ሎሪባር "አሥራ ሁለት ዓመት በአቢሲኒያ" Douze ans en Abyssinie በተባለው ማስታወሻው እንዲህ መዝግቦ አቆይቶናል።

**ገብረእግዚአብሔር፣** እግዚአብሔር የማይወደውን ነገር ነው የምትሠራው

**ባህታ፣** የሠራሁት የፍትሐ-ርትእና የብቀላ ሥራ ነው። በቅርቡ አገራችንን ለመውሰድ በመጡ በዝባዦቻችን ላይ ጠቅላላ አመጽ ይቀሰቀሳል። ራስ መንገሻ፣ ምኒልክ፣ አሳውርታዎችና ደርቡሾች አብረውን ይሰለፋሉ። ጣልያኖች ይደመሰሳሉ። አስካሪዎች ሁላ ከነመሳርያቸው ወደ እኛ ይገባሉ። ጣልያኖችን ፈጅተን የራሳችን ሀገር ጌቶች እንሆናለን። አንተም ከነሀ ርኩስ ፈረንጆች ጋር





ሆነህ ባካበትከው ዕውቀት ብዙ ታገለግለናለህ። እኔም ፕንዘብ ፈረስና ነፍጥ አሸልምሃለሁ። ከበታቼም እሾምሃለሁ።

**ገብረእግዚአብሔር፣** አይሆንም። ጣልያኖች ሳይደርሱልህ በፊት መናጢ ነበርህ። በጎ ለዋሉልህ ሰዎች በክህደት ብትመልስላቸውም እኔ እንዳንተ አይደለሁም። ካፒቴን ቤኒቲ አባቴ ሆኖ አሳድጎኛል። ሌሎችም ሹሞች በጋጣሚው ሁላ በጎ አድርገውልኛል። አሁንም ከንጹን ሳልንተራስ ጌታዮን ጥየው አልሄድም።

**ባህታ፣** (በንግግሩ ጥንካሬ ተማርኮ ትንሽ ዝምም ብሎ ከቆየ በኋላ) ይሁና እንግዲህ፡ ከኛ ጋር መሆን ካልፈለግህ እንዳሻህ። አስመራ ለምትኖረው አሮጊት እውር እናትህ ፕንዘብ ልስጥህና ይዘህላት ሂድ። ከበቅሎዎቼ ባንዲቱ ላይ ተቀመጠህ ወደ እናትህ ሂድና አዚያ ሰንብት።

**ገብረእግዚአብሔር፣** ጌታየን ሳትለቅቀው አልሄድም

**ባህታ፣** አይደረግም!

**ገብረእግዚአብሔር፣** ይሁና እንግዲህ! እንደሱ ከሆነ እኔንም አብረህ አስረኝ።

**ባህታ፣** ደረቅ ነህ! ለማንኛውም አሥርሃለሁ።

ሙግቱ በሁለት የተለያዩ ሰዎች መካከል ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የኑሮ እሴቶች መካከል ነው። ባህታ ሀጎስ ለሀገር ፍቅር መከራና ሞት ለመቀበል በተዘጋጀበት ሰአት ገብረእግዚአብሔር ጊላ ማርያም ለወዳጅ ፍቅር መከራ ለመቀበል ተሰናድቷል። በባህታ ዐይን ገብረእግዚአብሔር፣ አገሩን የከዳ ሲሆን በገብረእግዚአብሔር ዐይን ባህታ የቀድሞ ወዳጆችን አጉራሽ እጅ የነከሰ ከሀዲ ነው። ሁለቱ ጀግኖች እንደ ግሪክ ትራጄዲ ገጸባሕርያት ለፍርድ የሚያስቸግር የየቅል የሆነ ግን ተመጣጣኝ ክብደት ያለው እምነት ይዘው በፊታችን ይፋለማሉ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ የውጫሌ ውል ፈርሶ ኢትዮጵያና ጣልያን በትግራይ ምድር ተፋለሙ። በባህታ ሀጎስ እጅ ታግቶ ባስተርጓሚው ገብረእግዚአብሔር





ብልሃት እንዲያመልጥ የተደረገው መቶ አሊቃ በኮአቲ ጦርነት ተገደለ። ባህታ ሀጎስን የገደለው ማጆር ቴዚሊ በአምባላጄ ጦርነት ላይ ደመከልብ ሆነ። ኢትዮጵያውያኑ የቂም በቀል ስሜታቸውን ዋጥ አድርገው በክብር አስቀበሩት። "ኢትዮጵያ የበለጠ ታላቅ ናት" የሚለው የባህታ ሀጎስ ንግግር ደረቅ ትንቢት ሆኖ የደረሰ መሰለ።

ባድዋ ጦርነት ወቅት ገብረእግዚአብሔር ከጣልያኑ ዋና ጦር ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ባራቴሪ ጋር በፈረስ ተቀምጦ ባንዲራ ይዞ እንደተሰለፈ ተጽፎለታል ። ጦርነቱ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ሲጠናቀቅ ሽሽቶ መረብን በመሻገሩ እንደሌሎች ምርኮኛ አስካሪዎች እጁንና እግሩን ከማጣት ተርፏል። በጊዜው የሸሹ የጣልያን ወታደሮች ልብሳቸው ላያቸው ላይ አልቆ፣ ጫማቸው መንገድ ላይ ወልቆ በከፊል ርቃናቸው ወደ አስመራ መድረስ ችለዋል። በዚያ ጨርቅ አስጥል ቀውጢ ወቅት ገብረእግዚአብሔር የጣልያንን ባንዲራ ሳያስማርክ ወደ አስመራ ሸሽቶ በመግባቱ ባሳዳሪዎቹ ዘንድ እንደትልቅ ጀብድ ተቆጥሮለታል። በጦርነቱ ማግስት ሰወሬ ነጋሪ የተረፉ ጣልያኖች ማኸል አንዱ ሲጽፍ "ገብረእግዚአብሔር ለኛ ትልቅ ሁብታችን ነው ማለት ይቻላል። ያ ከሃያ ዓመት የማይበልጠው ብላቴና ሁሌም ደስተኛ ብሩህ ጭንቅላት ያለውና ንቁና ታማኝ ነው"[28] ሲል አሞግሶታል።

ጣልያን በአድዋ ከተዋረደች በኋላ በጣልያን ሹማምንትና በገብረእግዚአብሔር መካከል የነበረው ፍቅር ቀዝቅዟል። ጣልያኖች ይህንን በታማኝነት ሲመኩበት የነበረ ሰው ከምኒልክ ጋር ተመሳጥሯል በሚል ወንጅለው ናኩራ ውስጥ በሚገኝ ዘብጥያ ውስጥ ወርውረው አሰሩት። ከጥቂት ዓመታት በፊት ባህታ ሀጎስ ሳንጉቴን እግቶ በግር ብረት ሲያሥረው ገብረእግዚአብሔር "ጌታየ ሌባ አይደለም። እንደ ሌባ በእግር ብረት ልታሥረው መብት የለህም" ብሎ በመገሰጽ እንዲፈታው አድርጎት ነበር። አሁን እሱ ራሱ ትናንት መስዋእትነት በከፈለላቸው ሰዎች ተዋርዶ እንደሌባ በእግር ብረት ሲታሠር ስለነጻነቱ የሚሟገትለት ጠበቃ ከአጠገቡ አልነበረም። ለነገሩ ሰውየው የዋዛ ስላልነበረ

[28]Gabre Sghear, é un tesoro per noi, questo bel giovanotto pùi di venti anni, sempre gaio, intelligent, pronto e fedele. ximens, sul Campo di Adua (p163)





በእሥርቤቱን ዘበኞች በገዛ ጠመንጃቸው ገድሎ በማምለጥ ኤርትራን ድንበር አቋርጦ ራስ መኮንን ሥር ወደ ነበረችው ትግራይ ገብቷል።

ጣልያኖች በገብረእግዚአብሔር ላይ ያቀረቡት ውንጀላ እውነት አለው? ወደፊት ጊዜና ጥናት ይገልጠዋል። ከጣልያኖች ጋር በነበረበት ጊዜ ውስጥ ውስጡን ለምኒልክ መረጃ ያቀርብ እንደነበር የሚናገሩ ሊቃውንት አሉ። ፖል ሜረብ የተባለ የዐጼ ምኒልክ ሀኪም ገብረእግዚአብሔርን በስተርጅና ዘመኑ አግኝቶት ተወዳጅቶት ነበር። እናም ስለሱ ሲጽፍ C'est un homme d'une cinquantaine d'années, et qui a joué un grand role d'informateur en faveur du Choa pendant les années qui précédere la guerre italo –abyssine (የአምሳ ዓመት ሰው ነው። ከኢጣልያ ኢትዮጵያ ጦርነት ከመጀመሩ አስቀድሞ ባሉት ዓመታት ለሸዋ መረጃ ያቀብል ነበር) ብሎ ጽፏል።

## የባነነው አርበኛ

በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ቤተመጻሕፍት ብራና ክፍል ውስጥ ባልባሌ ካኪ ወረቀት ተገንዞ የተኛ አንድ ጥራዝ አለ። በዚያ ጥራዝ ውስጥ የገብረእግዚአብሔር ጊላማርያምን ፖለቲካና ሃይማኖታዊ ፍልስፍናዎችን የተሸከሙ ድብዛዛ ወረቀቶች ይገኛሉ። ገብረእግዚአብሔር ማስታወሻውን የሚጀምረው በሚከተለው ጦማር ነው፤

"እግዚአብሔርን የምትፈራና የምትወድ አርቶዶክሳዊ ወንድሜ ሆይ ያገራችን ኢትዮጵያ መከራና ያለፈውን እየሰማሁ አሁንም እያየሁ በልቤ ውስጥ ስለበረታብኝ አንተም ከኔ የምትበልጥ ማእምር ነህና እንድታዝንላት በተቻለህም ነገር ሁሉ ከደረሰባት መከራና ጭንቅ እንድታወጣት እማልድሃለሁ። በመዋረድዋም እንድታዝንላት በመንግሥትዋ እጅግ ታላቅ የከበረችም ብሔር እግአዚ ትባል ነበረች።"

ገብረእግዚአብሔር ተወልዶ ያደገው ኢትዮጵያ በብዙ "መከራና ጭንቀ" ማኸል ወድቃ አሳሯን በምታይበት ጊዜ ነበር። በተለይ ባፍላ ወጣትነቱ ጊዜ የተከሰተው ከፉ ቀን ተብሎ ቢታሪክ የሚታወቀው ዘመነ መከራ ስለአካባቢው በጥልቅ እንዲያስብ አስገድዶታል። በወቅቱ በአካለ ጉዛይ እናት ልጇን በልታለች። ቢድዋ ሰው እንደ ጅብ ተበላልቷል። በራብና በቸነፈር የሚረግፈው ሰው ቁጥር በጣም በርክቶ አስከሬን ቀባሪ አጥቶ አካባቢ መበከል ሲጀምር ጣልያኖች የሰው በድን ማቃጠል ተገድደዋል።

ከእለታት አንድ ቀን አንድ የጣልያን ፖሊስ በአስመራ ባንዱ ጥግ ላይ የወደቀ በድን ስለተመለከተ ዘብጥያ ሰለሞን የተባለ አሽከሩን እንዲያቃጥለው ያዘዋል። አሽከርየው ናፍጣ አርከፍክፎ ሲለኩስ ለካ በድን መሳዩ ሰውየ አልሞተ ኖሮ እሪታውን ይለቅቀዋል። በጊዜው በፈረስ ላይ ሆኖ አስመራን ሲዞር የነበረው ገብረእግዚአብሔር እሪታው ወደ ተሰማበት ቦታ ጋልቦ በመድረስ እሳቱን ከሰውየው ላይ አጠፋው። ሰውየው ግን አልተረፈም።

ገብረእግዚአብሔር እንደ እንደባነኑ የዘመን እቻዎቹ ሁሉ ባገሩ ላይ የሚያየው እስከፊ መከራ አሳስቦታል። አገሩ የተፈጥሮ ሀብታም ሆኖ ሳለ ህዝቡ በድኽነት የሚማቅቅበትን ምክንያት ግራ ገብቶታል።

"በአገራችን ድኽነት ሙብዛቱና መበርታቱ ጌቶች በዝተው እውነተኛ ዳኛና ጠባቂ ስለታጣ ነው። ያገራችን መሬት ፍርያማ ናት። ዝናም የሚበዛባት ስለሆነ፣ ይልቁንም ገሮየ እንደሚሰማው ዐይኔም እንደሚያየው በዐማራ ሀገር እህል ይበዛል። በመጫና በዳሞት ባገው ምድርና በሃማሴን ይልቁንም ባንሰባና በቦንስ በባርካና በሃባብ በአሳውርታ በአካለ ጉዛይ ቡትግሬ ሁላ የነበረ ላም ብዛት ለመቁጠር እጅግ ያስሸግር ነበር ይላሉ። ዝብዮስ የሚባል ሰው በዳሞት ነበረ። ላሙ ሽህ ስለተቆጠረ በወተትና በማር ደብልቆ ሁለትሺህ ጊዜ ታጠበ ይላሉ" በማለት ጽፏል።

አንድ የፈረንጅ ጸሐፊ፣ "ዘንድሮ ተስፋ የቆረጠ ወደ ድሮ ይሰደዳል" ይላል። ባለቀቢጸ-ተስፋዎች ወደ ድሮ ከመሰደዳቸው በፊት ድሮው እንዲመቻቸው አድርገው ያሳምሩታል። ከምናባቸው በሚመነጭ ውበት ያስጊጡታል። አብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ፍርያማ መሆኑ የማያጠራጥር ቢሆንም





ገብረእግዚአብሔር በሚነግረን መጠን የጥጋብ ታሪክ ኖሮን አያውቅም። በየዘመኑ ወደ ሀገራችን የመጡ የውጭ ሀገር ጎብኝዎችን ማስታወሻ እንዲሁም በሀገራችን ጸሐፊዎች የተጻፉ ዜና መዋእሎችን ስንመረምር የምንደርስበት ድምዳሜ ኢትዮጵያ የእጥረት ሀገር መሆኗን ነው። ማርና ወተት ደብልቀው ገላቸውን የሚታጠቡ ጌቶች መኖራቸው የገባሩን ሕዝብ የድኽነት ታሪክ አይሸፍነውም።

ገብረእግዚአብሔር ባለፈው ዘመን የጥጋብ ታሪክ ከመጽናናት ወጥቶ በዘመኑ ትክክለኛውን የጉስቁልና ምንጭ ሲፈትሽ ኋላቀሩ የባላባት ሥርዓት መሆኑን ይደርስበታል።

"ዳግመኛም ከእነዚህ ከቆጠርኋቸው መቅሰፍቶች የባሰ ሀገርን ያበላሸና ያጠፋ የተሰፋ ወደ ሀገር መግባት ነው። ገዥው እስከዚህ ወር ድረስ ጠዋት ነጠላ ማታ ድርብ እየተቀበልክ ተቀለብ ብሎ ጭፍራውን ይሰዳል። ያገር ሹምም የወታደሩን ቀለብ ተቀብሎ በአሥር አሥር ወይም በሚበዛ ባንድ ቤት ያገባል። ወታደሮቹም ባለቤቱ ድሃ ሲሆን እምጣ እያለ ያዳፋዋል። በጭራ ደም ከጣቱ እስኪወጣ ድረስ የፍጥኝ ያሥረዋል። በእሳትም ይለበልበዋል። በብርቱ ስቃይም ያስጨንቀዋል። ባለቤቱ ሀብታም ቢሆን ወታደሩ ከጠገበ በኋላ ምሽቱን ይቀማዋል። ሴት ልጁን ያስነውርበታል። እያባበለ ካባትዋ ወይም ከናትዋ ቤት ይወስዳታል።"

እያይዞ የወታደሩ ሥርዓት በባላገሩ ላይ የተጫነ ቀንበር እንደነበር ያብራራል። ገብረእግዚአብሔር በጥንቱ የወታደር ሥርዓት ላይ ያቀረበውን ትችት አሳጥሬ ሳቀርበው የሚከተለውን ይመስላል።

አንድ ተራ ወታደር ገረድ ትኖረዋለች። ከፍ ያለ ማእረግ ያለው መኮንን ደግሞ እመቤት ከነደንገጥሯ የማስከተል መብት ነበረው። እያንዳንዱ ወታደር ፈረስ የሚጭንለት ቋሚ ለጓሚ ያስከትላል ። ሻለቃ አጋፋሪ የሚባል ሹመት ያለው ወታደር ደግሞ በትንሹ በሥሩ አሥራ አምስት የቤተሰብ አባላት ያስተዳድራል። የሠራዊቱ አለቃ እያንዳንዱን ወታደር ጠርቶ ስንት ሰው በስሩ እንደሚያስተዳድ ይጠይቀዋል። ወታደሩም ጨማምሮ ፈረስና በቅሎውን ሳይቀር ቆጥሮ ይሄን ያክል እለብኝ ብሎ ይመልሳል። የሠራዊቱ አለቃ





ለእያንዳንዱ ወታደር ካንጓዡ የሚመግብ ገበሬ ይመድባል። "ከዚያ በኋላ" ይላል ገብረእግዚአብሔር አንቀጹን ሲቋጭ "ከዚህ በኋላ እንደ አንበጣ ባገሪቱ ላይ ይወርድባታል።"

በጊዜው በዚህ መንገድ ሕዝቡን እግር ተወርች አሥሮ የያዘው የጭቁና ሥርዓት እጅግ ከባድ በመሆኑ በዘመኑ የደረሱ የተማሩ ወጣቶች እንዲህ ካለው ቀንበር የሚገላግላቸው መሲህ ይናፍቁ ነበር። ይባስ ብሎ አንዳንድ የዘመኑ ሊቃውንት የቅኝ ግዛት ናፍቆታቸውን በግልጥ እስከመናዘዝ ደርሰዋል።

ለምሳሌ የገብረእግዚአብሔር አድናቂ የነበረው ገብረሕይወት ባይከዳኝ፤

"በዙርያችን ያሉትን አገሮች ስንመለከት አእምሮ ያላቸው ህዝቦች በብዙ ትጋት ሲያለሟቸው እናያለን። ይልቁንም በደርቡሾች ጠፍቶ የነበረውን የሱዳንን መሬት ብናይ እንግሊዞችን የሚመስል የአእምሮ ሕዝብ ሲገዛው ምድረበዳም ቢሆን የደስታ ገነት እንዲሆን ይመሰክርልናል። በዙርያችን ቅኞችን ኮሎኒዮች ይዘው ያሉ ህዝቦችም ያእምሮአቸው ኃይል እንቅፋትን ሁሉ እያሸነፈ ወደ ፊት ይጓዛል" በማለት ሲጽፍ፣ በልጅነት ሩሲያ ተሻግሮ ያደገው ተክለሐዋርያት ተክለማርያም በበኩሉ፤

"አንዳንዴ ሳስበው ምናልባት ሌሎች የሰለጠኑ ህዝቦች ጥቂት ዘመን አስተዳድረውንና አሰልጥነውን ቢሆን ይሻል ኖሯልን? እያልኩ ራሴን እስከመጠየቅ እደርሳለሁ። እንግሊዞች ካንድም ሁለት ጊዜ እድሉን አግኝተው ነበር። ግን ለመርዳት ስላልፈለጉ ምንም ሳያቋቁሙ ከሀገር ወጥተው ሄዱ" ብሎ ተቆጭቷል።

የአውሮፓን ቅኝ ገዥዎች ፖሊሲ ከስልጣኔ፣ ያገራችንን የጉሮ ዘይቤ ደግሞ ከገልቱነት ጋር አቆራኝቶ የማሰብ ዝንባሌ የሚመነጨው ከሊቃውንቱ የግል ገጠመኝ ይመስለኛል። እኒህ ሊቃውንት በፈረንጅ አሳዳጊዎች ቤት በፍቅርና በክብር ያደጉ በመሆናቸው ቅኝ ግዛትን ሲያስቡ ወደ አእምሮአቸው የሚመጣው፣ "የደሲታ ገነት" ቢሆን አይደንቅም። ቅኝ ገዥውን የጉዲፈቻ አባታቸው አምሳያ አድርገው ስለሚያስቡት ነው መሰል ከፉ ገጽታውን ለመልከት አይደፍሩም።





ገብረእግዚአብሔር በጌቶቹ፣ "ብሩህ ጭንቅላት ያለው ቀልጣፋ" እየተባለ በሚሞገስበት ዘመን፣ አብዛኛው የመረብ ምላሽ ሕዝብ ኩበረ-ነክ ዘለፋ ይወርድበት ነበር። ጣልያኖች ከፊታቸው ሆነው ደማቸውን የሚያፈሱላቸውን አስካሪዎች፣ "ደደቦችና ጅግኖች ተዋጊዎች" በማለት ነበር የሚጠሯቸው።

ገብረእግዚአብር ወደ ማኸል ሀገር ከገባ በኋላ፣ ኅብረተሰብን በማንቃት ዘመቻ ተጠመደ። ጣልያን ለብቀላ ጦርነት የመመለስ እቅድ እንዳላት ስለሚያውቅ ኢትዮጵያውያኑ ነቅተው እንዲጠብቁ መወትወት ጀመረ። የችጋርና የኋላቀርነት ምንጭ የሆነው አርጌው ሥርዓት ተለውጦ በሰልጡን ሥርዓት ካልተተካ አገሪቱ ልትደመሰስ እንደምትችል አስጠንቅቋል።

"ሁላችሁም ስሙኝ ከስላሙ እስካማራ፣
ጳጳሱ መነኩሴው ሰሞንኛው ደብተራ"

ብሎ ይጀምርና፣

"…. ከኤውሮፖች እንማር በጣም እንበርታ
ታሪክ እንመርምር እናንብብ ጋዜታ
ቋንቋም እንማር እንመልከት ካርታ
እሱ ነው ለህዝቡ ዐይናቸው የፊታ" በማለት፣

ዘመናዊ ትምርት ለሀገር ዐይን ከፋች መሆኑን ለማሳየት ሞክሯል ።

ለዛሬ አንባቢ "እንመልከት ካርታ" ብሎ ስብከት ካንድ ምሁር የማይጠበቅ በጣም ተራ ሊሆንበት ይችላል። ይሁን እንጂ፣ "እንደ ጸመድዓ መልኳ የረቀቀው/ እንደ ኢየሩሳሌም ወገቧ የራቀው" ተብሎ በሚዘፈንበት ኢየሩሳሌም የምድር መጨረሻ ሆና በምትቆጠርበት በዚያ ዘመን ትልቅ ምክር ነው።

ገብረእግዚአብሔር ባደባባይ የሚነዛቸው ስብከቶቹ በህዝቡ ማኸል ዘልቀው ውይይት ይፈጥራሉ ብሎ፣ ተስፋ ቢያደርግም ያገኘው ምላሽ ጭው ያለ ዝምታ መሆኑ ሳያስገርመው አይቀርም። ጳጳሱ፣ መነኩሴው፣ ሰሞንኛውና ደብተራው

ዘመናዊ ትምርት ሃይማኖትን ያስከዳል ብለው የሚያስቡ ነበሩ። ወታደሮች ባድዋ ድል ትምክህት ታውረው ስለደካማነታቸው የሚነግራቸውን ሰው ለመስማት ዝግጁ አልነበሩም። ሰባኪው ስብከቱ ብላሽ መሆኑ ያሳሰበው መሆኑን የምናውቀው የሚከተሉትን ስንኞች ስናነብ ነው።

"ዘውትር ብመከርም እሁድ እሁድ ሲታ
አንድ ሰው አጣሁኝ የሚነቅፈኝ ጌታ
ወይም የሚለኝ እውነት ነው እንዴታ"

የገብረእግዚአብሔርን ምክር ሰምቶ፤ "እውነት ነው እንዴታ!" ብሎ የሚደግፍ ባይመጣም ነቃፊ ግን ዘግይቶም ቢሆን ብቅ ማለቱ አልቀረም። የመጀመርያውን የነቀፋ ናዳ የለቀቀው ጉደኛው አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ነው። አፈወርቅ በወቅቱ ከጣልያናዊት ሚስቱ ጋር አስመራ ላይ ተደላድሎ ተቀምጦ፤ የሙሶሎኒ መንግሥትን፡"የብርሃን ጌታ" እያለ የሚያሞግስ ጸሐፊ ነበር። የገብረእግዚአብሔር ባገር ፍቅር የነደዱ ቅስቀሳ ለጣሊያን ቅኝ ግዛት እቅድ እንቅፋት ሆኖ ሳይታየው አልቀረም። አዛውንቱ የጦቢያ ደራሲ ይህንን አፍለኛ አርበኛ ለማሸማቀቅ እንደሳማ የሚለበልብ ብእሩን መዝዞ ከተፍ አለ።

"አስተርጓሚ ሆኖ ስሃን ሲፈገፍግ
አሁን ማን አገባው ከጨዋታ ከወግ
ታዛባ ሳይለይ ወድቆ ሲያድር ተፍግ
አከብረውህ ነበር ብለውህ ብላታ
በግር ብረት ገባህ ስለሆንህ ወስላታ
አር ስትጠርግ ነበረ ስትደፋ ባሬታ
ትሰድብ ጀመረ የብርሃኑን ጌታ።"

ግጥሙ በርካሽ ስድብ የተሞላ ቢሆንም፤ የተሰዳቢውን ያለፈ ሕይወት የሚገልጹ እውነቶችን ይዟል። ሌላው ቢቀር የገብረእግአብሔርን አስተርጓሚነት በጣልያኖች የተከበረ ሰው እንደነበረና መታሠሩን መስክሯል።





"ምላስህ መርዛም ነው ከንፈርህ መግላሊት
ሰባት ጊዜ ከደህ የለህም ሃይማኖት
ለሞኝ ይመስለዋል ገብረእግዚአብሔር ሲሉት
ዶሮውን ሳያርዱ ይገኛል መረቅ
ግጥም ገጠምሁ ይላል ዐማርኛ ሳያውቅ።"

አፈወርቅ ከዝርው ድርሰቱ ጋራ የሚመጣጠን የግጥም ችሎታ እንዳልነበረው ከላይ ያየናቸው መስመሮች ያሳብቃሉ። ስለዚህ የወላጆቹ ቋንቋ ያልሆነውን ዐማርኛን አጥንቶ ሐሳቡን በተሳካ መንገድ መግለጽ የቻለውን ገብረግዚአብሔር መዝለፉ እብሪትን እንጂ ሌላ ስም ሊኖረው አይችልም። ዓላማው ጸሀፊውን አሸማቅቆና አቅልሎ ዐማርኛን እርም ብሎ እንዲተው ይመስላል።

በርግጥ ገብረእግዚአብሔር ከበደ ሚካኤል አይደለም። በአገላለጹና በዜማው የሚያማልል ግጥም የመግጠም ችሎታ አልተሰጠውም። ለማስደነቅ ለማዝናናት ሳይሆን የለውጥ የሚያነሳሳ ሐሳብ ለማስተላለፍ የሚገጥም ነበር። ሬድዮ በሌለበት ጋዜጣ ባልተስፋፋበት፤ ከሺህ ዓመታት በፊት የተደረሰውን የዳዊት መዝሙር ከመድገም ያለፈ ደንበኛ ንባብ በማይታወቅበት በዚያ ጨለማ ዘመን እንዲህ ለማኅበራዊ ለውጥ ያለሙ ግጥሞችን ማቅረብ እንደ ትልቅ አብዮት ሊቆጠር የሚገባው ነው።

በዘመነ ገብረእግዚአብሔር ያገራችን ሰው ስለጠፈር ያለው ግንዛቤ እጅግ ዘልማዳዊ ነበር። ከምኒልክ ፈረንጅ ሎሌዎች አንዱ የነበረው ሙሴ ሞንዶ የዘመኑን የእንጦጦ ካህናት ምድር ትዞራለች የሚለውን ሳይንሳዊ ሀቅ ሊያስረዳቸው ሲሞክር ሊቀበሉት አልፈለጉም። አንድ ቀን፤ በጊዜው ስመጥር ከነበሩት ሊቃውንት አንዱ የሆኑትን አለቃ ለምለምን ሊጠይቃቸው ወሰነ።

"ለምለም"

"አቤት"

"አንተም ይህ ዓለም አይዞርም ትላለህ? ምድር አትዞርም ትላለህ?" አላቸው ተቆጡ።





"እንዲህ ያለው ምስጢር እንዲህ ባለ ተርታ ቀን ይጠየቃል?" ብለው መለሱለት።

"ምንድነው?"

"ጠጅ ወርዶ! አረቄ ወርዶ! እንዲህ ያለ ምግብ እንዲህ ያለ መጠጥ ተዘጋጅቶ ነው እንጂ!" አሉ።

"ተወው አጥፍቻለሁ።"

ሙሴ ሜንዶ የሊቁን ጥያቄ ተቀብሎ ግብዣውን ያሰናዳና አለቃን ይጠራቻዋል። ሁለቱ ሰዎች አረቄ ሲቀመቅሙ ካመሹ በኋላ፤ ሙሴ ሞንዶ በአልኮሉ ተረትቶ መንቀጥቀጥ ይጀመራል። ቀጥሎ ምን እንደተከሰተ አለቃ ለማ ሲተርኩልን፤

"ሙሴ ሜንዶን" አሉት አለቃ ለምለም።

"አ-አቤት" አለ።

"የኔ ሀገር ምድር ይሄው አሁን ዞረች።"

እስቃለሁ ሲል ወንበሩ ተገለበጠና እሱ በውስጥ ወንበሩ በላይ[20]

አለቃ ለምለም ለሙሴ ሜንዶ ያስተላለፉት መልእክት ሲጨመቅ "ካልዞረብህ በቀር ምድር ልትዞር አትችልም" የሚል ነው። ምድርን ሚያዞራት የተፈጥሮ ሕግ ሳይሆን ጌሾ ነው። በጊዜው አግዜር፤ "ሰማይን ያለ ባላ ምድርን ያለ ካስማ" አቁሟል፤ የሚለውን እምነት የሚገንድ ሐሳብ አንስቶ እንደ ሙሴ ሞንዶ በሳቅ በጨዋታ የሚሸኝ ብዙ እድለኛ ሰው አልነበረም።

ገብረእግዚአብሔር ጊላማርያም ሀረር ውስጥ ባደባባይ ምድር ትዞራለች ብሎ ሲያስተምር ስለተደረሰበት ተከሰሰ። ዋናው ከሳሽ የራስ መኮንን ንስሀ አባት የነበሩት ሞክሼው አለቃ ገብረእግዚአብሔር መሆናቸው ተወስቷል።

[20]መጽሀፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ገጽ185።





የሚገርመው፤ በአውሮፓዊ ዝንባሌአቸው የሚታወቁት ራስ መኮንን ይህንን ከስ ተቀብለው ገብረእግዚአብሔር በግር ብረት እንዲታሰር መፍረዳቸው ነው። ተቀብለው ገብረእግዚአብሔር በግር ብረት እንዲታሰር መፍረዳቸው ነው። ሜረብ የተባለው የምኒልክ ሀኪም ገብረእግዚአብሔር ለሳይንስ የከፈለውን መስዋእትነት ጥንታዊው የግሪክ ፈላስፋ አናክሳጎረስ ከደረሰበት እድል ጋር አመሳስሎታል።

ገብረእግዚአብሔር ጊላማርያም በ፲፱፻ አርፏል።

# ገመና ገላጭ

"ቤቴ
ገመና ከታቼ
ገመና መከተቱ ምንድነው ትርጉሙ
ወደ ጓዳ ገብቶ ዱቄትስ ቢቅሙ።"
(አዝማሪት ጣዲቄ)

*ገመና የሚለው ቃል ከሳቴ ብርሃን መዝገበቃላት ሲፈታው፣"መልካም ሆነ ክፉ ነገር ወይም ትዳር፣በቤት ውስጥ መሠወር ነውር ኃጢአት የማይገለጥበት" ይለዋል። ጤነኛ የሆነ ግለሰብ ሁሉ የቤቱን ጉድ አደባባይ እንዳይወጣበት ይታገላል። ገመናው ቤቱ ውስጥ ተሰውሮ እንዲቀር ይፈልጋል። ጉልበተኛና ገልቱ የሆነ ጎረቤቱ ገመናውን በግድ እንዳይገልጥበት የሚከላከልለት ኃይል ይፈልጋል። ጨዋ ዜጎች የራሳቸውን ገመና ማስደፈር እንደማይፈልጉ ሁሉ*





የሌላውንም አይደፍሩም። በዚህ ጉዳይ ምሳሌ ሆነው የሚጠቀሱት የብዙ ነገር ተምሳሌቶች የሆኑት ጥንታዊ ግሪኮች ናቸው።

ባንድ ወቅት፣ ግሪኮችና ፋርሶች ጦር ገጥመው ግሪኮች አሸነፉ። በድል መባቻ፣ ግሪኮች በተሸናፊዎች ድንኳን ውስጥ ብዙ ቁሳቁስ አገኙ። ከምርኮዎች መካከል ተሸንፎ የሸሸው የፋርሡ ንጉሥ ለፍቅረኛው የጻፈላት የፍቅር ደብዳቤ አንዱ ነበር። ግሪኮቹ ምንም ጠላት ቢሆን የተሸናፊውን የግል ገመና ሊገልጡበት አልፈለጉም።

ደብዳቤውን ሳይከፍቱ መልሰው ላኩለት። በዚህ ጨዋ ተግባራቸው ምክንያት ግሪኮች በሰለጠነው ማኅበረሰብ ዘንድ ይሞገሳሉ፤ ይመሰገናሉ።

የጤነኛ መንግሥት አንድ ተግባር፣ የዜጎቹን ገመና ካስገድዶ ደፋሪ መከላከል ነው። የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት የግለሰቦችን ገመና እንደማይደፍር እና እንደማያስደፍር በሚከተለው መልክ ቃል ገብቶ ነበር።

"...ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ፣ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት መኖርያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ሰውነቱና ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅን መብት ያካትታል።

"ማንኛውም፣ ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፋቸው በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች እንዲሁም በቴሌኮምኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም።"

ይህ የሕገመንግሥት አንቀጽ ስልጡን ሐሳብ ይዟል። ከሰው ልጆች ሰብአዊ ክብር ጋርም ይጣጣማል።

ይሁን እንጂ ከአንባገነን መሪ ፍላጎት ጋር አብሮ ሊሄድ አይችልም። አምባገነን ጌቶች በዜጎቻቸው ልብ ውስጥ የሚጉላላውን ሐሳብ ካላወቁ እንቅልፍ አይወስዳቸውም። ስለዚህ ዜጎቻቸውን በመሰለል ይጠመዳሉ። አንድ ስሙ ያልታወቀ ጸሐፊ በዐጼ ቴዎድሮስ ዜና መዋእል ውስጥ ትቶልን የሄደው ትረካ አሪፍ ምሳሌ ይወጣዋል።





ልቀንጭበው፣

"ዐጼ ቴዎድሮስ አንድ ቀን አንድ የሚያምኑትን ዘበኛ ይዘው፣ አልባሌ መስለው... ከጨለመ በኋላ በሠፈሩ ይዞሩ ጀመር። በየጎጆው እየተጠጉ ያደምጡ ነበር። እኩሉ ያልተኛ እኩሉም ተኝቶ። ከዝያ ወድያ ካንድ ወታደር ጎጆ ተጠግተው ቢያደምጡ ባልና ምሽት በግብረ ሥጋ ሲጣሉ ሰሙ። ወንዱ ይለምናል። ሴቲቱ አይሆንም ትላለች። ከዝያ ወድያ ወንድየው፤'በማርያም በሥላሴ' እያለ ቢለምን 'በጻድቃን በቅዱሳን' እያለ ቢቀባጥር እምቢ አለችውና፤

'በይ በቴዎድሮስ ሞት እንድትሰጭኝ' አላት። እሷም

'ቴዎድሮስማ ከሚሞት፣ ጎንደር አይታረስም' አለችና ሰጠችው።

"ንጉሡ ይህንን ከሰሙ በኋላ እየሳቁ ወደ አዳራሻቸው ገቡና ያን አብሮአቸው የነበረ ዘበኛ ያችን ጎጆ እንዳታሳስትህ ብለውት ነበርና በነጋታው ያንን ዘበኛ ባልና ምሽቱን ጠርተህ አምጣቸው ብለው ሰደዱት።

"እነሱም 'ምን ተገኘብን ይሆን?' ... ብለው እየተንዘፈዘፉ፣ እየተንቀጠቀጡ መጡና ከጃንሆይ ፊት ቆሙ። ንጉሡም 'እንዴት አደራችሁ' አሏቸው። እነዝያም እየተብረጀረጁ ሳይሰሙ ባጠገባቸው የቆመ ቢነግራቸው በግንባራቸው ተደፍተው እጅ ነስተው ቆሙ። ቀጥለው ንጉሡ

'ትላንት ማታ በምኝታ ጊዜ ከቤታችሁ ሆናችሁ ምንና ምን ብላችሁ ተናገራችሁ?' ብለው ጠየቋቸው።

'ጃንሆይ የተናገርነው የለም። ጠላት ነገር ሠርቶብን እንደሆነም ያጋጥሙኝ ድኻ ወታደር ባርያዎ ነኝ።' እያለ ይወላፍት ጀመር።

'ከምኝታችሁ ላይ ጥቂት የተናገራችሁት ነገር እንዳለ አስበህ ንገረኝ አይዞህ' አሉት።

እሱም ሰውነቱን አጠናከረና አስቦ ያንን ምሽቱ ያደረገችውን ነገር ነገራቸው። ንጉሡም ሳቁ። ሴቲቱም አፈረች።" (ስረዞች በጸሐፊው የተጨመሩ)





ይህ ትረካ ሐቅ ይሁን ልቦለድ ማረጋገጥ አልቻልሁም። እውነተኛ ገጠመኝም ይሁን ተረት በአምባገነን መንግሥትና በዜጎች ገመና መካከል ያለውን ግኑኝነት በደንብ ያሳያል ብየ ስላሰብኩ ጠቅሸዋለሁ። ይህንን ትረካ ደጋግሜ ባነበብኩት ቁጥር የዘመናዊ ሁለገብ አፈና (totalitarian) አገዛዝ ትንቢት ይመስለኛል። ትንቢቱ የተፈጸመው የጸረ-ሽብር ሕግ ተብሎ በሚታወቀው ጸረ-ጋዜጠኛ ሕግ ውስጥ ነው። ለናሙና የሚከተለውን አንቀጽ እንይ። አንቀጹ የጸረ-ሽብር ግብረኀይሉ አባላት የሚከተሉት ስልጣኖች እንዳሏቸው ይገልጻል።

*ሀ) በሽብርተኝነት ወንጀል የተጠረጠረን ሰው የስልክ፣ የፋክስ፣ የሬድዮ፣ የኢንተርኔት፣የኤሌክትኒክስ፣ የፖስታና የመሳሰሉ ግንኙነቶችን ለመጥለፍ ወይም ለመከታተል*

*ለ) ጠለፋውን ለማስፈጸም ወደ ማናቸውም ቤት ውስጥ በምስጢር መግባት ወይም*

*ሐ) ይህንኑ ለመፈጸም የማያስችሉ መሳሪያዎችን የማስቀመጥ ወይም ለማንሳት ይችላል።*

መጀመርያ፣ ይህ ሥልጣን፣ የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ሕገመንግሥት አፈር ድሜ ያስበላል። ስለዚህ የሕገወጦች ሕግ ነው።

ከላይ በጠቀስኩት ዜና መዋእል ውስጥ የምናገኘው ቴዎድሮስ አግዜር ስላልሆነ በየምኝታ ቤቱ ግድግዳ ላይ እየተለጠፈ የዜጎችን ልብ ሐሳብ ሁሉ የሚቆጣጠርበት ከሂል አልነበረውም። የዛሬ ዘመን መንግሥት ይህን ሁሉ ማድረግ የሚያስችለው ቴክኖሎጂ ታጥቋል። በተቃዋሚ ቤት ውስጥ "በምስጢር በመግባት" የስለላ ሶፍትዌሮችን፣ ረቂቅ ካሜራዎችን የስልክ መጥለፊያዎችን "ማስቀመጥ ወይም ማንሳት ይችላል"።

ይህ ችሎታ፤ መንግሥት እንደ እግዜር ሁሉን የሚያውቅ በሁሉም ቦታ የሚገኝ ድርጎታል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ፣ "ማንኛውም ሰው፣ የግል ሕይወቱ፣ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው" የሚለው የሕገመንግሥቱ ቃል ተአማኒነት የጎደለው ልቦለድ ይሆናል።

ልበለድ ስል ፍቅር እስከመቃብር ውስጥ ያሉት ወይዘሮ ውድነሽ በጣሙ ትዝ አሉኝ።

ትዝ ይላችሁ እንደሆነ፣ ውድነሽ በጣሙ፣ ፍቅር እስከመቃብር የተባለው ያቶ ሐዲስ ልበለድ ገጸባሕርይ ናቸው። እኒህ ሴት ቤታቸው ውስጥ ሉብታቸው ሆነው፣ ከብ የፊት መስታወታቸውን ፊታቸው ላይ ደቅነው ከራሳቸው ጋር የሚያደርጉትን ጭውውት ደራሲው በዚህ መንገድ ይተርከዋል።

"እንዲት ፍሬ ልጅ" አሉ፣ "እንዲት ፍሬ ልጅ፣ ሞት የምታስንቂ ፣የምታምሪ እንዲት ፍሬ ልጅ" አሉ እመስታወቱ ውስጥ ያለችውን ፊት እንደሚስሙ ሁሉ ከንፈራቸውን ወደፊት ሙጥሙጥ አድርገው እስዋም እንዲሁ አደረገች። ከዚያ እየሳቁ ወደ ኋላ ራቅ ሲሉ እስዋም እየሳቀች ወደ ኋላ ራቅ አለች።

"ወይ ጉድ! አሁን የማደርገውን ሁሉ ሰው የሚያይ ቢሆን ኖሮ ምን ይለኝ ነበር! "ወይ ጉድ! አሁን የማደርገውን ሁሉ ሰው የሚያይ ቢሆን ኖሮ ምን ይለኝ ነበር! የብቻ መኖር አንድ ጥቅሙ የሠሩትን ሠርቶ አብዳለች ትታሠር እባል ነበር! የብቻ መኖር አንድ ጥቅሙ የሠሩትን ሠርቶ ያልሠሩ መስሎ ለመታየት ማስቻሉ ነው። ለካ ሰውን እብድ የሚያሰኘው እብድ የሚያደርገውን ማድረግ አይደለም፣ እብድ የሚያደርገውን ሲያደርጉ መታየት ነው"

ያኔ ወይዘሮ ወድነሽ፣ ቤት "ገመና ከታች" በነበረበት ዘመን የኖሩ ናቸው። ያኔ "የሠሩትን ሠርቶ ያልሠሩ መስሎ ለመታየት" በርና መስኮትን መዝጋት ፣ግፋ ቢል በግድግዳህ ሥር የሚያርጮልቅ ሰው አለመኖሩን ማረጋገጥ ብቻ በቂ ነበር።

ለራሳቸው ለማስቀረት የዘመናቸው ውድነሽ በጣሙ ለራሳቸው የሚያደርጉትን ሁኔታ ይፈቅድላቸው ነበር!! ውድነሽ በጣሙ፣ ጃሮ ጠቢ የጸረ ሽብር ሕጉን ጠቅሶ፣ "ቤት ውስጥ በምስጢር መግባት" በሚችልበት በዚህ ዘመን ቢኖሩ ኖሮ በልበሙሉነት "ወይ ጉድ ! አሁን የማደርገውን ሁሉ ሰው የሚያይ ቢሆን ኖሮ ምን ይለኝ ነበር!" የሚል ቃል እንደበታቸው ማውጣት ይደፍሩ ነበር?! "ብቻ መኖር" የሚባለው ነገር በራሱ ከውድነሽ በጣሙ ጊዜ አይመስለኝም። ዛሬ ቤትህ ውስጥ በምስጢር የገባው ሰውየ አብሮህ የቀረ ብርቅ እድል ነው። እልጋህ ሥር መቅረጸ እየኖረ "የብቻ መኖር ጥቅሙ" ማለት ዘበት ነው።





ድምጽ፣ ግድግዳህ ላይ የማያንቀላፋ የስውር ካሜራ ዐይን ተለጥፎልሀል። አሁን የምታደርገውን ሁሉ ያያል። ገመና ከታች የነበረው ቤትህ ወደ ገመና ማጥመጃነት ተቀይሯል። ቤት ውስጥ መኖር ማለት ስቱድዮ ውስጥ መኖር ማለት ሆኗል።

የቅኝት ኑሮ!

ሰዎች ቤታቸውን በዚህ መንገድ ከተደፈረባቸው በኋላ ሰው ይሆናሉ? ክብት አይሆኑም! በቁማቸው ሞተዋል። ማሰብነታቸው ጥሏቸው ይሞታል። ክብት ሁኑ ማለት ነው። ክብት ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ሲተኛ ሲሳረር ያለ መጋረጃ በእረኛ ተመልካች ፊት ነው። የዜጎቿ ገመና የማይጠበቅባት ሀገር ውስጥ መኖር ግዙፍ በረት ውስጥ ከመኖር በምን ይለያል ?

የዜጎች ሕይወት ርካሽ ቀልድ ገመናን አስገድዶ በሚደፍር መንግሥት ፊት፣ የዜጎች ሕይወት ርካሽ ቀልድ ነው።

ንጉሡ ምኝታ ቤት ግድግዳ ላይ መግቢያው ላይ በጠቀስኩት ትረካ ውስጥ፣ ንጉሡ ምኝታ ቤት ግድግዳ ላይ ተለጥፈው የባልና ሚስቱን የግብረሥጋ ጭውውት ሲሰሙ ከቆዩ በኋላ ሚስት ስትረታ ሰምተው ሄዱ። ዝም ብለው ግን አልሄዱም። ያው "እየሳቁ ሄዱ"

በማግስቱ ባልና ሚስቱን አስጠርተው፣ ማታ የተባባሉትን እንዲነግሯቸው ካናዘዙዋቸው በሁዋላም፣ "ንጉሡ ሳቁ፣ ሴቲቱም አፈረች"

ምን ዐይነት ሳቅ ነው? የማዋረድ ሳቅ ነው። እሊቃ ጉብረሀና እንሥራ ኩብዷት ዳገት ስትወጣ በምትፈሳ ሴት የሚስቁት ዐይነት አሽማቃቂ ሳቅ። ጸረ-ሽብር ህጉ ባጎናጸፈው ገደብ የለሽ ሥልጣን ያለገደብ የሚባልገው የደህንነት ሹም፣ "በምስጢር ቤታችን ውስጥ ገብቶ ከመስታወታችን ፊት ቆመን ስናወራ፣ ጭገራችንን ስንላጭ፣ በሚስታችን ገላ ላይ ተከምረን ስንወራጭ እያየ የሚስቀው ሳቅ። ደሞ ይሄን ጉድ ይዘው፣ ባደባባይ ጭምጭ መስለው ይፎልላሉ እያለ ፍርፍር ብሎ የሚስቀው ዐይነት ሳቅ።





ጂም ኬሪ የሚጫወትበት ዘትሩመን ሾው የተባለ አሪፍ ፊልም ትዝ ይለኛል። በፊልሙ ውስጥ ያለው ትሩማን ከማህጸን ጀምሮ እስከጎልማሳነቱ በካሜራ ዐይን ውስጥ የሚኖር ገጸባሕርይ ነው። የሚኖርበት ከተማ፣ የሚያድርበት ቤት፣ የእለት እንጀራውን የሚያገኝበት መሥሪያቤት ሁሉ በዳይሬክተሩ የተገነባ ነው። ሚስቱና ጓደኞቹ ሳይቀር ስውር ቅጥረኛ ተዋናዮች ናቸው። የእለት ተእለት ሕይወቱ በምስጢራዊ ካሜራዎች እየተቀዳ ለዓለም እንደሚተላለፍ ምስኪን ትሩማን አያውቅም። ሕይወቱ ያለ እሱ እውቅና ለሕዝብ የሚቀርብ ሪያሊቲ ሾው መሆኑን መንቃት ሲጀምር ይሸበራል። ከዚያ የጉድ ዓለም ለመውጣት ትግል ይጀምራል።

ትሩማንን በግዙፍ ሰው ሠራሽ ዓለም ውስጥ አስቀምጦ፣ ገመናውን እየዘከዘከ የሚጫወትበት ዳይሬክተር ክሪስቶፈር ይባላል። የሚገርመው ክሪስቶፈር የግል ሕይወቱን ለጋዜጠኞች አሳልፎ ላለመስጠት እጅግ ጥንቁቅ መሆኑ ነው።

ጌቶች የዜጎቻቸውን ገመና አስገድደው የሚደፍሩትን ያክል የራሳቸውን ገመና ግን እንደ ክሪስቶፈር በመከላከል የታወቁ ናቸው። ጋዜጠኛ ዮናስ በላይ አዘጋጅቶ ባሳተመው፣ የቃለ-መጠይቅ መድብል ውስጥ ለቀድሞዋ ቀዳማዊት እመቤት ለአዜብ መስፍን የሚከተለውን ጥያቄ አቅርቦላቸው ነበር።

ጥያቄ-(መለስን) በሚጽፉቸው ጽሁፎች ነበር የወደድሽው?

መልስ- አሁን ወደ እዛ አልገባም።

ዮናስ በቃለመጠይቁ የግርጌ ማስታወሻ ላይ፣ ቀዳማዊት እመቤትን ስለትዳሯ ሊጠይቃት አቅዶ እንዳልተሳካለት ገልጾ፣ "ከትንሽ መረጃ በቀር የምታሳልፍ አልነበረችም" ይላል። ጋዜጠኛው ያገኛት፣ "ትንሽ መረጃም" እንዳትታተም ማሳሰቢያ እንደተላለፈለት ያስታውሳል። ለዚህም ምክንያቱ አቶ መለስ ባለቤታቸው፣ "ስለግል ሕይወታቸው" መረጃ የሚሰጥ ቃለመጠይቅ በጋዜጣ ላይ እንዳይወጣ መፈለጋቸው እንደሆነ ጠቅሷል።

አቶ መለስ ዜናዊ የትዳራቸው ገመና አደባባይ እንዳይወጣ መከላከላቸው ሰብአዊ መብታቸው መሆኑ አያከራክርም። ያም ሆኖ፣ ራሳቸው በዋናነት





ባረቀቁት ጸረ- ተቃዋሚ ሕግ፣ አማካኝነት የሕዝብ ቀሚስ እንዲገለብ መፍረዳቸው የታሪክ ምጸት ነው። ከጸጉሩ እስከ እግሩ ጥፍር ተከናንቦ፣ የጎረቤቱን ምኝታ ቤት አጮልቆ የሚያይ ሰውየ ምስል አይታያችሁም?

አንዳንዴ፣ መንግሥት ዐመሉን ወደ ሕብረተሰብ ያጋባል? እላለሁ፣ ወይስ በተገላቢጦሽ ነው ትክክል። መንግሥት ዐመሉን የቀዳው ከወጣበት ማኅበረሰብ ውስጥ ነው? ያከራክራል። ገዥና ተገዥ ተመሳሳይ ዐመል መጋራታቸው ግን አያጠያይቅም።

ልክ እንደ መንግሥት፣ የግለሰቦችን ገመና የሚደፍሩ ዜጎችን በየቦታው እናያለን። የመንግሥትን ያህል እንኳ ባይሆን፣ እቅመቢሶችን እጅ መጠምዘዝ የሚያስችላቸው አቅም አያጡም። ጉልበታቸው ሚድያ ሊሆን ይችላል። በዘመናችን ብዙ አድማጭ ያለው የሬድዮ ፕሮግራም፣ "ውስጥ ዐዋቂ" ይሰኛል። በዘመናችን እጅግ ተወዳጅ የነበረው የቲቪ ተከታታይ ድራማ "ገመና " ይባላል። የቀጣሪዎቿን የቤት ጉድ አደባባይ የምታወጣ ገረድ መሳይ ሴት ታሪክ ነው። ይች ሴት ገመና ማውጣቷን እንደ እንደ ችሎታ እንጂ እንደወንጀል ተቆጥሮባት ስትጠየቅ ወይም ሴራዋ እንደ ነውር ታይቶባት ስትነቀፍ አላየንም፣ አልሰማንም፣ አላነበብንም። ሠራተኛዋ ወይም በሠራተኛ ጭንብል ወደ ሰው ቤት ገብቶ የቀጣሪዎችን ጉድ መዘክዘክ የማኅበረሰብን ህልውና የሚያፈርስ ነውር መሆኑን አልገባንም? ወይም ደንታ አልሰጠንም?

በሸገር ሬድዮ ጣቢያ ማለዳ ማለዳ የሚተላለፍ አንድ ፕሮግራም ላይ ጋዜጠኛው አድማጮቹ የደበቁትን ምስጢር እንዲናዘዙለት ይማጸናል። "ምስጢር ነው የምፈልገው። ያጭበረበራችሁ በፍቅረኛችሁ ላይ የሄዳችሁ ንገሩኝ። ምስጢር ከመናገር የሚገኘውን እረፍት ታገኛላችሁ" ይላል። ጋዜጠኛው ነውር የመስማት ፍቅር ከመነሁለሉ የተነሣ የምሠራው ሥራ የግለሰቦችን ሕይወት አደጋ ላይ ሊጥልኮ ይችላል የሚል ሥጋት እንኳ አልደረሰበትም። ግለሰቦቹ ለቅርብ ወዳጃቸው ወይም ለንስሃ አባታቸው መንገር ሲችሉ አደባባይ ላይ ገመናቸውን የሚያሰጡበት ምክንያት እንደሌለ አልተገለጠለትም።

ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ የታተሙት ዝነኛ መጽሐፍት፣ "ገመና" ወይም "ጉድ፣ ምስጢር" የሚዘከዝኩ ናቸው። የወንዶች ገመና፣ የሴቶች ገመና፣ የእኛ ሰው ገመና፣ የንጉሡ ገመና፣ የቺቺኒያ ምስጢር ወዘተ...

በደርግ ጊዜ የደራሲዎችና የጋዜጠኞች ተመራጭ ጭብጥ፣ ውትድርና ሲሆን በዘመነ ኢህአዴግ ደግሞ ሽርሙጥና ነው። የዚህ ምክንያት ሽርሙጥና ከሌላው ዘመን በኢህአዴግ ጊዜ የበለጠ ስለበረከተ አይደለም። የዛሬ ዘመን ሰው፣ በዘመቻ ጊዜ እንኳ የጭንገረዶቻቸውን አስከትለው ከሚዘምቱት የድሮ ሰዎች የበለጠ አለሌ ስለሆነም አይመስለኝም። የግለሰቦች የወሲብ ገመና ብቸኛው ለእሥር የማይዳርግ ርእስ ጉዳይ ስለሆነ ነው። የመንግሥት ቁጥጥር የማይደርስበት ብቸኛው የደራሲው ክልል መሸታ ቤት መሆኑን ማን ይክዳል?

በዘመናችን እያሌ የሴተኛ አዳሪ ዜና መዋእሎች እየታተሙ ቢወጡም ስብሀት ገብረእግዚአብሔር ከጻፈው፣ "ሌቱም አይነጋልኝ" የሚመጣጠን፣ ስለሰው ሕይወት አዲስ ዕውቀት የሚጨምርልን ድርሰት ወይም የምርምር ሥራ የመጣ አልመሰለኝም። እናቶች ከቡናቸው ጋር አብረው የሚያከትሙትን ሐሜት በመጽሐፍ መልክ ጠርዞ ማውጣት ሙያ ተደርጎ ተወስዷል። ጋዜጠኛው፣ አንድ ታዋቂ የእግር ኳስ ተጫዋች መርጦ አንባቢው እንዲለየው የሚያስችሉ ምልክቶችንና ፍንጮችን ካላበሰው በኋላ፣ እንዴት ያለ ሴት አውል፣ እንዴት ያለ ጠጭ እንደሆን ይተርክልናል። ከሴቶች ጋር የሚዝናናበትን አልቤርጎ ስም መጥቀስ ሳይበቃው የሚወደውን የወሲብ ስልት ሁሉ ይነግረናል። "ሴቷን የአልጋውን ጫፍና ወንበር አስይዞ ግድግዳ ላይ ለጥፎ ዶጊ ስታይል መጨመር ይወዳል" እያለ ያማልናል። ርግጥ ነው፣ ያንድን ታዋቂ ኳስ ተጫዋች ያጨዋወት ስልት መረዳትና መተንተን ከባድ ነው። ቢያንስ፣ እስተዋይነትንና ዐዋቂነትን ይጠይቃል። ያንድን ኳስ ተጫዋች የወሲብ ባሕርይ ለመዘገብ ግን ባለጌ መሆን ብቻ በቂ ነው። አንድ ጋዜጠኛ ሙያውን ግለሰቦችን ለማዋረጃነት ሲያውለው ለጋዜጠኝነትም ሆነ ለሰብአዊነት ስድብ ነው።





አንድ ሰው የሌላውን ግለሰብ ገመና ለመድፈር ሲሞክር ራሱን እየገለበ እንደሆነ አይረዳም። ሰዎች በማጀታቸው ተሸሽገው፣ "ዱቄት መቃማቸው" እንዲሁም ያሻቸውን ዐይነት ግብረሥጋ ማድረጋቸው የራሳቸው ጉዳይ ነው። ለፍርድ አይመችም። በጎረቤት ምኝታ ቤት ግድግዳ ላይ ሸንቁር በስቶ ግብረሥጋን መስለል ግን ከወራዳነት ውጭ ሌላ ምን ስም ሊሰጠው ይችላል??





# ሴቶች በዋሉበት[30]

እንደ እምነታችን እና እንደባህላችን ሁሉ ቋንቋችንም ለወንድ ያዳላል። ወንድ የሚለው ቃል ቃጭል ማንጠልጠልን ብቻ የሚገልጽ ቃል አይደለም። በተለመደው ዐማርኛ፣ አንድ ሰው ወንድ ነው ሲባል ጀግና ነው፤ ልበሙሉ ነው ማለት ነው። ከእለታት አንድ ቀን ወደ ጦርሜዳ ለመዝመት የተዘጋጀ ካህን፣

"ወግድልኝ ዜማ ፤ወግድልኝ ቅኔ
ወንዶች በዋሉበት፤ መዋሌ ነው እኔ"

ብሎ ተቀኝቷል። በቅኔው ውስጥ ወንዶች ሲል ጀግኖች ማለቱ ነው። ወንድ የሚለው ቃል ጀግና ለሚለው አቻ ከሆነ በተቃራኒው ሴት ማለት ፈሪ ማለት እንደሆነ መገመት አያቅትም። አንዲት ሞት የምትንቅ ሴት በጉልህ ብቅ ካለች ወንድ ናት ትባላለች፤ ከሴት ባሕርይዋ አፈንግጣለች ማለት ነው። ይህ ትልቅ

[30] ማስታወሻነቱ፤ ለድምጻዊት ንግሥት አበበ።





ፍርደ-ገምድልነት መሆኑን ለመረዳት የሚፈልግ ታሪክን ወደ ኋላ ዞር ብሎ ይመልከት። ወንዶች ለብቻቸው የተሳተፉበት ጦርሜዳ መኖሩ ያጠራጥራል። ሴቶች ባዋላጅነት ከነበራቸው ሚና የማይተናነስ ሚና በጦር ሜዳ ተጫውተዋል። እናቶቻችን በጦር ወቅት፣ መሣርያ ያቀርቡ ነበር። ምግብ ያቀርቡ ነበር። ሐሳብ ያቀርቡ ነበር። ልብ ያቀርቡ ነበር። ደስታ ያቀርቡ ነበር። ምኑ ቅጡ።

## 1. መሣርያ

ዘመናዊ ጠመንጃ ከመምጣቱ በፊት ሴቶች፣ ከሰልና ጨው ወቅጠው፣ ባሩድ ያሰናዱ እንደነበር ያውቃሉ? ባሩዱ ዳሄራ ይባላል።

"ሴቶች ተሰብሰቡ እንውቀጥ ዳሄራ
ከርክር አይቀርም ከራስ አዳል ጋራ" እንዲሉ እናቶች።

የመጀመርያው የጦር መሣርያ ፋብሪካ የእናቶቻችን፣ ሙቀጫ መሆኑን ልብ እንበል።

በነገራችን ላይ ይሄን ግጥም ሴቶች የዘፈኑት፣ ንጉሥ ምኒልክ ራስ አዳል ጋራ ጦርነት ሊያደርጉ ሲሰናዱ ነው።

ግጥሙ የዋዛ ግጥም አይደለም። የወቅቱን የፖለቲካ መስመር በስንኝ የሚተነብይ ነው። እንግዲህ ሴቶች ባንድ ሙቀጫ ዙርያ፣ ማኅበረሰቡን ኬሚስት፣ ገጣሚና የፖለቲካ ተንታኝ ሆነው ማገልገላቸውን ልብ እንበል።

## 2. ምግብ

የድሮ ወታደር እንደ እንደቅርብ ጊዜው ኮቾሮውን፣ በላስቲኩ ውሃውን በኮዳው ይዞ የሚዘምት አልነበረም። ምግቡንና መጠጡን ከዚያው ከጦርሜዳ ነበር የሚያገኘው። በዚህ የተነሣ ሴቶች፣ ማጀታቸውን ወደ ጦርሜዳ ይዘውት መዝመት ነበረባቸው። ብዙ ጊዜ ስለ ጦርሜዳ ስናስብ ቶሎ የሚመጣልን ቶኪራ፣ ሽለላ፣ ሁልጊዜ የሚያባርር አርበኛ፣ ሁልጊዜ የሚወድቅ ጠላት፣ የመድፍ ተኩስ፣ የባሩድ ሽታ ወዘተ ነው። በጦር ሜዳ እንጀራ ሲጋገር፣ ወጥ ሲሠራ ፣ ጠጅ ሲጣል ማሰብ ለአእምሮ የተለመደ አይደለም። ግና ከባሩድ ጭስ በማይተናነስ መጠን የማእድ ቤት ጭስ ታሪክ ሠርቷል።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ እንዲህ ይላል፤

"እንዲህም እየሆነ፣ ዐጼ ምኒልክ ባዳራሹ እቴጌ ጣይቱ በልፍኝ ባለሟሎችዎን ወይዛዝሩን ይዘው ግብሩ አንድ ቀን ሳይጎድል፤ይዘምታሉ። ከዘመቻ ላይ ጠጁ ማሩ አለመጉደሉ፣ ስለምንድነው ያልህ እንደሆነ ይህነን ታሪክ መመልከት ነው። በስድስት ድንኳን እንጀራው ሲጋገር ሲያድር በአራት ደንኳን ወጡ ሲሠራ ሲያድር ጠጁ በቀንድ በኮዳ ደግሞ ሦስት መቶ ስድስት መቶ የሚሆን ገንቦኛ ሲጓዝ ግብሩ ይጎድል ይመስልሀል"

በኔ ግምት፣ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴን ያክል ለሴቶችና ለሴትኛ አስተያየት ቦታ የሰጠ ጥንታዊ ታሪክ ጸሐፊ ያለ አይመስለኝም። ባብዛኛው የኢትዮጵያ ታሪክ ያዳራሽና ያደባባይ ታሪክ ነው። የእልፍኝ (ጓዳ) ታሪክ ከቁጥር አይገባም። ገብረሥላሴ ግን፣ ጦር ሜዳ ዘምቶ፣ መድፉን፣ ነፍጡን እንደሚቆጥር ሁሉ እልፍኝ ገብቶ ምጣዱን እንጀራውን ቆጥሮልናል። አንዳንዴ በማጀቱና በጦርሜዳው መካከል ያለውን ድንበር በዘይቤ ያፈርሰዋል። ለምሳሌ፣ የኢትዮጵያ አርበኞችን የስለነልበና ዝግጅት ሲገልጽ፣ "የሰራዊቱ ልብ እንደ ምጣድ ግሞ ነበር" ይላል። የሰራዊቱን ወኔ ለመግለጽ የተመረጠው የጋለ ብረት አይደለም። እሳተ ገሞራ አይደለም። ወንድ ያስተውለዋል ተብሎ የማይታሰበው፣ "የጋለ ምጣድ" ነው።





የሆነው ሆኖ፣ ሴቶቹ "ግብሩ አንድ ቀን ሳይጎድል" ያን ያህል ጊዜ፣ (ከጥቅምት እስከ የካቲት) ያን የሚያክል መንገድ (ከእንጦጦ እስከ አድዋ) ሰራዊቱን መመገብ መቻል ከባድ መስዋእትነት ነው። ለዚህ መስዋእትነት ከብር ባንስጥ የእናቶቻችን አጽም ወስፌ ሆኖ ይወጋናል።

## 2. ሐሳብ

የብልህ ሴቶች መላ ታሪክ ቀይሯል። ዝነኛው ምሳሌ እቴጌ ጣይቱ በመቀሌ ጦርነት ያቀረበችው የጦር ስልት ነው። እቴጌ ከተለመደው፣ የወንዶች ደካማ ጎን ከሆነውና ወገንን ለዘግናኝ እልቂት ከሚዳረገው እሳትራታዊ የውግያ ልማድ ወጣ ብላ በማሰብ በጣልያኖች አይበገሬ ምሽግ አቅራቢያ ያለው ኩሬ በቁጥጥር ሥር እንዲውል አዘዘች። መቀሌ ላይ ጣልያኖች የተደፈሩት እንደ ንግሥት ሳባ በውሃ ጥም ምክንያት ነው ማለት ይቻላል።

ሴቶች ጦር ሜዳ ላይ መሣርያ ያቀርቡ ነበር፤ ምግብ ያቀርቡ ነበር፤ ሌላ ምን ቀረ? የሚቀረው ልብ ማቅረብ ነው። በጦርነት ውስጥ ሴቶች ለጀግኖች ልብ ያቀርቡ ነበር ብል፣ "አሁንስ በዛ" የሚለኝ ይኖር ይሆናል። ሽንገላ አይደለም ሐቅ ነው።

ዘመናዊ አዋጊ መኮንን ጠላቶቹን ወደ ፊት እንዲሄዱለት ሲፈልግ፣ ከኋላ እየተከተለ ባቀባበለው ሽጉጥ እያስፈራራ ይገፋቸዋል። ሲሸሽ በተገኘ ወታደር ላይ የሞት ፍርድ የሚፈረድበት አጋጣሚም ነበር። በወገን ጥይት ከመሞት በጠላት ጥይት ከመሞት የቱ ይሻልሀል ነው ምርጫው። የጥንቶቹ የጦር ሰዎች ግን ሌላ መንገድ ነበራቸው። ከፍርሀት ይልቅ እፍረት የሚባለውን ስሜት ጀግና ለመፍጠርያ ይጠቀሙበት ነበር። ይህን ለማድረግ ቀላሉ መንገድ ሴቶች ከወንዶች ጀርባ እንዲሰለፉ ማድረግ ነው። ወንዶች ተዋጊ ከሆኑ የውጊያው ደረጃ መዳቢዎች ሴቶች ናቸው። ወታደር፣ በሚስቱ ወይም በእህቱ ወይም በውሽማው እየታየ መሆኑ ሲገባው፣ የቁጠባትን ጉልበት ያወጣታል። ከለገመም ይበረታል።





ዋልተር ፕለውደን የተባለ በዘመነ መሳፍንት ዘመን አገራችንን የጎበኘ ፈረንጅ እንደመዘገበልን፣ የወሎ ኦሮሞ ሴቶች ጦርሜዳ ላይ ከወገን ጦር ጀርባ ይሆኑና፣ ወኔ የሚያነሳሱ ዘፈኖችን ይዘፍናሉ። የጀግንነት ቅኔዎችን ይቀኛሉ። የሚሸሽ ወታደር ሲያዩ ፊቱን ወደ ጠላቶቹ እንዲያዞር ይገስጻሉ። ፕላውደን የተመለከታቸው ሴቶች ማገዘራሽ ወይም አረሆ ይባላሉ። ሁለተኛው ስም አዳራሽ፣ መድረክ ላይ ሳይሆን አረህ ላይ ቆመው ስለሚዘፍኑ የተሰጣቸው ሲያሜ ነው።

ይህ በወሎ ብቻ የተወሰነ አይደለም።

አለቃ ተክለኢየሱስ ከደርቡሽ ጋር በተደረገው ጦርነት የጎጃም ጦር ከተሸነፈና ሽሽት ከጀመረ በኋላ የተከሰተ አንድ ትእይንት ሲተርክ፤

"ያን ቀን ላቀች የምትባል፣ ወረሴከ ጦር አጋጣሚ ስትሸሽ በቅሎዋ ጥሏት ከመንገድ ወደቀች። ያን ጊዜ የንጉሡ ጀግና ተገኝ አባ ጃፌ የሚባል ደርቡሽን ሲፈጅ ውሎ ሦስት ስናድር ማርኮ ግራ ቀኝ አንግቶ በጠገበ ፈረስ ደረሰላት። እርሷም እንዲህ አለች፤

"እኔስ ደከመኝ፤ ተፋሁ አሞት
አዙር ተገኝ፤ በንጉሡ ሞት"

የዚህን ጊዜ ተገኝ አባ ጃፌ ከወደቀችበት ከንዷን ነጥቆ ከፈረሱ ላይ አስፈንጥሮ ታደጋት። ከደርቡሽ ጋራ እየዞረ እየተታኮሰ ስንኳን ርሷን ሌላውን ደካማ እያበረታታ አወጣው" ብሏል።

ጀግናው ሰውየ ወይዘሮ ላቀችን እንጉርጉሮ እስኪሰማ ድረስ በሽሽት ላይ ነበር። ለዚያውም ሦስት የተማረከ ስናድር አንግቶ። የሴትዮዋ እጉርጉሮ ተአምር መፍጠሩን ልብ እንበል። "አዙር ተገኝ" ስትለው የፈረሱን አቅጣጫ አዞረ። ማፈግፈጉ ቀርቶ ማጥቃት ጀመረ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት አሳዳጅ የነበረው መልአከ ሞት አሁን ተሳዳጅ ሆነ። ምናልባት ከጳጳስ ግዝት በላይ፣ ከአዋጊ ማስፈራሪያ በላይ ከሴት እንደበት የሚወጣ፣ "አዙር" የሚል ቃል ኃይል





ነበረው። ሴቶች ጀግናው ልብ ሲከዳው ልብ ሲያቀርቡ እንደኖሩ ታሪክ ጮኮ ብሎ እንዲህ ይመሰክራል፤

በአድዋ የሆነውም እንዲህ ነው፡፡

እቴጌ ጣይቱ ባድዋ ከሴት ሠራዊቷ ጋራ ሆና ጥቁር ጃንጥላ አስይዛ፣ በባዶ እግሯ እየተራመደች ከሠራዊቷ ኋላ ትከተላለች። የሆነ ጊዜ ላይ ሠራዊቱ የጠላት ጦር ተጭኖት እንደመሸሽ ሲል እቴጌ፣ "አይዞህ አንተ ምን ሆነሀል! ድሉ የእኛ ነው በለው" አሉት። ሰውየውም የተናገሩትን ቃልና እቴጌን ባየ ጊዜ ሴት ሲያጠና (ሲያደፋፍር) ወንድ መሸሽ አይሆንለትምና ጸጥ አለ

ወኔ እንደ እጃችን እንደ እግራችን በተፈጥሮ ይዘነው የምንወለደው አይደለም። ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ እንጂ ከነጀግንነቱ ዱብ አይልም። ጀግንነት ማኅበራዊ ግኑኝነት ውጤት ነው።

በዘመነ ምኒልክ ከዘማች አዝማሪዎች መካከል አንጸባራቂ የነበረችው ዛሬ ግን የተረሳችው አዝማሪ ጣድቄ ናት። ጣዲቄ ባድዋ ጦርሜዳ የጀግኖችን ልብ ቆስቁሳለች። በመቀሌ ውጊያ፣ ጣልያኖች ለጊዜ መግደያ እርቅ ሲያስቡ ጣዲቄ ርቁን የይስሙላና የጊዜ መግዣ መሆኑን በመገንዘብ እንዲህ ስትል ትችት አቅርባለች።

"አውድማው ይለቅለቅ፤ በሮችም አይራቁ
ቀድሞም ያልሆነ ነው፤ ውትፍትፍ ነው እርቁ"

አብዛኛው ዘማች ገበሬ ስለሆነ ጣዲቄ ጦርሜዳውን ባውድማ፣ አርበኞችን በበሬ መስላ መግጠሟ ነው። አዝማሪዎች ጀግኖችን ከማወደስ፣ ፈሪዎችን ከመውቀስ አልፈው የንጉሥን ውሳኔ የሚሞግት ሐሳብ እንደሚያቀርቡ ያሳያል።

ባድዋ ድል ዋዜማና ማግስት ከተገጠሙ ግጥሞች መካከል የትኞቹ የእሷ እንደሆኑ ለማወቅ አልተቻለም። ግን ብዙ ቀስቃሽ ግጥሞች ከመግጠሟ የተነሣ ሃኪም ሜረብ የተባለ የፈረንሳይ ጎበኝ ከዝነኛው የስፓርታ የጦር ሜዳ ገጣሚ

ከጦርየስ ጋር ያወዳድራታል። ጣድቁ በአድዋ ጦርነት ላደረገችው አስተዋጽኦ ከምኒልክ እጅ ሽልማትና የወይዘሮነት ማእረግ ተቀዳጅታለች።

(ያገራችን ሰው የባለሙያን የሙያ ፍሬ የሚወደውን ያክል ባለሙያን አይወድም ነበር። ጎራዴን የሚያከብረውን ያክል ጎራዴን ቀጥቅጦ የሚሠራውን አንጣሪ አያከብርም። እንዲሁም፤ ባለፍ ገደም ካልሆነ በቀር ያገራችን የቤተክህነት ጸሐፍት ሥራየ ብለው ያዝማሪን ታሪክ አይጽፉም። ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የሕይወት ታሪክ በሚል መጽሐፉ የቀድሞ ትልልቅ ሰዎችን ታሪክ ሲጽፍ ላመል ያክል ያንድ አዝማሪም ሆነ ሠዓሊ ታሪክ አልጻፈም። ስለዚች ድንቅ አዝማሪ ትንሽ ዘርዘር አድርጎ የጻፈ ሃኪም ሜረብ የተባለው ፈረንሳዊ መንገደኛ ነው)

ሴቶች በጦርነት ውስጥ የተለመደውን ሥጋዊ ደስታ በመስጠትም ያገለግሉ ነበር። ሩካቤና ትግል አብረው አይሄዱም የሚለው የቅርብ ፍልስፍና ነው። ለዋቢነት የህውሐትን የትግል ታሪክ የሚጽፉ ፀሐፊዎች እንደሚነግሩን በትግሉ የመጀመርያ ዓመታት ወሲብ ለትልቅ ቅጣት የሚዳርግ ወንጀል ነበር። እንዲህ ዓይነቱን የዘማች ምናኔ አባቶቻችን አይጋሩትም። ቀደምቶቻችን በዚህ ጉዳይ ላይ ሆደሰፊ ናቸው። ወታደር "አብሬሽ አድሬ ሲነጋ ልሙት" ይል ይመስል፣ በጦር ዋዜማ ካብሮ ዘማች ሚስቱ ጋር ያድራል። የቅርቦቹ ወሲብ የከለከሉት ጉልበት ያዳክማል፤ ትኩረት ይሰርቃል ብለው ሲሆን ይችላል። ለጥንቶቹ ግን ትኩረት የሚሰርቀው ማድረግ ሳይሆን መናፈቅ ነው። ምኒልክ ከሚታወቅባቸው ጥቅሶች አንዱ፣ "ዕመልህን በጉያህ ስንቅህን ባህያህ" የሚል መሆኑን እንርሳ። ሴሎችን እስካልረበሸ ድረስ፣ የግል ጉዳይህ ከዘመቻ አይከለክልህም የሚል ሐሳብ ያዘ ነው።











የወገን ጦር ቀንቶት ድል ከነሣ ሴቶች ስለባ ይሰበስባሉ ድል ከተነሣ ራሳቸው ሰለባ ሆነው ይሰበሰባሉ። በባርነት ይፈነገላሉ። ውበታቸው የድል አድራጊውን ዐይን የሚስብ ከሆነ የጭን ገረድ፣ ጉልበታቸው የድልነሺውን ዐይን የሚማርክ ከሆነ ባርያ ይሆናሉ። ከድል አድራጊ ጀርባ ላሉ ሴቶች፣ "እንኳን እናቱ የወለደችው፣ አማቱ ኮራች የተጋባችው" እየተባለ የተዘፈነውን ያክል በለስ ላልቀናቸው፣ ቀን ለጎደለባቸው ምርኮኛ ሴቶች እንጉርጉሮ የሚበላ እንጉርጉሮ ሲወርድ ኖሯል። ባስበኩት ቁጥር ሆዴን የሚያላውሰውን የገላውዲዮስ ዜና መዋእል ደራሲ እንጉርጉሮ ላካፍል።

"ወለተ ኢትዮጵያስ ትትከደን፣ አዕዳለ ዘማእሰ ወእነዳ
ወትለብስ ሰቀ ከመ ስሌዳ
ወትዕንቅ ጋጋ ህየንተ ሐብለተ ወርቅ ዘውስተ ከሳዳ
ወህየንተ ቤተ-ወይን ወማህሌት ጽጌ እለ ይላሕው ትረሲ ዓውዳ
ወትከዐው ደባለ ዲበ ርእሳ ህየንተ መዓዛ ዕፍረት ወማየ ሬዳ"

ትርጉሙ ፤

"የኢትዮጵያ ልጅ ፤ቁርበት ደርባ
እንደ ስሌዳ ፤ማቅ ተከናንባ
በወርቅ ድሪ ሐብል ፋንታ፤ እንጊቷ ቀንበር ጠልቆላት
የዘፈን ቤቷ ፈርሶ
አደባባይዋ በልቅሶ
የትካዜ ጭጋግ ለብሶ
በሽቶ ማእዛና በጽጌረዳ ፈሳሽ ፋንታ
በገጽዋ ትቢያ ተነስንሶ።"

ጦር ካለ ምርኮ ብቻ ሳይሆን ሞት አለ። ሞት ባለበት አልቃሽ ሴቶች ይኖራሉ። የሴቶች የቀብር ላይ እንጉርጉሮ የተዋጣለት ፍልስፍና ነው። እንዲያውም የኢትዮጵያ ፍልስፍና የተወለደው ከእናቶቻችን ዝቅዝቅ ነጠላ ሳይሆን አይቀርም። ስለ ጥፋት፣ ስለ ሞት ስለ ሕይወት ስለ እምነት የነበራቸውን አስተያየት የምናየው በሙሿቻው ውስጥ ነው። የልቅሶ ግጥሞች ስሜት-መራሽ





ስለሆኑ እንደሸንት ቤት ግድግዳ ጽሑፍ እውነተኛውን የልብ ሐሳብ የሚገልጹ ናቸው። ብዙ ጊዜም ከዘልማዱ አመለካከት ጋር የሚጋጩ ሐሳቦችን የሚያመነጩት አልቃሽ ሴቶች ናቸው።

ለምሳሌ፣ ከቴዎድሮስ ጋር በተደረገ ጦርነት ጦስ የባእታ ማርያም ቤተክርስትያን ስትነድ የተመለከተች አንድ አልቃሽ የሚከተውን እመዳ ያዘለ እንጉርጉሮ አንጎራጉራ ነበር።

"በሰማይ ላይ ሆነህ፤ ስታላግጥ በሰው
እናትህ ነደደች፤ ሐዘኑን ቅመሰው"

አሳቡ አስቂኝ በዛው ልክ በጣም አደገኛ ነው። ፈጣሪን "ቅዱስ" ለፍጥረቱም አዛኝ አድርጎ በሚያምን ማኅበረሰብ ውስጥ እግዜርን እንደ አሲቃ ገብረህና በሰው ጉዳት የሚስቅ አድርጋ ማቅረቧ የድፍረቷን ልክ የሚመሰክር ነው። ሴትዮዋ ፤ "እግዚአብሔር ሰጠ፤እግዚአብሔር ነሣ"፣ እያለ የመጣውን ሁሉ በጅልነትም በለው በጸጋ ተሸከም ከሚኖረው አብዛኛው ሰው የተለየች ናት። ሐሳቧ ከዘልማዱ አመለካከት ጋራ መጋጨቱን የምንረዳው የሚከተለውን አጸፋ ምላሽ ማስከተሉን ስናነብ ነው። ለተለመደው ሐሳብ ወኪል ሆኖ አጸፋውን ያቀረበው ኅሩይ ወልደሥላሴ፣ የተባለው ባለሥልጣን ጸሐፊ ነው። የልቅሶ ዜማ በሚለው መጽሐፉ ይህንን ግጥም ከጠቀሰ በኋላ፣

"ይህች ሴት (ገጣሚዋን ማለቱ ነው) ያለዕውቀት በብስጭትና በሐዘን እንዲህ ብላ ገጠመች እንጂ እግዚአብሔርስ የሰው እጅ ከሠራው ከቤተክርስትያን ይልቅ እርሱ በሠራው በሠው መቃጠል እንዲያዝን የታወቀ ነገር ነው። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል።" ይሉና የቅዱስ ጳውሎስን ጥቅስ ያስከትላሉ።

እዚህ ላይ በማመንና በማመዛዘን መካከል ያለ ግብግብ በግልጥ ይታያል። ለኅሩይ የዕውቀት ምንጭ የተለመደው መጽሐፍ ነው። ሴትዮዋ ግን በራሷ ልብ ውስጥ የፈለቀውን ዕውቀት አዳምጣለች። ኅሩይ፣ የጳውሎስን ልብ ማዳመጥ በቂ ሆኖ አግኝቶታል ። የጳውሎስ ድምጽ የተረጋገጠ ዕውቀት ምንጭ

ሆኖለታል። እናም የአልቃሺቱ ሴት እንጉርጉሮ በመንፈስ ቅዱስ አናጋሪነት ሳይሆን፤ "በበስጭትና በሐዘን" ገፋፊነት የተገኘ በመሆኑ ውድቅ አድርገነታል።

ዐጼ ዮሀንስ አራተኛ፤ ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ጋር ተጣልቶ ጎጃምን በደበደበበት ወቅት ባላገሮች እግዜር በደላቸውን አይቶ እንደሚበቀልላቸው ጠብቀው ነበር። ግን ለጊዜው በንጉሡ ነገሥቱ ላይ የወረደ መብረቅ አልነበረም። አንዲት ተበዳይ ሴት ይህ ጉዳይ የእግዜርን ህልውና እንድትጠራጠር ስላደረጋት እንዲህ ብላ አንጎራጎረች።

"ከሀበሻ ወዲህ፤ ከሀበሻ ወድያ
ሰውንም ገረመው፤ እኔንም ገረመኝ
ዮሀንስ እግዜርን፤ ገድሎታል መሰለኝ።"[3]

"እግዜርን ገድለነዋል" በሚል መርዶው የሚታወቀው ፈላስፋ ፍሬደሪክ ኒቼ ነው። ይህ ሪዛም ጀርመኔ - ሴቶች ከማርገዝና ከመውለድ በቀር የረባ የአእምሮ ፍሬ አያበረክቱም የሚል እምነት ነበረው። እምነቱ የተሳሳተ መሆኑን ለመረዳት፤ እሱ ያነበበውን ያክል ሳታነብ በሦስት ስንኝ መስመር እሱ የደረሰበት ያስተሳሰብ ጥግ ላይ መድረስ የቻለች ይህች ባላገር ሴት ምስክር ናት።

[3] አሲታ ለምለም ፤ያጼ ዮሀንስና ተክለጊዮርጊስ ታሪክ (ያልታተመ)





# የማይድን ናፍቆት

(ለሙቅዲ)

ከጓደኛዬ ከተወልደ በየነ (ተቦርነ) ጋር በቨርጂኒያ ክፍለ ሐገር ውስጥ በሚገኘው፥ "ስካይ ላይን" በተባለው የአበሾች ሠፈር ስንዝናና አምሽተን ማስነባበቻችን ሲደርስ ወጥተን አስፓልት ዳር ታክሲ መጠበቅ ጀመርን።

ከውጭ ያለው ብርድ የሁለታችንንም አንደበት በማይታይ ዝማም ለጎመው።

ቀፋፊው "ዊንተር" እየገባ ስለሆነ አየሩ መላ ሕዋስን ይቆረጥማል። የስደትን ኖሮ መከራ ለመገንዘብ የሚፈልግ ሰው የአውሮፓን ወይም የአሜሪካን ዊንተር መቅመስ አለበት።

ዊንተር የሚለውን እንግሊዝኛ ክረምት በሚለው ዐማርኛ ቃል ያልተረጎምሁት ሆን ብዬ ነው። ምን አገናኛቸው፤ ያዲስአበባ ክረምት ሌላ ነገር ነው፤ የፈረንጆችን ዊንተር ካየሁ በኋላ አዲሳባ ውስጥ ዝናብ ዘንቦ ብዬ ጨለላ ፍሲጋ





የሮጥኩባቸውን ጊዜያት እያሰብኩ ራሴን አጥብቄ ወቀስኩ። ሰው እንዴት ከሚዘንብ መና ሮጦ ያመልጣል? አባቶቻችን ጃንጥላ የሚዘረጉት ከብራቸውን ለማሳየት ሲሉ መሆን አለበት። አለ አይደል ዛሬ "ሐመር መኪና" መንዳት ባለጸጋ እንደሚያስብል ያኔ ድባብ ማዘርጋት የክብር ምልክት ነበር። ጃንጥላ የዝናብ መከላከያ ነበር ቢሉኝ አላምንም። እንዴት ያዲሳባን ዝናብ ትከላከለዋለህ? እንዴት ራስህን ከጠበል ትከላከላለህ?

ዝናባችን ብቻ ሳይሆን በረዷችን በስንት ጣሙ!!

"ዱብ ዱብ ይላል እንደበረዶ
በልጅነቱ በረሀ ለምዶ" ይላል፤ ያገራችን አዝማሪ ያገራችንን አርበኛ ሲያወድስ።

ዱብ ዱብ ማለት የኢትዮጵያ በረዶና የኢትዮጵያ አርበኛ ልዩ ባሕርይ ነው። የፈረንጅ snow ዱብ ማለት የት ያውቃል? ሩጫዋን እንደጨረሰች እፉየ ገላ ወርዶ ይተኛል። በተኛበትም ይቀራል። ቀጣዩ መጥቶ ይተኛበታል። መስኮትህን ከፍተህ ስትመለከት ነጭ የትንኝ መንጋ የመሰለ ነገር፤በሰማይ ላይ አግድም ሲተም ይታያል። ከጥቂት ሰአታት በኋላ ኃያሊቱ ከተማ ከዳር እስከዳር በነጭ ብናኝ ተሞልታ የገጠር ወፍጮ መስላ ትታያለች። መኪናውን ከተቀበረበት የበረዶ ሥር እንደ አርኪዮሎጂስት ቆፍሮ ለማውጣት የሚወድቅ የሚነሣ ስደተኛ እያየሁ አሁን ይሄ ሀገር ነው፣ አሁን ይሄ ኖሮ ነውጣ ያልሁበት ጊዜ ጥቂት አይደለም።

"ትመጫለሽ ብየ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ
የልጅነት ዐይኔ ሟሟ እንደ በረዶ"

የሚል ያገራችን የናፍቆት ዘፈን አለ። መሟሟት የአገራችን በረዶና ያገራችን ዐይን ባሕርይ ነው። የፈረንጅ snow በቀላሉ መቅለጥ አይሆንለትም። የፈረንጅ በረዶ ከመቅለጡ በፊት ብዙ ጉልበትና ብዙ ንብረት ያቀልጣል። የከተማው አስተዳደር በየመንገዱ ላይ የተጋገረውን በረዶ ለማቅለጥ፤ አንድ ካሚዮን ሙሉ





ጨው ይነሰንሳል። በኛ ሀገር ጨው በክረምት፤ የጎመን ማጣፈጫ ሲሆን በፈረንጅ ሀገር የበረዶ ማቅለጫ ነው። ደሞ ስትራመድበት ተልባ ላይ መራመድ ማለት ነው። ጢት እንቅልፍህን ሳትጠግብ ተነሥተህ ተፈጥሮ በረንዳህ ላይ የደፋችውን ነጭ ተልባ ካልጠረግህ ወዮልህ!! ጎረቤትህ በደጅህ ሲያልፍ ተንሸራትቶ ወድቆ ጥርሱን ከለቀመ፤ ኧረ የምን ጥርስ፤ ሳንቲሙን ከለቀመ ፈረደብህ። ያሜሪካ መንግሥት፤ ለጎረቤትህ አምቡላንስ፤ ላንተ የፖሊስ መኪና ይልካል።
ነፋስስ ቢሆን፤ ለካ ስደተኛነት ነፋስንም እንደ እፍላ ፍቅረኛ ያስናፍቃል። የናፍቆት ከፋቱ የሌለ ነገር ፈጥሮ ማሳየቱ ነው። በናፍቆት ዐይን ስታየው፤ የአገራችን ነፋስ ሰላማዊ ነው። ለዘብተኛ ነው። ብብት ላይ የምትነፋው ፈሊት ማለት ነው። ቤት አያፈርስም። የቤትህን ጣርያ በባለቆብ ሚስማር ከገደገድከበት፤ ልብስ ሲያጥብ ኖሮ፤ ጥሮታ የወጣ የመኪና ጎማ ጣል ካደረግህበት ለክረምት በቂ ዝግጅት አድርገሀል ማለት ነው። ያገራችን ነፋስ ምን በረታ ከተባለ፤ ጣራህ ላይ የሰቀልከውን ዲሽ አቅጣጭ ይቀይርብህና ተጨማሪ ቻናሎች እንድታይ ያደርግሀል።

አግዚኦ የፈረንጅ ነፋስ!! ነውጠኛ ነው። ቆሞ የሚያገኘውን ዛፍ ሁላ በሾኬ እየጠለፈ ያጋድመዋል። እንዴውም አንዳንዴ ሳስበው የፈረንጅ ዛፍ በሥር ሳይሆን ስሉን በጨረሰ ሽራ ጫማ ላይ የቆመ ይመስለኛል። ትንሽ ነፋስ ታክኮት ካለፈ ባፍጢሙ ይከነበላል።

የኢትዮጵያ ዛፍ ይምጣብኝ። ኢትዮጵያ ውስጥ ዛፍ መትከል ብቻ ይሆን መንቀልም ከባድ ነው። ደጅን ላይ ዋርካ ብትተክል ሥሩን አጋዴን ላይ ብቅ ብሎ ታገኘዋለህ። የኢትዮጵያ ዛፍ መሬት አያያዙ እንደ ሥልጣን ነው። ተያዘ ያዘ ነው፤ አይለቅም።

አዲስአበባ ውስጥ በክረምት የሚያስፈልጉህ ቁሳቁሶች ጥቂት ናቸው። ያንገት ጅሶ የሚመስል ኮሌታ ያለው ቢትልስ ሹራብ፤ ብዙ ኪስ ያልበዛበት ጃኬት እና ወፈር ያለ ጢስ የጠገበ ጋቢ በቂ ነው። እጅህን ሲቆፈንንህ በሰበቃ

ታሞቀዋለህ። ወይም ትኩስ ትንፋሽ ትነፋብታለህ። አዲስአበባ ውስጥ ጓንት ለሀኪምና ለቦክሰኛ ነው።

ዊንተርን ዘግናኝ ካደረጉብኝ ነገሮች ዋናው በጓንት የመታሰር ግዴታ ነው። ጓንት ሳደርግ በጨርቅና በስፖንጅ የተሠራ ካቴና ያጠለቅሁ ይመስለኛል። ሰዎች መጣጣምን ለመግለጽ ሲፈልጉ "እጅና ጓንት" የሚሉበት ምክንያት አይገባኝም። እጅና ጓንትኮ ባላንጣ ናቸው። እግዜር እግርን ሲሠራ ጫማን እያሰበ መሆን አለበት። ለአዳም እግር ከመሥራቱ በፊት ጫማውን ሳይሠራለት አልቀረም። በጫማና በእግር መካከል አለመግባባት የማይታየው ለዚያ ይሆናል። በሌጣ እግርህ ማድረግ የምትችለውን ሁሉ በጫማህ ከማድረግ የሚያግድህ ነገር የለም።

እስቲ ወፍራም ጓንት አጥልቀህ በሞባይልህ ስሌዳ ላይ የባልንጀራህን ስም ታይፕ ለማድረግ ሞክር። ጣትህ አንድ ፊደል ለመንካት ሲሞክር ሳታውቀው አንድ ዐረፍተ ነገር ይጽፍበሀል። አንድ ጣትህ መዳፍ የሚሠራውን ሥራ መሥራት ይጀምራል። ጓንት ሳደርግ ሁሌም ከጨርቅ በተሠራ ሹካ እንጀራ በእጅ የምጠቀም አይመስለኝም። ይህን ይህን ስታይ እጅ ለእንጶስላ እንጂ ለጓንት ያልተፈጠረበትን ሀገርህ እያሰብክ ትተክዛለህ።

ተቦርነ "ታክሲ መጥቷል"፣ አለና ከራሴ ጋር ከጀመርኩት ጭውውት አናጠበኝ።

ባለታክሲው ቀይ ጸጉረ ሉጫ ጎልማሳ ነው። ጨዋታ ተጀመረና ከስመራ እንደመጣ ነገረን። ደንታ አልሰጠኝም። በዛን ሰሞን የኢትዮጵያ ዘፈኖችና ደራሲዎች ስለአስመራ እብዝተው ያንጎራጉሩና ይተርኩ ስለነበር ሰልችቶኝ ይሆናል። ጣና ሳይጎበኝ የሚያረጀው ሰውየ ስለቀይ ባሕር አንድ ደብተር ግጥም ሲጽፍ ሳይ ጉድ እላለሁ። አሁን ሳስበው ቀይባሕር የኢትዮጵያ አካል ሆኖ ቢቆይ ኖሮ ዞር ብሎ የሚያየው አልነበረም። ለአዋሽና ለአርባምንጭ ማን ዘፈኖላቸው? አባይ ራሱ ወደ ግብጽ ባይከዳ ኖሮ ይሄ ሁሉ ግጥምና ዘፈን አይጎርፍለትም ነበር። አንዳንዴ ግጥም ማለት ቤት የሚመታ ወቀሳ ወይም ቁጬት ማለት ሳይሆን አይቀርም። በግጥም ማመስገን፣ የደስታን ስሜት መግለጥ ከባድ ነው።





ባለታክሲው ከጥቂት ወሬ በኋላ፣ "እዚህ ለመድረስ ብዙ ነገር አይቻለሁ" ብሎ ተከዘ።

እዚህ ላይ ጆሮየን ዘንበል አደረግሁ። የምንሄደው ጉዞ አጭር ባይሆን ኖሮ ባለታክሲው ስላየው "ብዙ ነገር" እንዲያወጋኝ እጎተጉተው ነበር። ለነገሩ ብጠይቀውም ለመተረክ ፈቃደኛ ላይሆን ይችላል። ለምን እንደሆነ እንጃ ከኤርትራ ስደተኞች ጋር ስገጣጠም ሁሌም ትዝ የሚለኝ የጓደኛየ የድልነሳው እናት ታሪክ ነው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ ከእለታት አንድ ቀን እንደ ሎጥ ሚስት ወደ ኋላ ዞሮ ሲመለከት ከው ብሎ በቀረው የብሔራዊ ትያትር አንበሳ ሥር ቆሜ ጫማ አስቀባለሁ። አብሮ አደጌ ድልነሳው ተመስጌን (ስሙን ቀይሬዋለሁ) ከቸርችል ጎዳና አቅጣጫ ሲመጣ አየሁት። ድሌ ከዚህ በፊት መንገድ ላይ ተገናኝተን ሀያ ብር ስለፈለጠኝ እንዳይደግመኝ ሰማቹ ሰማይ ሰማዩን ማየት ጀመርሁ። እንዳላየሁት ለማስመሰል፣ እግረመንገዴንም እንዳያየኝ ለመጸለይ ነው። የፈራሁት አልቀረም፤ የጃኬቴ ጫፍ ሲጎተት ዞር አልሁ። በፈገግታ ተጥለቅለቆ አቀፈኝና፤

"ሻይ እንጠጣ" አለኝ፣ የሚጋብዘኝ ይመስል።

ሻዩን ጋበዝኩት፣ የሚከተለውን ታሪክ ጋበዘኝ።

*******

ወይዘሪት ጽጌ የምትባል እንዲት ያስመራ ቆንጆ ነበረች። ከማኽል ሀገር ወደ ኤርትራ ከዘመተ የቀድሞ ሠራዊት አባል ጋር ተዋደደች። ወታደሩ ወደ ትውልድ አገሩ ደብረማርቆስ መመለሻው ሲደርስ ይዟት ተመለሰ። ከዚያም





ወንድ ልጅ አስወለዳት፤ ስሙንም ድልነሳ ብሎ ጠራው። ባልና ሚስቱ ቀጥለው ሌላ አንዲት ቆንጆ ሴት ከነቃጭል ድምጿ ዱብ አደረጉ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ባሏ ሲሞት፣ ጽጌ ልጆቿን ለብቻዋ ማሳደግ ጀመረች።

ደብረማርቆስ ውስጥ ጥቂት የማይባሉ ከመረብ ወዲህና ወዲያ የሆኑ የትግራይ ሰዎች ይኖራሉ። ብዙዎቹ በመምህርነት፣ ግንበኝነትና ሹፌርነት ተቀጥረው ያገለግላሉ። የደብረማርቆስን ጋራጆች ገትረው የያዟቸው ዮሴፍ ስብሀቱና ኃይሌ ስብሀቱ የተባሉት ኤርትራውያን እንደነበሩ ትዝ ይለኛል ። እኔና አብሮ አደጎቼ በቢሳ ምላጭ ራሳችንን ከመላጨት ወጥተን በ"መኪኔታ" መስተካከል የጀመርነው፣ የሐማሴን ተወላጅ በሆነው ወልዳይ ጸጉርቤት ነው።

ጊዜው ገሰገሰ። ኢህአዴግ ሥልጣን ይዞ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ጌቶች፣ "ቅንድብ በሚያስም" ፍቅር የነሆለሉበት ሰአት ደረሰ። የኤርትራ ሪፈረንደም ላይ እንዲሳተፉ በየከፍሀገሩ ላሉ የኤርትራ ተወላጆች ጥሪ ቀረበ። ብዙዎቹ ጥሪውን ቸል አሉት። የደብረማርቆስን ጋራጅ የተቆጣጠሩት የኤርትራ ተወላጆች "ሀገራችን እዚህ ስለሆነ አንመርጥም" ብለው አሻፈረኝ ማለታቸው በየጠላ ቤቱ ተወራላቸው።

ብብሔርተኝነት ልባቸው የነደደ ሰዎች ግን ወደ ሪፈረንደሙ ተመሙ። ወይዘሮ ጽጌ ሹርባዋን በቀጭኑ ተሰርታ የወርቅ ቁና የሚያህል ጉትቻዋን አንጠልጥላ፣ እጇን በእንሶስላ አቅልታ፣ ያበሻ ቀሚሷን ለብሳ፣ ወደ ቀበሌ ልትሄድ ስትነሳ ተቃውሚት እንደነበር ልጇ ያስታውሳል። "አያገባህም!" አለችኝ ይላል ። ቀበሌው ድምጿን ተቀብሎ "ዴሞክራሲያዊ መብቷን ተጠቅማ መምረጥዋ የህዝቦች መራራ ተጋድሎ ውጤት" መሆኑን ደስኩሮ ሸኛት። ወይዘሮ ጽጌም ባለቤቷ የተጋደለላትን ሀገር በካርድ አሰናብታ ወደ ቤቷ ተመልሳ፣ በሁለቱ ክፍልፋይ ሀገሮቿ መካከል ተንጋላ ተኛች።

1990

በታሪካችን ውስጥ እጅግ አንግዳ ከሆኑ ንግግሮች አንዱ፣ "ያይናቸው ቀለም ካላማረን ውጡ ልንላቸው መብት አለን" የሚለው ያቶ መለስ ዜናዊ ንግግር





ነው። ይህ ንግግር ከጠቅላይ ምኒስትሩ አንደበት እስኪወጣ ድረስ፣ በዘራቸው ምክንያት ሰዎችን ከመኖርያ ቀያቸው ማፈናቀል ኢትዮጵያዊ ባህል አልነበረም።

ይህንን ንግግር ሳስብ፣ የሚከተለው ገጠመኝ አብሮ ይታወሰኛል።

ከጥቂት ጊዜያት በፊት፣ ከላሊበላ ወደ አክሱም በሚወስድ አውሮፕላን ውስጥ አንድ አባ ማናየ ብለው ራሳቸውን ካስተዋወቁኝ አዛውንት ጋር ተዋውቄ ነበር። የጀመርነውን ወግ ከዮሐንስ አውሮፕላን ማረፍያ እስከ ማውጋት ጀመርን። የጀመርነውን ወግ ከዮሐንስ አውሮፕላን ማረፍያ እስከ አክሱም ጽዮን ድረስ በሚወስደን አንድ ታክሲ ውስጥ ቀጠልነው። ልንሰነባበት ስንል፤

"ሀገርህ የት ነው?" ብለው ጠየቁኝ

የትውልድ ሀገሬን ነገርኳቸው።

"እሱማ ሀገርህ አይደለም"

"ኢትዮጵያ " አልሁ ያሻሻልሁ መስሎኝ።

"እሱም ሀገርህ አይደለም"

"ታድያ ምንድን ነው?"

"ሀገርህ ምግባርህ ነው፤ የሰው ሀገሩ ምግባሩ ይባላል"

አባባሉ ጠጠር ያለ እንቆቅልሽ ስለሆነብኝ ለመፍታት ሞከርኩ። የሰው ሀገሩ ምግባሩ ማለት ምን ማለት ነው? ባንድ ሀገር የመኖር ዋና መስፈርት ዘር፣ ወይም ተዋላጅነት ሳይሆን የግለሰቡ ባሕርይ ነው ማለት መሰለኝ። የግለሰቡ ባሕርይ ከሀገሩ ሕግ እና የኑሮ ዓላማ ጋር ከተጣጣመ ተወላጅ ባይሆንም የመኖር መብት አለው። ድንቅ የኢትዮጵያ ፍልስፍና ነው። ፍልስፍናው ወደ ምድር ወርዶ የኑሮ መርህ ሆኖ እንዳገለገለ የምናውቀው የአክሱሙን አርማህ ታሪክ ስናይ ነው። ንጉሥ አርማህ ባሕር ተሻግረው ወደ አክሱም ቤተመንግሥት የመጡትን የነብዩ መሀመድ ተከታዮች በሀገሩ እንዲኖሩ

ከመፍቀዱ በፊት ስለእምነታቸው ነው የጠየቃቸው። እምነታቸው የአክሱምን ሕግና የኑሮ ባህል የሚቃረን ሆኖ ስላላገኘው የመኖርያ ፈቃድ አልነፈጋቸውም።

በዘመነ መሣፍንት መግቢያ ላይ ራስ ወልደ ሥላሴ የተባለ ዝነኛ መስፍን ራስ ሚካኤል ባሳደደው ወቅት ከትግራይ ወደ ጎጃም መጥቶ ብዙ ዘመን ኖሯል።

በኦሮሞ ባህል ውስጥ ኦሮሞ ያልሆነም ሰው በሞጋሳ ወግ የመኖርያ ፈቃድ ያገኛል። ይህ እድል ለጥቁሮች ብቻ ሳይሆን ባሕር ተሻግረው ለመጡ ነጮችም ደርሷቸዋል። ክራፍ የተባለው የጀርመን ሐዋርያ ይህን እድል አግኝቶ ነበር።

በዐማራ ማኅበረሰብ ውስጥ እንዲሁ፣ እንግዳ ማስጠለል የማኅበሩ አባል አድርጎ ማኖር የተለመደ ነበር። ጊዮርጊስ የተባለ የግሪክ ሰው፣ እንጀራ እየበላ ጃኖ እየለበሰ በባዶ እግሩ እየሄደ፣ ብሄራዊ ውትድርና እየተሳተፈ የኢትዮጵያ ባላገር ሆኖ መኖር ችሏል።











በሌላ በኩል ያንድ አካባቢ ተወላጅ ሆኖ፣ ወንጀል የሠራ ሰው ካገር እንዲባረር ይደረግ ነበር። ባንድ ሀገር ውስጥ ለመኖር ዋናው መስፈርት ዘርና ተወላጅነት ሳይሆን ያገሩን ሕግ አክብሮ የመኖር ፈቃደኝነት ብቻ ነበር። "የሰው ሀገሩ ምግባሩ" ማለት ይሄ መሰለኝ።

ኤርትራውያኑን ኑሮቸውን መሥርተው ከሚኖሩበት መንደር ማፈናቀል ይህንን የቆየ ኑሮ መርሆችንን የሚጥስ ነበር። ዛሬ፣ ባንዳንዳድ ቦታዎች፣ "ካካባቢያችን ውጡልን" የሚል መፈክር ያነገቡ ሰዎች፣ ያለ ሀፍረት አደባባይ ውጥተው ስመለከት፣ "ይሄንን ያክል ከራሳችን ርቀናል?" እያልሁ እገረማለሁ።

ወደ ወይዘሮ ጽጌ ታሪክ እንመለስ። የኤርትራ ተወላጆች ከየቦታው እየታነቁ ወደ መጡበት ይባረሩ ጀመረ። በሪፈረንደም ያልተሳተፉት እንዳይባረሩ ህዝቡ ተሟገተላቸው። በሪፈረንደም ላይ የተሳተፉት ግን ስንዳቸው ከቀበሌ መዝገብ ውስጥ እየተመረመረ እንዲባረሩ ተደረገ። ወይዘሮ ጽጌ ከሴት ልጇ ጋር ፊቱን ወደ አስመራ ባዞረ አውቶብስ ላይ ተጫኑች። ያገሩ ነዋሪ አደባባይ ላይ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ ጎረቤቶቹን እያለቀሰ ሸኛቸው።

ጽጌ አስመራ እንደደረሰች ያላሰበችው ነገር ገጠማት። ሻእቢያ "የጨፍጫፊው የደርግ ወታደር ሚስት" እንደነበረች በደረሰው ጥቆማ መሠረት ይዞ ወደ ወህኒ ወረወራት። ሴት ልጇም እዚያው ታማ ሞተች። ጽጌ ካንድ ዓመት እሥር በኋላ አስመራ መቀመጥ አልቻለችም። ልጇ ድልነሳ ናፈቃት። በደናው ቀን ዓለሟን ያየችበት፣ ቤቷ ናፈቃት። የመጨረሻ ጌጦቿን ለድንበር አሻጋሪዎች አስረክባ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰች። ሁመራ ውስጥ አንድ ቡና ቤት ውስጥ ጥቂት ከሠራች በኋላ፣ ወደ ደብረማርቆስ ተሳፈረች።

ከልጇ ከከድልነሳ ጋራ ተገናኝታ ተላቅሳ ወደ ቤቷ ገባች። የሸረሪት ድር የወረሰውን ጀበናዋን ወልውላ፣ ቡና አፍልታ፣ አቦሉን ፉት ስትል በሩ ተንኳኳ።

"ማነው?"

በሩ ላይ ትልቅ ኩርኩም ወደቀ።





"ማነ...ው?"

"ከፊት ፖሊሶች ነን"

ወይዘሮ ጽጌ በሻእቢያ ሰላይነት ተጠርጥራ ወደ ወህኒ ተላከች። ከጥቂት ጊዜ በፊት፣ የሁለት ሀገር ዜጋ የነበረችው ጽጌ፣ የወህኒ ጠባቂዎች የሚቀባበሏት የሁለት ሀገሮች እስረኛ ሆነች። ድሌ ቢያለቅስ፣ ቢዝት ቢሳል እናቱ ላይ የጨከነውን እጣ ፈንታ መቀልበስ አልቻለም። ከስድስት ወር በኋላ ከእሥርቤት ተፈትታ ወደ ሸሬ ተጋዘች።

ድልነሳ፣ "ባለፈው ሳምንት ካናዳ ገባች" ብሎ፣ ከትካዜ ገላገለኝ። "በሚቀጥለው ሳገኝህ ብድሬን እከፍላለሁ"፣ ብሎ ጨመረ።

*****

ባለታክሲው እኔና ተቦርነን ጭኖ እየከነፈ ነው። ከሐሳብ ዘመቻዬ ስመለስ፣ ተቦርነና ባለ ታክሲው ሞቅ ያለ ወግ ይዘው ደረስኩ።

"አስመራን ታውቀዋለህ?" አለ ባለታክሲው በፊት ለፊቱ መስታወት ተቦርነን እየተመለከተ።

"አዎ" ሲል መለሰ ተቦርነ። አስከትሎም፣ "ትንብር ኔራ ቀጻሮ ጠሊማ" ብሎ አዜመ።

ባለታክሲው፣ "ትራኪብና ዶ ብወዝቢ አብ ሲኒማ" ብሎ ተቀበለው።

ተቦርነ፦ አብ ኩተማ ምጽዋ አብት ገምገም ባህሪ

ባለታክሲ፦ ሎሚ ተዘከርኒ ዝህለፈ ፍቅሪ

ካለ በሁዋላ "አንተ ትክክለኛ ያሥመራ ሰው ነህ" አለ ቢጋለ በስሜት። ከዝያ እኛን ብዙ ላለማስከፈል መንገድ እያቆራረጠ መንዳት ጀመረ። በመጨረሻ የዋጋ መቁረጫ መሺኑ "አሥራ አምስት ዶላር" የሚል ጽሑፍ አሳየን።

ተቦርነ፣ ሀያ ዶላር ከቦርሳው አውጥቶ ዘረጋለት

ባለታክሲው እሥር ዶላሩን መለሰለት።

"ከዋጋው በታች ለምን ትቀበለኛለህ?" ሲል ጠየቀ ተቦርነ፡፡

"ግዴለም ያዝ፤ በኔ ነው ኪሳራው ዛሬ" አለ ባለታኪሲው ፊቱ ላይ ያለው ፈገግታ እንደተቀጣጠለ።

ጾጾትን፣ ትዝታን፣ ዘፈንንና ዐማርኛ ቋንቋን የሚጋራ የመጨረሻውን ኢትዮ-ኤርትራ ትውልድ ተመለከትሁ። ይህ ታክሲ ቤቴ በር ላይ እስካደረሰኝ ሰአት ድረስ ኢትዮጵያና ኤርትራ ከተፋቱ ሃያ ዓመት አልፏቸዋል። ከፍቺም አልፈው ደመኝነት አራርቋቸዋል። ይሁን እንጂ የዝምድና ዝሀዎች ጨርሰው እንዳልተበጠሱ ታዘብኩ። ይህ በእንዲህ መቀጠሉን እጠራጠራለሁ። አዲስ ፕሮፖጋንዳ ተመግቦ ያደገ አዲስ ትውልድ በመነሣት ላይ መሆኑን አውቃለሁ። ባለፉት ሃያ አራት ዓመታት ውስጥ የተሰበከው የባዕድነት ፕሮፖጋንዳ ቀርቶ ስለዝምድናችን ስለወንድማማችነታችን መወያየት የምንጀምርበት ቀን እንዲመጣ እመኛለሁ። አለበለዝያ በመካከላችን የቆመው የበርሊን ግንብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለጠጠ ሄዷል። የኢሰማን አብዱራህማን ዘፈን የኤርትራውያን ብቻ ሲሆን የኤፍሬም ታምሩ ዘፈን የኢትዮጵያውያን ብቻ የሚሆንበት ጊዜ ይመጣል። የተቦርነ ልጅ እና የባለታክሲው ልጅ አሜሪካ ውስጥ ከባቡር ወንበር በቀር የሚጋሩት ነገር የሚኖር አይመስለኝም።





# የጁገልን በር ጥሰው የገቡ ሐሳቦች

ከጁገል በር ፊትለፊት፣ በር ላይ ስቆም ወደ አእምሮየ የመጣው፣ "የጦርነት በረከት" የሚል ሐረግ ነው። ጦርነት ደግሞ መአት እንጂ ምን በረከት አለው? የሚል ጥያቄ ካንባቢየ እንደሚወረወርልኝ እገምታለሁ።

የግራኝ አህመድ ሥልጣንና ሚስት ወራሽ የሆነው አሚር ኑር ጠላቶቹ ባያስጨንቁት ኖሮ ይሁንን የመሰለ ግንብ የመሥራት ሐሳብ ከየት ይመጣለት ነበር? በጊዜው ለሐረር ከኖራና ከዐለት የተሸመነ የጦር ልብስ ሠራላት። በኑር ዘመን ጥሩር የነበረው ዛሬ ያዘቦት ልብሷ ነው።

ያለጥርጥር፣ ጦርነት አፍራሽ ነው። ግን ዐልፎ ዐልፎ ብዙ የማይታይ ገንቢ ጎን አለው። ዳግማዊ ምኒልክ ጦሩን ይዞ አርሲን ለማስገበር ከመምከሩ በፊት በአዋሽ ወንዝ ላይ ለዘመኑ ሰው እጹብ የሚባል ድልድይ ማስገንባት ነበረበት። በጠቅል ዘመን፣ ዋቀ ጉቱ የተባለውን አመጸኛ ለማሳመን፣ ጀጋማ ኬሎ ታንክና ካሚዮን የሚያስተላልፍ፣ አሪፍ መንገድና፣ ድልድይ በእንግሊዝ ግንበኞች አስገንብቷል። ባሌ በሰላሙ ጊዜ ደጅ ጠንቶ ያላገኘችውን መሠረተ-ልማት በግጭት ዋዜማ አገኘችው።





ከጥቂት ወራት በፊት፣ ላስታ ውስጥ የሚገኘውን የይምርሀነ ክርስቶስን ጥንታዊና አስደናቂ ሕንጻ ጎበኘሁ። እንደወላድ እያማጥሁ ተራራውን ለመውጣት ግማሽ ሰአት መልፋት ነበረብኝ። አልቫሬዝ የተባለው የፖርቹጋል መነኩሴ የዛሬ አምስት መቶ ዓመት ገደማ፣ በመጫኛ እየተጎተተ፣ ተራራ እየቧጨረ እኔ የወጣሁትን ለመውጣት ግማሽ ቀን ፈጅቶበታል። ያኔ እንደ ዛሬ ወደ ተራራው የሚያወጣ ደረጃ አልተሠራም ነበር።

ይምርሀነ የሚባል ቅዱስ ንጉሥ ካላጣው ሜዳ እንደ ገመሬ ዝንጀሮ እዚያ ላይ የወጣበት ምክንያት ምንድን ነው? ምናልባት በቅዱሳን ልብ ውስጥ ተሸሽጎ ያለ ወደ ሰማይ የመቅረብ ፍላጎት ገፍቶት ይሆን? ይምርሀነ ተራራ ላይ የወጣው ቤቱን የጠላት ፈረስ ከማይደርስበት ቦታ ለማስቀመጥ ፈልጎ እንደሆነ የገባኝ ትንሽ ዘግይቶ ነው። ጠላት ይምርሀነ የሚኖርበት ቦታ ላይ ለመውጣት ከፈለገ ፈረስ ሳይሆን ድራጎን መጋለብ አለበት። ብዙ ያገራችን ገዳሞች እና ጥንታዊ ሕንጻዎች በሰላሙ ቀን ለቤትነት የሚያገለግሉ ምሽጎች ናቸው ማለት ይቻላል። የምሽግነት ባሕርይ የሌላቸው ቤቶች የኑሮን መስፈርት ማሟላት ስላልቻሉ ተደምስሰዋል።

ጦርነት፣ የሕንጻዎቻችን መሀንዲስ፣ የድልድዮችን አናጢ ብቻ ሳይሆን የጌጦቻችን ሁሉ ምንጭ ነው፡፡ ሎቲ ማንጠልጠል፣ ሹርባ መሠራት፣ ጎፈሬ ማበጠር የመሳሰሉት ጌጦች የወታደር ወጎች ነበሩ። "ሳይገድሉ ጎፈሬ" ይባል ነበር እስከቅርብ ጊዜ። ድሮ ጎፈሬ ለመሆን መስፈርቱ በቂ ጅብድ መፈጸም ሲሆን አሁን ለጎፈሬነት መሥፈርቱ በቂ ጠጉር ማጠራቀም ብቻ ነው።

ሀገር በቀል፣ ያካልና ያአእምሮ ማጎልመሻ ጨዋታዎቻችንን ስናይ ባንድም ሆነ በሌላ መንገድ የጦርነት ነጸብራቅ መሆናቸውን እንገነዘባለን። በጨዋታና በሞት መካከል ያለው ድንበር ይሄን ያክል ጠባብ እንደነበረ ማወቅ ያስገርማል። ጉግስ፣ ገጤ፣ ሰንጠረዥ አካዱራ፣ ገና የተባሉት ዛሬ በቪድዮ ጌም የተተኩ ጨዋታዎች የጦር ቃና ነበራቸው።

ለምሳሌ ጉግስን እንውሰድ። ፈረሰኞች ለሁለት ተቧድነው በወደረኞቻቸው ላይ ዘንግ እየተወራወሩ ጋሻ እየመከቱ የሚጫወቱት ጨዋታ ነው። በጨዋታ ላይ





ሕይወት ማጣት ብርቅ ነገር አልነበረም። የጉግስ ጨዋታ ተመልካች ሆኖ ወጥቶ ለቀስተኛ ሆኖ መመለስ የተለመደ ነበር።

ገጤ የሚባል ጨዋታ ደግሞ አለላችሁ። ልጆች ሹል ጫፍ ያለው ዘንግ በቁልቋል ላይ እያነጣጠሩ በመወርወር የሚጫወቱት ጨዋታ ነው። ቁልቋሉ እጅ ራስ እግር ስላለው ፣ሲወጉትም ደም ስለሚፈስሰው፣ የሰው ምትክ ሆኖ ያገለግል ነበር።

ከላይ ሲያዩት ጭምት ገጽታ ያለው፣ ሰንጠረዥ የተባለው ጨዋታ እንኳ የጦርነት ይዘት አይጠፋውም። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል በዝክረ ነገሩ ስለዚሁ ጨዋታ ሲጽፍ ፣ "በዚሁም ጨዋታ ውስጥ ያለው ጥቅም፣ በጦርነት ሰዓት እንደ ምን የሰልፍ ፀቅድና ውጊያ መካሄድ እንደሚገባው በመምራቱ ነው" ይላል።

ፈረንጆች፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች የውትድርና ልምምድ ባህል ሳይኖራቸው ብርቱ ተዋጊዎች በመሆናቸው ይገረሙ ነበር። የሰላሙ ቀን ጨዋታዎች በእጅ አዙርም ቢሆን ራሳቸውን የቻሉ የጦርነት ልምምዶች መሆናቸው የገባቸው አይመስለኝም።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምግብ ተደርጎ የሚቆጠረው ጥሬ ሥጋም የጦርነት ቅርስ ነው። አያቶቻችን ጥሬ ሥጋ መብላት የጀመሩት፣ ጥብስ ሰልችቷቸው፣ ወይም የእሳት አጠቃቀም ጠፍቷቸው አልነበረም። በጠፍ ጨረቃ፣ በዱር በገደል፣ ሲዘምቱ ጠላቶቻቸው የእሳትና የጭስ ምልክት ዓይተው እንዳያጠቋቸው፣ ሥጋውን በጥሬ ለመብላት ተገደዱ የሚል ወግ አለ። ነገሩ እንዲህ ከሆነ፣ ዛሬ በሰላሙ ጊዜ ተወዳጅ የሆነው ምግባችን ከእለታት አንድ ቀን የጦርነት ፍሬ ነበር ማለት ነው። ጦርነት ከሕንጻችን እስከምሰባችን ድረስ አሻራውን ትቷል።

አንዳንዴ የኢትዮጵያ ባህል የሆነው ሩጫ የጦርነት ገጸበረከት ይሆን እላለሁ። በሰላሙ ቀን እግር እስኪቃጠል ድረስ የሚያሯሩጥ ምን ነገር አለ? አሉቃ ገብረሥላሴ በኢትጵያውያንና በጣልያኖች መካከል አምባላጌ ላይ ስለተደረገው ጦርነት ከዘገበ በኋላ የሚከለውን ይጨምራል።

*"...የኢጣሊያ ሹም ከዚያው ጦር ላይ ሞተ። እሱ ግን አሸሻለሁ ብሎ መንገድ ጀምሮ ነበር። የኢትዮጵያ ሰው <u>ፈጣን</u> ነውና ሊማምለጥ አልተቻለውም።"*

የኢትዮጵያ ሰው፣ የፍጥነት ተሰጥኦ እንዳለው የተገነዘበው ጦርሜዳ ላይ ሳይሆን ይቀራል? በቀወጢ ቀን ለጠላት ማባረሪያና ከጠላት መሸሻ ሲጠቀምበት የነበረውን ተሰጥኦ በአበበ ቢቂላ አማካኝነት ወደ ባህል ቀየረው። አባቶቻችን ለጠላት ማሳደጃ ይጠቀሙበት የነበረውን ፈጣንነት አሁን አትሌቶቻችን ሜዳልያ ያሳድዱበታል።

አሁን ሐረር ውስጥ ነኝ። የዛሬ መቶ ዓመት አባቶቼ በወራሪነት የረገጡት ቦታ ላይ በቱሪስትነት ቆሜ ስለጦርነት ገጸበረከቶች እያሰብኩ ነው። ሐረር ራሷም የጦርነት ፍሬ ናት። ምኒልክ ሐረርን 1887 አስገብሮ የኢትዮጵያ አካል እስኪያደርጋት ድረስ ሐረር፣ በአሚሮችና በግብጾች በወረፋ ስትገዛ ኖራለች። አባ ዳኘው ሐረርን ወደ ኢትዮጵያ ከጠቀለለ በኋላ ጁልየ ቦረሊ ለተባለ ፈረንሳዊ የጻፈለትን ደብዳቤ ሐረሬ ብሄራዊ ሙዝየም በፍሬም ታጥሮ ተቀምጦ ለሕዝብ ሲጎበኝ ተመልከቸዋለሁ። ደብዳቤውን አጠቅሼና የራሴን ማብራሪያ አስከትላለሁ።

*<u>የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ</u>፣ ይድረስ ለሙሴ ቦረሊ. እንዴት ሰንበትክ። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። እኔም ወደ ሐረርጌ እሄዳለሁ ብየ ስጓዝ የሐረርጌው ሹም ሜታ ላይ ወራብሌ ከሚለው ቦታ አጥሩን አጥሮስ ሰውን አስከትቶ ጅሀድ እያለ የመሀመድ ወገን ሁሉ ሰብስቦ መድፋንም ነፍጡንም ሊድርን ሰልፍ አገኘሁት። ይታረቃል መስሎኝ ብልከበት መላእክተኞቼን አስሮ የልደት እለት እስፌሬ ድረስ መጥቶ ተዋጋ። የምሥራች በእግዚአብሔር ቸርነት ድል አድርጌ እሱ ብቻውን ሲያመልጥ ሰውን ፈጀሁት። መድፋም ነፍጡም ተያዘ። ሐረርጌም አከተማው ገባሁበት። በጥር 7 ቀን በሐረርጌ ከተማ ተጻፈ።*

ደብዳቤው ላንድ ግለሰብ ቢላክም ዘመን ተሻጋሪ ሰነድ እንዲሆን ተፈርዶበታል። ወይም ታድሏል። እስቲ ከደብዳቤው ውስጥ ቁልፍ ሐረጎችን እያወጣን እንቆዝምባቸው።





## "የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ"

ምኒልክ በወቅቱ ንጉሥ እንጂ ዐጼ ወይም ንጉሠ ነገሥት እንዳልነበረ ልብ ይበሉ። ንጉሠ ነገሥቱና የበላይ አለቃው ዐጼ ዮሐንስ አራተኛ ነበር። ዐጼ ዮሐንስ ሐረርን ራሱ ሊይዘው ፈልጎ ነበር። የሸዋው ንጉሥ ግን እኔ ላስገብረውና ምርኮውን አስረክባለሁ የሚል የብልጠት መልስ ሰጠ። ሐረርን እንዲያስገብርም በንጉሠነገሥቱ ተፈቀደለት።

## "ሙሴ ቦረሊ"

ቦረሊ የፈረንሳይ መንገደኛ ነው። ታታሪ ዘጋቢ ቢሆንም በጊዜው በፈረንሳዮች ዘንድ ፋሽን የነበረው የነጭ ዘረኝነት ልክፍት ነበረበት። በተገኘው አጋጣሚ ምኒልክንና ጣይቱን ይነቁራል። ያም ሆኖ መጽሀፋን በጥንቃቄ ለሚያነበው ሰው ብዙ ታሪካዊ መረጃ ያገኝበታል።

ምኒልክ ይህንን ደብዳቤ ለቦረሊ የላከው፣ ሀረርን መያዙን የፈረንሳይ መንግሥት እንዲያውቅለት ስለፈለገ ነው። ፈረንሳይ በወቅቱ ሐረር ባለቤት አልባ ሲሆን ዘው ብላ ልትገባበት የግብጾችን መውጣት ትጠባበቅ ነበር። የምኒልክ ደብዳቤ ቁርጣችሁን እወቁት፣ ዘመድ ከዘመድ ተደባልቋል ማለት ይመስላል።

## "እኔም ሐረርጌ እሄዳለሁ ብየ ስጓዝ"

ምኒልክ ወደ ሐረርጌ ያደረገው ዘመቻ እሱ እንደሚለው ዝም ብሎ "ጉዞ" አልነበረም። ሀያ ሺህ የማያንስ ኅብረብሄራዊ ሠራዊት ያስከተለበት ዘመቻ ነው።





## "የሐረርጌው ሹም"

ንጉሡ "የሐረርጌው ሹም" ብሎ ስሙን የዘለለው አሚር አብዱላሂ ነው። ግብጾች ሐረርን ለቅቀው ሲወጡ አሚሩ የሐረር መሪነትን ተረከበ። የፈረንጅ ፍራቻና ጥላቻ ነበረበት ይባላል። ይህ አባዜው መጥፊያው ሆነው። በርግጥ የፈረንጅ ጥላቻና ፍርሀት በውጭ አዝዛዥ ሲማቅቅ ለቆየ ሀገር ነዋሪ የሚጠበቅ ስሜት ነው። የጣልያን ልኡካንና መንገደኞች ወደ ሐረር ሲመጡ አሚሩ ወታደሮቹን ልኮ አስገድሏቸዋል። ይህ ርምጃ በጊዜው የአሚሩን ህጋዊነት ከጥያቄ ውስጥ ጣለው።

ምኒልክ፣ በአሚሩ ድርጊት የተቆጡ ጣልያኖች የወገኖቻቸውን ደም ለመበቀል በሚል ሽፋን ሐረርን እንደሚወሩ ገምቷል።፡ ይህ ከመሆኑ በፊት፣ ጥቁሩ የሸዋ ንጉሥ ሀረርን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ለማስገባት ተሽቀዳደመ።

## "ይታረቃል መስሎኝ ብልክበት"

ምኒልክ የሐረርጌ ግዛት ደም ሳይፈስ በእጁ እንዲገባ ፍላጎት ነበረው። ይህንን ፍቃዱን ቢፈጽም ኖሮ ለአሚሩ፣ ለጅማ የሰጠውን ዐይነት የውስጥ አስተዳደር ሊሰጠው ዝግጁ ነበረ። ለአብዱላሂ በጻፈለት ደብዳቤ፣ "ግባ፣ እኔ ላንተ ነው እንጂ የመጣሁት ሀገር ለማጥፋት አልመጣሁም። ተተገባህ ተተገዛህ ሀገር አልነካህም በኋላ ይጠጥትሀል።" ብሎ እንደላከበት በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሷል። ምኒልክ ያሰለፈው ሠራዊት የአብዱላሂን ሠራዊት ማሸነፍ እንደሚችል አስቀድሞ ያውቅ ነበር። "በኋላ ይጠጥትሀል" የሚለው ባዶ ጉራ ሳይሆን በአቅም ከመተማመን የፈለቀ አነጋገር ነው። ያንን ያህል ብቃት እንዳላው እያወቀ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ሀረርን መውረር ይችል ነበር። ንጉሡ ከነፍጥ በፊት የዘንባባ ዝንጣፊ ማሳየቱ ታላቅነቱን የሚያሳይ ይመስለኛል።





## "የልደት እለት እሰፈሬ ድረስ መጥቶ ተዋጋ"

አሚሩ በርግጥም የምኒልክን ጦር ለማጥቃት ልደትን የመረጠው ለዘዴ ነው። ልደት በምኒልክ ወታደሮች ከማንኛውም ዐይነት እንቅስቃሴ የሚቆጠቡበት በአል እንደሆነ ያውቃል። እምነታቸውን እንደ ደካማ ጎን መመረጡ ነው። ይሁን እንጂ ምኒልክ ከድል ጽድቅን የሚያስቀድም መነኩሴ አልነበረም። በዓመት አንድ ጊዜ የሚመጣውን የልደት በዓል እጅግ ብርቅ በሆነው ዘመቻ የሚለውጥበት ምክንያት አልታየውም ። ሠራዊቱ ዐይኑን በሥጋና በጠጁ ላይ በጣለበት ሰዓት የንጉሡ ዐይን በጦር ሜዳ መነጽሩ ላይ ተደቅኖ ነበር። የአሚሩ ሠራዊት የደፈጣ አደጋ ለመጣል አድብቶ ሲመጣ በንጉሡ መነጽር ክቡብ ውስጥ ገባ። ምኒልክ ነጋሪቱን አስመታ። የልደት በአል በመሆኑ በምኒልክ በኩል ያለው ሠራዊት በደንብ ተመግቧል ። ምናልባት አሚሩ የልደት በአልን በመምረጡ ትልቅ ስህተት ሳይሠራ አልቀረም።

## "ድል አድርጌ እሱ ብቻውን ሲያመልጥ ሰውን ፈጀሁት"

ይህ ኀይለ ቃል በጥንቃቄ መታየት ያለበት ነው። አንዳንዶች፣ "ሰውን ፈጀሁት" የሚለውን ጠቅሰው ምኒልክ ሰላማዊ ነዋሪ እንደፈጀ ራሱ መስክሯል ይላሉ። የሚለው ቃል "ሰራዊት" የሚል ትርጉም በተጠቀሰው ደብዳቤ ውስጥ "ሰው" የሚለው ቃል "ሰራዊት" የሚል ትርጉም ነው ያለው። ደብዳቤው በተጻፈበት ዘመን የነበረውን ዐማርኛ ስንመረምር ነገሩ በደንብ ግልጽ ይሆንልናል፡

ለምሳሌ አለቃ ገብረሥላሴ ቴዎድሮስ በሸዋ ስላደረገው ዘመቻ ሲጽፍ፣ "ዐጼ ቴዎድሮስም ከበጌምድር ተነሥተው በግስገሳ እንኮበር ደረሱ። በዚያም ቀን እስከማታ ድረስ ጥጉ ውጊያ ተዋጉ። ያጼ <u>ቴዎድሮስም ሰው</u> ቁጥር የሌለው <u>ብዙ ሰው</u> አለቀ" ብሏል። እዚህ ላይ "ያጼ ቴዎድሮስ ሰው" ሲል ያጼ ቴዎድሮስ ሠራዊት ወታደር ማለቱ እንደሆነ ልብ ይሏል። ምኒልክም ሰውን ፈጀሁት ሲል የአሚሩን ሠራዊት ፈጀሁ ማለቱ ነው። ያም ሆኖ የብሥራት ዜናው ላይ ግነት ይታያል። በጨለንቆ ጦርነት የአሚሩ ሠራዊት ሙሉ በሙሉ አላለቀም።

በጦርነቱ የተሳተፈው ከአራት ሺህ እንደማይበልጥ ታሪክ ጸሐፊዎች ነግረውናል። የሞተው አንድ ሺህ ያክል እንደሆነ በጦርነቱ ላይ የነበረው አውሮፓዊ ሐኪም መስክሯል።[32]

## ሐረርጌ እከተማውም ገባሁበት

ምኒልክ ወደ ሐረርጌ ገብተው ከተማዋን የተቆጣጠሩበት ጨዋ መንገድ ተምሳሌታዊ ተብሎ ተወድሷል። ወደ ከተማው በድል አድራጊነት እንደገቡ፣ "የሐረርጌ ሰዎች ገንዘባቸውም ቤታቸውም እንዳይነካ በደጃቸው ጥብቅ ቆመበት"። ማለትም በዛሬው አነጋገር የሰላምና መረጋጋት ኃይል በከተማዋ ውስጥ ተሰማራ። ንጉሡ ቀጥለና፣ "እስላሙና እሮሞው እንደ አባቱ ይደር" የሚል የሃይማኖት ነጻነትን የሚያረጋግጥ ዐዋጅ አስነገረ። ምኒልክ ሐረርን ለመያዝ ስለነደፈው እቅድ ለንጉሥ እምቢርቆ ሲያብራሩ፣ "ሐረርጌ ስገባ ሰውን ሁሉ በሃይማኖቱ እናኖራለን" ብሎ ቃል ገብቶ ነበር። ይህን ቃልኪዳኑን አክብሯል። በዚህ መልክ፣ ለሐረርን ገባር ሕዝብ በንብረቱና በመንፈሳዊ ሐብቱ ዋስትና ሰጥቶታል።

ከድሮ ወደ ዘንድሮ ልሸጋገር። አሁን ከጁገል በር ላይ ቆሜ ሳያት፣ሐረር ተስፋና ሥጋት እርግዝ ታየችኝ።

[32] Journal of Ethiopian studies, vol 9 No 2











የምን ተስፋ፣ የምን ሥጋት?

ከተስፋው ልጀምር። ባንድ ወቅት ስለሐረር አንድ ቀልድ ሰምቻ ነበር፤

ጥቂት ሰዎች ተሰብስበው አቶ መለስ ዜናዊ ዘንድ ይመጡና፣ "ሐረር ከተማ ውስጥ ቆሞ የሚገኘው የነፍጠኛው የራስ መኮንን ሐውልት ፈርሶ በቦታው የአሚር አብዱላሂ ሐውልት ይቁም"፣ የሚል አቤቱታ ያቀርባሉ።

መለስ ትንሽ አሰብ አደረገና፣ "የራስ መኮንን ሐውልት ማፍረስ አትችሉም። ነገር ግን፣ በራስ መኮንን ሐውልት ላይ አሚር አብዱላሂን ማፈናጠጥ ትችላላችሁ" ብሎ መለሰላቸው ይባላል።

ቀልዱን እንደሰማሁት ይህ የሐረር ሕዝብ እምነት እንጂ የመለስ ሐሳብ የሚያንጸባርቅ ቀልድ አይደለም አልሁ። የሐረር ሕዝብ ራስ መኮንን እና አሚር አብዱላሂን ባንድ ፈረስ ማስኬድ ችሏል። በከተማው ውስጥ የሁለቱ ሰዎች መታሰቢያዎች ይታያሉ። ኩታ ገጠም ድንበር ያላቸው ቤተክርስትያኖችና መስጊዶች ተቃቅፈው የሚኖሩባት ሆደሰፊ ከተማ ናት-ሐረር። ዩኔስኮ ይህንን የከተማዋን ልዩ ችሎታ አድንቆ፣ "የመቻቻል ከተማ" የሚል ማእረግ አጎናጽፏታል።

ይህ በጎ የሆነ የሕዝብ ባህል ከባለስልጣኖች ዓላማ ጋር ሲላተም አየሁና ሥጋት ገባኝ። ወደ ሐረሪ ብሔራዊ ሚዝየም ጎራ ስል በትልቅ ፍሬም በታጠረ የፎቶ ማኅደር ውስጥ ተቀምጦ የሚጎበኝ ምስል አየሁ። የጥንታዊ ሕንጻ ምስል ነው። ከምስሉ ራስጌ፣ "በምኒልክ ወረራ ወቅት ወደ ቤተክርስትያንነት የተቀየረው የቀድሞ የረሱፍ ባሻ መስጊድ ገጽታ" የሚል ለቁጭት የሚጋብዝ ማስተዋወቂያ ተጽፎበታል። በወረራው ወደ መስጊድ የተቀየረ የተባለው የመድኃኒዓለም ቤተክርስትያን ሀገር አማን ነው ብሎ በብሜ አጥር ተከብቦ ከተማው እምብርት ላይ ቁጭ ብሏል። ከቤተክርስትያኑ ፊትለፊት የጨለንቆ ሰማእታት ሐውልት እንዲቆም ተደርጓል። የምኒልክና ያብዱላሂ ሠራዊት የተዋጉበት ጨለንቆ ከሐረር ብዙ የሚርቅ መንደር ሆኖ ሳለ፣ በከተማው ውስጥ መታሰቢያውን ለማቆም ብዙ አማራጭ ቦታዎች እያሉ፣ "የጨለንቆ መታሰቢያ" ቤተክስያኑ ደጃፍ ላይ እንዲቆም የተደረገበት ምክንያት ምን ይሆን? ያስገባሪን





መታሰቢያና የገባሪን መታሰቢያ በቅርብ ርቀት በማፋጠጥ፣ ለኅብረተሰቡ የተዘጋጀለት ወጥመድ እንዳይሆን ሥጋት አለኝ።

መቼም ታሪክ አይቀየርም። መቀየር የምንችለው ታሪክን የምንመለከትበትን መነጽር ነው። ከታሪክ ውስጥ ካቴና የሚያይ እንዳለ ሁሉ እምባር የሚያይም አለ። ዛሬ እርር ኩምትር የምንልባቸው ትውስታዎች በሆደ ሰፊ ዓይን ብንመለከታቸው እንደ በረከትም ልንቆጥራቸው እንችላለን።

ፈረስ መጋላ የተባለው የዛሬዋ የሐረር ከተማ አደባባይ በአሚር አብዱላሂ ዘመን የፈረስ መሸጫ አደባባይ እንደነበረ እንብቢያለሁ። መስጊድ እንደነበረበት የሚገልጽ የታሪክ ሰነድም አለ። መስጊድን ወደ ቤተክርስትያን መለወጥ እንደ ሐዋርያዊ ትልቅ ተልእኮ የሚቆጥሩ ሰዎች ካስገባሪው ወገን ነበሩ። የጊዜው ጠባይ ነው። በሌላ በኩል፣ ጉልበት ሲሰማቸው፣ ቤተክርስትያንን ወደ መስጊድ የቀየሩ ወይም ለመቀየር ያቀዱ በየጊዜው ተነሥተዋል። ቴዎድሮስ ሸጉጡን ከጠጣ በኋላ ወይዘሮ መስታወት የተባለችው ወደረኛው በመቅደላ የነበረውን ቤተክርስትያን ወደ መስጊድነት ቀይራለች። የፖርቱጋሉ ወታደር ካታሆንዞ እንደሚነግረን ከሆን ግራኝ አህመድ የላሊበላን ቤተጊዮርጊስ ለመስጊድነት እጭቶት ነበር።

አባቶች የሃይማኖት መቻቻል መንፈስ አልተገለጠላቸውም። ግን ደግሞ ማፍረስን ትተው መውረስ መምረጣቸውን ማወቅ ያጽናናል። ቤተክርስትያን ወይም መስጊድ ሲቃጠል የሚጎዳው እምነቱን አይደለም። እምነቱማ በአመናን ልብ ውስጥ በእልከ ይብልጥ እየተንቀሳቀሰ ይኖራል። የእምነት ሥርአቱ ጠላት ባልደረሰበት ሀገር ውስጥ በሚገኝ ቤተ- አምልኮ ውስጥ ይቀጥላል። ቤተ-አምልኮዎች ሲቃጠሉ የሚደርሰው ትልቁ ጉዳት፣ ልዩ ልዩ እደ ጥበቦች መውደምና ዝርያቸው መቋረጡ ነው። ተወደደም ተጠላም ነገ ከነገ ወድያ ሳይንስ ሲጎለብት ሐብት እየተትረፈረፈ ሲሄድ የአምልኮ መንፈስ እየቀዘቀዘ እንደሚሄድ አያጠራጥርም። እምነት የሚባለው ነገር ጨርሶ እንኳ ባይወገድ አምልኮ በታን የሙጥኝ የሚል እምነት እንደሚወገድ መገመት ይቻላል። ለጥንታዊ ስነሕንጻዎች እና ለብራናዎች ያለን አድናቆት ግን በቀላሉ አይበርድም። ስነ-ውበት ከእምነት የተሻለ እድሜ ይኖረዋልና። ይህን ስናስብ፣

መስጊዱን በማፍረስ ፋንታ ቤተክርስትያን አድርገው ያቆዩንን፤ ቤተክርስትያኑን በማቃጠል ፋንታ ወደ መስጊድ ቀይረው ያስተላለፉልንን አባቶቻችንን እናመሰግናቸዋለን።

ሐረር ኢትዮጵያን ህልውና ለማይፈልጉ ሰዎች፣ ከሚመረጡ ስስ ብልቶች አንዷ ናት። ታሪኳን በቂምና በቁርሾ ዘይቤ ተርጉመው፣ ሕዝቧን ኅራ እስለይተው ለማፋጀት የሚፈልጉ ሰዎች የሉም ብየ አላስብም። ተስፋየ ገብረአብ አንድ ምሳሌ ሊሆን ይችላል።

ተስፋየ ገብረአብ "የቡርቃ ዝምታን" ካሳተመ በኋላ ዝም ብሎ አልተቀመጠም። በሀረር ታሪክ ዙርያ የሚያጠነጥን "የቋንዶዶ ፈረሶች" የሚል ልቦለድ ለማሳተም እቅድ ነደፈ። ይሁን እንጂ ተስፋየ እቅዱን ሳያሳካ በታሪክ ማአበል ተገፍቶ ካገር ወጣ። ሆኖም ለሐረር የደገሰላትን ጊዜውን ጠብቆ አወጣው። ከሚቀር ይጥቆር ብሎ የስደተኛው ማስታወሻ በተባለ መጽሀፉ ላይ "የጁገል ልባዊ ወግ" በሚል ምእራፍ ሥር አንድ በጣም ጉደኛ ሊባል የሚችል፣ "ቃለመጠይቅ" አቀረበ።

ተስፋየ፣ ለ"ታሪኩ" መሠረት ያደረገው አሙቴላ ሻሸ ከተባሉ የእድሜ ባለጸጋ ጋር በ1990 ዓ.ም. ያደረገውን ቃለ-መጠይቅ እንደሆነ ይነግረናል። አሮጊቷ በምኒልክ ዘመን ባይኖሩም ስለምኒልክ ዘመን ስለነበረው ሁኔታ ካያቶቻቸው የሰሙትን በልበሙሉነት ይተርኩሊታል። ተስፋየ ቃለመጠይቁን የሚያቀርበው ለኛ ላንባቢዎች፣ "ያለፈውን ዘመን በጠባብ ሽንቁር ለማሳየት ይረዳል" በሚል ዓላማ እንደሆነ ይነግረናል። ቃለመጠይቅ ተብየውን ስናነብ ግን በሽንቁር ሳይሆን በጉልህ ወለል ብሎ የሚታየን የተስፋየን አፍራሽ አመለካከት እንጂ ያለፈውን ዘመን አይደለም።

ተስፋየ ሁሌም ስለታሪክ ሲጽፍ የታሪክ ሰነድ ወይም የታሪክ ባለሙያ አያጣቅስም። ይህንን ቢያደርግ እውነታው በቀላሉ ያሸንፈዋል። ስለዚህ ከታሪክ ጋር እንኳ ባይሆን ከፕሮፖጋንዳው ጋር የሚጣጣም ቀደዳ የሚቀድዱ ገጸባሕርያትን ይፈጥራል። ቃለ-መጠይቅ ያደረገላቸው ሰዎችም የሱን ቋንቋና የእድሜ ልክ ሐሳቡን የሚያስተጋቡ በመሆናቸው ገጸባሕርይ ናቸው። መልክት





ማስተላለፍያ ሬድዮው ናቸው። ተስፋየ ሐረር ከዐማራ ብቻ በተዋቀረ ሁራዊት ተወረረች የሚል ሥዕል እስከመፍጠር ሄዷል።

ጥያቄ - የዐጼ ምኒልክ ወታደሮች አማሮች ብቻ ነበሩ?

መልስ - አማሮች ናቸው ነው የሰማን። ንግድ የሚነግዱ ጉራጌዎች አብረው መጥተው ነበር። እያሰሩ መለሷቸው። ጉራጌ ሀረር እንዳይገባ ዐዋጅ አውጀው ነበር። ጉራጌዎች እየተደበቁ ሀረር ይገቡ ነበር። ሲያገኟቸው እያሰሩ ይመልሷቸዋል።

ዐማሮች ከሚያስገብሯቸው ሕዝቦች ያነሰ ስልጣኔ ነበራቸው የሚለውን መልክት ለማስተላለፍ ደግሞ የሚከተውን ሞኖሎግ ገጸባሕርይዋ አፍ ውስጥ ያስቀምጣል።

"(ዐማሮች) ጫማ አልነበራቸውም። በባዶ እግራቸው ነበሩ። በብዛት ቆዳ ያገለደሙ ነበሩ(!) የእኛ አባቶች ያን ጊዜ የፈትል ልብስ ይለብሱ ነበር። ዐማሮቹ ቆዳ አገልድመው፣ ጠመንጃ ይዘው ስናይ የሚገድሉን መስሎን በጣም ፈራን።ብለው ነግረውናል። ሲቀርቧቸው ግን ደህና ነበሩ። ብቻ ጭካኔ ነበረባቸው። ሀረሪዎችን ግን ያከብሩ ነበር። ጫማችውን እያዩ፣ ልብሳቸውን እያዩ ተገርመው፣ ከየት አገኛችሁት? ብለው በአስተርጓሚ ይጠይቁ ነበር ብለውናል። በእነርሱ ሀገር አንደኛ የሚለብሱት መኳንንቱ ብቻ ነበሩ..."

ተስፋየ በዚህ አንቀጽ ውስጥ ለማስተላለፍ የፈለገው ግልጽ ነው። ገልቱ አማሮች በስልጣኔ ብልጫ የነበራቸውን ሐረሮች እስገበሩ ለማለት ነው የፈለገው። የምኒልክ ወታደሮች ቆዳ ለባሽ፣ ባለ ባዶ እግር፣ ጨካኝ ሆነው ሲሳሉ ባንጻሩ ሐረሮች ፈትል ለባሽ ባለጫማ ስልጡን ሆነው ቀርበዋል። እስቲ ይህንን ቅጥፈት በሰነዶች እንመዝነው።

S Pirre Petrides የተባለ ጸሐፊ le Heros d'Adoua በተባለ መጽሀፉ ስለ ጨለንቆ ጦርነት ትርኢት የሚከተውን ይላል፤ "ወድያው፣ተራራው ነጭ ሽማ በለበሱ፣ በሸዋ ጦረኞች፣ አንበሳ ለምድ የለበሱ መኳንንት፣ በኦሮሞ ፈረሰኞች





ተጥለቀለቀ። ከማኸል በጸሐይ ብርሃን ላይ በሚያጥበረብር የወርቅ ካባ በለበሱ ጦር ሚኒስተርና በሊቀመኳስ ታጅቦ የሸዋው ንጉሥ ብቅ አለ።"[33]

በዚህ ጥቅስ ብቻ የተስፋየን ሁለት አንቀጾች ማስተባበል ይቻላል። በመጀመርያ የምኒልክ ወታደሮች ዐማራ ብቻ ሳይሆኑ እንደ ሌላው ጊዜ ኅብረብሄራዊ እንደነበሩ እናያለን። የጨለንቆ ተራኪ፣ "በኦሮሞ ፈረሰኞች መጥለቅለቁን" ተነግሮናልና። እዚህ ላይ የኦሮሞ ፈረሰኞች ከምኒልክ ወገንም እንደነበሩ መጠቀሱን ልብ ይበሉ። የጨለንቆን ጦርነት የዘር ማጥፋት ጦርነት ማድረግ የማያስኬደው ለዚህ ነው።

ሁለተኛው፣ የምኒልክ ወታደሮችን ቆዳ አገልዳሚ አድርጎ ለማቅረብ የተደረገው ጥረት ልክ አለመሆኑን እንረዳለን። ወታደሮች ሽማ ለባሽ ናቸው። ያንበሳ ለምድን ቆዳ ብለው የሚያጣጥሉት አይደለም። በጥበብ የሚሠራ የክብር ልብስ ነው። "እነሱ ሀገር (ሸዋ) አንደኛ (ሐረር) የሚለብሱ መኳንንት ብቻ ናቸው" የሚለውም ጥራዝ ነጠቅነት ይመስለኛል። መኳንንት በልዩ የሚለብሱት ጃኖ ነው። መሸመት እስከቻለ ድረስ በየትኛውም ማእረግ ያለ ሌጋ ሽማ እንዳይለብስ የሚከለክል ሕግ አልነበረም።

እውነት ለመናገር በጊዜው የሀረሮች አለባበስ ከሸዋ ሰዎች ጋር ሲወዳደር መሠረታዊ ልዩነት አልነበረውም። በርግጥ በጊዜው ጫማ የማድረግ ልማድ በወታደሩ ዘንድ አልነበረም። ይህ የሆነው ግን በእጦት ሳይሆን ስላልመረጡት ወይም ስላልፈለጉት ነው። እርካብ ለመቆንጠጥ ስለማይመች በቸልታ ትተውት ነው። በሀረሮች ዘንድ የተለመደው ሽፍን ጫማ ሳይሆን ነጠላ ጫማ ነበር።

[33] Soudain, les collines se couvrirent des masses de guerriers du choa: multitude de « chammas » blanches, chefs portant criniere de lion, cavaliers gallas.A leur centre, parut le roi du choa, entoure de son etat-major et des ses « like-makous » aux uniformes d'or, resplendissant au soleil





አማሮች እንደብርቅ አይተውት ወይም ከዛ በፊት ሳያዩት ቀርተው፣ "ከየት አገኛችሁት" ይሉ ነበር፣ ማለት ቧልት ነው።

ተስፋየ ስለምኒልክ ወታደሮች ባሕርይ ሲገልጥ፣ "ሲቀርቡዋቸው ደህና ነበሩ" የሚል ሐረግ አምጥቶ ሚዛናዊ ለመምሰል ይሞክርና ወድያው ግን፣ "ብቻ ጭካኔ ነበረባቸው" በሚል ቃል ያፈርሰዋል። ደህና መሆንና መጨከን እንዴት አብረው ይሄዳሉ?

ተስፋየ ምናባዊትን አሮጊት በጣልያንና በዐማራ መካከል ስለነበረው ልዩነት እንዲነግሩት ከጠየቃቸው በኋላ የሚከተውን እንደመለሱለት ይነግረናል።

"በፍትሕ በኩል ግን ጣሊያን ይሻል ነበር። ዐማራ ሲመጣ፣ 'ሰው የገደለ ይገደል!' የሚል ዐዋጅ አመጡና ርስበራስ መተላለቅ ሆኖ ነበር"[34]

ይህ አንቀጽ፣ "የገደለ ይገደል" የሚለውን ሕግ ከዐማራ መምጣት በፊት በሐረር አይታወቅም ነበር የሚል ታሪክ ለመፈብረክ የተጻፈ ለመሆኑ አያጠራጥርም። ታሪከን ስንመረምር ግን በጥንቲቱ ሐረር የነበረው የፍትሕ ሥርዓት ከሰሜኑ የኢትዮጵያ ሥርአት ጋር መሠረታዊ ልዩነት እንዳልነበረው እንገነዘባለን። ለምሳሌ በአሚር አህመድ ዘመን አንድ ነፍስ ያጠፋ ሰው፣ በሟች ዘመዶች እንዲገደል ይፈረድበት ነበር። ታዋቂው የሀረር አሳሽ ሪቻርድ በርተን ዝርዝሩን እንዲህ ሲል ይነግረናል[35]፡

"ነፍስ ገዳዩ፣ እጅና እግሩን ታስሮ፣ ፊቱን ተጋርዶ፣ ገበያ ይወጣል። የሟቹ የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው በመከትከቻ የቄራ ቢላዋ አንገቱን ይቀነጥሰዋል። አስከሬኑ ለዘመዶቹ እንዲረከቡት ይደረግና የሙስሊም አቀባበር ይደረግለታል"

[34] የስደተኛው ማስታወሻ (ገጽ 46)

[35] The murderer is placed in the market street blindfolded, and bound hand and foot, the nearest of kin to the deceased then strikes his neck with a sharp and heavy butcher's knife and the corpse is given over to the relations for Muslim burial vol 2 (Page 21)

ይህ እንግዲህ ምኒልክ ሐረርን ከመጠቅለሉ አስቀድሞ ለዘመናት ሲሠራበት የነበረው የሐረር የወንጀለኛ ቅጣት ነው። "የገደለ ይገደል የሚለውን ፀማራ ይዞት መጣና መተላለቅ ሆነ" የሚለው ስም ማጥፋት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም።

ተስፋዬ በዚህ ቃለ መጠይቁ በጨለንቆ ጦርነት ሳብያ የሐረሬ ሕዝብ ቁጥር እንደተመናመነ ይጠቅሳል። መጀመርያ የኢድሜ ባለጸጋዋ እሙተ ኻሽ "ሐረሬ አነስ። ያኔ ያለቁብን ወጣቶች ምክንያት ይኸው ዛሬ ድረስ ሰው ትንሽ ነው" ማለታቸውን ሲጠቅስ መጣጥፉን ከመዝጋቱ በፊት፤ "ጥር 14፤ 2007 120ኛው የጨለንቆ ጦርነት ሲታሰብ፤ ታሪክ ዐዋቂው አብዱ ሰመድ እድሪስ ንግግር ማድረጉን በዜና ሰምቻለሁ። በንግግሩ የሐረሬ ሕዝብ ብዛት ትንሽ እንዲሆን አስተዋፅኦ ካደረገው መካከል የጨለንቆ ጦርነት ዋናው መሆኑን ጠቅሷል። በዚያን እለትም ለመጨረሻው የሐረሪዎች አሚር መታሰቢያ ተተክሏል" ይላል።

ተስፋዬ፤ "ታሪክ ዐዋቂው" ሲል አብዱ መሰድ እድሪስ የተባለው ሰውየ የተናገረውን ንግግር የታሪክ ዕውቀት አድርገን እንድንወስድለት መፈለጉን ያሳያል። ይሁን እንጂ ይህ በታሪክ ስም የቀረበ አሉባልታ ከታሪክ ዕውቀት ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም።

በጨለንቆ ጦርነት በአሚር አብዱላሂ በኩል፤ የተሰለፈው የኦሮሞ ሶማሌ ኢሳ፣ ሀረሬ እና ግብጽ ተወላጅ ወታደር ተደማምሮ ባጠቃላይ ከአራት ሺህ የማይበልጥ ሲሆን በጦርነት የወደቀው ከግማሽ በታች መሆኑ በታሪክ ተመዝግቧል።[36] በምኒልክ ዘመን የውጭ ሀገር ጎብኚዎች የሐረርን ሕዝብ ቁጥር አምሳ ሺህ ገምተውታል። ከዚህ ውስጥ የሞተው አንድ ሺህ ገደማ ነው። ከዚህ

[36]Passing through the battle field the nextday Rgazzi saw some hundred dead, mostly oromo and Issa Somali and noted that it was reported the Amir had lost a thousand dead while only a little over 100 shoans had been killed and 600-700 wounded. Journal of Ethiopian studies vol 9 no 2





መካከል ብዛት ያለው የኦሮሞና ኢሳ ወታደር መሆኑ ተጠቅሷል። ታድያ የጨለንቆ ጦርነት ሕዝባችንን አሳነሰው የሚባለው በምን አግባብ ነው?

የሐረሬ ሕዝብ ቁጥሩ ተመናምኗል ከተባለ፤ ሰበቡ አንድ ሰአት የፈጀው የጨለንቆ ጦርነት ሳይሆን በየጊዜው በአገሩ ላይ የሚደርሰው ወረርሽኝ መሆን አለበት። እዚህ ላይ የሐረር አስተዳዳሪ የነበሩት ራስ እምሩ በግለ ታሪካቸው፤ ገጽ 89 ላይ፤ "በሺህ ዘጠኝ መቶ አሥራ አንድ፤ ዓመተ ምህረት ባውሮፓና በእስያ አድርጎ የመጣው የንፋስ (የግሪፕ) በሽታ በኢትዮጵያም በመላው ሀገር ገብቶ ብዙ ሰው ሞተ። ያን ጊዜም ሐረር ነበርኩ። እዚሁም ሐረርጌ ከህዳር ወር ጀምሮ እስከጥር መጨረሻ ሰሞን ድረስ በጣም ከፍቶ በከተማው ውስጥ ብቻ እንኳ ከሰማንያ እስከ መቶ ሃያ በየቀኑ ይሞት ነበር።" ብለው ጽፈዋል።

የዘመናችን የብሔር ፖለቲካ ልሂቃን ኅብረብሄራዊነትን እና መቻቻልን በመኮትኮት ፋንታ ቅሬታን በመፍብረክ ተጠምደው ቆይተዋል። የቅሬታ ፍብረካው ቤተሙከራ ከሆኑት ከተሞች አንዷ ሀረር መሆኗን ከላይ ያነሳኋቸው ነጥቦች የሚያሳዩ ይመስለኛል። የቅሬታ ፍብረካውን ያስፈሪነት መጠን ለመረዳት የአርሲን ዘመቻ ታሪክ መፈተሽ ይጠበቅብናል።





## ምኒልክና አርሲ

ኢትዮጵያዊው ቢስማርክ ዳግማዊ ምኒልክ ማእከላዊ መንግሥትን ለማቋቋም ካደረጋቸው ዘመቻዎች ውስጥ ትልቅ ምኪታ የገጠመው አርሲ ላይ ነው። ምኒልክ አርሲዎች ክንድ ተከታታይ ሽንፈት ከደረሰበት በኋላ በራስ ወልደ ገብርኤልና በራስ ዳርጌ አልከ አስጨራሽ ዘመቻ አማካኝነት አሸንፎ አርሲን ወደ ግዛቱ ቀላቀለው። በጦርነቱ ከአስገባሪውና ከገባሪው ወገን አያሌ ወታደሮች አልቀዋል። ውጊያው የተካሄደው፤ ነፍጥ ቢታጠቁ የነጉሡ ወታደሮችና ከጦርና ጋሻ ፈረስ ውጭ ምንም በሌላቸው የአርሲ ጎበዞች መካከል በመሆኑ ከተከላካዩ ወገን ያለቀው በቁጥር እንደሚልቅ እሙን ነው:: የአርሲ ጦርነት ከተካሄደ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ወደ ኦሮሞ ምድር የደረሰው ደ ሳልቪያክ የተባለ የፈረንሳይ ሀዋርያ ከአርሲዎች በሰበሰበው መረጃ ተመሥርቶ እንደጻፈው ራስ ወልደገብርኤል የአርሲዎችን አይበገሬነት ለመስበር ባንድ ቀን ብቻ የአራት መቶ አንጋፋዎችን ክንድ አስቆርጧል። ይህ ጸሐፊ ከንዳቸውን ካጡት ትልልቅ ሰዎች ጥቂቶቹን ባይኔ በብረቱ አይቻለሁ ብሏል።





ምንም እንኳ በማስገበሩ ዘመቻ ወቅት ከፋና ወላይታም የማያንስ ጉዳት የደረሰባቸው ቢሆኑም "የምኒልክ አስከፊ በደል" ማሳያ ተደርጎ በብሔርተኞች የተመረጠው አርሲ ነው። ይህ ታሪካዊ ክስተት በወንድማማች ህዝቦች መካከል የጥል ግድግዳ ሆኖ ለቆመ ሐውልት መሠረት ሆኗል።

ርግጥ ነው፤ አርሲ በስጦታ ወይም በስምምነት የተደባለቀ ሀገር አይደለም። የተገኘው በብዙ አገሮች እንደተደረገው፤ በጉልበትና በነውጥ ነው።

የብሔርተኛው ወገን፤ "እፍኝ ቆሎ ይዞ ወደ አኖሌ" ይጠጋል። ይህ ወገን፤ የአምቢተኛ ወታደር እጅ ተቆረጠ ሲባል፤ "ሰላማዊ ሴቶች በሰልፍ እንዲያልፉ ተደርጎ ጡታቸው ተቆረጠ፤ አባዱላዎች ተመርጠው እንዲኮላሹ ተደረገ፤ ምኒልክ ነፍጥ አልበቃ ብሎት ፈንጣጣ ፈብርኮ ሰላማዊ ሕዝብ ፈጀ" እያለ በተደረገው ላይ ያልተደረገ የምናብ ፍሬ እየጨመረ የሚተርት ነው። በተለይ አንዳንድ ምሁራን ከዚህ ዐልፈው ጦርነቱ በ"ወራሪው ፀማራ"ና፤ በ"ሰላማዊው ኦሮሞ" መካከል የተደረገ አስመስለው ለማቅረብ መሞከራቸው አሳዛኝ ነው።

በሌላ በኩል በጉልበት ሌላውን ማስገበር አያሌ ህዝቦች በፈረቃ ያደረጉት ሆኖ ሳለ አንድ ንጉሥና አንድ ብሔረሰብ ብቻ ጠቅልሎ የያዘው አድርገው ለማሳየት የሚሞክሩ አሉ። የዚህ ምእራፍ ዓላማ ከላይ የተጠቀሱትን የተሳሳቱና ጠንቀኛ አስተሳሰቦች ማቃናት ነው።

ከብሔርተኛው ጎራ የሚቀርበው ክርክር መነሻ ሰብአዊ መብት ነው። ሰብአዊ መብት የሚባል ነገር ዛሬ በምናውቀው መልኩ ባስገባሪም ሆነ በገባሪ አባቶቻችን ዘንድ አይታወቅም። ለቀደምቶቻችን፤ በጉልበት የሚያንሳቸውን ጎረቤት ንብረት ርስትና ሕይወት መንጠቅ የጉሮ ዘይቢያቸው ነበር። ይህንን ሁናቴ በዘመናዊ ሰብአዊ መብት መለኪያ መገምገም የሚያዋጣ አይመስለኝም።

እስቲ ስለሰብአዊ መብት፤ ስለርህራሄና ስለጭካኔ ከማውራታችን በፊት በቅድመ ምኒልክ ስለነበረው ስለጥንታዊው የአርሲ ማኅበረሰብ እንመርምር።

## ቅድመ ምኒልክ አርሲ

ዊልያም ሐሪስ የተባለ በምኒልክ አያት በሣሕለሥላሴ ዘመን ሸዋንና አካባቢውን የጎበኘ አሳሽ በጊዜው ስለነበረው የአርሲ ማኅበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ሲጽፍ፤

"በተራራ እቅፍ ውስጥ የሚኖሩትን ፣ከላይ እስከታች ሰውነታቸውን ስብ ተለቅልቀው ራቁታቸውን የመዋጋት ልምድ ያላቸውን የጦር-ጭልፊቶች (ሣሕለሥላሴ) ጦር ሊያዘምትባቸው አልደፈረም። ምህረት የለሽና ሌላውን የማጥቃት ልማድ ያላቸው ሲሆኑ ... በዙርያቸው ያሉትን ጎሳዎች የሚያሸብሩ እንደሆኑ ይነገርላቸዋል" ይላል።[37]

ሀሪስ ገለጻውን በመቀጠል የዘመኑ አርሲ ወንዶች በውጊያ ላይ አንዱን ፈረስ ለሁለት ተፈናጠው እየተጋገዙ እንደሚዋጉ፣ እንደ መጋዝ ጥርስ ያለው ጦርና በኤሊ ድንጋይ አምሳል የተሠራ ጋሻ ለውጊያ እንደሚጠቀሙ መዝግቧል።

ይህ መንገደኛ ባካባቢው በነበረበት ወቅት አንድ የአርሲ ቡድን በከረዩ አርብቶ አደሮች ላይ አደጋ ጥሎ፣ አርብቶ አደሮቹን ሁሉ በጦር ገድሎ ከብት ዘርፎ መሸሹን ዘግቧል።

የጥንቶቹ አርሲዎች፣ በገዳ ሥርአት በመተዳደርና በቋንቋ ከሌላው የኦሮሞ ጎሳዎች ጋር አንድ ቢሆኑም ያኗኗር ሥርአታቸው ከሌሎች በበለጠ ነውጠኛ ነበር ይባላል።ሀንቲንግፎርድ The Oromo of Ethiopia, the Kingdoms of kafa and Janjero በተባለው መጽሐፉ ስለጥንታዊው የአርሲ የአኗኗር ዘይቤ የሚከተለውን ጽፏል።

Even the rest of the Oromo themselves looked up on Arsi as especially ferocious, for them to murder at the time of great festivals, is both an honor and a social necessity, though if an

[37]The highlands of Ethiopia (page 225)





Arusi kills a fellow-tribesman it is believed that he will get leprosy; but inter-tribal murders are allowed without penalty, particularly at the end of each Luba period. Before setting out to commit a "murder for honor" the Arusi drinks large quantities of blood, which produces a condition of frenzy. Since the murder nearly always a cowardly one, they hide and kill unsuspecting wayfarers, emasculating them and taking home the genitals a trophy. On their return the murderers enact the scene, with cries of triumph and derisive imitation of the victim's anguish. Only after such a murder may a man wear a copper ring in his ear. When several men take part in a murder, the honor goes to him who strikes the first blow. Hence there is often much quarreling. A man who sets out before a festival to kill and returns unsuccessful is not only ridiculed, but is branded on the forehead and given a small jar of milk which he has to make into butter as a sign that he is not a man. No man could hold a position in the gadaa-government unless he had killed a man or a large animal (p 64)

ፍሬ ነገሩን ተርጉሜ ሳቀርበው ይሄን ይመስላል

"ሌሎች የኦሮሞ ጎሳዎችን ሳይቀር አርሲዎች ነውጠኛ አድርገው ይመለከቷቸው ነበር። ለነሱ እያንዳንዱ ክብረ- በአል መጨረሻ ላይ ሰው መግደል የክብር ምልክት እና ማኅበራዊ ግዴታ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። አንድ አርሲ ሌላውን አርሲ ከገደለ ለቆምጥና ይዳረጋል የሚል እምነት ነበር። ይሁን እንጂ አርሲ ከገደለ ለቆምጥና ይዳረጋል የሚል እምነት ነበር። ይሁን እንጂ አርሲ የሌላውን ጎሳ አባል እንዲገድል ተፈቅዶለታል። አንድ አርሲ ለግድያ ከመሰማራቱ በፊት ለወኔው ማነሳሻ ብዙ(የኩባት) ደም ይጠጣል። ከዚያም





ሆገር አማን ነው ብሎ የሚሄደውን መንገደኛ አድብቶ ይገድልና ብልቱን ቆርጦ ወደጎጆው ይመለሳል። ሲመለስ ፉከራ ያሰማል። እንዲሁም የተገደለው ሰው ያሰማውን የጣእር ድምጽ አስመስሎ በመጮህ ያፌዛል። አንድ ወንድ ይህን ማድረግ ከቻለ ብቻ ነው በጆሮው ላይ የብር ሎቲ ማንጠልጠል የሚፈቀድለት።

"ግድያው የተፈጸመው በቡድን ከሆነ፤ የመጀመርያ በትር ያሳረፈው የገዳይነቱን ክብር ይቀዳጃል። በዚህ ምክንያት (እኔ ነኝ የቀደምሁ) በሚል ፉክክር ጠብ የሚቀሰቀስበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ከክብረበአሉ በፊት ሰው ገድሎ መመለስ ያልቻለ ሰው ውርደት ይከናነባል።. አንድ ሰው ትልቅ አውሬ ወይም ሰው ካልገደለ በቀር በገዳ ሥርዓት ውስጥ ቦታ አይኖረውም።"

የምኒልክ ሠራዊት ፈጸመ የሚባለውን ግፍ ከዚህ ታሪካዊ መደላደል ላይ ቆምን ካላየነው በቀር ቀና ፍርድ ልንፈርድ አንችልም። ግድያና የነውጥ ዘይቤ ድሮም የነበረ ነው እንጂ ለመጀመርያ ጊዜ በዳርጌ ፈረስ ተጭኖ ወደ አርሲ የመጣ አልነበረም።

በቅርቡ ፣ መብራትና ውሃ ብርቅ በሆነበት ያርሲ ገጠራማ መንደር ውስጥ ሀያ ሚሊዮን ብር የፈጀ ሐውልት ተገንብቷል። ከቀራጺውና ከጥቂት ጥቅም አብሮቹ በቀር በሐውልቱ መገንባት የሚጠቀም ያለ አይመስለኝም።

በሰለጠኑ አገሮች ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የሰማእታት ሃውልቶች ማራኪና አይነጉብ ሆነው የተሠሩ ናቸው። የውበትንና የኪነትን ስሜት ከፍ አድርገው ይሰቅላሉ። ተስፋን ይቅርባይነትን በተመልካች ልብ ውስጥ ያቀጣጥላሉ። ዲሲ የሚገኘው የማርቲን ሉተር ሐውልት ለጠብና ለቂም የሚያነሳሳ መልክት የለውም። ኪንግ ጅንን ብሎ ቆሞ ከጀርባው፣ "ከተስፋ መቁረጥ ተራራ ተፈልፍሎ የወጣ የተስፋ ዐለት" የሚል ልብን በበጎ ሐሳብ የሚሞላ ጥቅስ እናያለን። በሰለጠኑ ያውሮፓና ያሜሪካ ከተሞች አደባባይ ቆመው ያየኋቸው ሐውልቶችና መታሰቢያዎች የሕይወትና የኪነጥበብ ፍቅር እንዲያድርብን





የሚያደርጉ ናቸው። የአኖሌን ሐውልት የጠረበውና ያስጠረበው አካል ግን ስለ ሕይወት፣ ስለ ውበትና ስለኀላፊነት ደንታ ያለው አይመስልም።

ከሐውልቱ ጀርባ ያሉ ፖለቲከኞችና ባለስልጣኖች ለምን ይህን አደረጉ? ምናልባት በማስገበሩ ጦርነት ወቅት ሕይወታቸውንና አካላቸውን ያጡ ያካባቢው ሰዎችን ማሰብ ፈልገው ይሆናል እንበል። ጉዳዩን እስቲ በ"ሰብአዊነት" ሚዛን እንመልከተው። በምኒልክ የጦር አበጋዞች አማካኝነት በነፍጥ ለረገፉና እጃቸውን ለተቆረጡ የአርሲ ወታደሮች የሚቆረቆር ዜጋ፣ አግረ መንገዱን ቀደምት አርሲዎቹ ለክብር ሲሉ በየጊዜው በወጡበት ያስቀሯቸውን የሌላ ብሔር ተወላጆችን ማስታወስ አይጠበቅበትምን? ማስታወስ ማለት የተወጋነውን ብቻ መርጦ ማስታወስ ማለት አይደለም። ባባቴ ላይ የደረሰውን ግፍ አልረሳም የሚል ሰው አባቱ በሌሎች ላይ ያደረሰውን ግፍም አብሮ ለማስታወስ ወኔው ሊኖረው ይገባል። አለበለዝያ ያንዱ ሕይወት ከሌላው ሕይወት የበለጠ ዋጋ አለው ወደሚል አድልኦ ይመራል።

የዘመናችን የብሔረሰብ ፖለቲካ የታሪክ አተረጓጎም ዋናው ስህተት ታሪካዊ በደሎች የመነጩት ከዘመኑ መንፈስ ሆኖ ሳለ ካንድ ብሔር ተፈጥሮአዊ ጠባይ የተቀዱ አስመስሎ ማቅረቡ ነው። ብሔረሰቦች በባህል እና በቋንቋ ቢለያዩም ዞሮ ዞሮ ያንድ የዘመን ባሮች ናቸው። ለምሳሌ፣ በዮሀንስና በምኒልክ ዘመን መንግሥት የአመጸኛን አካል በማጉደል መቅጣት ፍትሐነገሥትን መሠረት ያደረገ ነበር። ይሁን እንጂ ከፍትሐነገሥት ውጭ የነበረው የኦሮሞ ማኅበረሰብም ለዚህ አይነቱ ቅጣት እንግዳ አልነበረም። ለምሳሌ፣ በኦሮሞ ሕግ ከሌላ ሰው ጋር ሲያመነዝር የእጅ ከፍንጅ የተያዘ ሰው እጅና እግሩን ይቆረጥ እንደ ነበር ዲአባዲን ጠቅሶ ሀንቲንግ ፎርድ ዘግቧል።[38]

ያም ሆኖ ፤ ከጥንት ጀምሮ በሰውነት ድካማቸው የተነሣ እጅና እግራቸውን ላጡ ኦሮሞዎች ተቆርቁሮ ሐውልት ለማቆም የሞከረ አልነበረም። ስለዚህ

[38]ሀንቲንግፎርድ፣ ከላይ ከተጠቀሰው (ገጽ 62)

ጉዳዩ ጭካኔን የማውገዝና "ስብእዊነትን" የማክበር ጉዳይ ሳይሆን አንዱን ወገን ጭራቅ አድርጎ የማሳየት ዘመቻ ይመስላል።

ምኒልክ የፈጠረውን መንግሥት ወርሶ ከጠረፍ ሀገር ነዋሪዎች ግብር የሚሰበስብ ገዥ ፓርቲ ጸረ ምኒልክ የሆኑ ሃውልቶች እንዲሠሩ መፍቀዱ በራሱ ምጸት ነው።

ምኒልክ ቤተመንግሥት ውስጥ ወሳኝ የነበሩ ሰዎች ከተለያየ ብሔረሰብ የተገኙ እንደ ሆኑ ሁሉ በማስገበር ዘመቻ የተሳተፈው ሠራዊትም እንዲሁ ኅብረብሄራዊ መሆኑ እሙን ነው። ይልቁንም ኦሮሞ ያልተሳተፈበት የምኒልክ ዘመቻ ማግኘት ይከብዳል ። ወላይታንና ከፋን ለማስገበር በተደረጉት ዘመቻዎች አባ ጅፋር የኦሮሞ ፈረሰኛ ጦር ይዞ ከመዋጋቱ በላይ የምርኮ ተካፋይ እንደ ነበር በታሪክ ተመዝግቧል ። የጂማው ሞቲ የየምን ግዛት በምኒልክ መልካም ፈቃድ ከተቆጣጠረ በኋላ የሞችን በባርነት በመፈንገል የገቢ ምንጭ አድርጓቸዋል። በወላይታ ዘመቻ ጦናን አቁስለው የማረኩት የራስ ሚካኤል ኦሮሞ ነፍጠኞች ናቸው።

የአርሲ ጉዳይም ከዚህ የተለየ አይደለም። ቾሩሊ "የኦሮሞ ሕዝብ ሥነቃል" በተሰኘው ሥራቸው መዝግበው እንዳቆዩልን በአርሲ ዘመቻ ከሚኒልክ ወገን ቀደም ዘማቾች አንዱ ፊታውራሪ ዱፌራ የሚመራ የኦሮሞ ጦር ነበር። ባስገባሪውምና በገባሪው በኩል የቀረቡ ተቃራኒ ይዘት ያላቸው የኦሮምኛ ፋከራዎች ይህንኑ ሐቅ ያረጋግጣሉ። እስከንድር ቡላቶቪች የተባለው የሩሲያ ወዶገብ ወታደር በዘመኑ የታዘበውን ሲመሰክር in recent subjugation of the Oromo by the Abyssinians, the most violent fighters in the ranks of the Abyssinians were themselves Oromo.

"ኦሮሞን ለማስገበር በቅርቡ ባበሻዎች በተደረገው ዘመቻ ባበሻው ሠራዊት ውስጥ እጅግ ነውጠኛ የሚባሉት ተዋጊዎች ራሳቸው የኦሮሞ ተወላጅ ነበሩ" ይላል። ነገሩን የጠቀስኩት የኦሮሞ ወታደሮች ከሌላው የበለጠ ነውጠኞች ነበሩ፤ የሚል መልክት ለማስተላለፍ አይደለም። የምኒልክ ሠራዊት





ኅብረብሄራዊ ይዘት እንደነበረው ለማስታወስ ያክል ነው። ይሄን ማስታወስ፣ "የሞትንም እኛ ያለንም እኛ" የሚለውን እውነታ አስረድቶ ያቻችለናል።

## የጡት ቆረጣ ነገር

ባርሲ ዘመቻ የምኒልክ ወታደሮች የሴቶችን ጡት ቆርጠዋል የሚለውን ክስ ብዙ በራሽ ብሔርተኛ ጸሐፊዎች ባንድ ድምጽ የተቀበሉት ቢሆንም ተስፋየ ገብረአብ ያክል ሲኒማዊ ምስል ስሥቶ ያቀረበው የለም። ተስፋየ አንድ ገጸባሕርይውን እንዲህ ያሰኘዋል።

"(ነፍጠኞች) የሴቶቻችንን ጡት እኛ ከበግ ላይ ጸጉር እንደምንሸልተው እንዲያ ነበር የሚቆርጡት። እነዚህ ሰዎች በግ ሲያርዱ በስምአብ ብለው ይጀምራሉ። ግን ሃይማኖት አለን የሴቶቻችንን ጡት ሲቆርጡ ግን በስምአብ አይሉም። ይሉናል።"[39]

የበደሉ ሴቶችን ጡት በመቁረጥ መቅጣት በታሪክ ውስጥ በቀዳሚነት ተጠቅሶ የምናገኘው በአክሱም ነገሥታት ዜና መዋእል ውስጥ ነው። ዮዲት የተባለች የንጉሥ ዘር የሆነች እንዲት ሴት ትቾገርና ወደ አክሱም ትወርዳለች። በዚያም በሴተኛ አዳሪነት ትሰማራለች። በዚህ ዐይነት ስትኖር ከአክሱም ጽዮን ዲያቆናት አንዱ በፍቅሯ ይነደፋል። የግብረሥጋ ጥያቄ ሲያቀርብላት እምቢ ትላለች። በፍትወት የነደደው ዲያቆን እሷን ለመማረክ ካክሱም ጽዮን ቤተክርስትያን የወርቅ መጋረጃ ቀድዶ ያመጣላታል። በዚህ የተቆጡት ያክሱም ጽዮን ካህናት ዮዲትን አይቀጡ ቅጣት እንድትቀጣ ይፈርዱባታል። ቅጣቱ ምን ነበር? "ወፈትሁ ፍትሐ እንዘ ይብሉ ይምትሩ አጥባእቲሃ ዘየማን ወይስድድዋ እምሃገር ወገብሩ ከማሁ" ይላል ታሪክ ነገሥት፣[40] ትርጉሙ፣ "ቀኝ ጡቷን

[39] የቡርቃ ዝምታ ፤ ገጽ 93
[40] የቁስ ዝዘዝ ተክለሃይማኖት ያክሱም ታሪክ ነገስት በስርግው Ancient የተጠቀሰ፤ (ገጽ 228)





ቆርጠው ካገር እንዲያባርሯት ፈረዱባት። እንደፈረዱትም አደረጉ" ማለት ነው።

ዮዲት ቁስሏ ከዳነላት በኋላ ለብቀላ በአብያተክርስትያናት ላይ ውድመት እንዳደረሰች በሰፊው ይተርካል። ትረካው እውነት ይሁን አይሁን ማረጋገጥ ከባድ ነው። ይሁን እንጂ የጡት ቆረጣ ቅጣት የማይታሰብ እንዳልነበረ ይህ ትረካ ያስረዳል።

"ለኔ የማይገዛ ካለ ወንዱን ቁላውን ሴቱን ጡቱን እሰልባለሁ" የሚለው ዐዋጅ በነገሥታት እና ዘመን ባስነሳቸው አምባገነኖች ይነገር ነበር። አለቃ አጥመ ጊዮርጊስ፤ የየጁው ኦሮሞ ጉግሳ እና በሸዋው መርድ አዝማች ስብስትያኖስ ጡት መሰለብን የሚገልጽ ዐዋጅ እንደነበራቸው ሲጠቅስ ፤ አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ ደግሞ ዐጼ ዮሃንስ አራተኛ ወደ ጎጃም በዘመተ ጊዜ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ዐዋጅ እንዳስነገረ ጠቁሟል።[41]

ይሁን እንጂ እንዲህ ያለው ዐዋጅ ሽብር ከመንዛት ዓላማ ባለፈ በተግባር ስለመፈጸሙ የሚያስረዳ ሰነድ አልገጠመኝም። የወንድን ብልት መስለብ በብዙ ቦታ ይፈጸም እንደነበር የሚያሳዩ የተረጋገጡ ሰነዶች ከውጭ ሀገር መንገደኞችም ሆነ ከአገራችን ጸሐፊ ትእዛዛት ስናገኝ ጡት ቆረጣ መፈጸሙን የሚያረጋግጡ ምስክርነቶች ግን አልደረሱንም።

አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት፣ በአርሲ ጦርነት የሴቶች ጡት ተቆርጦ ከሆነ በጊዜው የነበሩት የታሪክ ጸሐፊዎች ለምን አልመዘገቡትም? የሸዋ ጸሐፊዎች አለቃ አጽሜና አለቃ ገብረስላሴ በዚህ ጉዳይ ላይ የመዘገቡት ነገር የለም። እኒህ ጸሐፊያን የራሳቸው ወገን የሆነው ሰራዊት የሚፈጽመውን ግፍ በኩራት አልፎ አልፎም በወቀሳ የመዘገብ ልምድ እንዳላቸው ስናይ፣ ሆን ብለው ዘለውት ነው የሚለውን ድምዳሜ መቀበል ያቅተናል።

[41] "ከዚህ በኋላም አጤ ዮሀንስ ስምቶ ተናደደ፤ ስትገባ ግባ ሳትገባ ሴቱን ጡቱን ወንዱን ብልቱን አይተርፈኝም ብሎ ላከ"፤ የአለቃ ተክለኢየሱስ ዋቅጅራ ዜና መዋእል፤ በግርማ ጌታሁን የተጠረዘ የእጅ ጽሁፍ፤ (ገጽ 128)





ስለአርሲ ጦርነት መረጃ የሰበሰቡ፣ የኦሮሞ ወዳጅ እና የምኒልክ ነቃፊ የነበሩ ያውሮፓ መንገደኞች ስለ ጉዳዩ ያሉት ነገር አለመኖሩ ጥርጣሬያችንን የበለጠ ያጎላዋል። ለምሳሌ ማርቲያክ ደ ሳልቪያክ ከጦርነቱ ጥቂት ጊዜ በኋላ መጥቶ ከአርሲዎች የሰበሰበውን ታሪክ ሲያካፍል ስለጡት መቁረጥ የዘገበው ነገር የለም ። ይህ ጸሐፊ የምኒልክ ሰራዊትን፣ "ጭካኔ ማጋለጥ" የሕይወቱ አንድ ትልቅ ተልእኮ አድርጎ የሚቆጥር ሰው እንደመሆኑ መጠን፣ ጡት ቆረጣው ተፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ሳይመዘግብ አያልፈውም ነበር።

ጁልየ ቦረሊ የተባለው ሌላው በወረራው ዘመን የነበረ የፈረንሳይ ጎብኝ ከአርሲ ዘመቻ በኋላ፣ የወቅቱን አባ ሙዳ አነጋግሯል። ከኦሮሞ ጓደኞቹ መረጃዎችን አሰባስቧል። ጡት ቆረጣን አስመልክቶ ግን ያስቀረልን አንዳች ነገር የለም። ይህ ጸሐፊ ምኒልክንና ጣይቱን ውሃ ቀጠነ ብሎ በመዝለፍ የታወቀ በመሆኑ የንጉሡን ገመና ይደብቃል ተብሎ የሚጠረጠር አይደለም። ስለዚህ በየትኛውም አግባብ እንዲህ ዐይነቱን ዐቢይ ዜና ሰምቶ ሊያልፍ የሚችልበት ምክንያት አልነበረም። እንድያውም ቦረሊ በመጽሐፉ፣ ምኒልክ በአርሲ ጦርነት ወቅት አንድ ባስገባሪው ሰራዊት በኩል የተሰለፈ ወታደር (ወታደሩ ብሄሩ አልተገለጸም) የወደቀ አርሲ ሲሰልብ አግኝቶ ሞት እንደፈረደበት ዘግቧል። ምኒልክ ብሔርተኞች እንደሚስሉት ዓይነት ጭራቅ ቢሆን ኖሮ ሰላቢውን ወታደር ሹመት እንጂ ሞት አያቀዳጀውም ነበር፡

ቾሩሊ የተባሉት የጣልያን ሊቅ፣ "የኦሮሞ ሕዝብ ስነቃል" በሚል ጥናታቸው በአርሲ ወረራ ወቅት በአርሲዎች የተገጠሙ አያሌ ግጥሞችን እንጉርጉሮዎችን እና ሽለላዎች አጠራቅመው አሳትመዋል። ይሁን እንጂ ከተሰበሰቡት ግጥሞች መካከል ስለ ጡት ቆረጣ የሚያወሳ አንድም ስንኝ የለም። ይሄን የመሰለ ክስተት ደርሶ ከሆነ ካዝማሪዎች እንጉርጉሮ እንዴት አመለጠ?

ባጠቃላይ በምኒልክ ተፈጸመ የተባለው ያኖሌ ጡት ቆረጣ፣ ባገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሰነዶች ላይ ያልተመሠረተ ለመሆኑ ይሄ በቂ ማስረጃ ይመስለኛል። በአርሲ ታሪክ ጥናት ዋና ባለሙያ የሆነው ፕሮፌሰር አባስ ገነሞ በመጽሐፉ

ውስጥ ጡት ቆረጣን መፈጸሙን የሚያሳይ አንድም የታሪክ ሰነድ ማቅረብ አልቻለም።

## አምስት ሚሊዮን ኦሮሞ?

የምኒልክን ጨፍጫፊነት ለማሳየት በብሔርተኞች ከሚጠቀሱት ጽሑፎች ዋናውና ዝነኛው፣ከሩሲያዊው ወታደር ከአሌክሳንደር ቡላቶቪቼ መጽሐፍ የተወሰደ አወዛጋቢ አንቀጽ ነው። አንቀጹ በሪቻርድ ሰልተር ትርጉም እንደሚከተለው ይነበባል፤

"The dreadful annihilation of more than half of the population during the conquest took away from the Galla all the possibility of thinking about any sort of uprising."

(በወረራው ወቅት በደረሰው ከግማሽ በላይ የሚገመተው ሕዝብ እልቂት፣ ኦሮሞ ማናቸውም ዐይነት አመጽ የማስነሳት እድሉን አከሽፎበታል)

ይህን ጥቅስ በመጥቀስ ምኒልክ አምስት ሚሊዮን ኦሮሞ ጨፍጭፏል የሚለውን ውንጀላ ሚያንጸበርቁ ምሁራን ጥቂት አይደሉም። ለዋቢነት ፕሮፌሰር አሰፋ ጃለታ ሩስያዊው በደፈናው "እልቂት" ብሎ የጠራውን እርሱ "massacre" (በጦር መሳርያ የሚደረግ ፍጅት) በሚል አጥብቦ ሊተረጉመው ሞክሯል። አንባቢ የራሱን ፍርድ እንዲሰጥ ፕሮፌሰሩ ያለውን ቃል በቃል ላቅርበው፡፡

The Ethiopian government massacred half of the oromo population (5 million) and their leadership during its colonial expansion according to Alexander Bulaovichi።

ሙቸም በሰናድርና በወጨፎ አምስት ሚሊዮን ሕዝብ መጨረስ እንደማይቻል ለማወቅ ፈላስፋ መሆን አይጠይቅም። ይህንን ቀላል እውነት ለመረዳት ጥቂት





የሂሳብ ስሌት ብቻ በቂ ነው። ሌላው ቀርቶ ምኒልክ አቶሚክ ቦምብ ቢጥል እንኳ ይሄን ያህል ሰው መግደል አይችልም ነበር። ለማነጻጸርያ አሜሪካ በሄሮሺማ ላይ የጣለችው አቶሚክ ቦምብ መግደል የቻለው ሰማንያ ሺህ ሕዝብ መሆኑን እናስታውስ። ንጉሥ ምኒልክ አምስት ሚሊዮን ሕዝብ መፍጀት ችሏል ማለት ከአቶሚክ ቦምብ እጅግ ብዙ የሚልቅ መግደያ ማሽን ነበረው ማለት ነው። አለያም ከባድ መሬት መንቀጥቀጥን የሚያዝ መለኮታዊ ኀይል ታጥቋል ማለት ይሆናል።

በመሠረቱ ሩስያዊው ወዶ ገብ ወታደር ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ጭፍጨፋ ከተባለው ክስተት ከተከሰተ አሥር ዓመታት በኋላ ነው። እዚህ ድምዳሜ ላይ የደረሰው ሳይንሳዊ የሕዝብ ቆጠራ አድርጎ አልነበረም። የጣልያን ቄሳር መንግሥት ባገራችን እስኪመሠረት ድረስ የነበረው የሕዝብ ቆጠራ በግምት ላይ የተመሠረተ እንደነበር የታወቀ ነው። ከግምት ውጭ የነበረው የመረጃ ምንጭ ያስገባሪውን ሠራዊት አባላት ስንት ጠላት እንደገደሉ በመጠየቅ የሚሰበሰብ ነበር። የዚህ አይነቱ መረጃ አሰባሰብ ደግሞ አስተማማኝ አልነበረም። ተጠያቂ ወታደሮች ለዝና እንዲመቻቸው ብዙ መግደላቸውን እያጋነኑ ስለሚናገሩ የተጋነነ ድምር ማግኘት የማይቀር ነበር። ለምሳሌ፣ በወላይታ ዘመቻ የተሳተፈው ፈረንሳዊው ጆብደኛ ቫንዳርሀይም በዚህ መንገድ ከወታደሮች በሰበሰበው መረጃ በጦርነቱ 96 ሺህ ሰው መሞቱን ገምቶ ነበር። ወድያው ግን ይሄ ቁጥር ከተመለከተው እውነታ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ስላገኘው ቁጥሩን ወደ ሃያ ሺህ አካባቢ አውርዶታል።

ርግጥ ነው፣ ቡላቶቪች አንቀጽ ፍሬ ሐሳብ በራሱ ስህተት ወይም ውሸት አልነበረም። በማስገበር ጦርነቱ ወቅት አያሌ ገባሮች አልቀዋል። ይሁን እንጂ የእልቂቱ ዋና ሞተር በጊዜው የደረሰው የተፈጥሮ መቅሰፍት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑ ሰነዶችን እንዳሳይ ይፈቀድልኝ።





የኦሮሞ ሀገር ሐዋርያ ደ ሳልቪያክ በወቅቱ የኦሮሞ ምድር በድርቅ ፈንጣጣ እና ረሀብ አካባቢው መመታቱን አስታውሶ በተለይ በወቅቱ የተከሰተው የከብት በሽታ የነዋሪዎች ዋና ምግብ የነበረውን ወተት እንዲጠፋ ማድረጉን ተርኳል፡[42]

ይሄው ጸሐፊ ወረድ ይልና ፤

"የደቡብ አርሲዎች ከሰሜን ወንድሞቻቸው ጋር አምብዛም የጋራ ዓላማ አልነበራቸውም። ወረርሽኙ፣ በህዝቡ ላይ ያደረሰው ፍጅት ተባብሮ የመነሣትን እድል አምክኖታል" ይላል[43]

ከላይ ሩሲያዊው ወታደር የጠቀሰው "annihilation" በጊዜው የከኒህ ክስተቶች ጋር ተጣጥሞ ሲታይ ትርጉም ይኖረዋል። በወቅቱ የደረሰው እልቂት በጦርነት ብቻ ሳይሆን፣ ፈረንሳዩ ጸሀፊ በመዘገበው ድርቅ የእንስሳ በሽታ ርሁብና የፈንጣጣ ወረርሽኝ አማካኝነት የተከሰተ መሆኑ ግልጽ የሆነልን ይመስለኛል። ይህ ተፈጥሮአዊ መቅሰፍት አብዛኛውን የኢትዮጵያ ክፍል ጭምር ያደቀቀ እንጂ አርሲን ብቻ በልዩ መርጦ፣ ያጠቃት አልነበረም። ለምሳሌ የንጉሥ ምኒልክ ከተማ የሆነችው አንኮበር በዚህ ርሁብና ወረርሽኝ እስከፊ እልቂት ስለደረሰበት በአውሮፓዊው ጎብኝ ቫንዳርሀይም እንደቡት "የሞት ከተማ" ተብላ እስከመጠራት ደርሳለች።

አንዳንድ ሰዎች፣ ፈንጣጣን ወደ አርሲ ያመጣው ምኒልክ ነው ብለው የሚያስተዛዝብ ነገር ጽፈዋል። ይህ ውንጀላ በኩረጃ የተገኘ መሆኑን ለማሳየት ብዙ ምርምር አይጠይቅም። የአሜሪካን ታሪክ የሚያውቅ ሰው አቅኝ ነጮች ወደ አሜሪካ ሲመጡ፣ ቀይ ህንዶችን ለማጥፋት ፈንጣጣ አስገቡ የሚል ታሪክ

[42]Le ciel lui-méme se mit contre les Oromo et le éléments conjurés, famine causée par une longue sécheesse, petite vérole, épizootie qui privait de lait les habit፤ ants tout fauchait rang à vue d'oeil (Page 332)

[43]እዚያው





መስማቱ ወይም ማንበቡ የማይቀር ነው። ለምሳሌ H.L ingle የተባሉ ታሪክ ጸሀፊ፤

"ህንዶች ከነጮች የተወሰኑ የክርስትና ገጽታዎችን፣ አልኮል መጠጥና አውዳሚና በካይ የሆነውን ፈንጣጣ ወስደዋል" በማለት ጽፈዋል ።[44]

ጥቂት ጸረ- ምኒልክ ምሁራን ይህንን ታሪክ በመኮረጅ በቀይ ህንድ ቦታ ኦሮሞን፣ በነጭ ሰፋሪዎች ቦታ ደግሞ ምኒልክን ተክተው አቅርበውልናል።

በመሠረቱ ፈንጣጣ ከምኒልክ በፊት በኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ እንግዳ ስላልነበረ ምኒልክ አስገባው የሚለው ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። ይህን ለማረጋገጥ የሚፈልግ ያባ ማስያስንና በዘመነ መሳፍንት ዘመን ኢትዮጵያን የጎበኘውን የፕላውደንን ማስታወሻዎች ማንበብ ይችላል።

[44]From the white man the Indians quickly picked up…facets of Christianity, liquor and the lethal and infectious smallpox virus

# ምኒልክ የጭካኔ ቁንጮ የሆነው ከነማን ጋር ተወዳድሮ ነው?







አባትህ ለገዛ፤ እያትህ ለኑዳ
አንተ ምን አግብቶህ ትከፍላለህ ዕዳ ?
(ተመስገን ተካ፤) "ይልቅ መላ ምታ"

ሬነ የተባለ የፈረንሳይ ሊቅ፣ "ሀገር ምንድናት" በተባለ ስመ ጥር ስብከቱ፣ 'ሰዎች ሀገር ለመገንባት ከፈለጉ በታሪክ ውስጥ የተፈጸሙ አንዳንድ ግፎችን ለመርሳት ዝግጁ መሆን አለባቸው" ይላል። ለምሳሌ፣ ፈረንሳዮች፤ የቅዱስ በርተሎሜዎስን ጭፍጨፋ መርሣት ነበረባቸው። (የቅዱስ በርተሎሜዎስ ጭፍጨፋ የፈረንሳይ ካቶሊኮች በፕሮቴስታንቶች ላይ የፈጸሙት ነው። ይህ የሬነ አስተያየት ሁለት ዋና ፍሬ ነገሮችን ያስገነዝበናል። አንድም፣ ዛሬ ሀብታምና ኀያል የሆኑ አገሮች ባንድ ወቅት በነውጥ በዱላ የተፈጠሩ ናቸው። አንድም፤ አብሮ ለመኖር ሲሉ ትውስታቸው እስከመጨቆን ድረስ ሄደዋል።

በኛ ሀገር፣ በዚህ ዘመን-ዳፍንት የሬነ ምክር ጥቅም ያለው አይመስለኝም። አያሌ ዜጎች ያለፈውን በማስታወስ ተጠምደዋል። ያለፈውን ላለፉት ሰዎች እንተውላቸውና ወደፊት እንራመድ የሚል ሰው ብቅ ካለ፣ "የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ" የሚል አንገት አስደፊ መልስ ይጠብቀዋል። ያለፈውን እንርሳ በማለት የሚጎተጉት ዜጋ ያባቶቹን በደል ለማረሳሳት የሚፈልግ ብልጣብልጥ ተደርጎ ይፈረጃል።

ኢትዮጵያ ውስጥ፣ "ታሪካዊ በደሎች እውቅና መስጠት" የሚለው አጀንዳ የተወሰነ የማኅበረሰብ ክፍል የዴሞክራሲና የፍትሕ ጥያቄ እንዳያነሳ ማፈኛ ዘዴ ነው። ጌቶች፣ ገባሩን "ጭጭ ብለህ ተገዛ! አለበለዚያ በአባትህ አበሳ ምክንያት ሊበቀልህ ያሰፈሰፈውን ቡድን እንለቅብሃለን፤" እያሉት ነው። ግን ነገሩ በዛቻ ብቻ ተገድቦ አልቀረም። ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት በኦሮሚያ፣ በደቡብና በቤንሻንጉል ብዙ ሰላማዊ የዐማራ ተወላጆች በግፍ የተገደሉትና የተፈናቀሉት የታሪክ ዕዳ ተሸካሚ ናችሁ፤ በሚል ጦስ ነው።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምናልባት ማድረግ የምንችለው አንድ ነገር አለ። ሰዎች በአባቶቻቸው ላይ የተደረገውን ሲያስታውሱ እግረ መንገዳቸውን አባቶቻቸው





በሌሎች ላይ ያደረጉትን አብረው እንዲያስታውሱ ማገዝ ያስፈልጋል። ለራስ ማድላት ደመነፍሳዊ ነው። ደመ ነፍሳችንን ገርተን፣ ያለ አድልኦ ማየት ስንጀምር በኢትዮጵያ ታሪክ የተደረጉ ታሪካዊ በደሎች ሁሉ በፈረቃ የተፈጸሙ መሆናቸው ይገባናል።

በዘመናችን ምኒልክን የዱር አውሬ ነው፣ ሂትለር ነው ተብሎ ተዘፍኖበታል። ረጋሚዎችንና ዘላፊዎችን ልቡና ይስጣችሁ ህሊናችሁ ይፍረድባችሁ ብሎ፣ ዞር ማለት በቂ አይደለም። በምኒልክ ላይ ቀፋፊ ስድቦችና ርግማኖች የሚወርዱበት ምን የተለየ ነገር አድርጎ ነው? ዶሴው ይውጣና ይታይ። ንጉሡ የኦሮሞና የትግራይ አውራዎችና ጦረኞች ካደረጉት የተለየ ነገር አድርጓል?

ምኒልክን እንደ ጭራቅ የሚስሉ ሰዎች ለመሆኑ ከምኒልክ በፊት የነበሩትን ባላባቶችን ታሪክ ያውቃሉ?

የራስ ሚካኤልን ታሪክ አላነበቡም ይሆን? ያድዋ ተወላጁ ራስ ሚካኤል ስሑል ባንድ ወቅት ወረኛ ፋሲል ከተባለ የኦሮሞ ጉልበተኛ ጋር ተዋጋ። ፋሲል ተሸንፎ ሸሸ። ስሑል ሚካኤል ድል አድርጎ የማረካቸውን ሃያ የሚደርሱ የኦሮሞ ወታደሮች ዐይናቸውን በወስፌ እየነለነለ አውጥቶ ጅብ እንዲበላቸው ቡተከዚ ዳርቻ ጣላቸው። ወረኛ ፋሲል በዚህ መንገድ የታወሩት ወታደሮች ወደ አገራቸው ተመልሰው ህዝቡን እንዳያሸማቅቁበት ስለሰጋ ገደላቸው። ብሩስ የተወሰኑትን አትርፎ ለራሱ እንዳስቀራቸው ጽፏል።

ዋጨቃ የተባለ ሌላ ምርኮኛ በራስ ሚካኤል ፈራጅነት ከነሕይወቱ ቆዳው እንዲገፈፍ ተፈርዶበታል። የሚካኤል ስሑል አድናቂ የሆነ በጊዜው የነበረ ያይን ምስክር ይህን አስመልቶ ሲጽፍ፣ "ወእምድኅረዝ ተውህበ ዋጨቃ ለእለ ይጠብህዎ ከመ ዳቤላ ጠሊ. (ከዚያ በኋላ ዋጨቃን እንደፍየል ይበልቱት ዘንድ አስረከቡት) ብሏል።

በወቅቱ አገራቱን የነበርነው ያቆብ ብሩስ የዋጨቃ ቆዳ ባደባባይ ይሰቀሎ እንደ ነበር ዘግቧል። የጭካኔ ሥራ ከትግራይና ከዐማራ በመነጩ አምባገነኖች ብቻ





የሚተገበር አልነበረም። ራስ ወልደ ሥላሴ ትግራይን ለብቻው በሚያስተዳድርበት ዘመን ከቱሉማና ከጃዌ ጎሳ ወገን የሆነው የዘመኑ አባዱላ ጉጂ የተራቀቁ ጭካኔዎችን ይፈጽም ነበር። ባላንባራስ ወልደ ተክሌ የተባለውን የላስታ ባላባት ከማረከ በኋላ ጣቶቹ እንዲቆረጡ አድርጓል።

ጉጂ በጭካኔ የሚዝናና ሰው ነበር። በ1809 ጉጂ ከራስ ወልደሥላሴ ጋር ይጣላል። እናም የትግራዩ ባላባት ከሁለት ዓመት በፊት የፈጸመበትን ወረራ ለመበቀል ከህንጣሎ 12 ሰላማዊ ሰዎችን ያስጠልፍና ወደ ቤታው ይመልሳል። ከዚያ አሥራ ሁለት ውስጥ ያሥራ አንዱን ምርኮኞች ዐይን እንደ ሙጃሌ እየተነቀለ እንዲወጣ ያደርጋል። የአሥራ ሁለተኛው ሰለባ አንድ ዐይኑን ያወጣና አንድ ዐይኑን ያስተርፍለታል። ጉጂ ይህንን ያደረገው እንጥፍጣፊ ርህራሄ ስለተረፈው አልነበረም። እንዲይናው ሰውየ አሥራ ሁለቱን ሰለባዎች እየመራ ወደ አገራቸው እንዲመልሳቸው ነው። ይህንን ታሪክ የሚነግረንና ጉጂን ባካል የሚያውቀው ናትናኤል ፒርስ፣ ይህንን ጉደኛ ታሪክ የሚዘጋው በሚከተለው አንቀጽ ነው፤ "This is a trifling instance of Gojee's barbarity of which I have heard examples to horrid to relate" "ይህ ከጉጂ የጭካኔ ሥራ ዎች ውስጥ እዚህ ግባ የማይባለው ነው። ሌሎች ግን በጣም ዘግናኝ በመሆናቸው የተነካ ለወሬ እንኳ አይመቹም"[45]

ናትናኤል ፒርስ ለወሬ አይመቹም ብሎ የዘለላቸውን ጭካኔዎች አሌቃ አጽመ ጊዮርጊስ መዝግበውቸዋል። አሌቃ እንደሚነግረን፣ "ጉጂ...የታላላቆችን ራሳቸውን ያስፈልጥ ነበር።"

ዐይን በማሳወር መቅጣት ምኒልክ ወደ ሥልጣን እስኪመጡ ድረስ ቀጥሏል። በዙፋኑ ካሳ (በኋላ ዐጼ ዮሀንስ) ንጉሠ ነገሥት ተክለጊዮርጊስን በጦርነት

[45]The Life And The Adventures of Nathanel Pearce (Page 75)

ከማረከ በኋላ ዐይኑን በጋለ ብረት እንዳጠፋው የሚገልጽ ታሪክ በልዩ ልዩ ሰነዶች ተመዝግቦ ይገኛል።[46]

እንግሊዛዊው ጄኔራል ጎርዶን በ1879 ባጼ ዮሀንስ ሥር ትተዳደር ስለነበረችው ኢትዮጵያ በጻፈው ማስታወሻ፣ "የምጽፍው በጥድፍያ ነው። ይሁን እንጂ ስለኢትዮጵያ ያለኝን ትዝብት ባጭሩ እገልጻለሁ። ንጉሡ እየለየለት ነው። ሱረት የሚስቡ ሰዎችን አፍንጫ በመፎነን ትምባሆ የሚያጨሱ ሰዎችን ከንፈር በመቁረጥ ይቀጣል፤ የበደሉትን ሰዎች እጅና እግር ይቆርጣል።" በማለት ጽፏል።[47]

ራስ አሉላ አባ ነጋ፣ በ1886 የባርያ ብሔረሰብ መሪ በቂ ግብር አላስገባም በማለቱ በነዋሪው ላይ የጅምላ ቅጣት ፈጽሟል። ይህንን አስመልክቶ ሃጋይ ኤርሊክ የተባለው የራስ አሉላ አድናቂ ታሪክ ጸሐፊ ሲጽፍ፤

"አሉላ በባርያ ብሔረሰብ ታሪክ ውስጥ ከባድ የሚባለውን ውድመት አስፈጸመ። በሕዳር የመጨረሻዎቹ ሳምንታት በጋሽ ወንዝ ሰሜን ከልል የሚኖረው ሁለት ሦስተኛው የባርያ ኩናማ ብሔረሰብ ሕዝብና ቀንድ ከብት አለቀ" ይላል።[48]

ዐጼ ዮሐንስ አራተኛ ለንግሥ ቪክቶርያ በጻፈው ደብዳቤ የሚከተለውን ይላል።

[46]W.Loring a confederate solider in Egypt, (Page 323) Impressions d'ethiopie vol3 (page 17) Conti Rossini, storia d'ethiopia .vol 2, (page 238)
[47]General Gordon's journal, (page 216)
[48]Then he (Alula) ordered the greatest plunder in the history of the Baria tribes. During the last week in November, two third of the people and the cattel of Baria and Kunama north of the Gash were destroyed. -The biography Of Alula (page 105)





"ከግዛቴ ውስጥ አንዲት ሀገር አለች። ስምዋ አዘቦ የምትባል። በውስጥዋ ያሉ ሰዎች እስላምና ኦሮሞ ናቸው። እነዚያ ሸፈቱ። እኔም ዘመትኩባቸው። የመጣሁብት ነገር በእግዚአብሔር ኀይል ቀንቶኝ ተመለስሁ።"

ዮሐንስ ለቪክቶርያ ቀንቶኝ ተመለስሁ ያለውን ለንጉሥ ዊልያም አራተኛ ሲያብራራለት፤

"ባገሬ አዘቦ የሚባል የኦሮሞ ስላም ሀገር አለ። ከርሱ ሸፍታ ተነሣብኝ፤ እርሱን ለማጥፋት ዘመትሁ። እርሱንም በእግዚአብሔር ሃይል አጠፋሁት።" ብሏል። የአዘቦ ሙስሊም ኦሮሞዎች ያጼ ዮሐንስን የሃይማኖት ፖሊሲ በመቃወማቸው በሰይፍ ተደብድበዋል።

ዛሬ ታድያ፣ ራስ አሉላና ዮሐንስ ስማቸው በመንግሥት የመገናኛ ብዙሀን በስድብ አይነሳም። የመጀመርያው መቀሌ ላይ፤ ሁለተኛው አክሱም ላይ አውሮፕላን ጣቢያ ተሰይሞላቸዋል። የሚያማምሩ ሐውልቶችን ቆመውላቸዋል። የሀገር ፍቅር ስሜት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ደራሲያን ተውኔትና ግጥም ሲያጎርፉላቸው ኖረዋል። አሉላና ዮሐንስ የጭካኔ ታሪክ ቢያጡም በኢትዮጵያ ህልውና የሚቆረቆሩ ሰዎች ዘንድ የሚታሰቡት ግን በሀገር ፍቅራቸውና በጀግንነታቸው ነው። በኔ አስተያየት ይህ ተገቢ ነው። የምኒልክም ጉዳይ መታየት ያለበት ከዚህ አንጻር ይመስለኛል። ቀደምቶቻችንን ሁሉ በስሩት ግፍ ብቻ የምንስፍራቸው ከሆነ፣ "ጥቁር ሂትለር" ከሚል ስድብ የሚያመልጥ አባት አይኖረንም።

ጥንታዊ የኦሮሞ ጦረኞችም ከዚህ በጦርነት ወቅት ከዚህ ያማራው ወይም የትግራዩ መስፍን ከሚያደርገው የተለየ የሚያደርጉ አልነበሩም። ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ በሚል ዐይነት፣ ጦር ሜዳ ላይ ከሚያገኙት ወታደር ባሻገር፣ በሰላማዊው ነዋሪ ላይ በትራቸውን ያሳርፉበት ነበር። ይህንን ታሪካዊ ሐቅ ለመካድ ተረት የሚፈጥሩ ያልተመዘገበ የሚተርኩ ሰዎች አልጠፉም።

ብሔርተኛው ምሁር ፕሮፌሰር መሀመድ ሀሰን ምኒልክ ሀገር ለማስገበር ባደረገው ጦርነት ስለደረሰው ሰብአዊ ውድመት አውግቶ አያባራም። ነገር ግን፣





በሌላው ገጽ፤ ኦሮሞ ውስጣዊ መስፋፋት ባካሄደ ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ ሲጽፍ የኦሮሞ ወታደሮች ላባ ጨብጠው ወደ ጦርሜዳ የገቡ ይመስል ከደም ነጻ ሊያደርጋቸው ይጥራል። ለምሳሌ፤ በ Ethiopian Review/ June 1992 ላይ በጻፈው መጣጥፍ ኦሮሞዎች ውስጣዊ መስፋፋት ባድረጉበት ወቅት ከፊታቸው የገጠማቸውን ነዋሪ ምን እንዳደረጉት ሲነግረን፤

"በመጀመርያዎቹ የፍልሰት አሥርት ዓመታት ኦሮሞዎች በጂሃድ ጦርነት በወደሙትና ከሞላ ጎደል ሰው አልባ በሆኑ ጠፍ መሬቶች አቋርጠው ተንቀሳቅሰዋል። የተረፉት ነዋሪዎች ወይ ከኦሮሞዎች ፊት ሸሽተዋል አለበለዝያም ወደ ኦሮሞነት ተሰውጠዋል።" ይላል[49]

መሀመድ ሐሰን በዚህ ዐይነት፣ ነዋሪዎች ቤታቸውን ማንነታቸውን መነጠቃቸው ያምንና ሕይወታቸውን ማጣታቸውን ይዘለዋል። ኦሮሞ ሲያስገብር የገባር ነዋሪዎች እጣ፣ ሽሽትና ባዲስ ባህል መዋጥ ብቻ አልነበረም። አያሌዎቹ ሕይወታቸውን አጥተዋል። በግራኝ አህመድ ጂሃድ ጦርነት ማብቂያ ላይ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ቤርድሙዝ በጊዜው ለነበረው የኦሮሞ እንቅስቃሴ ያይን ምስክር ነው። አስገባሪ ወታደሮች ምን እንደሚያደርጉ ሲጽፍ፤

"ባስገበሩት ሀገር ውስጥ ያገኙትን ወንድ ሁሉ ይገድላሉ። የወንድ ልጆችን ብልታቸውን ይቆርጣሉ። አሮጊቶችን ገድለው ወጣቶችን ሳገልጋይነት ይማርካሉ" ይላል።[50]

[49]During the first few decades of their migration, the Oromo moved across lands that were devastated and depopulated by the Jihadist wars, the lands relatively empty of people either fled before them or were adopted and assimilated by them.

[50]"In the place they conquer they slay all the men, cut off the privyparts of the boys, kill the old women and keep the young for their use and service"
Richard Pankhurst, The Ethiopian Borderlands (page 284)





ምኒልክን፣ "የዱር አውሬ" ብሎ፣ የሚዘፍን ሰው፣ ምኒልክ ጥቁር አባብ ምኒልክ Minilik bofa gurracha ብሎ የሚገጥም ሰው፣ ከምኒልክ በፊት የነበሩት ባላባቶች እንዴት ያለ ጠባይ እንደነበራቸው እንዲያውቅ የሚከተለውን አንቀጽ አጋብዘዋለሁ። በንጉሥ ሣሕለ ሥላሴ ዘመን ኢትዮጵያን የጎበኘው ሀሪስ Ethiopian highlands በተባለው መጽሐፉ ቅጽ ሦስት ላይ ስለጎማው ኦሮሞ ባላባት ሲነግረን፣ "የጎማው ባላባት የሚፈጽመውን ጭካኔ ለማሰብ ይከብዳል። ጥፋተኞች እጃቸውን አፍንጫቸውንና ጆሮአቸውን ይቆረጣሉ። ዓይናቸው በጋለ ብረት ይፈርጣል። በዚህ ዐይነት ከተቆራረጡ በኋላ ሕዝቡ ይማርባቸው ዘንድ በገበያ ማኸል እንዲያልፉ ይደረጋል። የጦር ምርኮኞች በመቶ በመቶ እየተመደቡ አንገታቸው ላይ ድንጋይ ታስሮ ዳማ ተብሎ ይጠራ በነበረው ወንዝ ውስጥ ይወረወራሉ" በማለት ጽፏል።[51]

(The cruelties practiced by the chief of Goma are almost incredible offenders are deprived of hands, nose and ears and their eyes have been seared with a hot iron. The mutilated victims are paraded through the market place for edification of the populace.

The sight of all prisoners taken in war is similarly destroyed- and a stone having been tied about the neck they are thrown by hundreds into a river formerly styled Damma)

በምኒልክ ዘመን ሌቦችንና አመጸኞችን እጅና እግራቸውን በመቁረጥ መቅጣት አልቀረም። ያም ሆኖ ምኒልክ ከሱ በፊት የነበሩት ባላባቶች የሚፈጽሙትን ዐይነት ብዙ የአብሪት ግፍ አስቀርቷል። በኦሮሞ፣ ትግራይ፣ ከፋ፣ ዐማራና አፋር ወታደሮች የሚተገበረው የማስለብ ባህል እንዲቀር ዐዋጅ ወጥቷል። ይሁን እንጂ ባህሉ በጣም ሥር የሰደደ ስለነበር በቀላሉ ሊወገድ አልቻለም።

[51](ገጽ 160)

በወላይታ ዘመቻ ከምኒልክ ጋር አብሮ የዘመተው ከዘመቻው በኋላ የምኒልክ ነቃፊ የሆነው ፈረንሳዊ ወዶ ገብ ይህን አስመልክቶ ሲጽፍ፤

"ንጉሥ ምኒልክ በጦርነት ወቅት ቁስለኛ መስለብ እንዲቀር ትልቅ ጥረት አድርጓል። ይሁን እንጂ በወላይታ ዘመቻ አብሬው ስዘምት ይህ ባህል በአማሮችና በኦሮሞዎች እና በሌሎች የምሥራቅ አፍሪካ ነጎዎች ልብ ውስጥ ሥር የሰደደ ባህል መሆኑን ተረድቻለሁ። ዐዋጅ ቢያስነግርም፣ ሕግ ቢያወጣም፣ በዜጎች ዘንድ እጅግ የተከበረ ቢሆንም ንጉሡ ይህንን ዘግናኝ ልማድ ሊያስወግደው አልቻለም" ይላል።[52]

ለማጠቃለል፡

በጥንታዊት ኢትዮጵያ ሰዎች ይመሩበት የነበረው የሕዝብ አስተዳደር ሕግ ጥንታዊ ነው። ገዥዎች የፈጸሙትን ግፍ በዘመናዊ የስነምግባር እና ሰብአዊ ሙብት መለኪያ በማየት ፊት መፍጀትና ደረት መድቃት የሚጠበቅብን አይመስለኝም። አባቶችችን የዘመናቸው ሥርዓትና ወግ ባርያ በመሆናቸው፣ ያደረጉትን ከማድረግ ውጭ አማራጭ አልነበራቸውም። ጠላትን መቁረጥ መፍለጥ ለኛ በደል ሲሆን ለቀደምቶቻችን ግን ደንብ ነበር። በዘመናቸው በቦታቸው በሁኔታቸው ውስጥ ብንሆን እኛም እነሱ ያደረጉትን ከማድረግ አንመለስም ነበር።

የሁላችንም አባቶች የሁላችንም ጌቶች በፈረቃ ግፍ መጸፋቸው በታሪክ ተመዝግቧል። ይሁን እንጂ ከዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ድረስ ባስተዳደር ብዙ ጉልህ መሻሻሎች ታይተዋል። ከአብሪት የሚመነጭ የጭካኔ ቅጣት በመጠንና ባይነት ቀንሷል። ዘመናዊ ትምርትን

[52]... L'empereur Ménélik fait tous ses efforts pour empecher la castration des blessès àla guerre ; mais lorsque j'accompangi sa majesti contre les Oulamos je vis que cette coutume est enracinée dans les maeurs des Abyssins des Gallas et des peuplades d l'Afrique orientale.





የቀሰሙ ኢትዮጵያውያን እና አውሮፓዊ አማካሪዎች ተጽእኖ እንዲሁም የመሪዎች ብሩህነት እና ቀናነት ለዚህ መሻሻል አስተዋጽኦ አድርጓል። በዘመናችን የምሬትንና የቂም በቀል ቱከራን ርግፍ አድርገን ትተን በሚያቀራርቡ በሚያስተባብሩ ሐሳቦች ላይ ከተጠመድን ከባቶቻችን የተሻለ ዓለም እንደምንፈጥር ጥርጥር የለኝም።





## ሲደጋገሙ እውነት የመሰሉ ውሸቶች

አብርሃም በበንቶ የተባለ የወላይታ ብሔረሰብ ተወላጅ ጸሐፊ፣ "ለምለሚቱ ወላይታ" በተባለው መጽሐፉ፣ "ምኒልክ በወላይታ ድልን ከተጎናጸፈ በኋላ ሕዝቡን በመናቅ ወላሞ ብለው ያለ ስሙ ስም አወጡለት (ገጽ 40) በማለት ጽፏል። ወልደ ዮሀንስ ወርቅነህ እና ገመቹ መልካ የተባሉ ጸሀፊዎች በጥሩ ዐማርኛ በተጻፈ ግን በስሜት በነደደ መጽሐፋቸው የወላይታን መገበር ታሪክ በሰፊው ከዘገቡ በኋላ፤

"በዚህ ወይነት የወላይታ ሕዝብ ገናና ታሪክ አበቃ። ሕዝቡ ለባርነት ከየቦታው የሚታደን ሆነ። በጦና አመራር ዘመን ለማንም የማይገብረው የወላይታ ሕዝብ ስሙ ጭምር ተለውጦ ወላሞ ተባለ። ወላሞ ማለት ዋ! ላም (ወዮልህ አንተ ከብት ወይም ላም) ማለት ነው የሚሉ አሉ። አባባሉ ፍጹም ከህዝቡ ጥላቻ የመነጨና ዘረኝነት የተላበሰ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው" ይላሉ።[53]

[53]ኦሮሚያ1 የተደበቀው የግፍ ታሪክ (ገጽ 95)





ተሰፋዩ ገብረአብ "የቡርቃ ዝምታ" በተባለው ልቦለዱ ከላይ ከነገመቹ መጽሐፍ ብዙ ሐሳቦችን ቀድቶ በሚንቀለቀል ዐማርኛ በማስተጋባት ተጠምዷል። ደራሲው የልቦለዱ ዋና ገጸባሕርይ የሆነችውን ሀወኒን እንዲህ እንደሚያናግራት እንስማ፤

"...አንዳንዶች የወላይታን ሕዝብ ታሪክ ባለማወቅ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ወላሞ እያሉን ስንጠራቸው ነበር። የወላይታ ሕዝብ ወላሞ የሚለውን ስያሜ አለመቀበል ብቻ ሳይሆን ቃሉን ሲሰማው ከፋኛ ይቆጣል። ምክንያቱ ግልጽ ነው። ወላሞ የሚለው ቃል ዋ ላሞ ከሚለው የመጣ ነው። ነፍጠኞች ከብቶች ናችሁ ላሞች ናችሁ ሲሏቸው ሲፈልጉ እንደዘበት የብሔረሰቡ አባላት ላይ የለጠፉት የንቀት ስያሜ ነው። ምኒልክና ነፍጠኞቹ የፈለሰፉትን ይህን ስድብ የኃይለሥላሴ መንግሥት እንዳለ ተቀብሎ ነበር ያስተናገደው።"[54] (ሰረዝ የተጨመረ)

ሦስቱ ጸሐፍያን ለስሜታቸውና ለዓላማቸው ተስማሚ ሆኖ እስካገኙት ድረስ ከምድር ወድቆ ያገኙትን አሉባልታ ብድግ አድርገው ሳይመረምሩና ሳያበጥሩ በተደበቀ ታሪክ ስም ለአንባቢያቸው ለማቀበል አላፈሩም። ከላይ በጠቀስኳቸው አንድም ሦስትም በሆኑ ጥቅሶች ውስጥ የሚከተሉትን ሦስት ጉልህ ስህተቶች እናገኛለን፤

1. ወላሞ የሚለውን ቃል የፈለሰፉት ምኒልክና ነፍጠኞች ናቸው።

2. ወላሞ የሚለው ቃል ዋ ላሞ ከሚለው ዐማርኛ የመጣ ነው።

3. ምኒልክ የወላይታን ሕዝብ እንደከብት እንጂ እንደ ሰው አልቆጠሩትም

እውነታው ግን ከላይ ከተጠቀሱት ቅጥፈቶች ጋር አይገናኝም ። "ወላሞ" የሚለው ቃል ምኒልክ ከመወለዱ እጅግ ብዙ ዘመናት አስቀድሞ ይታወቅ

[54]የቡርቃ ዝምታ (ገጽ 285)

ነበር። ሌላው ቢቀር በ1559 እንደተጻፈ በተረጋገጠው ፉትህ አል አበሻ በተባለው የየመኑ ታሪክ ጸሐፊ ድርሳን ውስጥ በግልጽ ሠፍሮ እናገኘዋለን።[55]

(እንዲሁም፣ የምኒልክን አያት ሣሕለሥላሴን የጎበኙት ክራፍ እና ኢዘንበርግ "ወላሞ" የሚለውን ቃል በማስታወሻቸው በብዙ ስፍራ መዝግበውታል። ስለዚህ ምኒልክና ነፍጠኞቹ ወላሞ የሚለውን ቃል ፈለሰፉት የሚባለው ተራ ስም ማጥፋት ነው እላለሁ።

ወላሞ የሚለው ቃል የወላይታን ሕዝብ ላሞች ናችሁ ለማለት የተፈጠረ ነው የሚለው ክስ የከሳሹን ክፋት ከማሳየት ያለፈ ፋይዳ የለውም። ለዚህ አፍራሽ ውንጀላ የስነ-ልሳንም ሆነ የታሪክ ማስረጃ አይገኝለትም።

በበኩሌ፣ ወላሞ የሚለው ቃል መነሻው ምን እንደሆነ አላውቅም። ቃሉ ስድብ መሆኑን የሚገልጽ አሳማኝ ማስረጃ የለም። እንዲያውም የቃሉ ምንጭ ዐማርኛ አይደለም። በዘመነ መሳፍንት የዛሬውን ደቡብ ኢትዮጵያ የጎበኘው እንግሊዛዊው ሊቅ ቤኪ ወላሞ የሚለው ቃል የኦሮሞዎች አጠራር ዘይቤ መሆኑን ጽፏል[56]።

ምኒልክ የወላይታን ሕዝብ እንደከብት ይመለከት እንደነበር የሚያሳይ አንዳች መረጃ የለም። ንጉሡ ለወላይታ ንጉሥ ጦና በጻፈው ደብዳቤ፣ "ሰውህንም አታስፈጅ ሀገርህን አታስጠፋ ግብርህን ይዘህ ግባ" ማለቱን በጸሐፊ ትእዛዛቸው ተጠቅሶ ተገኝቷል። ምኒልክ የጦናን ባለሀገርነት ብቻ ሳይሆን በአገሩ ውስጥ የሚኖረውም ሰው እንደሆነ ለመቀበል ችግር እንዳልነበረበት ጥቅሱ ያስረዳል። ይህ ሆኖ ሳለ በራዥ ብሔርተኛ ጸሀፊዎች ጦናና ምኒልክ ተመሳሳይ ያገዛዝ ዘይቤ እንደነበራቸው ባለማወቅ ወይም አውቆ በመካድ የወላይታ ሕዝብ በምኒልክ ዘመን ከነጻነት ወደ ባርነት እንደወደቀ አድርገው መጻፋቸው ያስገርማል፤ ያሳዝናልም።

---

[55]The conquest of Abyssinia, Trans : by Lester Stenhouse (ገጽ 332)

[56]Respecting wolita _this is the native name, wolamo being the Oromo designation





ወላይታ እንደሌሎቹ ብሔረሰቦች ሁሉ ከባርነት ሥርዓት ጋራ የተዋወቁት በምኒልክ አማካኝነት አልነበረም። የምኒልክ ፈረስ ወላይታን ከመርገጡ በፊት እነጦና በባርያ ንግድ ሀብት ያደልቡ እንደነበ በታሪክ ተመዝግቧል።[57] ምኒልክ ከታማ፣ የሚታማበት ጦና የተረከበውን የባርያ ፍንገላ በማስቀጠሉ እንደሆን እንጂ ታይቶ የማይታወቅ የባርያ ፈንጋይ ሥርዓት በማስተዋወቁ ከቶ ሊሆን አይችልም።

ተስፋየ ገብረአብ በተጠቀሰው መጽሐፉ ጃንጀሮ ተብሎ ይጠራ ስለነበረው ብሔረሰብ ስያሜም የሚለን አለው። "ደርግም ጃንጀሮ የሚለውን ስያሜ ተቀብሎ አሁን ድረስ ይጠቀምበታል። ጃንጀሮ በሚል ስያሜ የሚጠራው ብሔረሰብ ትክክለኛ ስም የም ነው። ጃንጀሮ የተባሉት ተራራ ላይ ወጥተው ወራሪዎቻቸውን በድንጋይ ስለፈጁት ነው። ዝንጀሮ ለማለት ጃንጀሮ የሚል ስያሜ ሰጥተው ሕዝብን ያህል ነገር በደንታቢስነት የሚያዋርዱት። የነፍጠኛው ሥርዓት ከርፋት እዚህ ድረስ ጠልቆ ሊሰማን ይገባል።"

ተስፋየ ጃንጀሮ በሚል ሲጠራ የነበረው ሕዝብ ትክክለኛ ስሙ የም መሆኑን የገለጸው እውነት ነው። ይህንን ተከትሎ የመጣው ድምዳሜ ግን እቦ ስጡኝ ይመስላል። ጃንጀሮ የሚለው ስያሜ ምንጭ ምንድነው? ቃሉ በጣም ጥንታዊ ነው። ደቡብ ኢትዮጵያንና ኦሮሞን ያጠናው የፈረንሳዩ ሊቅ አንጦኒዮስ ደ አባዲ የኢትዮጵያ ጂኦግራፊ በተባለው ጥናቱ ይህን መጠርያ አስመልክቶ ሲጽፍ ሚከተለውን ይለናል፤

"የም የጃንጀሮ ሕዝብ ራሱን የሚጠራበት ስም ሲሆን ይሄ የመጨረሻው ስም ግን በከፋ ሰዎችና በኦሮሞዎች የተሰጣቸው ስያሜ ነው።"[58]

የብሔረሰብ ስያሜ ከተነሣ አይቀር ሌላው አወዛጋቢው ሆኖ የቆየው የኦሮሞ ስያሜ ነው። ኦሮሞ የሚለው ቃል የባለቤቱ ሕዝብ መጠርያ ሆኖ መቆየቱን

---

[57]Une expédition (Page167)

[58]Yamma est nom national de janjiro.ce deriner nom leur est donne par les gens de kaffa et par les Oromo, (page 71)





የሚጠራጠሩ አልጠፉም። ከጥንት ጀምሮ የነበረው ትክክለኛ ስያሜ ጋ* ሲሆን ኦሮሞ የሚለውን ቃል በኀይሌ ፊዳ የተፈለሰፈ ነው ብሎ የተከራከረኝ ሰው ገጥሞኝ ያውቃል። ይሄ እውነት አይደለም። በብሔረሰቦች ጥናት ፋና ወጊ የሆነው አንጦኒዮስ ደአባዲ ኦሮሞዎች ራሳቸውን ኦሮሞ ብለው እንደሚጠሩ ጎረቤቶቻቸው ግን ጋ* ብለው እንደሚጠሯቸው ጽፏል።[59]

የመከባበር ሁሉ መጀመርያ በቅጡ መተዋወቅ ነው። አንዳንዴ፤ ጠንከር ካለ ስብከት በተሻለ መንገድ ለዘብ ያለ ቅራኔ ሌላውን በጥልቅ የምናውቅበት አጋጣሚ ሊፈጥርልን ይችላል። ልጅ እያለሁ በሰፈራችን "ቆዳ" ተብሎ የሚጠራ ልጅ አውቃለሁ። ልጁ በስድብ ስሙ እጅግ ከመታወቁ የተነሣ ዋናው ስሙን የሚያስታውስ አልነበረም።

አንድ ቀን መንገድ ላይ ከታላቅ ወንድሙ አገኘኹና፣ ወንድሙን አይቸው እንደሁ ሲጠይቀኝ፤ ኮራ ብየ፣ "ቆዳን ነው?" ብየ መለስሁለት ። በወንድምየው ፊት ላይ ያየሁት የቁጣና የመደፈር ስሜት እስከመለከት ድረስ ቆዳ የሚለው ቃል ደንበኛ ስም እንጂ ስድብ መሆኑ አልተገለጠልኝም ነበር። ባገራችን፣ "ስም ይወጣል ከቤት ይከተላል ከጎረቤት" የሚል አባባል ቢኖርም በሕዝብና በሕዝብ መካከል ባለው ግኑኝነት ታሪክ ውስጥ ግን የተከሰተው በተቃራኒ ነው። ጎረቤት የለጠፈው ስም ባለቤቱ ያወጣውን ስም ሲያስንቅ ኖሯል። ስለፍቅርና ስለአብሮ መኖር የሚገደው ሰው ጎረቤቱን በክብርና በቁልምጫ ስሙ ይጠራል እንጂ እንዳሻኝ እጠራሃለሁ ብሎ ድርቅ ማለት የለበትም። ዛሬ ዛሬ፣ የእርቅ ምልክት ይሆናሉ ብየ የማስባቸው ሽማግሌ ምሁራን ሳይቀር እንዲህ አይነቱ ቅንነት ሲጎድላቸው ላይ አዝናለሁ።

በተረፈ፣ ባንድ ዛሬ ጸያፍ መሆናቸው ታውቆ የቀሩ መጠርያዎች በጥንታዊ መጽሐፍ ላይ ተጽፈው ሲገኙ ለመደምሰስ መሞከር ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። ያለፈንበትን ሁሉ የምንደመስስ ከሆነ ከየት ተነሥተን የት እንደደረስን ማወቅ አንችልም።

---

[59]Géographie, (Page 8)





## ስለ ገዥ መደብ

በዘመናችን የፖለቲካ ሙግት ውስጥ "የዐማራው ገዥ መደብ በብሔርብሔረሰቦች ላይ ያደረሰው ጭቆና" የሚል የቸከ አባባል መስማት የተለመደ ነው። አባባሉ በጣም ከመደጋገሙና ከመለመዱ የተነሣ ብዙ ሰው አሜን ብሎ ተቀብሎታል። ግን የዐማራ ገዥ መደብ ሲባል ምን ማለት ነው? የኢትዮጵያ ገዥዎች በዘር ዐማራ ነበሩ ማለት ነውን? ዐማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ነበሩ ማለት ነው? ወይስ ዛሬ ዐማራ ከሚባለው ክልል የወጡ ናቸው ማለት ነው? ለነኚህ ጥያቄዎች የሚያረካ መልስ የሰጠ ያለ አይመስለኝም።

በተለምዶ በባላጋራ ብእር "ዘመነ መሳፍንት" ተብሎ የሚታወቀው የየጁ ሥርወመንግሥት በግልጽ የኦሮሞዎች መንግሥት ነበረ። ራስ አሊ ዐማርኛ ተናጋሪ የወሎ ኦሮሞ ነበሩ። የዳሞት ገዢ ደጃዝማች ጎሹ፣ "አባ ኢብሳ" እያለ የሚፎክር የተጠመቀ ኦሮሞ ነበር።

የየጁን ሥርወ መንግሥት ያፈረሰው ቋረኛው ካሳ በድሉ ማግስት፣ "ጋ*ችን አባረርኳቸው" እያለ ደብዳቤ ይጽፍ የነበረው የገረሰሰው መንግሥት በኦሮሞ ተወላጆች መገንባቱን በትክክል ያውቅ ስለነበረ ነው። የካሳን ታሪክ ለመከለስ ከሞከሩት ብሔርተኛ ጸሐፍት መካከል ወልደ ዮሀንስ ወርቅነህና ገመቹ መልካ ይጠቀሳሉ። እኒህ ጸሐፊዎች ቋረኛው ካሳ ከየጁው ራስ አሊ ጋር ላካሄደው ጦርነት ሠራዊቱን አንጋዶት እንደመለመለ ሲጽፉ፤

"በወታደራዊው ምልመላ ወቅት ደጃች ካሳ የሠራዊቱን አቋም በጸረ ኦሮሞ ስሜት ላይ ከመቀሰቀሳቸውም በላይ የዐማራ ብሔርተኝነትን በስፋት ተጠቅመዋል" ይላሉ።

ይህ አባባል፣ ቴዎድሮስ ሥልጣን የጨበጠው በዐማራ ብሔርተኝነት መሠረት ላይ ተንጠራርቶ ነው ወደሚል ስሁተት ያመራል። ብዙ ሰው እንደሚያውቀው፤ የካሳ ማኅበራዊ መለዮ፣ "ቋረኛው ካሳ" የሚል እንጂ፣ "ዐማራው ካሳ" የሚል አልነበረም። ካሳ የቋራ ብሔረሰብ ተወላጅ ነው። በጊዜው ቋራ ራሱን የቻለ

ቋንቋና ባህል ያለው በጎንደር የሚገኝ አናሳ ብሔረሰብ መሆኑ ይታወቃል። የዳግማዊ ቴዎድሮስ ምርጥ የሚባሉ ወታደሮቹ የቅማንት ብሔረሰብ ተወላጅ ነበሩ፡[60]፡ እዚህ ላይ፤ በዘመነ ቴዎድሮስ የተወለደውን አለቃ አጽሜ የተባለውን ታሪክ ዐዋቂ መጥቀስ ተገቢ ነው፤

የዐጼ ቴዎድሮስን ነገር እዚህ ትንሽ እናመለክታለን። ሀገራቸው ቋራ ነው። የዐማራ ዘር አይደሉም። ዐማርኛ ይናገራሉ እንጂ። ቋረኛ የሚባል ቋንቋ አለ። ደግሞ በቋራ እስከዛሬ ሦስት ዐይነት ሕዝብ አለበት። አንደኛ ሄራ ይባላል። ዐጼ መልከሰገድ ወግተው ገዙት። ሁለተኛ ፈላሻ፤ ዋነኛው ትልቁ ምኩራብ እስከዛሬ በቋራ አለ። ሶስተኛ ቅማንት በደሚቢያ በአላፋ በጣቁሳ አለ። እርሳቸው በነገሡ ጊዜ ኮጉት ሆኖ የማያውቀውን ቅማንቶችን ሾሙ፤ አከበሩ። እነደጃች ጣዩን እነደጃዝ ገልሞን ቅማንትን እጅግ ያከበሯቸውና ያምኗቸው ነበር። ዐማራንና ክርስትያንን አይወዱም ነበረ" (ሰረዞች የተጨመሩ)

ያለው ይህንን ያረጋግጣል።[61]

በአለቃ አጽሜ አባባል ሦስት ነጥቦችን እናገኛለን።

1. ቴዎድሮስ ዐማራ አይደለም።
2. የገዥ መደቡ በቅማንት ተወላጆች የተዋቀረ ነበር።
3. ለዐማራ ሕዝብ የተለየ ችሮታ አልነበረውም፤ እንዲያውም ይበድለው ነበር።

የተለያዩ የፖለቲካ ዓላማዎች ካላቸው ምሁራን የተለያዩ የታሪክ ትርጓሜዎች መገኘታቸው የትምና መቸም የነበረ ነው። ነገር ግን፤ ባንድ ታሪካዊ ሰው እና ክስተት ላይ የሰማይና የምድር ያክል የሚራራቁ ትርጓሜዎች የሚያቀርቡ ምሁራን ያሏት ሀገር ኢትዮጵያ ሳትሆን አትቀርም። "ዐማራንና ክርስትያንን አይወዱም ነበር" ተብሎ፤ በዘመን ጓዶቹ ሲወቀስ የኖረው ቴዎድሮስ ዛሬ "የዐማራ ብሔርተኝነትን"፤ በማቀንቀን ሲወቀስ ማየት ግራ አያጋባም?

[60]L' Abyssinie et Le roi Téodore,Antoine d'abadie (Page 11)
[61]አለቃ አጥሜ፣ወርጊስ በባይሩ ተፍላ 1 (ገጽ 564)





ከቴዎድሮስ ቀጥሎ የመጣው ንጉሠነገሥት ተክለጊዮርጊስ ሲሆን፣ የሰቆጣ አገው ተወላጅ ነው። ይህንን ንጉሥ አሸንፎ ሥልጣን ላይ የወጣው በዝብዝ ካሳ የትግራይ ሰው መሆኑ አያሻማም።

ምኒልክ ዐማርኛ ተናጋሪ በባህል ክርስትያን ከመሆኑ ባሻፈ የጠራ ዐማራ ስለመሆኑ የምናውቀው ነገር የለም። የምኒልክ ቀደምቶች እንደብዙዎቹ የሸዋ መሳፍንት የተለያየ ብሔር ድምር እንደሆኑ የሚጠቁም ፍንጭ አለ። ለምሳሌ፤ የሸዋ ሥርወ መንግሥት መሥራ ች የሆነው ነጋሤ ክርስቶስ በመሞቻው ሰአት፤

"አልጋየን ለካዋ ጦሬንና የብር ካራየን ለስብስቴ"ብሎ መናዘዙ ተጽፏል።[62] (ሰረዝ የተጨመረ)

በአልጋ ወራሽነት የታጨው ልጅ ስም፤ "ካዋ" መሆኑ ምንን ይገልጻል? ካዋ የሚል የዐማርኛም ሆነ የግእዝ ቃል መኖሩን አላውቅም። በኦሮምኛ Kaawoo የሚል ቃል አለ። ሞገስ ማለት ነው። የምኒልክ አባቶች እንደብዙዎቹ የሸዋ ሰዎች ለኦሮሞ ባህልና ትውልድ ባዕድ እንዳልነበሩ የሚያመላክት ነው።

ዋናው ነጥብ ግን ይሄ አይደለም። ምኒልክ ከየትኛውም ዘር ይምጣ እጅግ የሚያስደንቅ ጸጋ ነበረው። ግለሰቦች ከየትኛውም ብሔርና መደብ ይምጡ የላቀ ችሎታ ካየባቸው ለመሾምና ለማክበር ዝግጁ ነበር። ለዚህ ማስረጃ ይሆኑኝ ዘንድ በዘመኑ የነበሩትን ዋና ዋና ሹማምንት ማንነት እንቃኝ፤

ሀብተጊወርጊስ ዲነግዴ (ኦሮሞ)

ይህ ሰው ከጦር ሜዳ ምርኮኝነት ወደ ጦር ምኒስትርነት ደረጃ መድረስ የቻለ ነው። የመማከርት ሊቀመንበርም ነበር። በፍርድ ዐዋቂነቱ አባ መላ ተብሎ ተጠርቷል። የምኒልክ ሃኪም ዶክተር ሜረብ፤ "የምኒልክ ቀኝ እጅ" ብሎ ይጠራዋል። በጅሮንድ ተክለሐዋርያት የሰውየው ሥልጣን እስከምን እንደሆነ

[62]ያቤቶሁን ያእቆብ ትውልድና ታሪክ ፤ብታደሰ ዘውዴ፤(ገጽ 17)





ሲጽፉ፤ "በፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ አንደበት የሚነገረው ሁሉ ትእዛዝ ነው። የሌሎች ምክር ነው" ብለዋል[63]።

አፈንጉሥ ነሲቡ መስቀሎ (ኦሮሞ)

ምኒልክ የመጀመርያዎቹን ሚኒስትሮች ሲሾም ይህንን ሰው የፍትሕ ምኒስትር ሥልጣን ሰጥቶታል። አፈንጉሥ ነሲቡ፤ መተኮ ቦርጃ የተባለው የንጉሥ ሣሕለሥላሴ ዘመን የኖረ ጀግና ልጅ መሆኑን መርስኤ ሐዘንወልደቂርቆስ ተርከውልናል።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ (በእናት ጉራጌ ባባት ኦሮሞ[64])

ገብረሥላሴ ወልደአረጋይ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ የተባለውን ዝነኛ መጽሐፍ የጻፈ ሰው ነው። የምኒልክ ደብዳቤዎችንና አዋጆችን የዚህ ሰው እጅ ሥራ ውጤት ናቸው። ምኒልክ የመጀመርያዎቹን ምኒስትሮች በሾመ ጊዜ አለቃ ገብረሥላሴን የጽሕፈት ምኒስትር ብሎ ሹሞታል።

ባልቻ ሳፎ (እናት ጉራጌ አባት ኦሮሞ[65])

የቤተመንግሥት ግምጃ ቤት ኀላፊ ነበር። (ከምኒስትሮች መቋቋም በፊት የገንዘብ ሚኒስትርን የሚመጥን ሥልጣን ነበረው)

የጦር ምርኮኛ ቢሆንም፤ በምኒልክ ቤተመንግሥት ውስጥ በንክብካቤ አድጓል። መጀመርያ በወላይታ ዘመቻ ቀጥሎ ባድዋ ላይ ባሳየው ጀብድ የደጃዝማችነት ማእረግ አግኝቷል። ሲዳሞን ተሹሟል።

ወህኒ አዛዥ ወልደጻድቅ፤ ያንኮበር ገዥ (ጉራጌ)

[63]አቶባዮግራፊ ፤ (ገጽ 303)
[64]Maurice de Coppet, Guébré Sellassie (መቅድም)
[65]፡ በሰው፤ማህተመ ሥላሴ ወልደመስቀል 1 (ገጽ 35)





ባርያ ነበር። በችሎታው ተመዝኖ ትልቅ ሥልጣን ላይ ደርሷል። በምኒልክ ላይ የተቃጣ መፈንቅለ መንግሥት አክሽፏል። ክፉ ቀን የተባለው ዘመነ ወረርሽኝ ወቅት በሽታው መጠቃቱን ሲያውቅ ወደ ሌላ ሰው ላለማዛመት ዱር ውስጥ ለብቻው ኖሮ ሲድን ተመልሷል። አደን የተባለው የፈረንሳይ መንገደኛ በጣም ብሩህ አእምሮ ያለውና ለወዳጆቹ የታመነ ብሎ ያመሰግነዋል። ከጉራጌ መወለዱን የጻፈልን ኸርሊ የ በረሊ ነው።

እነዚህ አብይት ሹማምንት ሲሆኑ ሌሎች ባለሟሎች መካከል ጥቂቶችን ለማስታወስ፤

ሻለቃ ኢብሳ፤ የልፍኝ አስከልካይ (ኦሮሞ)
ፊታውራሪ ደቻሳ፤ የልፍኝ አስከልካይ (ኦሮሞ)
ፊታውራሪ ገብረማርያም፤ የልፍኝ አስከልካይ (ጉራጌ)
ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም፤ አማካሪ (አገው)
ገብሬል ጎበና፤ ዋና አስተርጓሚና አማካሪ (ኦሮሞ)
ዮሴፍ ዘገላን- አስተርጓሚ (ኦሮሞ?)
ዮሴፍ ንጉሴ፤ አማካሪና አስተርጓሚ (የአካለ ጉዛይ ትግሬ)

እዚህ ላይ ማየት እንደሚቻለው ዐማርኛ ከመናገራቸው በቀር ብዙዎቹ የምኒልክ ወሳኝ ሰዎች ከተለያዩ ብሔሮች የተገኙ ነበሩ።

ስለባንዳነት

በዘመናችን በተደጋገሙ ቁጥር እውነት ከመሰሉ ውሸቶች አንዱ ትግራይን ከባንዳነት ጋር የማገናኘት ፍረጃ ነው ። ከሁሉም ብሔረሰቦች መካከል ለጣልያን ማደር የመረጡ ሰዎች እንደ ነበሩ መርሳት አይገባም።

ዛሬ ዛሬ፤ አንድን ባለሥልጣን በሠራው ግፍና ስህተት ራሱን ተጠያቂ ከማድረግ ይልቅ "ወትሮስ ከባንዳ ምን ይጠበቃል" ብሎ ማጠቃለል

የተቃውሞ ፋሽን ሆኗል። ግፍና ያስተዳደር ጉድለት እንደ ቂጥኝ በዘር የሚተላለፍ ይመስል፤ "አባቱም እኮ ባንዳ ነበር" ብሎ መወንጀል ተለምዷል።

ግለሰቦችን ባባታቸው በጎ ምግባር ማሞገስ፤ ባባታቸው በደል መውቀስ ለዘመናችን የማይመጥን አሪታዊነት ነው።

ጌቶችን በግል በሠሩት ግፍ ራሳቸውን ነጥሎ መውቀስ እየተቻለ የወጡበትን ማኅበረሰብ ገድል መርገምና ታሪካዊ መልኩን ጥላት መቀባት የሚያኗኑር ነገር አይደለም ። በሁለተኛው የጣልያን ወረራ የትግራይ ነዋሪ ከቀሪው ኢትዮጵያ ሠራዊት ቀድሞ መዋጋቱና መሞቱን መካድ ፍርደ ገምድልነት ይመስለኛል። በጊዜው ከነበሩት ያይን ምስክሮች አንዱ የሆነው ጊዮርጊስ ስቲር የዘገበውን ማንበብ የተሳሳተ ፍርዳችንን እንድናቃና የሚያግዘን ይመስለኛል፤

"የትግራይ ነዋሪዎች በመጀመርያ (የንጉሡ ነገሥቱ) ወታደሮች ጎን ለመቆም ዝግጁታቸውን አሳይተዋል። ከራስ ኀይለሥላሴ ጉግሳ ጋር ሳይሆን ከራስ ሥዩም ጋር መሰለፍ መርጠዋል።"

(ጦርነቱ ሲጀምር) የትግራይ ሰላማዊ ነዋሪ መንደሮች በጣልያን አየር ጥቃት በፍጥነት ተደበደቡ። የኢትዮጵያ ሠራዊት መሸኀባቸዋል ተብሎ የሚጠረጠርባቸው ቦታዎች ተደመሰሱ። የቅጣት ዘመቻዎች ተከፍተው አብያተክርስትያናት ተቃጠሉ።

"...ትግራይን ለወራሪው ጥሎ መውጣት የንጉሡ እቅድ አካል ነበር፡ በንጉሠ ነገሥቱ የሊጉ ፖሊሲና የሽምቅ ውጊያ ስልት ሳቢያ ለጣልያን ተላልፈው እንደተሰጡ የገባቸው ነዋሪዎች ጦርነቱን ቢቀጥል እንደሚወድም ጦርነቱን ቢያቋርጡ በሰላም ጎጂቸው ውስጥ እንደሚኖሩ ተገነዘቡ" ይላል።[66]

ታድያ ይህ ሆኖ ሳለ፤ የብሔር ፖለቲካ ከበርቴዎቻችን ለምን ከታሪክ ጥሬ ሀቅ ጋር የማይገናኝ ፕሮፖጋንዳ ይነዛሉ? ግራ ያጋባል። ኡምበርቶ ኤኮ የተባለ የጣልያን ደራሲ "አንዳንድ ሰዎችና ቡድኖች ማንነታቸውን ለመግለጽ አቅም

---

Cesar in Abyssinia (Page 62)





እንዳላቸው ለማሳየት ሲሉ ጠላት ባይኖር እንኳ ጠላት ይፈብርካሉ" ይላል። ይህ በትክክል እኛን የሚገልጸን ይመስለኛል። ምኒልክ የወላይታን ሕዝብ ላሞች ናችሁ ለማለት ወላሞ ብሎ ጠራ ብሎ ትውልድ የሚመርዝ ሰው ጠላት እየፈበረከ ነው። ኦሮሞ ብለህ ጥራኝ ሲልህ ጋ* የሚለው ስም መች አነሰህ ብሎ የሚደርቅ ሰው ጠላት እየፈበረከ ነው። ከተለያዩ አካባቢዎችና ብሔሮች የወጡ ጌቶች ሀገር መግዛታቸው በታሪክ የተቀመጠ ሀቅ ሆኖ ሳለ፤ "የዐማራ ገዥ መደብ፤" ብሎ መሰፈፍ ጠላትን መፈብረክ ነው። አንድ ሕዝብ እሳት ከሚያዘንብ የውጭ ወራሪ ጋር ባልሞትባይ ተጋዳይነት ተፋልሞ የከፈለውን መስዋእትነት በመካድ የባንዳነት ባሕርይ ማላበስ ጠላትን ጠፍጥፎ መሥራት ነው። ጠላትን ካልፈበረኩ እንጀራ ሥልጣን እና የሕይወት ትርጉም ማግኘት ከማይችሉ ሰዎች ጋር መኖር ምንኛ ከባድ ነው?





# የንቀት ውሃ ሙላት ሲወስድ እያሳሳቀ ነው

*"ሰናይ ምግባር የሚከሰተው የባላጋራዎቻችንን መኖር በመካድ ሳይሆን፤ ባላጋሮቻችንን በቅንነት በመረዳት፤ በነሱ ቦታ ሆነን ነገሮችን በመመልከት ነው። ሌሎችን በቅንነት መረዳት ማለት ደግሞ ልዩነትን ሳንክድ ወይም ቸል ሳንል የኢድልኦ አስተያየቶችን ማስወገድ ማለት ነው"*

(Umberto Eco, Inventing The Enemy)

ዋሽንግተን ዲሲ ለመጀመርያ ጊዜ የመዝናኛ ዝግጅቴን ሳቀርብ የገጠመኝን ነገር አልረሳውም። ከመድረክ ጀርባ ሆኘ እያሟሟቅሁ ሳለ አንድ ከየት መጣ ያልተባለ የመድረክ አስተዋዋቂ መድረክ ላይ ጉብ ብሎ ዘግናኝ ቀልዶችን





ማውራት ጀመረ። የቀልዶቹ ዋና ገጸ ባሕርያት ኦሮሞና ጉራጌ ናቸው። የኦሮሞው ገጸባሕርይ ተምሮ የማይገባው ማሞ ቂሉ፤ የጉራጌው ገጸባሕርይ ደግሞ ንፉግ ሆኖ ተስሏል። የሰውየውን ጅምላ ጨራሽ ቀልዶች ከመጋረጃው ጀርባ ሆኘ ስሰማ የእዳራሹ ወለል ተከፍቶ ቢውጠኝ በወደድኩ። ደግነቱ፤ ሰውየው ለኩብረ-ነክ ቀልዶቹ ከተመልካቹ ያገኘው ምላሽ የተቃውሞ ቃና ያለው ማጉረምረም ነበር። ከዚያ ቀደም እንደዚህ ዐይነት ዘግናኝ ቀልዶችን በመፈልሰፍ የተካኑ እንዲሁም በቀልዶቹም እንባ እስኪፈስሳቸው ድረስ የሚንከተከቱ ሰዎችን አውቃለሁ። ያንቀን ግን ባዳራሹ ውስጥ የነበረው ተመልካች በኩብረነክ ቀልዶች ለመሳቅ አለመፍቀዱን መታዘቤ እንድ በጎ ተስፋ አሳደረብኝ። የመድረክ መሪ ተብየው ግን ካፈርሁ አይመልሰኝ ብሎ ቢድርቅና "ሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ ጋ*..." ብሎ ሊቀጥል ሲል፤ ከፊት በክብር እንግድነት የተቀመጡት ታዳሚዎች በቀልዱ ማኸል በማጨብጨብ ነውሩን አቋርጦ እንዲወገድ አደረጉት።

በየትኛውም ሀገር ውስጥ በየትኛውም ዘመን ላይ ሰዎች በጎረቤቶቻቸውና በወደረኞቻቸው ላይ መቀለዳቸው ያለ ነው። ሰዎች ዘር-ቀመስ ቀልዶችን እንዳይቀልዱ ሙሉ በሙሉ ማገድ የሚቻልም የሚገባም አይመስለኝም። ይሁን እንጂ ባገራችን የሚነገሩት የብሔር ቀልዶች የቀልዱ ሰለባ ከሆነው ብሔረሰብ መፈጠርን የሚያስጠሉ ናቸው።

ኅብረ-ብሔራዊ በሆነች ሀገር ውስጥ ምንኖር ዜጎች እንደመሆናችን መጠን በህዝቦች መካከል የጡብና የመለያየት ምልክት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን መቀነስ ይገባናል። "ቀልድና ቅዘን ቤት ያበላሻል" የሚለው ተረት፤ ተወላጅነትን መሠረት አድርገው የሚነገሩ የትምክህት ቀልዶችን በደንብ ይገልጻቸዋል። መሳቅና መዝናናት መልካም ነው፤ ግን ለመዝናናት ሲባል አብሮ መኖራችንን የመስዋእት በግ አድርገን እንዳናቀርብ መጠንቀቅ አለብን። በእንዲህ ዐይነት ቀልዶች ምክንያት የሚመጣውን መዘዝ "እንዴ ምን ታካብዳለህ? ቀልድ ቀልዶች አይደል እንዴ" በሚል ማቅለያ ማብረድ የሚቻል አይደለም።

በጥንት ጊዜ ባንድ ብሔረሰብ ላይ የሚሰጠሩ አሉታዊ መለዮዎች ከጦርነትና ከእምነት ቅራኔ የሚፈልቁ ነበሩ። ጠላትህ ጋር ከመደባደብህ በፊት እንዳይሸጥ

እንዳይለወጥ አድርገህ ትሰድበዋለህ። የተፋላሚውን ጦር መሪ ከነቤተሰቡን ከነዘርማንዘሩን ታሸሚጥጣለህ። በተቃራኒው ራስህንና የራስህ ወገን ታሞግሳለህ፤ ትቀድሳለህ። ይህ እንግዲህ፤ የወገንን ጦር ያሸናፊነት ስሜት በጠላት ኪሳራ ለመገንባት የሚደረግ ዘዴ ነው። ፉከራ ኄረርሳ እና ቀረርቶ የተፈጠሩት ለዚህ ዓላማ ይመስለኛል።

ሁለተኛው፣ የንቀት ምንጭ በገናናው ባህል (ክርስትና) እና በአረሚ ባህል መካከል ያለው ግልጥ ቅራኔ ነበር። ክርስትና በጥንታዊ ቁመናው እንደማንኛውም ያንድ አምላክ ሃይማኖት፣ ሌሎችን አምላኮችና ሌሎችን ባህሎች የሚችልበት ሆደሰፊነት አልነበረውም። እምነቱን ባስፋፉት ሰዎች አስተያየት፤ የክብር የእውነት እና የቅድስና ምንጭ አንድ ሃይማኖትና አንድ ጥምቀት ሲሆን፣ ከዚያ ውጭ ያለው የሚናቅና የሚነቀፍ ነበር። ክርስትና የነገሮች መስፈሪያ በሆነበት ዘመን ላይ የዋቄፈታና የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነውን ዜጋ በአረሚነት መፈረጅ የተለመደ ነበር።

ከዚህ አልፎ አሮሞን በአላዋቂነና በፈሪነት ስሎ ማቅረብ የቅርብ ክስተት ይመስለኛል። የሚገርመው ነገር አሮሞን በአላዋቂነት የሚያቀርበውን ተረት ጀማሪዎች አውሮፓ ትምርት የቀመሱ ሊቃውንት መሆናቸው ነው። ለምሳሌ ዕውቁ ደራሲ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ሮም ተቀምጦ ለጣልያኖች በደረሰው የዐማርኛ ሰዋስው ማስተማርያ ድርሳኑ የሚከተለውን ተረት ይተርካል። ትረካው በዘመናችን ለሚነገሩት "የተጨቆኑ ቀልዶች፡" እምሳል ነው፤ እስቲ ሙሉውን ልጥቀሰው።

"አንድ አባ ዱላ አሮምና አንድ ተንኮለኛ ዲያቆን

አንድ አባዱላ አሮም ክርስትና ለመነሣት ተመኝቶ ተቄስ ቤት ውሰዱኝ ብሎ ሄደ። ያን የሄደበትን ቄስ ክርስትያን ለመሆን መጥቻለሁና አጥምቁኝ አንቱ ቄስ አለው። ያ ቄስም ደስ ብሎት ምን ክፋኝ ደግ ነው እንጂ ነገር ግን ሳትጠመቅ በፊት የክርስቶስን ነገር ብትማር ደግ ነውና በዚህ ሰሞን እየመጣሁ ቶቤትህ አስተምርሃለሁ አለው።





ያ አባወራ አሮም እሺ ዛሬ ማታ ጀምራ ኢንታ ቲንታ ቲመጫለሽ እኒም ተቤት ይቋያል አለና ወደ ቤቱ ተመለሰ። ያ ደግ መነኩሴ ተዚህ ወዲህ ቶሎ ቶሎ እየሄደ የክርስቶስን ከሰማየ ሰማያት መውረዱን ከድንግል ማርያም መወለዱን ለኛ ሲል መሰቀሉን መሞቱን ቀጥሎም መነሳቱን ነገረው። ደሞ ክርስትያን የሆነ ሁሉ የሚያደርገውን ክርስቶስ የሚወደውን ሥራ ነጋገረውና ተቤተክርስትያን ወስዶ አጠመቀው።

ያ አባ ዱላ ቅዳሴው ተጀምሮ እስቲጨረስ ድረስ ተቤተክርስትያኑ በየገጹ ተተሣለው ሥዕል ዐይኑን ተክሎ አባኩ ! አባኩ ! ዋቅ ! ዋቅ ! ሲል ዋለና ባስተርጓሚ ሥዕሉን ሁላ ይሄ ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው። ይሄ ቅዱስ የህንስ ነው፤ እያሉ የሰማእታትን የጻድቃንን የደናግል የሰማእታት የመነኮሳን ሁሉ ስም አስተገድላቸው ነገሩትና ወደ ቤቱ ከንፈሩን እየመጣጠ እንደ ቁራ ዋቅ ዋቅ አባኮ አባኮ ኢያለ ኢያለ ሄደ።

ያጠመቁት መነኩሴ ምንም ቢሆን ክርስትያን ተሆንህ ወዲያ ቤተክርስትያን እንድትስም ይልቁንም ባመት በእልና በእሁድ ቀን አትቅር ብለው ነግረውት ነበርና አንድ ቀን በእሁድ ማለዳ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ቢሄድ ተደጀሰላሙ እስተቅድስቱ ድረስ ቤተክሲያን ሳሚ ዘበበት አገኘ። አንዱንም ቢያይ አንዱንም ቢያይ ሁሉም ጸሎት ይዞ በየፉ ቱ ቱ ቱ ሲል አየና ኢቺ ሰው ሁሉ ከንፈሯን ኢያንቀሳቀሱች ሚን ሚን ቲላሉች ብሎ ጠየቀ። አብሮት ያለው አስተርጓሚ ሁሉም ቅዱስ ጊዮርጊስን ይለምናል አለው። ከዚህ በኋላ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሥዕል ቀረብ ብሎ ያ አባ ዱላ እኒ ቂኒጥ ሚኒጥ እያውቅም ቅዱስ ጊዮርጊስ ነገ አሸከር ሲደጅ፤ አንድ በሬ እኒ ይሰጓል አለና ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ይሄን የሰማ ዲያቆን በማግስቱ በማግስቱ ማለዳ ከዚያ አባዱላ ሄደና ነቅዱስ ጊዮርጊስ አሽከር ነኝ፤ ትናንት ያበለልኝ (ቃል የገባልኝ?) በሬ አለና ሄደህ አምጣ ብሎኝ መጥቻለሁ አለው። ያ አባዱላ በዚህ ጊዜ ዋቀዩ ዋቀዩ አባኮ ኢቺ ጊዮርጊስ እቺ ጊዮርጊስ ኢንዴት ሰሚ ናት! ኢኔ ጊና ይህን የተናገርሁ ጊዜ ቀስ ብየ ነበር። አለና ሻኛ ፍሪምባውን መሸከም ያቃተው በሬ ተብረቱ መርጦ፣ "ዋቃ ጊዮርጊስ እንዴት እንዴት አደርሽ በልልኝ" ብሎ ሰደደለት።





ያ ሸንከ ዲያቆን በልቡ እየሳቀ ነድቶ ወስዶ ጤፍና ሰንዴውን ያናግዝልበት ጀመር። ተሁለት ወር በኋላ ያ ተንኮለኛ ዲያቆን የዚያን አሮሞ የዋህነት ተረድቶት ተቀንጃ በሬ ጥማድ ይሻላል አለና እንደገና ተዚያ አባወራ አሮሞ ሂዶ ለቤተክርስትያን መሰዋእት የሚሆን ሰንዴ የሚዘራበት ደግመህ አንድ በሬ ስደድልኝ ብሎሃል አለው። ያ የዋህ አዲስ ክርስትያን አሮሞ እውነት መስሎት ተመንጋው ሁሉ ማኸል እንደፊተኛው ያለ ፍሪምባው ሻኛው የሚዋልለውን በሬ መርጦ ሲሰድ ትፍታ ጊዮርጊስ ተቤተክርስትያን በፈረስ ተቀምጠሽ ለብሰሻት ያየሁሽን ለምድ ስደጅልኝ አባኮ ብሎ ለዲያቆኑ ነግሮ ላከበት።

እንደሱ እንደሱ ድሮ ተቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር ባለሟል ሁኗል። እንደሱ እንደሱ የሰደዳቸው በሬዎች ለቅዱስ ጊዮርጊስ የሚጠቅሙ እንጂ ለዚያ ዲያቆን ጉበስና ሰንዴ የሚያነናዝሉለት አልመሰለውም። እንደሱ እንደሱ ተቤተክሲያኑ ገጽ ላይ ያየው የጊዮርጊስ ኑበስ ያለው ልብሱም በመቀስ የተቀደደ በመርፌ የተሰፋ ግምጃ እንጂ በክሰል የተኳደረ በቀለም የተቀባ ሥዕል አልመሰለውም ነበር።"[67]

አፈወርቅ፣ አባ ዱላውን በጊወርጊስና በጊወርጊስ ሥዕል መካከል ያለውን ቀላል ልዩነት የማያጡቅ ቂሉ ማሞ አድርጎ ስሎታል። ደራሲው፤ በተለመደው አገራዊ የተረት አተራረክ ዘይቤ፣ "አንድ ሰውዮ" ብሎ፣ በመጀመር ፈንታ፣ "አንድ አባ ዱላ አሮሞ" ብሎ መጀመር መምረጡ የግለሰብ ባሕርይን ከብሔረሰብ ባሕርይ የሚቀዳ አስመስሎታል። በዚህ ትረካው አፈወርቅ አሮሞን አለቅጥ የዋህ በቀላሉ የሚታለል አድርገው ለሚስሉት ዘመናዊ የብሔረሰብ ቀልዶች አባት ልንለው እንችላለን። ይህ ንቀት-ጠገብ ተረት አፍራሽነቱ በሁለት በኩል ነው። ባንድ በኩል አባ ዱላውን ቂሉ ማሞ አድርጎ የሳለውን ያክል ቤተክስያንን ደግሞ፣ የቀጣፊዎች ዋሻ ሆና እንድትታይ አድርጓታል።

የአፈወርቅ የዘመን ጓድ የሆነው ገብረሕይወት ባይከዳኝም ተመሳሳይ እንከን ነበረበት። የአድዋው ሊቅ ዐጼ ምኒልክ እና ኢትዮጵያ የተባለውን ረጅም መጣጥፉን የጻፈው አፈወርቅ ገብረኢየሱስ በትግራይና በዐጼ ዮሐንስ ላይ ያወረደውን ስድብና እድልኦ ለመተቸት እንደሆነ ይታወቃል። ጸሐፊው ወገኑን

[67]Grammatica della lingua Amarica (page 312)





ካድልኦና ከዘለፋ ለመከላከል መነሳቱ ተገቢ መሆኑ አያጠያይቅም። የሚገርመው ግን ገብረሕይወት በዚያው መጣጥፉ፣ "እንኳን አእምሮ ያላቸው ነገሥታት አሮሞውም ቢሆን" የሚል ሐረግ በመደንቀር አሮሞውን በጅምላ አእምሮ አልባ አድርጎ ማቅረቡ ነው። ይህ ሰው፣ "የመንግሥትና አስተዳደር" በተባለው መጣጥፉ፤ አሮሞዎች የዕውቀታቸው ደረጃ ዝቅ ያለ በመሆኑ በወረራ የወሰዱት ሀገር ወደ ረግረግና ደን እንደለወጡት ጽፏል።

አፈወርቅና ገብረሕይወት ለሃገራችን ብዙ ጠቃሚ ሐሳብ ያበረከቱ ብሩህ ሊቃውንት መሆናቸው የሚገባቸውን ዋጋ አያጡም። ይሁን እንጂ፤ እነህ ሊቃውንት ሌላውን ሕዝብ በተመለከተ ያላቸው ዕውቀት በጣም ግልብ ስለነበረ ለሚዛናዊ ፍርድ አላበቃቸውም። በብሔረሰቡ ማኸል ኖረው ስለአኗኗሩና ስለባህሉ ተመራምረው የሚፈርዱበት እድል አልነበራቸውም። ስለሌላው ሕዝብ ያላቸው አመለካከት ከአሉባልታ የዘለለ አልነበረም። ስለዚህ ሳያውቁ በስህተት የበየኑትን ይቅር ብሎ ማለፍ ተገቢ ነው እላለሁ።

በብሔረሰቡ መካከል የተወሰነ ጊዜ የኖሩ፣ ቋንቋውንም የተማሩ የፈረንጅና ያገርቤት ሊቃውንት አሮሞን በኅብረተሰብም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ዐዋቂ እና የብሩህ አእምሮ ባለቤት እንደሆነ ይመሰክሩ ነበር። ከደብተራ ዘኑብ ጋር ሆኖ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አፋን አሮሞ የተረጎመ ጀርመናዊ ክራፍ፣ የአሮሞ ተወላጅ ባሮች በዐረብ የባርያ ፈንጋዮች ተፈላጊ ያደረጋቸው ምክንያት ብሩህነታቸውና ትምርት የመቀበል ችሎታቸው እንደሆነ ጽፏል።[68]

[68]They are principally of dark and brown color,by which no less,than by intelectual capacity and teachablness,they are so advantageously , distinghushed from all other east Africans that the Galla slaves,especially the young women are much sought after by the slave dealers (Travels page 74)

ዋላስ ባጅ የተባለ ታዋቂ የታሪክ ተመራማሪ ስለኦሮሞ ሕዝብ ሲጽፍ፣ "In intelligence they are superior to all the other peoples in East Africa"ብሏል።[69]

የእንግሊዙ አሳሽ ቻርለስ ቤኪ፣ ምእራብ ኢትዮጵያን በእግር በፈረስ ሲያካልል ቆይቶ ሊሙ እናርያ ሲደርስ በተመለከተው የስልጣኔ ፍሬ መደነቁን አልሸሸገም፤

"የእናርያ ነዋሪዎች በስልጣኔ የታወቁ ኦሮሞዎች ናቸው። በየትኛውም በዚህ አፍሪካ ክፍል ውጭ የማይታይ የእደ ጥበብ ሥራ እዚህ አብቧል።" በማለት ጽፏል።[70]

በዚህ ዐይነት የተደነቀውን የእናርያ ግዛት የመጎብኘት እድል ከገጠማቸው መንገደኞች አንዱ ዝነኛው የጣልያን ሐዋርያ አቡነ ማስያስ ነው። ይህ የካቶሊክ ሐዋርያ ወደ እናርያ ቤተመንግሥት ጎራ ያለው ንጉሡንና ገባሮችን ለማጥመቅ አቅዶ ነበር። በወቅቱ አቡኑ፥ እናርያን ሲገዛ የነበረውን ሞቲ አባ ባጊቦ (ኢብሳን) ከጎበኘ በኋላ የተመለከተውን ሲጽፍ፤

"ኢትዮጵያ ውስጥ በቆየሁባቸው ዓመታት ልኡላንና ነገሥታትን የማግኘት እድል ገጥሞኛል። የአባ ባጊቦን ያክል ያስደነቀኝ ግን አልነበረም። እሱ ታላላቅ ተሰጥኦዎች የታደለ ነበር።

"በአፍሪካ ከስንት አንድ የሚገኝ ዐይነት ሰው ነው። ረጅም፣ ጽዱና ጉልህ መልክ ያለው፣ የቀይዳማ ነው። ራሱ ትልቅና ማራኪ፣ ድምጹም ግርማሞገስ ያለው፣ የፊቱ አገላለጽ ጨዋ ገጽታ የተላበሰ ነው።... ተወዳጅ አልፎ አልፎም ጨካኝ፣ በፍርዱ ቀጥተኛ ቀልጣፋ...በዙርያው ባሉት ሰዎች የተወደደም ነው....

[69]History of Ethiopia; (page 131)
[70]Inhabitants of Enarea enjoyed the reputation of bieng the most civilized of all the Oromo and manufactures flourish here in a higher degree than anywhere in this quarter of Africa (Page 258)





"በራሱ ልዩ ትእዛዝ በተሠራ ፥ብርማ ዘፋን ላይ ተቀምጦ ነበር። ግርማ ሞገሱ ላቅ ያለ በመሆኑ ጠቢቡ ሰሞንን የሚያስታውስ ነው። ቤተመንግሥቱ በህገርኛ ጥበብ የተሠራ ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ መሰል አይገኝለትም።

"....ብሩህ አእምሮ የታደለ በመሆኑ፤ አባ ባጊቦ በትክክለኛ ትምህርት የማግኘት እድል ቢያገኝ ኖሮ ኢምፓየር መምራት የሚችል የተዋጣለት ፈላስፋ ይሆን ነበር።" በማለት አሞግሶታል።

አቡነ ማስያስ እንደሚነግረን ሞቲ አባ ባጊቦ በልማድ እስልምና እምነት ተከታይ ቢሆንም ውስጥ ውስጡን ግን ራሱ የፈለሰፈውን እምነት ይከተል ነበር። በድብቅ የሚከተለው እምነቱ ወደ ዴኢዝም ይጠጋል። ሁሉንም እምነቶች ያከብራል። አባ ማስያስ ሊያጠምቀው ቢሞክርም አልተሳካለትም።

ምንም እንኳ የአቡነ ማስያስ ሙገሳ ትልቅ ዋጋ ያለው ቢሆንም ከዘረኝነት የጸዳ አልነበረም። ለምሳሌ የአባ ባጊቦን ዐዋቂነትና የቤተመንግሥቱን ሥርዓት ካደነቀ በኋላ እንዲህ ያለ ታላቅነት ከጥቁር ዘር ይፈልቃል ብሎ ማመን ስለከበደው፣ "አባ ባጊቦ የአውሮፓ ደም ሳይኖረው አይቀርም" የሚል ዘረኛ አስተያየቱን ቋጭቷል።







ጉብረሕይወት ባይከዳኝ ያንን መጣጥፍ በሚጽፍበት ዘመን አብዛኛው ዜጋ የሚገለገልባቸው ከብረት፣ ከእንጨት፣ ከሸክላና ካጥንት የሚሰሩ የቤትና የአደባባይ ቁሳቁስ የሚመረቱት በኦሮሞ እደጥበብ ሰዎች መሆኑን የውጭ ሀገር መንገደኞች መስክረዋል[71]።

[71]Une expedition ... J.Gaston Vanderheym (Page 93)





ጉረል የተባለ ጀርመናዊ አሳሽ ጅማን ከጎበኘ በኋላ፤ "የጅማ ኦሮሞዎች ያለምንም ቢሰማርና ያላንዳች ብረት የተዋጣለት ድልድይ ይሠራሉ። አውሮፓዊ ኢንጂነር በተመሳሳይ መሳርያና ቁሳቁስ፣ በግንዶችና በቅርንጫፎች ተጠቅሞ እነሱ ከሚሠሩት የተሻለ ሊሠራ አይችልም።" በማለት ጽፏል።[72]

አሌክሳንደር ቡላቶቪች ከሌቃው ከጅ ከኩምሳ ሞረዳ ጋር ከሰነበተ በኋላ በጻፈው ማስታወሻ፤

"ደጃዝማች (ጉብረእግዚአብሔር) በጣም ብሩህ እና ሩህሩህ ሰው ነው። ሁሉን ለማወቅ ይጣጣራል። የህዝቡን ታሪክና ባህል ማራኪ በሆነ መንገድ ይተርካል" በማለት መዝግቧል።

ሳሙኤል ጎባት በዛሬ አነጋገር የጴንጤ ሐዋርያ ነበር። ዘመነ መሳፍንት ተብሎ በሚታወቀው ዘመን ማገባደጃ ላይ፣ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ መጥቷል። በወቅቱ በማስታወሻው ከመዘገባቸው ትውስታዎች አንዱ ስለ አንድ ደቀመዝሙሩ ይተርካል።

"እውነትን አጥብቆ ከመፈለጉ የተነሣ አንድ ወጣት የኦሮሞ ተወላጅ በቀን ሁለቴ ይጎበኘኛል፡፡

"ዛሬ፣ የሕይወት ታሪኩን ባጭሩ አጫወተኝ። በአሥራ አራት ዓመት እድሜው፣ በጦርነት ተማርኮ፣ በባርነት ተፈንግሏል። አሁን ገና ሠላሳ አልሞላውም። ላንድ ጎጃሜ ጌታ ተሸጦ ሲኖር፣ ጌታው ክርስትና አንስቶ ነጻ አወጣው። ያላስተማሪ፣ ያለ ማንም ድጋፍ ራሱን አስተምሮ፣ ደህና የሚባል የግእዝ ዕውቀት አካብቷል።

"ለጽሑፍ የሚሆን፣የራሱን ብራና ፍቆ አሰናድቷል፤ የጽሕፈት አስተማሪ ባይኖረውም ጽህፉ እጅግ ተነባቢ ነው።"

ሳሙኤል ጎባትን እንደገጠመው ዐይነት፤ በአፋን ኦሮሞ አፋቸውን ፈትተው፤ ካደጉ በኋላ ዐማርኛንና ግእዝን አጥንተው የሚራቀቁ ሊቃውንት ነበሩ። ለምሳሌ፣ በጎጃም ስመጥር የሆነው ባለቅኔ የደብረ ኢልያሱ አለቃ ገብረሥላሴ

[72]ጋዝዜረስት ኢኮኖሚክ ሂስትሪ (ገጽ 301)

(የዮፍታሄ ንጉሴ መምህር) እና የንጉሥ ተክለሃይማኖት ታሪክ ጸሐፊ የነበሩት አለቃ ተክለኢየሱስ ዋቅጅራ ወለጌዎች ነበሩ። እንዲሁም የሱስንዮስ ጸሀፊ ትእዛዝና የስነመለኮት ሊቅ የነበረው አዛዥ ጢኖ በዚህ ረድፍ ይሰለፋሉ።

ሄነሪ ዱፍተን የተባለ በቴዎድሮስ ዘመን ሰሜን ኢትዮጵያን የጎበኘ መንገደኛም የቴዎድሮስ እሥረኛ ስለነበረው ጓደኛው ቫልድማየር በጻፈው ማስታወሻ ውስጥ የሚከተለውን አስፍሮልናል፤

"ቫልድማየር አደጥቡብ እንዲማሩ ከንጉሡ ቴዎድሮስ በአደራ የተረከባቸው፣ ብዙ የኦሮሞ ወላጅ ባሮች ነበሩት። ከኒህ ማኽል አንዱ ዋና ባለሙያ ሆነ። ይህ ሰው፣ ያናጢነት ሥራን፣ በጥራትና በብቃት ስለሚሠራ በተመሳሳይ ሁኔታ ከሚሠሩ አውሮፓውያን ይወዳደር ነበር። የዚህ ሰው የአእምሮ ብሩህነት በእደጥበብ ሙያ ላይ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። በቀለም ትምርት ዘርፍ ተመሳሳይ ችሎታውን ማሳየት ችሏል። በዐማርኛ ጽሬትና ንባብ የተዋጣለት ነበር። ባንድ ወቅት ኩሎ ተብሎ የሚጠራውን፤ እምስት መቶ ማይል ወደ ደቡብ ርቆ የሚገኘውን የትውልድ ቦታውን በሚያስደንቅ መልክ በካርታ ስሎ ለሚስተር ሌጃን አሳይቶት ነበር"[73] ይላል።

ካገራችን ሊቃውንት መካከል እንዲሁ ከውጭ ሀገር መንገደኞች ጋራ የሚመሳሰል አስተያየት የሰጡ አልጠፉም። አለቃ ገብረእግዚአብሔር ኤሊያስ የተባሉ የሸዋ ዐማራ፣ የቤተ መንግሥት ጸሀፊ፤ የኢያሱና የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን ታሪክ በጻፉበት ዜና መዋእል ውስጥ ባልጋወራሽ ተፈሪ አነቃቂነት ስለተጀመረው ዘመናዊ ትምርት ሰፊ ሐተታ አቅርበዋል። በሐተታቸው የኦሮሞ ተወላጅ ስለሆኑ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የትምርት ይዞታ የሚከተለውን ባድናቆት ጽፈዋል፤

"እነሆ የተደመጸ ብራና የጻፉበትን ሁሉ በቀይ በጥቁር ቀለም ቢጽፉበት እንዲቀበል እንዲሁ የኦሮሞ ሕዝብ ያስተማሩትን ትምህርት፣ ያመለኩትን

[73] Narrative (page 165)





ዕውቀት፣ በቶሎ ይቀበላል። ለማጥናትም ይሽቀዳደማል። ከቀድሞ ጀምሮ የወሊጋና የጅማ ኦሮሞ ብዙ የእጅ ሥራዎችን ያውቃል። የሚሠራቸውም የእጅ ሥራዎች ዓይነትና በምን እንደተሰሩ የሚያስረዳ ቀጥሎ ያለው ነው።

1. ከዝሆን ጥርስ የተሠራ ከዘራ፣መለኪያ ሚዶ፣የቢላዋ እጅታ፣ ወለባ
2. ከአውራሪስ ቀንድ የተሠራ ዋንጫ ብርሌ የሻምፓኝ መለኪያ፣ የሰይፍ እጀታ
3. ከጎሽ ቀንድ የተሠራ ዋንጫ መለኪያ የእንዝርት ራስ
4. ከማይነቅዝ ዕንጨት፣ የአልጋ ሸንኮር ጠረጴዛ፣ ባለጌጥ ወንበር፣ አንዱን እንጨት ፈልፍለው በምስማር ሳያጋጥሙ ክብ ሞሰብ፣ ባለ መግጠሚያ የወጥ ማቅረቢያ ሣህን በየአይነቱ፣ የአበባ ማስቀመጫ ባለጌጥ ይሠራሉ። አለስልሰው፣ የቅርጹና የጌጡ ማማር ፈረንጆች በፋብሪካ የሚሠሩትን ይወዳደራል። ከዚህም ሌላ በየወንዛቸው አሸዋውን በሰፌድ እያንገዋለሉ፣ በወንፊት እየነፉ ወርቅ ያወጣሉ። ከዚህ በፊት ወርቅ የሚወጣባቸው ቦታዎች ቀጥሎ ያሉት ናቸው።"

ጸሐፊው፤ ወርቅ የሚገኝባቸውን ቦታዎች ከዘረዘሩ በኋላ፣ የሚከተለውን ይጨምራሉ፤

"ለዚህም የወርቅ ሥራ፣ እያና ብሩ፣ የወለጋ ተወላጅ የሆነ በልኡል አልጋወራሽ ራስ ተፈሪ ፈቃድ ወደ እንግሊዝ ሀገር ሄዶ፤ ስለተማረ ፤ለወርቅ ሥራ ተሹሞ ወርቅ ማውጣት ጀምሮ ነበር።

የአለቃ ገብረእግዚአብሔር ኤሊያስ አስተያየት በመስክ ጥናት ላይ የተመሠረት እንደሆነ ግልጽ ነው። በነገራችን ላይ የኒህ ሰው ጽሑፍ በሩደልፍ ሞልቬር አማካኝነት Prowess, Piety, and Politics በሚል ርእስ ከእንግሊዝኛ ትርጉም ጋር ታትሞ ተባዝቷል።

የኢትዮጵያ ታሪክ ባብዛኛው የካህናትና የወታደሮች ታሪክ ነው። የምሁራን ታሪክ በሚገባ ባለመጠናቱ ማን ምን እንደሆነ ማወቅ አምልጦናል።





በዳግማዊ ምኒልክ ንግሥና ዘመን ለሀገር ምስረታ አስተዋጽኦ ያደረጉ የኦሮሞ ተወላጅ የአእምሮ ሰዎች በርካታ ናቸው። በጣም ከታወቁት አንዱ ገብረማርያም ይባላል። ይህ ሰው በልጅነቱ ከወላጆቹ በሙስሊም ባርያ ፈንጋዮች ተሰርቆ በሸዋ ገበያ ተፈንግሏል። በማርሴል ሊቀጳጳስ ካሳ ከፋይነት ነጻ ካወጣ በኋላ በግብጥና በፈረንሳይ የክላሲክ ትምርት ተከታትሏል። ገብረማርያም በጸሃፊነት ለንጉሥ ምኒሊክ በሚሠራበት ወቅት ፈረንሳይኛ ጥልያንኛ ኦሮምኛ ዐማርኛ ላቲን አፋርና ጥቂት እንግሊዝኛ መጻፍና መናገር እንደሚችል ተመስክሮለታል። ገብረማርያም ይሄንን መጠነ ሰፊ ዕውቀት ባካበተበት ወቅት እድሜው ከሰላሳ አልዘለለም ነበር፡[74]

በዘመነ ምኒልክ የኢትዮጵያ ዲጵሎማሲ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ከነበራቸው የኦሮሞ ተወላጆች መካከል ብዙ ያልተነገረለት ገብርኤል ጎበና ይገኝበታል። ገብርኤል ጎበና እንደ ገብረማርያም በባርያ ፈንጋዮች ከኢሊባቡር ወደ ግብጽ ተሸጦ፤ ባንድ ከበርቴ አማካኝነት በጉዲፈቻ አድጓል። ከዚያም በካይሮና በኢየሩሳሌም ተምሯል። በግብጽ ምኒስተር መሥርያ ቤት ውስጥ ትልቅ የሚባል ሥልጣን ነበረው። ይህ ሁሉ ርካታ ሳላሰጠውና አገሩን የማገልገል ፍላጎት ስላደረበት በንጉሥ ምኒልክ አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ የቤተመንግሥት ዋና አስተርጓሚና አማካሪ ሆኗል ።

የብዙ ጊዜ ባለንጀራው የነበረው፣ ኸልየ ቦረሊ እንደመሰከረለት፣ ገብርኤል ጎበና፣ ሰባት ወይም ስድስት ያክል ቋንቋዎችን አጠናቅቆ መናገርና መጻፍ ይችል ነበር። ባረብኛ፣ ፈረንሳይኛና ጣልያንኛ ስለኢትዮጵያ በውጭ ሀገር ጋዜጠኞች የተጻፉ ዘገባዎችንና ዜናዎችን ተርጉሞ ለንጉሡ ማንቡብ የገብርኤል ጎበና ድርሻ ነበር። በውጭ ሀገር ቋንቋ ለፈረንጆች የሚጻፉ የቤተመንግሥት ደብዳቤዎች ባብዛኛው የሱ እጅ ሥራ ውጤቶች ነበሩ።

ገብርኤል ጎበና የምኒልክ አስተርጓሚ ብቻ ሳይሆን አማካሪ ጭምር ነበር። ምንም እንኳ በወቅቱ በጣልያንኛ ችሎታው ተመራጭ ቢሆንም የውጫሌን ውል የማስተርጎም ሥልጣን የተሰጠው አይመስልም። የማስተርጎሙን ድርሻ

[74] ሰሊሊ. (ገጽ 118)





የወሰደው ከፈረንሳይኛ በቀር ሌላ የውጭ ሀገር ቋንቋ የማያውቀው ባላንጣው ግራዝማች ዮሴፍ ነበር።

የውጫሌ ውል 17ኛው የጣሊያንኛው ክፍል መዘዝ እንዳለው ለመጀመርያ ጊዜ ያጋለጠው ገብሬል ጎበና ነበር። የውሉ የጣልያንኛው ክፍል ጣልያንን በኢትዮጵያ ላይ የበላይ ጠባቂ እንድትሆን ሥልጣን የሚሰጥ መሆኑን ከደረሰበት በኋላ "እልቆልናል! የጣልያን የበላይ ተቆጣጣሪ መሆን ቅኝ ግዛት ማለት ነው። ቅኝ ግዛት ደግሞ ወደ ወረራ ይመራል" ብሎ ምኒልክን አስጠንቅቋል።[75] ገብሬል ጎበና ለሀገራቸው ብዙ ሠርተው ያለመታሰቢያ ከቀሩ የኢትዮጵያ ሊቃውንት አንዱ ነው።

የየጁ ወረሼህ መንግሥት በተቋቋመበት ወቅት የኦሮሞ ተወላጅ መሳፍንት ሁለት ተራማጅ አመለካከቶች ለኢትዮጵያ አበርክተዋል። ራስ ጉግሳ በዘር የሚወረስ የመሬት ርስት ልማድን የሚያስቀር የመሬት ንድፈ ሐሳብ አስተዋወቀ፤ "መሬት የረቢ ናት። ሰው የመሬት ተጠቃሚ ከመሆን ያለፈ ሚና የለውም። ሰው ምድርን ያለማትና ያልፋል። ምድርም ትውጠውና ትፋፋለች።...ከዛሬ ጀምሮ መሬትን በዘር መውረስ መብት የሚባል የለም። ረቢ ለፈለገው ይሰጣል። እነሆም ለኔ ለጉግሳ ሰጠኝ። እራሽ እረስ ነጋዴም ነግድ" የሚል ዐዋጅ ማውጣቱ በሚካኤል ደ አባዲ ተመዝግቧል።

ጉግሳ ይህንን ዐዋጅ ያወጣው በማይወለድበት ደብረታቦር ውስጥ ሥልጣን በጨበጠ ጊዜ ነው። ዐዋጁ ራሱን ከእንግድነት ወደ ባለቤትነት ለማሸጋገር የፈለሰፈው የግል ጥቅም መሣርያ ቢሆንም የፈጠረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም። ምድር ለተወሰኑ ባለአባቶች ብቻ የተሰጠ ንብረት ነው የሚለውን የዘልማድ አስተሳሰብ አፍርሶታል።

ከበደ ሚካኤል ከብዙ ዘመናት በኋላ ቼሊ በተባለው ገጸባህርይው አፍ፤

"መሬት የእግዚአብሔር ናት ባለቤት የላትም
ጎይለኛ እየሄደ ያስገብራል የትም"

[75] Gli Itliani in Africa Orientale, Del Boca, (Page 390)

ሲል የጉግሳን ሐሳብ ማስተጋባቱ ይሆን?

ራስ ጉግሳና ወራሾቹ ባገራችን ብዙ ያልተለመደውን የብዙ እምነት ባህል ለማስተዋወቅ ሞክረዋል። ሙከራቸው ከዘመኑ ርምጃ የቀደመ መሆኑ የሚገባን በሊቃውንት የተሰጠውን ምላሽ ስናይ ነው። ታሪክ ጸሐፊው አለቃ አጥሜ የጋ" ታሪክ በተባለው መጽሐፉ "ራስ ጉግሳ ወረ ሴክ ስለሆነ (ቢሆንም?) በመሀመድ ሕግ አልገዛም፤ በስመ ክርስትያን ገዛ። ...የኦሮሞንና የእስላምን ሕግ አለወጠም። የአምኃራን ሕግ አላፈረሰም። ከተማውን ደብረታቦር አደረገ ። በጌታችን በኢየሱስ ስም ቤተክርስትያን አሠራ ። ክርስትያን መሰለ። በዘመኑ ምሥርና ዐረብ ሀገር እስከ መካ ድረስ በፈረንሳይ ቱም በናፖሊዮን በናፖርት ተገዛ። ናፖሊዮን ቦናፖርት ከምድረ ግብጽና በኢትዮጵያ መካከል ያሉ እስላሞችን ተባብረን እንውጋቸው ብሎ ወደ ራስ ጉግሳ ላከ። ራሰ ጉግሳ ግን ለግብጽ ገዥ ለናፖሊዮን መልስ አልሰጠም። ነገሩ በዚህ ይታወቃል።" ብሎ ጽፏል።

ከጽሑፉ መረዳት እንደሚቻለው አለቃ አጽመጊዮርጊስ ራስ ጉግሳን እንደ ሀቀኛ ክርስትያን አልቆጠረውም። እሱ በነበረበት ዘመን ፤ ሀቀኛ ክርስትያን መሪ የእምነት ጽናቱን ለማሳየት ከፈለገ አረሚውንና እስላሙን ጨፍልቆ ክርስትያን ማድረግ ወይም መደምሰስ ይጠበቅበታል ። ዜጎች እንደ እምነታቸውና ባህላቸው እንዲኖሩ መፍቀድ እንደ አስተዳደር ጥበብ ሳይሆን በስመ ክርስትያን የሚፈጸም ደባ ይቆጠር ነበር። ራስ ጉግሳ የናፖሊዮን ቦናፓርቴን የመስቀል ጦርነት ግብዣ ቸል ብሎ ማለፉ በዘመናችን የፖለቲካ መስፈርያ ሲታይ የብልህ መሪ ውሳኔ ነው። አለቃ አጥሜ ግን ይህንን የገለልተኝነት ውሳኔ ለእስልምና በማዳላት የተፈጸመ መሆኑን ጠርጥሮ " ነገሩ በዚህ ይታወቃል" ብሎ ዘግቶታል።

የጉግሳ ወራሽ የሆነው ራስ አሊ፣ ክርስትያን ቢሆንም ከዘመኑ ልማድ ውጭ ክርስትያኖች ጋር ብቻ ሳይሆን ከሙስሊሞችም ጋር ይበላ እንደነበር በጊዜው





በነበሩ ታዛቢዎች ተመስክሮለታል።[76] እስላሙ የክርስትያን ምግብ በሚጸየፍበት፤ ክርስትያኑ የእስላም እጅ የነካውን እርም በሚልበት ልማድ ውስጥ እንዲህ ዐይነትን የኑሮ ዘይቤ መከተል ያስተሳስብ አብዮት ነው።

እዚህ ላይ ኦሮሞ ተወላጆችን የእምሮ አስተዋጽኦ በዝርዝር ለመዘገብ አይቻለኝም፤ የብሔረሰቡን ተወላጅ እንደ አላዋቂ አድርጎ የመሳል ዝንባሌ ከታሪካዊና ከነባራዊው እውነታ ጋር እንደማይጣጣም ለማሳየት ከላይ በብድግ ብድግ የጠቀስኳቸው ምሳሌዎች በቂ ናቸው ብየ አምናለሁ።

[76] Ras Ali Mangeait indifferemment à la table des chrétiens et la table des muslumans; Ferret et Galinier, voyage vol 2, (Page 79)





# አሜሪካን ዐየን

አሜሪካ ስገባ ለመጀመርያ ጊዜ ዐይቸ የገረመኝ የደኑ ብዛት ነው። አሜሪካ ውስጥ ደን ከመብዛቱ የተነሣ ያሜሪካ ሕዝብ አድኖ የሚበላ ሕዝብ መስሎኝ ነበር። ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት ባዲሳባ ውስጥ ያሉት ጫካዎች ሁለት ብቻ ናቸው። አንደኛው እንጦጦ ማርያም ቤተክርስትያን ግቢ የሚገኘው የባሕር ዛፍ ጫካ ሲሆን፣ ሁለተኛው አራት ኪሎ ቤተመንግሥት ውስጥ የሚገኘው የጥድ ጫካ ነው። እኒህን ሁለት ደኖች አውሮፕላን ላይ ሆነን ወደ ታች ስንመለከታቸው ባዲስ አበባ ብብቶች ላይ የበቀሉ ጸጉሮች ይመስላሉ።

የጫካ ችግር በከተማ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ባንድ ገጠር ቀበሌ አንድ ዛፍ በስንት መከራ ከተገኘ ሥራ ይበዛበታል። የመንደሩ ታታሪ ገበሬ የማር ቀፎ ይሰቅልበታል፤ የመንደሩ ታታሪ ሰካራም የማር ጠጅ ጠጥቶ ከስሩ ይሸናበታል፤ ከግንዱ ላይ "መቶ ሜትር በግራ በኩል ወደ ውስጥ ገባ ሲሉ የቀበሌ ማህበሩን ጽሬት ቤት ያገኙታል" የሚል ማስታወቂያ ይለጠፍበታል። ባጠቃላይ በመንደር





ውስጥ የሚገኝ አንድ ዛፍ ባንድ ጊዜ የግብርና መሣሪያ ነው፤ ሽንት ቤት ነው፤ ጂፒኤስ ነው።

አሜሪካ በገባሁ በማግስቱ ቫይቡና ለማለት ዳንኪን ዶናት የሚባል ቤት ገባሁና እጅግ ከመድረቁ የተነሣ ጽሑፍ እንጂ ንግግር በማይመስል እንግሊዝኛ፤

"ኩድ አይ ጌት ኤ ግላስ ኦቭ ሚልክ?" አልኳት አስተናጋጇን፤

"ስሞል ሳይዝ ሚድየም? ሳይዝ?" ብላ አማረጠችኝ።

ስሞል ሳይዝ? ምን በወጣኝ! ስሞል ሳይዝ አስመርሮኝ አይደል እንዴ ካገሬ የተሰደድሁት?

" ኧረ ሚድየም ሳይዝ ፕሊስ" አልሁ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፣ አስተናጋጇ ባሊ ሊሆን ማንጠልጠያ በቀረው ወጠምሻ ኩባያ ንፍር ወተት አምጥታ አሸከመችኝ። ወይ ሚድየም ሳይዝ! ሚድየም ሳይዝ ስላት ባሊ ወተት ያመጣችልኝ "ላርጅ ሳይዝ" ብላት ኖሮማ ላሟን እየነዳች ታመጣልኝ ነበር ብየ አሰብኩ። አሜሪካኖች የእናት ጡት ወተት በበቂ ሁኔታ ሳልጠባ እንዳደግሁ መረጃ ሳይደርሳቸው አልቀረም። የቀረበልኝን ኩባያ ከፍቸ ሳየው የቀረበልኝ ወተት ያንድ ቀበሌ ነዋሪዎችን ጦም ማስፈታት የሚበቃ ነው። ኩባያውን በስተው ዋሸንት የሚያህል መምጠጫ ወይም ስትሮው ሰኩተውበታል። ስትሮውን እንደ እናጢ እርሳስ በጆሮየ ላይ አስቀመጥሁና በከንፈሬ መጠጣት ጀመርሁ። ሰው ከንፈር ይዞ ተፈጥሮ ሳለ በኩንቢ የሚጠጣበት ምክንያት አይታኝም።

የተረፈኝን ወተት ልደፋው ካሰብኩ በኋላ ጡር ፈራሁ። በኋላ ግን እኔ በቁንጣን ከምደፋ ያሜሪካ ወተት ይደፋ ብየ ወደ ቆሻሻ ገንዳው ተራመድሁ።

በነገራችን ላይ እንደ አበሻ ለሳይዝ የሚያስቸግር ሕዝብ ያለ አይመስለኝም። እዚህ ሀገር አበሻ በልኩ የሚያገኘው ነገር ካለ ያይን መነጽር ብቻ መሆን አለበት። አሁን እኔ በቀደምለት ኬማርት የተባለ ሱቅ ገባሁና ሻጯ ሴትዮ ሱሪ እንድታሳየኝ ጠየኳት። ሴትዮዋ ሱሪ ነው ብላ ያመጣችልኝን ሳየው ባለሁለት

ክፍል የአብርሃም ድንኳን ነው። ካልሲ ብላ ያሳዩችኝን ስለካው ስቶኪንግ ሆነኝ።

በዚህ አጋጣሚ ያሜሪካ ጥቁር ወንድሞቻችንን ሱሪና በሱሪያቸው ውስጥ ያለውን መጠን የተመለከተ ሰው ተስፋ ቆርጦ ወደ አገሩ መመለሱ አይቀርም። አሁን ትናንትና አንድ የማርቲን ሉተር ኪንግን ሐውልት የሚያክል ሰውየ ከኔ አጠገብ ቆሞ የመሽናት እድል አጋጥሞት ነበር። እና ዚፑን ከፈት ሲያደርግ ሾፍ ባደርገው በቃ ምን ልበላችሁ የድሮ ሻንጣ ከፍቶ ንብረት የሚያራግፍ ነው የሚመስለው። እና ከእነዚህ ጋር ተወዳድረን ነው ወልደን መሳም የምንችለው?

የሳይዝ ነገር ሲነሣ አስቅድሞ የሚመጣብኝ ፍሪጃቸው ነው። አይ ፍሪጅ! ያሜሪካ ፍሪጅ እኮ በረንዳ ቢሠራለት መስኮት ቢገጠምለት አሪፍ የወንደላጤ ቤት ይወጣዋል። እውነቴን ነው ያሜሪካ ፍሪጅ ወደ ኢትዮጵያ ይገቴ ብሄድ በቤትህ ውስጥ ቤት ደብቀህ ተገኝተሀል ተብየ ልታሰር እችላለሁ። የኢትዮጵያ ፍሪጅ ካሜሪካ ጋር ብታወዳድረው ፍሪጅ አይደለም። በኮረንቲ የሚሠራ የምሳ እቃ ነው።

አንድ ቀን ጓደኞየ ቤት ሄጄ ሎሚ እንዳማረኝ ስነግረው ከፍሪጁ ውስጥ ከብርቱካን ከፍ ከዱባ ዝቅ ያለ ነገር አቀበለኝ። አሜሪካኖች በጥምቀት በአል ላይ ሎሚ ወርውረው ደረት የማይመቱበት ምክንያት የገባኝ ያኔ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ሴት ሎሚ መወርወር አኩሪ ባህል ሲሆን አሜሪካ ውስጥ ሎሚ መወርወር የግድያ ሙከራ ነው።

በነገራችን ላይ ከኢትዮጵያ የሚመጡ ዘፋኞች አንድ ሆቴል ውስጥ ሳንድ ወር ያክል ካርታ ሲጫወቱ ከርመው ሲመለሱ "አሜሪካን ዐየን ከአግር እስከራሱ" ብለው እንደሚዘፍኑ ታውቃላችሁ? እውነት ለመናገር አሜሪካ እግርም ሆነ ራስ የለውም። አሜሪካ አንድ ትልቅ ሆድ ማለት ነው።

እንደ አሜሪካኖች ያለ ሆዳም አለ?! ባለፈው አባቴ ከኢትዮጵያ ደወለና፣ "በእውቄ አሜሪካኖች እንደ ዐረቦች ሾርባ በቂጣ ይበላሉ የሚባለው እውነት ነው?" ሲል ጠየቀኝ።





"አይ ፋዘር አሜሪካኖች ትንሽ ከራባቸው ሾርባ በቂጣ አይደለም፤ ሾርባ የነካው ፎጣ አይምሩም" አልሁት።

አሜሪካኖች ምሳ ሰአት ላይ ምን ያደርጋሉ? መጀመሪያ ሄሊኮፍተር ማሳረፍ የሚያስችል ጠረጴዛ ይዘረጋሉ። በላዩ ላይ ኢትፍሩት ባመት የሚያመርተውን ያህል ፍራፍሬ ይከምሩበታል። ቀጥለው ኤልፎራ ለፋሲካ የሚያቀርበውን ያክል ስሀን እንግበው መንሽ የሚያህል ሹካ ሹካ ታጥቀው "ፈርስት ኮርስ ሰከንድ ኮርስ" እያሉ በምግቡ ላይ ይዘምቱበታል። ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ ድራሽ አባቱን ያጠፉታል። በእኛ ሀገር ኮርስ ማለት እየተመላለሱ መማር ማለት ሲሆን፣ ባሜሪካ እየተመላለሱ መብላት ነው።

አሜሪካኖች በጣም የሚወዱት ምግብ ዶሮ ነው። ለነገሩማ ያሜሪካ ዶሮ በርግጥ ዶሮ ነውን? ሲጀምር ተፈጥሮአዊ እናትና አባት የለውም። ማለቴ ያሜሪካ ዶሮ በእናቱ ኢንኩቤተር፣ ሲሆን ባባቱ ኮምፒውተር ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ እንቁላል ሲሸመት "የቄብ ዶሮ እንቁላል ነው፤ ወይስ የእናት ዶሮ እንቁላል ነው?" እንደሚባለው ሁሉ አሜሪካ ውስጥ organic non organic ተብሎ ለሁለት ይከፈላል። non organic እንቁላል ከላይ ስታዩት እንደማንኛውም እንቁላል ነው። በጸሐይ አቅጣጫ አነጣጥራችሁ ስታዩት ግን እንደ ሰርዲን open here የሚል ጽሑፍ አለው። organic እንቁላል ከእጅ ካመለጠ እንደ ብርጭቆ እንክት ይላል። non organic እንቁላል ግን ከፎቶቹ ፎቅ ወድቆ እንኳ እንደኩባያ ይንከባለላል።

ባለፈው ኳስ ለማየት <u>ስፖርት ባር</u> የተባለ ቡና ቤት ገባሁ። ገና እሥራ ስምንት ያልደፈኑ ኮረዶች መቀመጫቸውን በቁምጣቸው፣ ግታቸውን በጡት ማጎደራቸው፣ ወጥረው እንደ ዝሀ ዘጊ ባጠገቤ ይመላለሳሉ። ትንሽ ሞቅ ሲለኝ ኳሱን መከታተል ትቸ ቆነጃጅቱን መከታተል ጀመርሁ። በተለይ አንዷ አላፊ ጠፊ ፈገግታዋን ብልጭ አድርጋልኝ Can I get you something sweetheart? ብላኝ ስታልፍ መቀመጫዋን በጥፊ ቸብ ለማድረግ እጄን ብድግ አደረግሁት። ወድያው ግን እንደልብ መጎምጀትን እንጂ እንደልብ





መንካትን የማይፈቅደውን ያሜሪካ ሕግ አስቤ ተውኩት። እጄን እንደመፈከር አውራጅ ባየር ላይ አንከርፍፌ ትንሽ ካቆየሁት በኋላ፣ ወደ ኪሴ መለስኩት፡

እና የነጻነት ሀገር የምትሉት ይሄንን ነው? አዲስ አበባ አንዲት ቆንጆ ባጠገብህ ካለፈች መቀመጫዋን እንደጥምቀት ከበሮ መደለቅ ትችላለህ። ፖሊስ ይይዘኛል ብለህ መጨነቅ የለብህም። ቀይ መስመሩን እስካላለፍክ ድረስ የገሸረውን ፓርቲ መቀመጫ እስካልነካህ ድረስ የሚነካህ አይኖርም።

አሜሪካ ውስጥ ሴት እንደቀስተደመና የሚታይ ግን የማይዳሰስ ነገር ስለሆነ ስደተኛው በዚያ ነገር ርሀብ በጣም ይጠቃል። ለዚያ ነው መሰል የዲያስፖራ ወንዶች ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ይጠቀማሉ። አንዳንዱማ ገና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ትኬት በእጁ ሲገባ ያልቤርጎ ቁልፍ በእጁ የገባ ይመስል ይቆምበታል። አንዳንዱ አበሻ ወንድ ከኢትዮጵያ ሲወጣ አንድ ከረጢት ኮረሪማ ይዞ ይወጣል። ሲመለስ አንድ ከረጢት ኮንደም ይዞ ይገባል።

አንዱ ባለፈው፣ ቦሌ አየር ጣብያ ላይ በፈታሾች አንድ ሻንጣ ሙሉ ኮንደም ተማረከበት። ለዲኬቲ ርዳታ ልሰጥ ነው ቢል ማን ይስማው። ፍርድ ቤት ሲቀርብ ምን ተብሎ ተከሰሰ መሰላችሁ? እናት አገሩን ለመድፈር ሲዘጋጅ በቁጥጥር ሥር ውሏል ተብሎ ተከሰሰ።

ስፖርት ባር ገብቸ፣ መጠጥ ሳዝዝ አስተናጋጇ ሀያ አንድ ዓመት እንደሞላኝ ለማረጋገጥ መታወቂያ ጠየቀችኝ። በሰላሳ ሁለት ዓመቴ ከሀያ ዓመት በታች የሚገኝ ጎረምሳ መስየ መታየቴ አስደሰተኝ። በሌላ በኩል ግን ሰው ሃያ አንድ ዓመት ካልሞላው ካቲካላ በደረሰበት እንዳይደርስ የሚባልበት ሀገር "የነጻነት ሀገር" ተብሎ መቆጠሩ አናደደኝ።

በልጅነቴ፣ አባቴ ጠላ ቤት ሲሄድ፣ በሰላሙ ጊዜ ጃንጥላውን በጠቡ ጊዜ ከዘራውን ተሸክሜ አከተለው ነበር። ባለጠላዋ እማ ሸንበቆ፣ አባቴን አጎዛ በለበሠ ሳጥን ላይ ታስቀምጠውና በክቡር ዘበኛ ብርጭቆ ማለፍያ ጠላ ትቀዳለታለች። እኔን ደሞ ሰኔል በለበሰ ሙቀጫ ላይ ታስቀምጠኝና ቅራሪ ትቀዳልኛለች። ላባቴ በቀዳችለት ቁጥር በጠላው ውስጥ መርገዝ አለመጨመሯን





ለማረጋገጥ አንድ እፍኝ ለራሷ ቀድታ ፉት ትላለች። አሥር እፍኝ፡ ፉት ካለች በኋላ በእኔ ጥዋና በአባቴ ብርጭቆ መካከል ያለው ልዩነት ይምታታባታል። ለሁለታችንም ከዋናው ብርጭቆ ትቀዳልናለች።

አባየም አሥር ብርጭቆ ከጠጣ በኋላ በእናቴና በእማ ሸንበቆ መካከል ያለው ልዩነት ይምታታበታል። እና እማ ሸንበቆ ባጠገቡ ባለፈች ቁጥር እንደ መንደር መርፌ ወጊ እጁን ወደ መቀመጫዋ ሰደድ ያደርጋል። እኔ ያኔ የቤት ጣራን ለመጀመርያ ጊዜ ያየሁ ይመስል ዐይኔን ጣራው ላይ ልኬ እቆያለሁ።

ከእማማ ሸንበቆ ጣራ ወደ አሜሪካ እንመለስ። ብዙ ጊዜ ካውሮፓና ከኤሽያ የመጡ ስደተኞች አሜሪካ ሲገቡ ጾታቸውን ይቀይራሉ ይባላል። እኛ ኢትዮጵያውያን እንዲህ ያለ እብደት አይነካካንም። ኢትዮጵያውያን ቀየሩ ከተባለ ሙያቸውን ቢቀይሩ ነው።

በዚህ መሠረት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ዶክተር ፤ እዚህ ሲመጣ ወይተር፣

ኢትዮጵያ ውስጥ አምባሳደር፣ እዚህ ሲመጣ ወዛደር፤ እልፎ አልፎም ወታደር

ኢትዮጵያ ውስጥ ታዋቂ ሯጭ፤ እዚህ ሲመጣ ሥጋ ቆራጭ

ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስተር፤ እዚህ ሲመጣ ቤቢሲተር

ኢትዮጵያ ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስተር፤ እዚህ ሲመጣ ፓስተር፣ ለዛውም እማተር።

አሜሪካ ውስጥ የሚኖሩ አበሾችን በአራት ከፍየ ለማየት ሞክርያለሁ። የመጀመርያው ቡድን አስመላሽ ተብሎ ሲታወቅ ሁለተኛው አስታዋሽ ይባላል።

ዕቃ ገዝቶ፣ ለጥቂት ቀን ተጠቅሞ ገንዘቡን የሚያስመልስ ሰው አስመላሽ ይባላል። አስመላሽ አንድ ሱፍ ገዝቶ ሠርግ ላይ ከዘነጠበት በኋላ ጠበበኝ ብሎ ለባለ ቡቲኩ ይመልሳል። እውነቴን ነው፤ ዲሲ ውስጥ አንድ ቡቲክ ውስጥ ገብታችሁ አንድ የተሰቀለ ኮት አግኝታችሁ ኪሱን ብትፈትሹት ባማርኛ የተጻፈ የሠርግ መጥሪያ ካርድ ታገኛላችሁ። አንዳንዱ አክራሪ አስመላሽ ኮንዶም

ከተጠቀመ በኋላ "ስሞክረው ሰፋኝ የዝሆን ኮንዶም ነው እንዴ የሰጣችሁኝ?" ብሎ ይመልሳል። ወይም "ልጠቀምበት ብለካው፣ እየተንሸራተተ አስቸገረኝ ከተልባ የተሠራ ኮንደም ነው እንዴ የሰጣችሁኝ?" ሊል ይችላል።

አስታዋሽ የሚባለው፣ በአካል አሜሪካ ውስጥ እየኖረ በመንፈስ በጥንቲቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ነው። "አስታዋሽ" ምግቡን ከኢትዮጵያ ስሁኑን ካሜሪካ ይወስዳል። በዚህ ምድብ ውስጥ ያለውን ሰውየ አፓርታማ ከፍታችሁ ብትገቡ የድርቆሽ ከረጢት ያደናቅፋችሁና፣ የሚጥሚጣ ፌስታል ላይ ባፍጢማችሁ ትወድቃላችሁ።

አስታዋሾች በድሮ ትዝታቸው ይኖራሉ። ባለፈው አንድ ሽማግሌ ባሊታክሲ ከሜሪላንድ ወደ ዲሲ ሲወስዱኝ፣

"የት ነው ሠፈርህ?" አሉኝ።

"ውሃ ልማት" አልኳቸው።

"ያስመራ መንገድ እንዴት ነው ? "

"አስመራ አያደርስም እንጂ ደህና ነው"

ትንሽ ቆይተው፣

"ካራት ኪሎ መጽሐፍት ቤት ፊትለፊት፣ ዊልቸር ላይ የሚቀመጠው ለማኝ ደህና ነው?" አሉኝ።

በጣም ደህና ነው። አሁንማ ዊልቸሩን ሸጦ ባጃጅ ገዝቷል።

አሜሪካ ውስጥ ጊዜ የለም። በሥራ ቀን ሰው ቁርስ የሚበላበት ጊዜ ስለሌለው፣ ኩባያውን ይዞ ሲግተለተል የጠበል ተጓዥ ይመስላል።

ወደ አሜሪካ ልመጣ ኢምባሲ ደጅ ስጠና ሽሮሜዳ ግድም ያገኘሁት አንድ ዲያስፖራ፣





"አንተ ቀንቶህ አሜሪካ ና እንጂ እኔ አሜሪካን እንደ ገበር ገልብጬ አስጎበኝሀለሁ" ብሎኝ ነበር።

መጣሁና ደወልኩለት።

"አበረ፣ አሜሪካ ነኝ" አልኩት።

"መጣህ እንዴ፣ በጣም አሪፍ ፤ስትመለስ ለእሁዬ ላፕቶፕ ይዘህላት ትሄዳለህ" አለኝ፡፡

አልፈርድበትም። አሜሪካ ውስጥ ጊዜ ውድ ነው። የአሜሪካ ቄሶች ጸሎታቸው እንኳ አጭር ነው፤"God bless America" ብለው ወደ ሥራቸው ይሠማራሉ። የኢትዮጵያ ቄስ በቂ ጊዜ ስላለው ፊታ ዘና ብሎ "ምእመናን እግዚእ መሐርነ ክርስቶስ እንበል አሥራ ሁለት ጊዜ" ይላል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ተገናኝተው ሲያወሩና በስልክ ሲያወሩ ፍጥነታቸው ይለያያል። ተገናኝተው ሲያወሩ፣ "እንደምን አደራችሁ፣ በጎም አላደራችሁ" ብለው፣ ጀምረው "በስላም በጤና ያገናኘን" ብለው ይዘጋሉ። አሜሪካን ሀገር ስልክ ርካሽ ስለሆነ አንድ ሰው በስልክ ማውራት እንዴ ከጀመረ፣ ስልኩን ከጆሮው ላይ ሌባ ካልነጠቀው በቀር፣ አያቆምም። ባለፈው አንዱ ደወለልኝና ለሁለት ሰዓት ያክል ዛፍ እየተገደፍሁ፣ በጆርባየ እየተንበለበልኩ፣ በባቡር እየሄድሁ ካዳመጥሁ በኋላ፣ ምን ቢለኝ ጥሩ፣ ነው? "በል አልያዝህ፤ ከሀያ ደቂቃ በኋላ እደውልልህና በሠፊው እንጫወታለን።"





# ነጻ መሬት

(ታሪክ ቀመስ ልቦለድ)

የሀዴግ ሰራዊት ደብረማርቆስን ለመቆጣጠር፣ አራት መኪራከር ተራራ ላይ ሲመሽግ፣ አንድ የደርግ አውሮፕላን በደብረማርቆስ ሰማይ ላይ አንጃበበና አንድ ከረጢት ሙሉ የወረቀት ነዶ በተነ። የወረቀት ነዶው ገበያው ላይ እንዲወድቅ ቢታለምም፣ ነፋስ ካማጺዎች ጋር የተባበረ ይመስል፣ወደ ገጠር እየገፋ ወስዶ በአያ ህብስቱ የኑግ ማሳ ውስጥ በተነው። በራሪ ወረቀቶችን፣ እንደ ቢራቢሮ እያሳደድን፣ ማሳው ላይ ደረስንባቸው። እቅፋችን ላይ እስኪወድቁ አላስቻለን ብሎ እየተንጠራራን፣ እየዘለልልን ቀለብናቸው። ወረቀቶችን ለመያዝ በተደረገው ሽምያ ሁለት ልጆች ተጨፍልቀው ሲሞቱ እያሌ ሰዎች ተፈነካከቱ። እያ ህብስቱም አዝመራየን ደቅድቃችሁብኛል፤ በሚል አባርረው መያዝ የቻሉትን ብላቴና ሁሉ ደበደቡ። ብዙ ልጆች ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ ደረሰባቸው። ደርግ እድለቢስ መንግሥት ስለሆነ እንኳን በምብ ወረቀት ሲጥል ሕዝብ ይፈጃል።





በነገራችን ላይ፣ "ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ ደረሰባቸው" የሚለው ከኔ ሀማርኛ የማይጠበቅ የተሰለቸ ሐረግ መሆኑ ይገባኛል። ግን የዚህን ችኮ ሐረግ ጥቅም ማን አስተውሎት ያውቃል። እስቲ አስቡት! በየሬድዮው፣ "ከአዲስ አበባ ወደ አዋሳ አምሳ ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ የነበረ አውቶብስ ተገልብጦ አሥር ሰዎች አከርካሪያቸው እንክት ድቅቅ ሲል፣ አምስቱ ከወገባቸው በታች ተጎምደዋል፣ የተቀሩት አይኖቻቸው ፈርጧል" የሚል ዜና የምንሰማ ቢሆን ኖሮ ሰው አውቶብስ ሊሳፈር ይችል ነበር?። የምን አውቶብስ! ሰው በዚህ ምድር ላይ ይኖር ነበር? ይኖር ነበር ወይ? በፍጹም። ስለዚህ፣ "ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ ደረሰባቸው።" ብለን እያድበሰበስን ሕይወትን እንሸውዳለን። "ሠራዊታችን ሸሸ" ላለማለት፣ "ስልታዊ ማፈግፈግ አደረገ" እንላለን። "ደመ ከልብ" የሆነውን ሰውየ "ተሰዋ" ብለን አወዳደቁን እናሳምርለታለን። ይህ በእንዲህ እንዳለ "የቀድሞው ታጋይ አቶ መብራቱ ባደረበት የደም ብዛት በሽታ ትናንት ከምሽቱ ሁለት ሰአት ላይ ተሰውቷል።"

ደሞ በቲቪ ዜና "ኢትዮጵያ ከቻይና ተበደረች" ላለማለት፣ "በኢትዮጵያና በቻይና መካከል የብድር ስምምነት ተፈጸመ" ይባልልኛል። ማን ነው አበዳሪ? ማን ነው ተበዳሪ? ለይ! "ዘረፈ" የሚለው ቃል ሲያስቦካን፣ "ማረከ" እንላለን። በነገራችን ላይ የሕወሀት ሠራዊት ባከሱም አፕሬሽን ከሕዝብ ባንክ ከሁለት መቶ ሺህ ብር በላይ ማርኳል።

አድበስባሽ ቃላትና ሀረጎች የሕዝብ ጫት ናቸው። የዲያብሎሱን እውነታ ለጊዜውም ቢሆን መላክ አስመስለው ያሳዩናል።

ደርግ የበተናቸው ወረቀቶች ምን እንደሚሉ አሁን ሙሉ በሙሉ አላስታውስም። ግን በተረትና ምሳሌ የታጨቀ መልክት እንደነበራቸው ትዝ ይለኛል። "ጀግናው የጎጃም ሕዝብ ሆይ! አበው፣ መተው ነገሬን ከተተው እንዲሉ፣ ጦርነትን ትተህ በሰላም ስትኖር እንደነበረ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ 'በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል' ነውና የናት ጡት ነካሾች ሰላምህን ለመበጥበጥ ተነሥተዋል። 'ምከረው ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው' ነውና እምቢተኛ ወንበዴዎችን በገቡበት ገብተህ ደምስሳቸው" እያለ ይቀጥልና

መጨረሻ ላይ "በቆራጥነት ተፋልመህ የምትማርከውን ወያኔ እጅን ለመንግሥት መሳሪያውን ላንተ" ብሎ ይዘጋል።

ይህ ወረቀት ደርግ ለጎጃም ገበሬ መቀስቀሻ የበተነው ወረቀት ነው። አሁን ሳስበው ግን ደርግ ለጎጃም ገበሬ የላከው የመጨረሻው የስንብት ደብዳቤ ኑሯል።

የህዴግ፣ በማርቆስ ደጃፍ መድረሱ ሲሰማ ሁላችንም እንዳይማረከብን የምንፈራውን ነገር ሁሉ ለመቅበር ተሽቀዳደምን።

አባቴ ለብዙ ዘመን በሻማ ማስቀመጫነት ያገለገለውን፣ "ዳስ ካፒታል" የተባለውን ግብዳ መጽሐፍ ለመቅበር ጓሮአችንን ቆፈረ። ሲቆፍር፣ ጃንሆይ የወረዱ ቀን፣ አያቴ በበርኖስ ጠቅልሎ የቀበረውን፣ "ሕይወቴና የኢትዮጵያ ርምጃ" የተሰኘ መጽሐፍ አገኘ። እናቴ በበኩሏ አባቴ የላከላትን የፍቅር ደብዳቤ ከሙዳይዋ አውጥታ ቀበረች። አባቴ በጊዜው፣ ሴት አፍቃሪነቱ፣ ከአብዮታዊነቱ እንደማያዘናጋው፣ ለማሳየት በፍቅር ደብዳቤው መጨረሻ ላይ "ወታደራዊ ዓለማቀፋዊነት ይለምልም" የሚል መፈክር ጣል ያደርግ ነበር። እኔ ምን ቀበርሁ? ከፕሌይ ቦይ መጽሔት፣ በቢሳ ምላጭ ተቆርጣ የወጣች ያንዲት ፈረንጅ ርቃን ፎቶ በደብተሬ ልባስ ሥር ሸሽጌ እኖር ነበር። እና ደብረማርቆስ ሲቃጠል ፎቶይቱ ለብቻዋ ተነጥላ እንድትተርፍ በመርቲ ጣሳ ውስጥ ከትቸ፣ ከዳማከሴው ሥር ማስ ማስ አደርጌ ቀበርኳት።

የቀኝ ጎረቤታችን አቶ ርሶም፣ በመሠረተ ትምህርት ዘመቻ በመሳተፉ፣ ከራሱ ከመንጌ እጅ የተቀበለው፣ በየቀኑ በዳንቴል የሚወለውል መስታወት ውስጥ አስገብቶ ግድግዳው ላይ የሰቀለው፣ የምስክር ወረቀት ነበረው። ታድያ እሱን ለመቅበር ርቆ ሲሄድ በወያኔዎች ከልል ገብቶ ኖሮ ተማረከ። ወያኔዎች በመጀመርያ፣ በዶማ ሊፋለማቸው የመጣ መስሏቸው አደነቁት። "ጠላትም ቢሆን ጀግና ነውና ሊደነቅ ይገባል" አለ ተጋዳላይ ተፈሪ።

"ጀግናም ቢሆን ምርኮኛ ነው ፣ ምሽግ ሲቆፍር ይባጅ፣" አለ ተጋዳላይ ሲራጅ።





አቶ ርሶም፣ ለሶስት ቀን ምሽግ ከቆፈረ በኋላ በታጋዮች ታንክ ተፈናጥጦ ወደ ማርቆስ ተመለሰ። ከዚያ ፒፒሲ ጠመንጃ አንግቶ፣ ስንዳል ጫማ ተጫምቶ በከተማው ናኘበት። ቅዳሜ ቅዳሜ በተሀድሶ ፕሮግራም ላይ የሚዘመረው መዝሙር "በደሙ በላቡ መልካም ታሪክ ጻፈ" የሚለው ስንኝ ላይ ሲደርስ፣ ርሶም ከኪሱ ውስጥ የስእለት ግምጃ የሚያክል መሀረም ጎልጉሎ አውጥቶ ከመጠን በላይ እየተናፈጠ፣ በመጠኑ ያለቅሳል። አባቴ፣ "ምን ሆነህ ነው" ሲለው፣ "ምን ባክህ፣ ደርግን ለመደምሰስ የከፈለነውን መስዋእትነት ሳስብ ስሜቴን መቆጣጣር ያቅተኛል" ብሎ ይመልሳል።

ካልተሳሳትሁ የህዴግ ወደ ማርቆስ የገባ የካቲት ወር ላይ ይመስለኛል። እጅ የሰጠችው ደብረማርቆስ እጅ ካልሰጠችው አዲስአበባ ጋር ስለተቆራረጠች ቀለብ የሚሰፍርላት አጣች። ከተማይቱን ካሰቃቂ ራብ የታደጋት ደርግ ለ17 ዓመታት ጎተራ ውስጥ ያጠራቀመው በቆሎ ነው። ያ በቆሎ ባይኖር ኖሮ ዛሬ ባብማ ቤተከርስትያን ጓሮ ስታልፉ፣ "በዕውቀቱ ሥዩም ከ1972-1983" የሚል ጽሑፍ የሰፈረበት ነጭ የስሚንቶ ስሌዳ በዳዋ ማኸል ብቅ ብሎ ማየታችሁ አይቀርም ነበር።

የህዴግ ሰራዊት ደብረማርቆስ መግቢያ ላይ ተዘርግሮ ከሚገኘው የኢሬን ኑውክሊየር ጣቢያ ከሚመስለው ጎተራ ደርሶ፣ በሩን በከላሽ ሰደፍ ... አደርጎ ለከተማው ነዋሪ በቆሎ ማከፋፈል ጀመረ። እንዲያውም የህዴግ መንግሥትነትን የተለማመደው ለደብረማርቆስ ሕዝብ በቆሎ በማከፋፈል ሳይሆን ይቀራል!

በደብረማርቆስ ተቋቁሞ የነበረው ጊዜያዊ መንግሥት፣ ከንቲባ፣ አስተዳዳሪ ምናምን የሚባል የሥልጣን ተዋረድ አልነበረውም። ትዝ የሚሉኝ ሹመኞች የሚከተሉት ናቸው። "ተጋዳላይ መሐሪ፣ የበቆሎ ወረፋ ተራ አስከባሪ፣ ተጋዳላይ ተፈሪ፣ የበቆሎ ከረጢት ጥራት ተቆጣጣሪ፣ ተጋዳላይ ሲራጅ፣ ዋና ጫኝና አውራጅ፣ እንዲሁም የበቆሎ ፈጭ ሴቶች አደራጅ . . . ወዘተርፈ፣

እግር ጥሎህ ፍርድ ቤት ብትገባ የከተማው ተለማማጅ ዳኛ፣ "ተከሳሽ አቶ ማናየ፣ ጊዚያዊ መንግሥት በሰፈረለት አምሳ ኪሎ በቆሎ ላይ አላግባብ ሁለት ኪሎ ሲያጭበረብር እጅ ከፍንጅ በመያዙ እጁ ከተያዘበት ቀን አንስቶ በሆስት





ወር ጽኑ እሥራት ተፈርዶበታል።" ብለው ከፊታቸው ላይ ያለውን ዴስክ በቆሮቆንዳ ወቅረው ፋይል ሲዘጉ ትደርሳለህ። በማግስቱ የአስረኛው ዘመዶች የበቆሎ ቂጣ ስንቅ ይዘው ባጠገብህ ሲያልፉ ታያለህ። ደብረማርቆስ፣ የህዴግ ሕዝብ ማስተዳደር እንደሚችል ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ በቆሎ ብቻ እየበላ መኖር እንደሚችል መሞከርያ ላብራቶሪ ሆነች።

ደርግ ስልታዊ ማፈግፈግ ባደረገበት ሰአት ብዙ ወታደር አልቋል፤ አቤት ስንት ወጣት ወደቀ! ስንት ጀግና አለቀ! ዳሩ ማን ሥራዩ ብሎ ይቆጥራል! ወያኔ ከገባ ከጥቂት ቀናት በኋላ በከተማይቱ የምንገኝ፣ ታዳጊዎች እስከጉልበታችን የሚደርስ ከስክስ ጫማ አድርገን ታየን። ያለቀውን ወታደር ቁጥር ለማወቅ ከስክስ ጫማዎቻችችን ደምሮ ለሁለት ማካፈል ነው። በጊዜው ለቀድሞ ወታደር ሐውልት መሥራትን የሚያስብ ማንም ሰው አልነበረም። ግን እኛ ሳናውቀው የጀግኖችን መታሰቢያ በእግራችን ይዘን እንዞር ነበር። እኒያ ከስክስ ጫማዎች! "ላልታወቀ ወታደር" የሚል ስውር ጽፈት ያለባቸው፣ በቆዳ የተሠሩ ሐውልቶች!

አንድ ጎስቆል ፣ ጠቆር ያለ ጎረምሳ በኮባ የተጠቀለለ ነገር ተሸክሞ ስሚዛውንና ኮሸሻውን እየጣሰ ሲሄድ ከተመለከታችሁ ለወሬ ነጋሪ የተረፈ ወታደር መሆኑን ጠርጥሩ። ከፊት ፊት ያገኛትን ጎጆ፣ ሲፈራ ሲቸር፣ በጣቱ ከዳበሳ በማይልቅ ለዘብታ ያንኳኳል።

ሲከፈትለት፣ "እንዴት ዋላችሁ፤ ከጦር ሜዳ የተመለስሁ ወታደር ነኝ። በራብ እጅግ ስለተጎዳሁ ግማሽ እንጀራ ካበላችሁኝ ክላሼን ከካርታ ሙሉ ጥይት ጋር እሰጣለሁ" ይልና ወታደራዊ ሰላምታ ለመስጠት እጅን ሲያነሳ ክንዱ እንደፓስታ ጥውልግልግ ብሎ ታፋው ላይ ተመልሶ ይወድቅበታል። ገበሬው የወታደሩን ክላሽ ከተቀበለ በኋላ ማጀት፣ ጨለማው ውስጥ እድፍጦ ከተቀመጠው ጎታ ውስጥ፣ ቅድም ካንዱ ወታደር ከተቀበለው ክላሽ ጎን ያስቀምጠዋል።

ወይ ጊዜ!! ወታደራዊው መንግሥት በቆሎ በጎታ ውስጥ አጠራቀመ ሲባል የሚያምን እንደማይኖር ሰላማዊው ገበሬ በጎታው ውስጥ ክላሽ ያጠራቅም ነበር ቢባል ማን ያምናል!





ወታደሩ እንጀራውን እየጠቀለለ ሲጎርስ ገበሬው በግርምት እየተመለከተው፤ "ወይ የወንቃው ጊዮርጊስ፣ አሁን ይሄ ወታደር ነው ወይስ በካኪ ኮቱ ውስጥ ከንፋን የደበቀ መላከ? ታሪክ እኮ ነው! በያዘው ብረት ባፍጢሜ ደፍቶ፣ ሞሰቡንና ሰታቴውን ገልብጦ ብስና እስኪይዘው መብላት ሲችል ከፊቴ ተጎልቶ እንደ ልጃገረድ ይቅለሰለሳል! እምጵ!...ጉድ! ድሮ በራስ ኀይሉ ጊዜ፣ ሰው በጥይት ይገበያያል ሲባል እስቅ ነበር። አሁን እድሜ ስጥቶኝ ድሮ ከተባለው ጊዜ ደርሽ አየሁት።"

ወድያው ጓዳው በር ላይ ወደ ቆመችው ሚስቱ ዞሮ፣ "አንች የእንጭጭ ልጅ! ሰው እህል ሲበላ አይተሽ አታውቂም? ለመሆኑ የሚጠጣው ቅራሪ አለሽ ወይስ ግብርውሃ ወጥተሸበታል?" ከዚያ ወደ ወታደሩ በትህትና ዞሮ፣ "እይዞህ ብላ! እሥር አለቃ! ያዝ እንጂ! አልጣመህም እንዴ! እንግዲህ የክላሽ ለውጡ ምሥር ወጥ ነው። ላውንቸር ይዘህ ብትመጣ ኖሮ ጠቦት አርድልህ ነበር።"

ደብረማርቆስ፣ የህዴግ "ነጻ መሬት" ከሆነች ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ከወፍጮ ቤት ስመለስ ስብሰብ ብለው የቆሙ ሰዎች ተመለከትሁ። በመደዳ የተገተረውን ሰው እየጣስሁ ወደ ውስጥ ስዘልቅ በጊሪደር ተቆፍሮ የወጣ የሙታን አጽም ተከምሮ አየሁ። አንድ ረጅም አፍንጫ ያለው (አፍንጫውን በቪያግራ ያቆመ የሚመስል) አዲስ ምልምል ካድሬ ከአጽሙ ክምር ፊትለፊት ቆሞ እንዲህ ሲል ሰማሁት።

"በፕሮግራማችን መሠረት፣ በመጀመርያ እኒህ ንጹሐን ዜጎች፣ ባስከፊው የደርግ ሥርዓት ባሰቃቂ መንገድ ተገድለው በጅምላ መቃብር ውስጥ እንዴት እንደተወረወሩ ሰፊ ማብራሪያ ይደረጋል። በማስቀጠል ከተሳታፊዎች የለቅሶና፣ ራስን ስቶ የመውደቅ ስነ-ሰርአት ይካሄዳል። በመጨረሻ የደርግን እስከፊነት የሚገልጽ ጸሎት ይከናወንና የበአሉ ፍጻሜ ይሆናል።"

"እዚህ ጋ አስተያየት" የሚል ድምጽ ከህዝቡ ማኸል ተሰማ። ሁሉም ባይኑ ፈለጋቸው። እማሆይ ወለተ ማርያም ናቸው።

"ይቀጥሉ እማሆይ። አሁን የተናገርኩትን ደግፈው የመጻፍ የመናገርና ሰላማዊ ሰልፍ የመውጣት መብትዎ በሕገመንግሥቱ የተረጋገጠና የተደነገገ ነው ይቀጥሉ" አለ፤ ካድሬው።

"እኔ እንግዲህ እንደምታዩኝ፣ ልጤ የተራሰ፣ ጉድጓዴ የተማሰ ባልቴት ነኝ። ለየትኛው እድሜዬ ሐሰት ልናገር! እኒህ ሰዎች ደርግ አደለም የፈጃቸው። ጣልያን ከደጃች በላይ ጋር አብራችሁ ሸፍታችኋል ብሎ ማርቆስ ገበያ ላይ ሲረሽናቸው እጣን ልጅ ብሆንም ትዝ ይለኛል። እንደምታዩት ሙታን የለበሱት ሱሪ ተነፋነፍ ነው። ኪሳቸው ቢበረበር ሊሬና ማርትሬዛ ይገኝበታል። ይህ ደሞ በጥልያን ዘመን ለማለቃቸው ጥሩ ማረጋገጫ ነው። በነገራችን ላይ እኔ ደርግ አይገድልም አላልሁም። ደርግማ እሳምሮ ይገድላል።"

(እሳምሮ ይገድላል የምትለውን ቃል ባሰብኳት ቁጥር ፈገግ እላለሁ። አይ እማሆይ! መግደል ፎቶ ማንሳት መሰላቸው እንዴ! አስቲ ደርግ እሳምሮ ሲገድል ባይነህሊናችሁ ሳሉት። የደርግ ወታደር፤ አንዱን ወጣት ከፊቱ ያቆመውና ጢሙን ያስተካክለዋል፣ የተመሰቃቀለ አፍሮውን ያበጥርለታል። የፍርሀት ላብ ያወዛው ብብቱን ዶዶራንት ይቀባለታል። ከዝያ ከፊትለፊቱ በርከክ ብሎ ክላሹን ደረቱ ላይ እያነጣጠረ:"እስኪ ትንሽ ፈገግ! እ... እንደሱ እዎ! እንዴት እንዳማረብህ! አሁን ቃታ መሳብ እችላለሁ" ቅው ድም! አይ እወዳደቅ! እኔ ብዙ ታጋይ ሲወድቅ አይቻለሁ! እንዲህ እጁን በኪሱ እንደከተተ ዘንጠ የወደቀ ሰው ግን አልገጠመኝም)

"ደርግማ እሳምሮ እንደሚገድል የታወቀ ነው።" ቀጠሉ እማሆይ፣ " ነገር ግን እንደተናገርሁት ይሄ የፋሺስት ጥልያን ሥራ መሆኑን በእናቴ ባብማይቱ ማርያም ስም ምየ አረጋግጣለሁ"

ካድሬው ተናደደ። ግን ንዴቱን ዋጥ አድርጎ፣

"እማሆይ በተናገሩት ላይ ተቃውሞ ያለው አለ? እማሆይ የተናገሩትን በመቃወም የመናገር፣ የመጻፍና ሰላማዊ ሰልፍ የመውጣት መብት በሕገመንግሥቱ የተደነገገ ነው።"





እማሆይን የሚቃወም ሰው ስላልተገኘ ራሱ ቀጠለ።

"እህህ ጥሩ እንግዲህ። እማሆይ እንዳሉት እኒህ ሰዎች ግድያ የተፈጸማቸው በጣልያን ሊሆን ይችላል። ቢሆንም ደርግ ፣ገዳዮችን ለፍርድ ባለማቅረቡ ምን ያህል አስከፊና አረመኔ ሥርዓት እንደሆን አመላካች ነው።"

ካዲስ አበባ ደብረማርቆስ የተዘረጋው መኪና መንገድ፣ ማንኛውም መኪና እንዳይተላለፍበት መዘጋቱን የሚገልጽ ዜና ሰማን። ድሮ፣ "ካባይ ወዲህ የጎጃም ካባይ ወድያ የሸዋ" ሲባል የነበረው ቀርቶ "ካባይ ወዲህ የህዴግ ፣ ካባይ ወድያ የደርግ" መባል ተጀመረ። አባቴና ጥቂት ቆራጥ መምህራን፣ ደሞዛችንን መቀበል በሚል ሰበብ ከህዴግ ነጻ መሬት አምልጠው፣ በእግራቸው ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ተነሡ። አባቴ "ፍቅር እስከመቃብር" ውስጥ ሰዎች በእግራቸው አባይን አቋረጡ የሚል ነገር ሲያነብ ድሮ ባለመፈጠሩ እምላኩን ያመሰግን ነበር። ምስኪን አባቴ። ኢትዮጵያ ውስጥ፣ "ድሮ" ወደ ፊት የሚመጣ ነገር መሆኑን መች አውቆ! ይሄው መቆየት አይቀርም ድሮን ደርሶ ተመለከተው።

አባየ ከጓደኞቹ ጋር እየወደቀ እየተነሣ፣ ወይም በሌላ አነጋገር፣ ጓደኞቹ እየወደቁ እሱ እየተነሣ አባይን አቋርጦ ገሰገሰ። ሁለት ወር ያህል ከተጓዘ በኋላ ልብሱ በላዩ ላይ አለቀ። ቦላሌው በጋሬጣ እየተዘነጠለ ጎህ ጽዮን ላይ ሲደርስ ሽርጥ ሆኖ አገኘው። ከማርቆስ ሲወጣ አጥልቆት የነበረው ሸራ ጫማ ገርበ ጉራቻ ላይ ሲደርስ ነጠላ ጫማ ሆነ። ለስላሳ ቆዳው ወደ ቅርፊት ሲቀየር ታዘበ። ከዚህ መከራ በኋላ እንድ ማለዳ ላይ ከሩቅ ሸገርን ተመለከታት።

እስዋ ናት! አዲስ አበባ ናት! ባቅራቢያው ከሚገኘው ትምርትቤት ውስጥ፣ "ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ ቅደሚ" የሚል ኅብረ ዜማ እየተመመ ሲመጣ ሰማ። ዞር ሲል ከመንገዱ ዳር የደበዘዘ የኢትዮጵያ ካርታ ተመለከተ። አሁንም ኢትዮጵያ አሥራ አራት ክፍለሀገሮች አሏት። ከሁለት ወራት በፊት የሚያውቃት ኢትዮጵያ! አብዮታዊት ኢትዮጵያ! ሙቅ የደስታ እንባውን ባይበሉባው ጠርጎ ዞር ሲል፣ ባጠገቡ ታንክ እየተንከባለለ ሲያልፍ ተመለከተ። ታንኩ ከደብረማርቆስ ግድም እንደመጣ ያወቀው የታንኩን ሹፌር በቆሎ ሲግጥ ስለተመለከተው ነው።





በታንኩ ጀርባ ላይ ቁምጣ የለበሱ፣ ላብ የጠገበ ያንገት ልብስ የጠመጠሙ ጎፈሬያም ሰዎች ሰፍረውበታል።

አባየ ሰውነቱ ስለተዝለፈለፈበት ቀጣዩ ታንክ ቆሞ እንዲያፈናጥጠው እጁን ማወዛወዝ ጀመረ።

*******************

ከአሜን ባሻገር